# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፪ ግንቦት/ሰኔ ፲፱፻፺፮ ዓ.ም




የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ጉዞ
በኀትመት መገናኛ ብዙኃን


www.eotcmk.org

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## እንታረም

አንድ ሁሌ የሚያሳስበኝ ጉዳይ አለ፡፡ በአካባቢያችን የሰንበት ት/ቤቶችንም ሆነ የዐውደ ምሕረት ጉባኤያትን ስንመለከት ዘወትር በምእመናን የሚሞሉት አዳዲስ ሰባክያን ወይም መምህራን መጡ ሲባል ነው፡፡ አዳዲሶቹ ሰባክያንና መዘምራን የተያዘላቸው መርሐ ግብር ተጠናቆ ሲመለሱ ግን እንደ ተለመደው ዐውደ ምሕረቱም ሆነ አዳራሹ ባዶ ይሆናል፡፡ በእውነቱ ይህ ተገቢ አካሔድ አይደለም፡፡ እኛ የምንሰማው በሰዎች አድሮ የሚናገረውን እግዚአብሔርን እንጂ ሰዎችን አይደለም፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ሰዎችን ሳንመለከት በዐውደ ምሕረት እየተገኘን ቃሉን እናዳምጥ፡፡

ገ/ኢየሱስ
/ደሎ መና/

## ሥርዓት ይጠበቅ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እንከን የሌለበትን መሠረተ እምነቷን የምትፈጽምባቸው በወግ የተሠሩ ሥርዓቶች አሏት፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ካለማወቅም ይሁን በግድ የለሽነት እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ሲጣሱ ይታያሉ፡፡ ለአብነት ለመጥቀስ በተለያዩ የንግሥ በዓላት ጊዜ የቃል ኪዳኑ ታቦት ቆሞ የሰንበት ት/ቤት ዘማርያን በሚዘምሩበት ወቅት በተለይ ሁሉም ከበሮ ለመምታት ሲል የሚፈጠሩ ግር ግሮች ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህ ችግር በሁሉም ቦታ ይከሰታል ለማለት ባልደፍርም በአንዳንድ ቦታዎች ተመል ክቼአለሁና ይስተካከል፡፡

ሳሙኤል
/አሣሣ/

## መዝሙርን እንደ ፋሽን

አንዳንድ ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችንን ሕግና ሥርዓት ጠብቀው የሚወጡ መዝሙሮች ቃለ እግዚአብሔር መሆናቸውን እየዘነጋን የቆዩ መዝሙራትን በመተው አዳዲሶቹን ብቻ ስናዳምጥ ይታያል፡፡ በመሠረቱ የቃለ እግዚአብሔር አሮጌ የለውም፡፡ ዓለም የቆዩትን ዘፈኖች እየተወ አዳዲስ ናቸው የሚላቸውን እያሳደደ በሚያዳምጥበት በዚህ ዘመን በምእመናን ዘንድም እንዲህ ዓይነት መጥፎ ልማድ ሊፈጠር አይገባምና ልናስተውል ይገባል፡፡

ማሞ
ግምጃ ቤት

*መንገደኛው*

## እንዲህ ነው የድፍረት ኃጢአት

«የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ፤ ያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ፡፡» /መዝ 18÷13/፡፡ ሰባኪ የሆንኩ አይምሰላችሁ÷ ዛሬም መንገደኛው ነኝ፡፡ ጥቅሷ ግን ጸሎት ናት፡፡ እኔ እንኳን ስለ ጸሎት ባውቅም አልጸልይም፡፡ መንገደኛ ነኝ፡፡ አሁን ግን ግድ ስለመጣ÷ መጸለይ ጀምሬያለሁ፡፡ «የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ፡፡»

ዕለቱ እሑድ፣ ሰዓቱ ከሰዓት፣ ጣቢያው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ ፕሮግራሙ መዝናኛ፣ ቦታው ከአንድ መዝናኛ ስፍራ ነው፡፡ መንገደኛው እግሬ መሔድ አይታክተው ወደ መዝናኛ ይዞኝ ዘው፡፡ የምወደውን ነገር ይገፌ ቁጭ፡፡ በቴሌቪዥኑ መስኮት አሻግሬ ባይ አንዱ «ይዘፍናል»፡፡ « ሁሌ ... ሁሌ...» ዘፈኑ ነው፡፡ ዘፈኑ ብዙ ቅንብር አለው፡፡ አንደኛው ቅንብር ግን የመንገደኛውን ልብ .ያቆሰለ ነው፡፡ መነኩሲት ናቸው፤ ቆብ አድርገዋል፤ መቋሚያ ይዘዋል፡፡ ልብ አድርጉ መቋሚያቸውን ወርውረው፣ ወደ ዘፈኑ ሲገቡ ያሳያል ቅንብሩ፡፡ አሮጊት ሳይሆኑ መነኩሲት መሆናቸውን በቆባቸው ተረዱ፡፡ መነኩሲቷ ቆቧን፣ መቋሚያዋን ረስታና ጥላ ወደ ዘፈን ስትገባ፡፡ አንድ ድፈረትና ንቀት፡፡

«የቅንብሩ ድፍረት» ሌላ ብዙ ብዙ ድፍረቶችን አስታወሰኝ፡፡ አንዱ አርቲስት ነኝ ባይ በቁሶቹ ሲቀልድ ደግሞ የሰማሁት ቀልዱንና ድፍረቱን እንደ ቁም ነገር ካሳተመው ካሴት ነው፡፡ ምን ብሎ እንደማትሉኝ ነው፡፡ የእርሱን የድፍረት ቃል መጻፍ ራሱ ተባባሪ መሆን ነው፡፡ አርቲስቱ «የአርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነኝ» እንደሚል ነው የሰማሁት፡፡ በ40ኛው ቀኑ አጥምቆ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆን ባደረገው ቄስ ላይ ይቀልዳል፡፡ ሁለት ድፍረት፡፡

ሦስተኛው÷ ድፍረት÷ ሌላኛዋ አርቲስት ናት፡፡ ሰውዬውን ወድዳው እርሱ ደግሞ ቸለል አላት መሰለኝ፡፡ ስለዚህ «የእንጦጦዋ ማርያም ገላግይኝ፤ ከእርሱ ለይኝ አስጥይኝ..» እያለች ዘፈን ልበል እንትትን ታስነካዋለች፡፡ አርቲስቷ ባለትዳር መሆኗን የሰማሁት በኋላ ነው፡፡ የእንጦጦዋን፣ የግሽን ማርያም እያለች የምትዘፍነው ለካስ በእውነት ተቸግራ ሳይሆን Business System ነው፡፡

አራተኛውን ድፍረት ልንገራችሁ፡- ወንድ አርቲስት ነው፤ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንደነበር ሲያወራ አንድ ቀን የሰማሁት መሰለኝ፡፡ እርሱም የመድኃኔዓለምን ግርፋትና ሕማም እየተወዛወዘ ሲዘፍንበት ያን ሰሞን በሰሙነ ሕማማት ወቅት በዚሁ በቴሌቪዥን ዐየሁ፡፡

ጸሐፊው ቢጽፍ፣ ዘፋኙ ቢዘፈን፣ ባለተውኔቱ በመድረክ ቢተውን፣ ባለቅንብሩ ቢያቀናብር፣ ጋዜጠኛው ቢተች አርቶዶክስን፣ቀሳውስትን፣ ዲያቆናትን፣ የአብነት ተማሪዎችን ነው፡፡ የዘፈኑ የቀልዱ ሁሉ «ማጣፈጫ» የእንጦጦዋ÷ የግሸኗ ማርያም ነው፡፡ ግን ለምን? የመንገደኛው ጥያቄ ነው፡፡ ማጥላላት፣ ማስጠላት፣ መተቸት ወይስ ሌላ? በዓላማ፣ ለገንዘብ፣ የዕውቀት ማነስ ወይስ...? ሁሉስ ቢሆን?

መንገደኛው ዕውቀት የለውም፡፡ አንድ ነገር ግን ያስባል፡፡ ለምንድን ነው አንዳንድ አርቲስቶች ቤተ ክርስቲያንን የሚዳፈሯት? ካህናቶቿንስ የሚንቋት? እንደ መንገደኛው አሳብ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡

1. አለማወቅ
2. ፈንገጥ ያለ ነገር አቅርቦ ታዋቂነትን ለማግኘት
3. ከዘፋኞቹ በስተጀርባ ያሉ ሰዎች ተጽዕኖ
4. የቤተ ክርስቲያኒቱና የአገልጋዮቿ ዝምታ
5. የትንቢት ፍጻሜ፤ « የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች በሁሉ ይገፋሉ፣ ይጠላሉ፣ ይናቃሉ፡፡» /1ቆሮ.4÷10-13/

መንገደኛው ልቤ አንድ ነገር ይላል፡፡ ቀልድና ትችት የግለሰብን ኑሮ ይደጉም እንደሆን እንጂ አገርን አያለማም፡፡ እንደ ቀልድ ከተባለስ ምነው በድርቁ፣ በረኀቡ፣ በጉበኛውስ ለትዳር ጓደኛው አልታመን ባለውስ ቢቀልድ? ለዚያውም አስቆ አዝናንቶ ማለፍ ሳይሆን ሊያርም ሊያስተካክል በሚችልበት መልኩ ቢሆንስ? ከዚህ ውጭ ግን እናቴ ናት እያልን ቤተ ክርስቲያንን፣ አባቴ ነው ብለን መስቀሉን እየተሳለምን ቄሱን የምንተች ከሆነ አርቲስት ከመባል ሌላ ስያሜ ቢሰጠን ይሻላል፡፡ እናቱን አባቱን የሚተች የጥበብ ሰው ሊሆን ስለማይገባው መንገደኛው ልቤ «በቃኝ÷ እንሒድ» አለኝ፤ «ሕግ የለ፣ ጠያቂ የለ፣ ጉልበተኛ የለ» ብሎ ከመዳፈር አውጣኝ፡፡ በቸር ያሰንብተን፡፡


**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ**

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለባለው ታደለ እና/ወይም መስፍን ጥላሁን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አራዳ ቅርንጫፍ
Balew Tadelle and/or Mesfin Tilahun
የባንክ ሒሳብ ቁጥር 68608 አዲስ አበባ ከፍለው
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ



## ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ

ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የከንባታ፣ ሀዲያ፣ጉራጌና ስልጢ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ::

በቦታው የአገልግሎት ጊዜያቸውን ባጠናቀቁት በብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ የጅማ፣ ከፋ ሸካና ቤንቺ ማጂ አህጉረ ስብከት ጳጳስ የተተኩት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ቤተ ክርስቲያንን እንዲመሩና እንዲያገለግሉ ከፍተኛ ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል::

ብፁዕነታቸውም የተጣለባቸውን ከፍተኛ የቤተ ክርስ ቲያን ኃላፊነት ተቀብለው ሥራቸውን ጀምረዋል::

ማኅበረ ቅዱሳን ለብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆንላቸው ምኞቱን ይገልጻል::

ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር -መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ፍቅርተ ኃይሌ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org

«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

ሐመር
፲፪ኛ ዓመት ቁጥር ፪
ግንቦት/ሰኔ ፲፱፻፺፮ ዓ.ም.

# ይዘት

የማኅበሩ መልእክት
- የማይገለጥ የተከደነ ÷ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም.......................................፪
ደብዳቤዎች .......................................፬
ከሰሞኑ በረከት
- የእግዚአብሔር መዓዛዎች.......................................፮
ትምህርተ ሃይማኖት
- ተዘክሮተ ሞት.......................................፱
- ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም.......................................፲፬
ኪነ ጥበብ
- ሰባኪ ሕይወት.......................................፲፮
እናስተዋውቃችሁ
- አባ ሃደራ .......................................፲፰
- ቅዱስ አርሳንዮስ .......................................፳
ዓምደ ወራዙት
- ወጣትነት እንደ ዮሴፍ.......................................፳፩
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
- ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?.......................................፳፫
ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
- የኢ.ኦ.ተ.ቤ መገናኛ ብዙኃን.......................................፳፭
- ዝክረ አቡነ ጴጥሮስ .......................................፴፫
- የጽሕፈት ቋንቋ የሆነው.......................................፴፭
ስሙጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
- ተውሳከ ግስ.......................................፴፱

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::

## «የማይገለጥ የተከደነ ÷ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም::»

/ሉቃ.12÷2/

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ይህንን ቃል የተናገረው ከብዛት የተነሣ መቆሚያ መቀመጫ አጥቶ እርስ በርሱ እስኪረጋገጥ ድረስ ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታና ጊዜ ነበር:: ቅዱሳት መጻሕፍትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሚያስተምሩት ጌታ አዳምንና ልጆቹን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዚህ ምድር በሚያስተምርበት ዘመን በየዕለቱ ቁጥሩ ከአምስት ገበያ ያላነሰ ሕዝብ ይከተለው ነበር:: ይህ ሁሉ ሰው ጌታን ቢከተልም የሚከተልበት ዓላማና ምክንያት ግን የተለያየ ነበር:: አንዱ ከበሽታው ለመፈወስ ሲከተለው፣ ሌላው ምድራዊ ምግቡን /ኅብስት ምድራዊ/ ለማግኘት ይከተለው ነበር፤ አንዱ መልኩን ለማየትና ድምፁን ለመስማት ሲከተለው፣ ቀሪው ደግሞ ጌታን ለመወንጀል ÷ ይህን ተናገረ! ይህን አደረገ! በማለት ለማኅበረ አይሁድ ወሬ ለማቀበል ይከተለው ነበር:: ከዚህ ሁሉ ሕዝብ መካከል ቃሉን ሰምቶ ሕይወትን ለማግኘት የሚከተለው በጣም ጥቂት ሰው ነበር:: ከዚያም መካከል እንደ ይሁዳ ያሉት ወዳጅ መስለው ቆይተው በመጨረሻ ሰዓት ጌታን በሠላሳ ብር ሸጠውታል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሁሉንም ልቡና /አሳብ/ ያውቅ ነበርና «የማይገለጥ የተከደነ÷ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም» /ሉቃ. 12÷2/ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱ ተናገረ::

ከአዳም ጀምሮ የሰውን ልጅ ታሪክ ሳንመለከት በአብዛኛው መጥፎ ነገር ለመሥራት ሲያስብ ማንነቱንና ዓላማውን ደብቆ ይይዛል:: ተቆርቋሪና አሳቢ መስሎ ይቀርባል ÷ ያታልላል፤ ውስጡ ግን ሌላ ነው:: ይህንን ውስጣዊ ምንነት ጠንቅቆ ማወቅ ለሰው ልጆች ቢረቅም ለእግዚአብሔር ግን ሁሉም ነገር ግልጥ ነው:: ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር እርሱ ሁሉንም ከመሆኑ አስቀድሞ ያውቀዋልና:: አንድ የተደበቀ ዓላማ በሥራ ከተፈጸመ በኋላ ግን እውነትንና ሐሰትን፣ ደግነትንና ክፋትን፣ ቅንነትንና ተንኮልን ሁሉም ሰው ለመለየት የሚችል መሆኑ ተገልጿል:: ተግባር የውስጣዊ ማንነት መገለጫ ፍሬ ስለሆነ መልካሙና ክፉው በቅጠልና በአበባ ወቅት ሳይሆን ከፍሬው ይታወቃል:: ጌታም «ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ» /ማቴ. 7 ÷ 20/ ብሏል::

ማኅበረ ቅዱሳን በዚህ ርእስ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተነሣበት ምክንያት ከጥቂት ዓመታት በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ተሰብስበው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነት፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትና ታሪክ የሚያጠፋ ተግባር ሲፈጽሙ የነበሩና አሁንም እየፈጸሙ ያሉ አንዳንድ አካላት ከቀደመ መጥፎ ተግባራቸው ሳይመለሱ ለቤተ ክርስቲያንና ለወንጌል አገልግሎት ተቆርቋሪ መስለው ለመታየት የሚያደርጉት ጥረት ቤተ ክርስቲያንን እንዳይጎዳ ለምእመናንና ለሚለከታቸው አካላት ለማሳሰብ ነው::

ዛሬ እነዚህ አካላት ከየአቅጣጫው በልዩ ልዩ መልክ የሚሰነዝሩት ሐሳብ ለቤተ ክርስቲያንና ለወንጌል አገልግሎት ከመቆርቆር የመነጨ እንደ ሆነ አድርገው ለማቅረብ ሲጥሩ ይታያሉ:: ይኸውም ከቤተ ክርስቲያን አንጻር ቆመው «ቤተ ክርስቲያን ተጐዳች፤ ተከፋፈለች፤ ኃይሏን እያጣች ነው፤ ለወደፊቱም ህልውናዋ ያሰጋል፤ እነ እገሌ ይህን ሠሩ! እነ እገሌ ደግሞ ይህን መሥራት ሲገባቸው አልሠሩም ወዘተ» እያሉ በመናገርና በመጻፍ ምእመናንን ለማሳሳት እየሞከሩ ይገኛሉ:: ነገር ግን የእነዚህ አካላት ተቆርቋሪ መምሰል «መምህር ሆይ ÷ ጌታዬ ሆይ» እያለ ጌታውን ከሸጠው ከይሁዳ ተለይቶ የሚታይ አይደለም:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስምዖን ቤት ተቀምጦ ሳለ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ሽቱ አምጥታ በጌታ እግር ላይ ስታፈስ ይሁዳ ለድሆች ተቆርቋሪ በመምሰል «ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው?» ብሎ ተናግሮ ነበር:: ዮሐ 12፥5:: ይህ የይሁዳ አባባል ማንነቱን ለማያውቅ ሰው ደግኛ ሐሳብ የያዘ ቢመስልም፤ ውስጣዊ ማንነቱን በሚገባ ያውቀው የነበረው ወንጌላዊው ዮሐንስ ግን «ይህንንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው::» ብሏል:: ዮሐ. 12፥6::

በዘመናችን ያሉ ተረፈ ይሁዳዎችም እውነተኛ ማንነታቸውንና ዓላማቸውን በውስጣቸው ይዘው ለቤተ ክርስቲያን ህልውናና ክብር የተቆረቆሩ በመምሰል ከእነርሱ ያልሆኑ የማወናበጃ አሉባልታዎቻቸውን በተለያዩ መንገዶች ሲያሰሙ ይታያሉ:: «አናውቅሽም፣ አላሳደግሽንም፣ አላስተማርሽንም» ብለው የተለዩአትን ቤተ ክርስቲያን የቅሰጣ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ሲሉ «ቤተ ክርስቲያን ተደፈረች፤ ሊቃውንቷ በአሳዳጆች ተንገላቱ፤ የቀደመ ማንነቷን አጣች፤ ታሪኳ፣ ትምህርቷ፣ ሥርዓቷና ትውፊቷ ተበረዘ» በማለት ውስጠ እሬት «አሳቢነታቸውን» ይነዛሉ:: በዚህ መልክ ለሚዘረዝሯቸው የፈጠራ አሉባልታዎች በተጠያቂነት ከሚያስቀምጧቸው አካላት አንዱ ማኅበራችን እንደ ሆነ በየጊዜው እያባዙ ከሚበትኗቸው የአሉባልታ ክታቦቻቸው ለመገንዘብ ይቻላል:: ማኅበረ ቅዱሳን «ስንቅና ውሸት እያደረ ይቀላል» እንደ



' www.eotcmk.org

ሚባለው የእነዚህ ሰዎች ማንነት ቀድሞም ሆነ አሁን እንደ ሆነው ወደ ፊት በይፋ እንደሚገለጥ ያምናል። ይሁን እንጂ ለጊዜው ይህንን ወተቱን የሚያጠቁር፣ እሬቱን የሚያጣፍጥ አሉባልታ በማውራት የሚተጉባቸውን ምክን ያቶች ምእመናን ዐውቀው በያሉበት ጥንቃቄ በማድረግ ቤተ ክርስቲያናቸውን ይጠብቁ ዘንድ ይህንን ለማድረግ ያነሣሷቸውን ምክንያቶች በሚመለከት ጥቂት ነጥቦችን ለማቅረብ እንወዳለን፡፡

እነዚህ አካላት ማኅበራችንንም ሆነ ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል የሚተጉ ሌሎች አካላትን በተለያዩ መንገዶች ለመወንጀል የሚተጉት ለምን ይሆን?

1. ኑፋቄንና ክህደትን ለማስፋፋት፡-

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምናውቃቸው አብዛኞቹ መናፍቃን ኑፋቄያቸውን በግልጽ አስቀምጠው ፊት ለፊት የሚከራከሩ ቢሆኑም፤ በአፍኣ መልካምና ለቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ እምነት ጠበቃ መስለው አመቺ ጊዜና ቦታ ሲያገኙ የኑፋቄ መርዛቸውን የሚረጩ መናፍቃን አልፎ አልፎ አልጠፉም። «አንድ አካል አንድ ባሕርይ ብዬ በማስተማሬ ተወገዝኩኝ» ብሎ ታላላቆቹን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ያሳሳተውን አውጣኪን ማስታወስ ለዚህ አባባል ማስረጃ ይሆናል። በጉባኤ ኤፌሶን የንስጥሮስ የሁለት ባሕርይ ትምህርት ከተወገዘና የተዋሕዶ ሃይማኖት ከተደላደለች በኋላ በቁስጥንጥንያ የአንድ ገዳም አበ ምኔት የነበረው ይህ ግሪካዊ መነኩሴ ቀድሞ የንስጥሮስን ትምህርት ይቃወም እንዳልነበር የአሪስጣጣሊስን የቅመማ ሕግ በምሥጢረ ሥጋዌ አስገብቶ «ሥጋና መለኮት በተዋሕዶ ጊዜ መለኮት ሥጋን ውጦታል፤ መጦታል» እያለ በአደባባይ ይሰብክ የነበረ ሰው ነው። ይህ ትምህርቱ በተሰማ ጊዜ በፍላብያኖስና በሀገረ ስብከቱ ኤጲስ ቆጶሳት አማካይነት በጉባኤ አድያም ተወግዞ ተለየ። ይሁን እንጂ ይህ መናፍቅ ውግዘቱን ባለመቀበል «የቅዱስ ቄርሎስን ሃይማኖት ስለ መሰከርኩ በሐሰት ተወገዝኩኝ» በማለት ያወገዙትን ሊቃውንት በዐይነ ደረቅነት ተቃውሞ ነበር።

በዚህ እኛ በያዝነው ዘመን ያሉ መናፍቃንም ሞያ ብለው የያዙት ፈሊጥ ይኸንን ፍጥጥ ያለ የማሳሳቻ መንገድ ይመስላል። የኑፋቄ ትምህርታቸው በወሬ ሳይሆን በተጨባጭ ማስረጃ የተገለጠባቸው፤ በዚህም በቅዱስ ሲኖዶስና በሊቃውንት ጉባኤ ፊት ቀመው የተመሰከረባቸውና ተወግዘው የተለዩ ሆነው ሳለ «እኛ ምንም ዓይነት የክህደት ትምህርት አላስተማርንም፤ እኛን የጠሉ እንደ ማኅበረ ቅዱሳን ያሉ ስማችንን አጥፍተው እንድንለይ አደረጉን እንጂ» በማለት ለውርደታቸው ምክንያትና ተጠያቂ ሲያስቀምጡ ይታያሉ፣ ይሰማሉ። በዚህ ረገድ መናፍቃኑ ባሉበት ሆነው «ጠላታችን፣ አሳዳጃችን ወዘተ.» በማለት የሚከሱት ማኅበራችንን ነው። በመሠረቱ በኑፋቄ ተገኝቶ፣ ያንንም ቤተ ክርስቲያናችን አጣርታ ከለየችው ማንኛውም ግለሰብም ሆነ ድርጅት ጋር ማኅበራችን ምንም ዓይነት ግንኙነት አይኖረውም። በዚህም ጠላት የሚለው ስም ቀርቶ ሌላም ቢሰጠው ይደስታል እንጂ አያዝንም። ብርሃን ከጨለማ፣ ጽድቅ ከዐመፅ፣ የሚያምን ከማያምን ጋር ኅብረት የለውምና። 2ኛ ቆሮ.6 ፥ 14 - 17።

እነዚህ ሰዎች ዛሬ በቃልም ሆነ በጽሑፍ በሰፊው እያሠራጩ ያሉት አሉባልታ «ማኅበረ ቅዱሳን ታላላቅ የቤተ ክርስቲያኒቱን ሊቃውንት እያሳደደ ቤተ ክርስቲያኒቱን ባዶዋን ሊያስቀራት ነው» የሚል ነው። ይህ አባባል ፍጹም ሐሰት ከመሆኑም በተጨማሪ በመሠረቱ ለቤተ ክርስቲያንና ለሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ከመቆርቆር የመነጨ አይደለም።

ለመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን ያሳደዳቸው ሊቃውንት እነማን ናቸው? ምናልባት በአገር ቤት በመናፍቃኑ አዳራሽ ፓስተር ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩትንና አሁን ውቅያኖስ ተሻግረው «ንስሐ ገብተናል፣ ቅስና ይገባናል» የሚሉትን ይሆንን? ነው ወይስ ማንነታቸው በተጨባጭ ማስረጃ ተገልጾ ቤተ ክርስቲያን አውግዛ የለየቻቸው መናፍቃን ይሆኑን? ወይስ «ምንኩስና አያስፈልግም፣ እስከ አሁን በውስጡ መቆየታችንም ስሕተት ነበር» በማለት አርአያ ምንኩስናቸውን በሕዝብ አደባባይ አውልቀው ወደ መናፍቃን አዳራሽ ጠቅልለው የገቡትን ይሆንን?

በመሠረቱ እነዚህን መናፍቃን ከቤተ ክርስቲያን አንድነት የለየቻቸው ለልጆቿ መንፈሳዊ ጤና አብዝታ የምታስብ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንጂ ማኅበረ ቅዱሳን አይደለም። በዚህ ሒደት የማኅበረ ቅዱሳን ድርሻ ቀሳጥያኑ በገቡበት ገብቶ ፥ የተጠቀሙበትን መሣሪያ ተጠቅሞ ፥ ትክክለኛ ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ለወሳኙና ቤተ ክርስቲያንን እንዲህ ከመሳሰሉት በሽታዎች ሊጠብቁ አደራ ለተሰጣቸው አባቶች ማቅረብ ብቻ ነበር። ነገር ግን ይህ የማኅበራችን አስፈላጊና ወቅታዊ እንቅስቃሴ ተቋርጦ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጣብቀው የክህደት ዓላማቸውን ለማሳካት ያሰቡ አካላት «ማኅበረ ቅዱሳን አሳደደን፣ ሊቃውንትን እያሳደደ ቤተ ክርስቲያንን ኦናዋን ሊያስቀራት ነው» በማለት ምእመናንን ለማደናገር ጥረት ያደርጋሉ። ለነገሩ ይህንን የሚሉት አካላት የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ስለሌላቸው፣ ታሪኳንም ስለማያውቁ ሊገነዘቡት አልቻሉም እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሚያወጣቸውም ሆነ የሚያኖራቸው ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ አምላክ በመሆኑ እንኳን «የአንድ ማኅበር አሉባልታ» የተወረወረ ጦርና የተሠነዘረ ሰይፍም ቢሆን ሳያሳድዳቸው በአታቸውን አጽንተውና ከአገልግሎታቸው ሳይርቁ የኖሩና የሚኖሩ ናቸው።

ማኅበረ ቅዱሳን ግን መናፍቃኑ እንደሚሉት ሳይሆን ሁሉም በሚያየውና በሚረዳው ሁኔታ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በሀገር የመጣ ችግር ግንባር ቀደም ተጠቂዎች ናቸውና በሥጋቸው የሚመጣባቸውን ፈተና በያሉበት አሸንፈው አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ከተለያዩ በጎ አድራጊ ምእመናን ጋር በመተባበር ድጐማና ደመወዝ እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ይገኛል። ወደ ፊትም አምላክ አበውን አጋዥ በማድረግ ይህንኑ ተግባሩን በሰፊው ይቀጥልበታል።

2. የቀደመው መጥፎ ታሪክ እንዳይነሣ ለመከላከል፡-

በመሠረቱ አንድ ክርስቲያን ተሳስቶም ይሁን አስቦበትና ኾነ ብሎ ለሠራው በደል ንስሐ መግባትና ከአምላኩ ጋር መታረቅ ይገባዋል። በተለይ በአደባባይና በግልጥ የተሠሩ ጥፋቶች በታሪክ ዐይን እየተነሡ



' www.eotcmk.org

መወሳታቸው አይቀርም:: ጥፋተኛው በሕይወት ባለበት ዘመን ግን ጥፋቱን በጥሩ ሥራ ለማስተካከል ጊዜ አለው:: ይኽንንም ሊጠቀምበት ይገባል:: በዘመናችን ያለው ሁኔታ ግን ሁሉም የሚያውቀውን ጥፋት ማኅበረ ቅዱሳን ካወቀው ስለ ማያስቀምጠን አስቀድሜ ማኅበሩ «ለቤተ ክርስቲያን አይጠቅምም፤ አደጋ ነው» ብዬ ልቅደመው ሆኗል:: ይህ ሐሳብ ለቤተ ክርስቲያን ከማሰብና ከመቆርቆር የተገኘ አይደለም:: ራስን ለመከላከል የተደረገ የሞኝ ጥበብ ነው:: እነዚህ ሰዎች ይህንን የሞኝ ጥበባቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ለማኅበሩ የተለየ ስምና ታሪክ እየሰጡ በውስጥም ይሁን በውጭ በሚታተሙ ጋዜጦች አሉባልታቸውን ሲያናፍሱ ይታያሉ::

በመሠረቱ ማኅበራችን የግለሰቦችን ያለፈ ታሪክ እየመረመረ የሚገልጽበት ጊዜውም ፍላጎቱም የለውም:: በቤተ ክርስቲያን ታሪክም መጥፎ የሠሩ ሰዎች ሥራቸው ይገለጽ ዘንድ ማኅበር ወይም ግለሰብ አያስፈልግም:: ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ አምላክ ራሱ ማንነታቸው ይገልጸዋልና:: «የማይገለጥ የተከደነ ፥ የማይታወቅ የተሰወረ የለም» እንዳለ:: /ሉቃ. 12 ፥ 2/:: በዚህ መንገድ የሌለውን ስምና ዓላማ ፥ ያልዋለበትን ታሪክ እየሰጡ ማኅበራችንን ለመጉዳት የተነሡ ሰዎች ከዚህ ይልቅ በእግዚአብሔርም ሆነ በሰዎች የሚታወቅ መጥፎ ሥራቸውን በንስሐ ለመደምሰስ ቢተጉ መልካም ነው እንላለን::

3. **በክፉ የቅንዓት ስሜት ከመቃጠል፡-** ክፉ ቅንዓት ዛሬ ሳይሆን የሰው ልጅ የትውልድ ሐረግ ገና በወግ ሳያቆጠቁጥ የተጀመረ መጥፎ ምግባር ነው:: ቃየን በቅንዓት መንፈስ ተነሣስቶ የእናት የአባቱን ልጅ አቤልን ገድሏል:: /ዘፍ. 4 ፥ 8/:: ይህ መንፈስ ከሰው ልጆች ይርቅ ዘንድ አበው መምህራን በየዘመኑ አስተምረዋል:: በሕይወታቸው እየተረጎሙም ሰብከውታል:: ይሁን እንጂ የሆነው ጥረት ሁሉ ቢደረግ ይህ መጥፎ መንፈስ ከሰው ልጆች አልራቀም::

ዛሬ በማኅበራችን ላይ እየተሰነዘረ ያለው መሠረተ ቢስ ውንጀላና የስም ማጥፋት ዘመቻ ከመጥፎ ቅንዓት የመነጨ እንደ ሆነ ማኅበራችን በውል ይገነዘባል:: ማኅበሩ ጥሩ ሠርቶ ከተገኘ «እርሱ ማነውና ነው ይህንን የሚሠራው? ለምን እንዲሠራ ይፈቀድለታል?» የማኅበሩ አባላትና መምህራን በአገልግሎታቸው ምእመናን ሲቀበሉአቸው ከታየ ደግሞ «የት ተምረው ነው የሚያስተምሩት?» ወዘተ እያሉ ስምን በማጥፋት መኖር ለቤተ ክርስቲያን ከመቆርቆርና ከመልካም ስሜት የመነጨ አይደለም:: ዋናው ቁም ነገር መሆን የሚገባው ማንም ይሥራው የተሠራው ሥራ ጠቃሚ ነው? ወይስ አይደለም? ትምህርቱስ ስሕተት አለው? ወይስ የእውነተኞቹ ኦርቶዶክሳውያን አባቶቻችን ትምህርት ነው? ብሎ መጠየቅና ስሕተትን ማረም ነው:: ማንም ሰው ቢሆን ሳይማር የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርት እንደ ፍላጎቱ እያጣመመ እርሱ በመሰለው ትርጉም እንዲያስተምር አልተፈቀደለትም:: የቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት ፥ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ ሊያስተምር ይገባል:: ወንድ ሴት፣ ትልቅ ትንሽ፣ ሀብታም ድኻ ብላ ሳትለይ ሁሉንም በእኩል ዐይን እንደ አንድ ቤተሰብ በምታስተዳድር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዱ ለሌላው ያለምንም ምክንያት እንቅፋት መሆን የለበትም::

ማኅበረ ቅዱሳን የእውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጆችንና ማኅበራትን ዕድገት እንጂ ጥፋት ለማየት አይፈልግም:: በመሆኑም በዓላማ አንድ ከሆኑት ጋር አብሮ ይሠራል:: በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ተሰባስበው በእውነት ለእውነት ለሚያገለግሉ አካላት አንዱ ለሌላው አካሉ እንጂ ጠላቱ አይደለምና:: ቤተ ክርስቲያንን የሚያውክ ስውር ዓላማ ይዘው የሚመጡ ትን ግን መቼም ቢሆን ማንነታቸውን ከመግለጥ አይቆጠብም::

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተገለጹት ዋና ዋና ምክንያቶች የተነሣ ስውር ዓላማንና የግል ፍላጎትን ለማሳካት የተነሡ አካላት በጥፋት ጎዳናቸው ላይ እንቅፋት ሆኖ የከለከላቸው ማኅበሩ እንደ ሆነ በማሰብ ሊያወርዱበት የሚያስቡትን ማንኛውንም የፈጠራ ወሬ በመናገርና በመጻፍ ላይ ይገኛሉ:: ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደ ምንማረው ተረፈ አርዮሳውያን ቅዱስ አትናቴዎስን «ኤጲስ ቆጶስን ገድሏል፣ ካህኑን ደብድቧል፣ በዝሙት ተገኝቷል፣ ፖለቲከኛ ነው» በማለት በሐሰት ከሰውት ነበር::

ዛሬም ማኅበረ ቅዱሳንን በእርሱም ሰበብ ቤተ ክርስቲያንን ለመውጋት ያሰቡ አርዮሳውያን ለማኅበሩም ሆነ ለአባላቱ ልዩ ልዩ ስም እየሰጡ በመወንጀል ሲተጉ ይታያሉ:: ከውንጀላዎቻቸውም ውስጥ «ማኅበሩ ቤተ ክርስቲያን ልታገኝ የሚገባትን ገንዘብ ወደ እርሱ ካዝና ይከታል፤ የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ለመያዝ ይንቀሳቀሳል፤ ቤተ ክርስቲያን መደበቂያ አድርጎ ስውር ፖለቲካዊ ዓላማውን በማስፈጸም ላይ ይገኛል፤ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ያሳድዳል፤ አባላቱ ሌቦች ናቸው፣ ዘማ ናቸው ወዘተ.» የሚሉት ይገኙበታል::

በመሠረቱ በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ሕይወት በልዩ ልዩ መንገድ መወንጀልና መከሰስ በማኅበራችን የተጀመረ አዲስ ክስተት አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ለሰው ልጆች ድኅነት ራሱን በመስቀል ላይ ቤዛ ባደረገ አምላክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ የነበረና ወደ ፊትም የሚኖር ነው:: በመሆኑም ማኅበራችን ማንነታቸውን ጠንቅቆ በሚያውቃቸው አሉባልተኞች ከእዚህም በላይ ስም እየወጣለት ቢወንጀልም ወንጀሉን እስካልፈጸመው ድረስ አያፍርበትም:: ለዚህም መልስ ለመስጠት ወርቃማ የሥራ ጊዜውን አያጠፋም:: «ሰይጣን ሆይ ፥ እፈር፤ አገልግሎቴን አጠናክሬ እቀጥላለሁ» ይላል እንጂ ፈጽሞ አያዝንም:: አጽራረ ቤተ ክርስቲያን እንኳን ለእኛ ለቅዱሳን ሐዋርያት ማኅበርም የተለያዩ ስሞች ይሰጡ ዘንድ የከፋ ተፈጥሯቸውና ሸውራራ ዓላማቸው ግድ ይላቸዋልና::

ስለዚህ ምእመናን ፥ መምህራንና የቤተ ክርስቲያን አባቶች እውነትን ከሐሰት፣ ብርሃንን ከጨለማ በመለየት ቤተ ክርስቲያንን ከቀሳጥያን ሊጠብቁ ይገባል:: ጌታችን እንደ ተናገረው ተደብቆ የሚቀር ምንም ነገር የለም:: ጊዜውን ጠብቆ ሁሉም ይፋ ይወጣል:: እውነትን ለመያዝና መልካም ሥራን ለመሥራት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ዝግጁነት ልንተጋ ያስፈልጋል:: የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት፣ የቅዱሳን ረድኤትና በረከት አይለየን:: አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር::*



www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

## ጥር 12

በመጋቢት /ሚያዝያ እትም ኪነ ጥበብ ዓምድ «ከመጋረጃ ጀርባ» በሚል ርእስ የወጣው ልብ ወለድ ትምህርት እንደ እኔ ሁሉ ሌሎችንም እንዳስተማረ እርግጠኛ ነኝ:: ነገር ግን አንድ ጥቆማ አለኝ:: ይኸውም ከልብ ወለዱ እንዳነበብነው ያጋጠማቸውን ፈተና ሁሉ በእግዚአብሔር ኃይል ተቋቁመው ለቅዱስ ጋብቻ የደረሱት ወጣቶች የተጋቡት በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጥር 12 ቀን እንደሆነ ተገልጿል:: በዚህ ቀን ሁላችንም እንደምናውቀው የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ወርዶ ሥርዓተ ቅዳሴውም ሆነ ንግሡ የሚፈጸመው በዚያው በባሕረ ጥምቀቱ ነው:: ስለዚህ ወጣቶቹ ጥር 12 ቀን በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን ፈጸሙ የተባለው ስሕተት ይመስለኛል::

*ፍቅርተ ሥላሴ ጐባ*

ከአዘጋጁ:- እናመሰግናለን::

## ተመስሰ

የትንሣኤ እርድ ጉዳይ ለረጅም ዘመናት እኔንም ሆነ ቤተሰቦቼን ሲያስጨንቅና ሲያከራክር የኖረ ጉዳይ ነበር:: ነገር ግን ምስጋና ለመጽሔታችሁ ይሁንና ባለፈው መጋቢት/ሚያዝያ 1996 ዓ.ም. እትሟ ይህንን ጥያቄያችንን በሚገባ መልሳልናለች:: እግዚአብሔር ይስጥልን:: በተመሳሳይ ሁኔታ ሌሎች ጥያቄዎቻችንንም የቤተ ክርስቲያን አባቶችን በማነጋገር እንድትመልሱልን አደራ እላለሁ::

*ጌቱ ከበደ አ/አ*

## እንጠይቅ

በተለይ እኛ ወጣቶች ዜና ሕይወታቸውን እንዲሁም ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት ሲሉ ስለተቀበሉት የሰማዕትነት ጽዋ የማናውቅላቸውን ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን የሕይወት ታሪክ ባለፈው እትማችሁ በማቅረባችሁ ምን ያህል እንደ ተደሰትኩ መግለጽ ይሳነኛል:: በእውነቱ ቅዱስ አባታችን እምነታቸውንና ጽናታቸውን በተግባር የገለጹ ደገኛ አባት ናቸው:: የእርሳቸውን ዜና ሕይወትና ተጋድሎ ስናነብ ሁላችንም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ምን ዓይነት ዋጋ እየከፈልን እንደ ሆነ ልንጠይቅ፤ መልሱንም በተግባር ልናገኝ ይገባል::

*ዲ/ን ድረስ ረታ ደሎ መና*

## ጠቅሞናል

በእውነቱ ጥንታዊውንና የመንፈሳዊ ሀብታችን በር የሆነውን የግእዝ ቋንቋ ለማወቅ እንድንችል ዓምድ ከፍታችሁ እየሰጣችሁን ያለው ትምህርት እኔንም ሆነ ጓደኞቼን በእጅጉ ጠቅሞናል:: በግሌ ድሮ ባዕዳ የሆነኩለትን የቤተ ክርስቲያን ድምፅ ሰምቼ ለመረዳት ባልችል እንኳን ጆሮዬ ተከፍቶ እንድሰማው ትርጉሙን ለመገንዘብም ጥረት እንዳደርግ አድርጎኛል:: በዚሁ ቀጥሉልን::

*ወለተ መድኅን ደሴ*

## ወቅታዊ ጽሑፎች

በመጽሔቷ ከምታስተላልፋልን ወቅታቸውን የጠበቁ ትምህርቶች ብዙ እየተማርን ነው:: ለምሳሌ ባለፈው በሰሙነ ሕማማት በወጣችው እትም ላይ ሰሙነ ሕማማትን፣ የትንሣኤ እርድን በሚመለከት የተጠስተናገዱት ጽሑፎች በእጅጉ አስተምረውናል:: እባካችሁ በዚሁ ቀጥሉ::

*ጥላሁን በደሌ ጫጫ*

## ቢስተካከል

ባለፈው መጽሔት ላይ አንዳንድ የታይፕ ስሕተቶች ተመልክቼአለሁ:: በመሆኑም የሚከተሉት ቢስተካከሉ:: ገጽ 8 «ዓርብ» በሚል ንዑስ ርዕስ ሥር «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» ለሚለው የተሰጠው ጥቅስ ዘፍ. 20፥21 የተባለው ዘፍ.1፥26 ተብሎ ቢስተካከል:: ገጽ 14 «በትንሣኤ በዓል እርድ መከናወን ያለበት መቼ ነው?» በሚለው ርእስ ስር አንቀጽ 2 የመጨረሻ መስመር ላይ «በእውነት ደዌአችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከመ» ለሚለው የተ ሰጠው ጥቅስ ኢሳ. 53፥2 የተባለው በኢሳ 53፥4 ቢስተካከል::

*መ/ር አማረ ወንድሙ ባሌ አጋርፋ*

ከአዘጋጁ:- ለተፈጠረው የታይፕ ስሕተት ይቅርታ እየጠየቅን ስለተሰጠን ማስተካከያ እናመሰግናለን:

## አስደሳች

ማኅበረ ቅዱሳን ቁጥር 2 የኦሮምኛ መዝሙር አሳትሞ በማሠራጨቱ የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ በእጅጉ እቸገራለሁ:: ይኸኛው መዝሙር ከቁጥር አንዱም ሆነ ከሌሎች የኦሮምኛ መዝሙሮች ልዩ የሚያደርጉት በርካታ ነገሮች አሉ:: ጥቂቱን ለመጥቀስም በኦሪጅናል ካሴቱ ውስጥ በወረቀት በተስተካከለ ሁኔታ ተጽፎ የሚገኘው የጠቅላላ መዝሙሩ ስንኞች ሰንበት ት/ቤቶች በቀላሉ እንዲያጠኑት ሆኖ መዘጋጀቱ ካሴቱን ልዩ ያደርገዋል:: በእውነት ማኅበሩ ለኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ ምእመናን እያበረከተ ያለው አገልግሎት መናፍቃንን እያሳፈረ በመሆኑ በዚሁ ይቀጥል እላለሁ:: እግዚአብሔር ማኅበሩን ይጠብቅ::

*መ/ር ፍቅሩ ጉርሙ /ምዕ/ወለጋ - ሻምቡ/*

## አሳዛኝ

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ8/8/96 ዓ.ም ከቀኑ 7:300-8:00 ሰዓት ያስተላለፈው ዝግጅት በእውነቱ ሁላችንንም እንቅልፍ የሚነሳ ጉዳይ ነው:: ይኸውም በትግራይ ክልል የሚገኙ ጥንታውያት ገዳማት ያጋጠማቸውን ችግር የሚመለከት ነው:: በእውነቱ በአባቶቻችን ተጋድሎ የቆዩን ጥንታውያት ገዳማት በእኛ ዘመን እየጠፉ መሆናቸው የሚያሳዝንና የሚያስከፋ ነው:: ስለዚህ ሁሉም ምእመን እነዚህ ገዳማት ተጠብቀው በሚቆዩበት መንገድ ዙሪያ ሊወያይና የመፍትሔ ርምጃ ሊያስቀምጥ ይገባል::

*አሸብር ጥሩነህ*



www.eotcmk.org

# የእግዚአብሔር መዓዛዎች

/ዲያቆን ያረጋል አበጋዝ/

**«በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክርስቶስ መዓዛ ነንና፣ ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን።» /2ቆሮ.2÷15–16/**

ፈጣሬ ዓለማት እግዚአብሔር በባሕርይው ልዑል ምጡቅ ይሁን እንጂ በመግቦት በረድኤት ከፍጥረቱ የተለየ አይደለም። እንዲህም ስለሆነ በአምሳሉ በአርአያው የፈጠረው ሰው ከእርሱ ጋር ፍጹም የኾነ ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል፤ ሰው ወዳጅ አምላክ ነውና ሕይወቱ ከእርሱ ፈቃድ ጋር እንዲስማማ ይፈቅዳል።

በአንጻሩ ሰው አእምሮ ግዕዛን ያለው ፍጡር ነው። ለባዊ /ዐዋቂ/÷ ነባቢ /ተናጋሪ/ ነው። የወደደውን ለመሥራት የመምረጥ ነጻነት ተሰጥቶታል። በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ነው። የሰው የመጨረሻ ዓላማው ፈጣሪውን መምሰል÷ እርሱን ማመስገንና ከእርሱም ጋር መኖር ነው።

ዳሩ ግን በፈጣሪው ከተወሰነለት ድንበር አልፎ በምክረ ከይሲ የተታለለው ሰው ከፈጣሪው ተቀያየመ። በፍጡርና በፈጣሪ መካከል ኃጢአት የወለደው ልዩነት ተከሰተ። በዚህ ጊዜ የጥፋቱን÷ የስሕተቱን ዋጋ ተሰጥቶት ከነበረው ጸጋ ተራቆተ፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መኖር ተቋረጠ። ምንም እንኳን ግዕዛኑ ባይለየውም እግዚአብሔርን የሚያስደስት ጥሩ ሥራ ለመሥራት አልቻለም፤ እያደር እየባሰበትና እየደከመ ለዛውና ውበቱ ተጎሳቆለ፤ ከመራራቅም የተነሣ ፈጣሪውን እየዘነጋው ሔደ።

ሰው በዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ እንዳለ የመዳን ተስፋ የነበረው በራሱ መፍጨርጨር ሳይሆን ከእርሱ ውጭ በኾነ በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነበር። አዳም ከጠብ÷ ከድቀቱ በፊት የነበረው ጸጋ÷ ከውጭ ከአምላክ የተሰጠው እንጂ የባሕርዩ እንዳልነበረ÷ አሁንም ወደ ነበረበት ለመመለስ የእግዚአብሔር ጸጋ አስፈለገው። ስለዚህም ቀድሞ በረድኤት ሲመግበው የኖረ አምላክ በኋላ ዘመን ሰውን በፍጹም ይቅርታ ሊታረቀው÷ ወደ ቀደመ ቦታው ወደ ቀደመ ክብሩ ሊመልሰው ወደደ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችንም የመዳን ትምህርት (Soteriology) በጥንተ ተፈጥሮ የፈጠረውን ሰው ቃለ እግዚአብሔር÷ ወልደ እግዚአብሔር በራሱ÷ በባሕርይ አባቱ በአብ÷ በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ባደረገው አትሕቶ ርእስ አርአያ ገብርን ነስቶ በተለየ አካሉ በተ ወላዲነት ግብሩ ሰው ኾኖ ሥጋ ለብሶ *በሐዲስ ተፈጥሮ* ፈጠረው፤ ያጣነውን ልጅነት ለመስጠት፣የተራቆትነውን ጸጋ ለማምጣት። ሐዲስ ተፈጥሮም *«አምላክ መኾን»* ማለት ነው። አምላክ ሰው ኾኖ እኛ አማልክት ዘበጸጋ እንኾን ዘንድ፤ የባሕርዩ ተሳታፊዎች እንኾን ዘንድ፤ በአጠቃላይም የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆነ። /2ጴጥ.1÷4፤ ዮሐ.10÷34፤ 1ዮሐ.3÷1-10/። ኃጢአት ባመጣው ቅጣት ተንኮታኩቶ በወደቀ ጊዜ ተወስዶበት የነበረው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተመለሰለት። በክርስቶስ ያመኑ ሁሉ ከቁስለ ነፍስ ተፈወሱ፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገሩ፤ ከሙስና መቃብር ዘለዓለማዊነትን፤ ተስፋ ትንሣኤን አገኙ።

በሌላ በኩል ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈላቸው ክታቡ እንደ ተናገረው፦ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በሐዲስ ተፈጥሮ የተፈጠርነው ለበጎ ምግባር ነው። «እስመ ተግባሩ ንሕነ ዘፈጠረነ በኢየሱስ ክርስቶስ ለምግባረ ሠናይ፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።» /ኤፌ.2÷10፤ ቲቶ.2÷14/። ወልደ እግዚአብሔር ሰው የኾነበት አንዱ ዋነኛ ምክንያት ለበጎ ምግባር አርአያ ሊኾነን ነው። «የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኃጢአት አላደረገም÷ ተንኰል ከአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም÷ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር÷ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤» እንዲል። /1ጴጥ.2÷21-24/። *አሮጌው ሰውነታችን ተወግዶ በሐዲስ ተፈጥሮ ገንዘብ ባደረግነው አዲስ ሰውነት የምንፈጽመው በጎ ምግባር ለእግዚአብሔር የምናቀርበው በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕታችን ነው።* ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ እንዲህ ይላል፦ «በፍቅር ጸንታችሁ ኑሩ፤ ክርስቶስ እንደ ወደዳችሁ÷ ራሱንም ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ሊሆን መሥዋዕት ቁርባን አድርጎ እንደ ሰጠላችሁ።» ኤፌ.5÷2። የጌታችን እኛን መውደዱ የተገለጠው ልጅነትን በመስጠት፣ ጸጋን በማምጣት፣ ያማረ የተወደደ በጎ መዓዛ/መዓዛ ሠናይ/ ያለው ቁርባን÷ መሥዋዕት አድርጎ ራሱን ስለ እኛ ቤዛ በማቅረብ ነው።

ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው፣ ከብልየት ታድሰው፣ የመድኃኔዓለም ክርስቶስን ፍለጋ ተከትለው፣ አርአያውን ነስተው፣ በሃይማኖት አብበው መዓዛ ምግባራቸውን ማቅረብ የጀመሩ ቀደምት ክርስቲያኖች ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው።

ፍሩሀን የነበሩ ጥቡዓን /ደፋሮች/ ኾነው፣ ፈርተው የካዱትንና እየተንቀጠቀጡ ጥለውት የሸሹትን የክርስቶስን መስቀል ለመሸከም አላወላወሉም። ትንሣኤ ክርስቶስን ለመመስከር በየአደባባዩ ሲሯሯጡ የአይሁድና የአሕዛብ ቁጣና ተግሣጽ አልመለሳቸውም። /ግብ.ሐዋ.2÷38፤6÷30/። እንዲያውም ከአይሁድ ሸንጎ ተገፈውና ተገርፈው ሲወጡ የንጉሥ ማለፊያ ቀምሶ እንደ ወጣ ባለሟል ደስ ይላቸው ነበር። /ግብ.ሐዋ.5÷40/። ከዚህም በላይ እስከ ሞት ድረስ ሲወገሩ «ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው» /ግብ.ሐዋ.7÷60/ ብለው ለበደሏቸው ይቅርታን በመጠየቅ በእግር የተከተሉትን ጌታቸውን በግብር መስለውታል። /ሉቃ.23÷34/።

«ተመሰሉ በእግዚአብሔር ከመ ውሉድ ፍቁራን፤ የተወደዳችሁ ልጆች እንደ መሆናችሁ እግዚአብሔርን ምሰሉ» /ኤፌ..5÷1/ እንደ ተባለ ክፉውን በክፉ አልተቃወሙም፤ ጠላቶቻቸውን ወድደው÷ የሚረግሟቸውን መርቀው÷ ለሚጠሉዋቸው መልካም አድርገው÷ ለሚገድሏቸውና ለሚያሳድዷቸው ጸልየው ለሰማያዊ አባታቸው ልጆች ኾኑ÷ ሰማያዊ አባታቸውን መሰሉ። ለአልጫው ዓለም ጨው፣ ለጨለማው ዓለም የተራራ ላይ መንደር÷ የመቅረዝ ላይ መብራት በመሆን በሞት ዐዘቅትና መንገድ የሚዳክሩትንና የሚቀበዘበዙትን ወገኖች ለክርስትና ሕይወት ያበቁ÷ ያማሩና የተወደዱ የእግዚአብሔር መዓዛዎች ኾነዋል። የበጎ ምግባር መዓዛቸው አሳዳጆቻቸውን ሳይቀር ስቦ አቅርቦ በሰማይ ያለ አባታቸውን እንዲያውቁት፣ እንዲያምኑት፣ እንዲከተሉትና እንዲያመሰግኑት አገብሯቸዋል። ማቴ.5÷13-16፤ ግብ.ሐዋ.6÷7።

የጌታችን ትንሣኤ በቅዱሳን ደቀ መዛሙርቱ በምድር ላይ ከተገለጠና



www.eotcmk.org

ከተሰበከ፥ የሐዋርያት ድምፅ በምድር
ሁሉ ከደረሰ፥ ክርስትና ማፍራት ከጀ
መረ፥ ከቤተ እሥራኤል ቅዱስ ጳውሎስን
ያህል ሐዋርያ ከተጠራና ቤተ ክርስቲያን
ከአይሁድ ቤተ መቅደስና ዛኒጋባ ወጥታ
ወደ ብሔረ አሕዛብ ገብታ ከተስፋፋችም
በኋላ ክርስቲያን ከስሙ ጀምሮ እስከ
ተግባሩ የክርስቶስን ስምና ትእዛዙን
ተሸክሞ የሚኖር መሆኑ በተግባር ታይ
ቷል። ቅዱስ ጳውሎስ «የኢየሱስ ሕይወት
በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢ
የሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞ
ራለን» /2ቆሮ.4÷10/ እንዳለ ከሐዋርያ
ትም በኋላ በትሩፋታቸው፥ በትምህር
ታቸው እነርሱን መስለውና አኽለው
የተነሡ ሐዋርያውያን አበው፣ አፖሎጂ
ስቶችና ሊቃውንት ለሃይማኖታቸው ያላ
ቸውን ፍቅር በሰማዕትነት አሳይተዋል።

እንጨት በመዓዛው እንዲታወቅ
በእግዚአብሔር ዘንድ የክርስቶስ መታወ
ቂያው ሽታ ኾነዋል። መታወቂያነታቸውም
ድኅነት ሊኾንላቸው፥ ድኅነትን ሊያመ
ጣላቸው፥ ድኅነት የሚያመጣ ዕውቀት
በሚሰጣቸው ምእመናንና ሞት ሊኾን
ባቸው ሞትን የሚያመጣ ዕውቀት በሚሰ
ጣቸው ዓላውያንና መናፍቃን ዘንድ ሁሉ
ነው። ይህንንም ሐዋርያው ሲገል
ጽ «ወተዐውቀ በላዕሌነ መዓዛ አእምሮቱ
በኵሉ በሐውርት፤ በያገሩም የክርስቶስ
መታወቂያ በእኛ ላይ ታወቀ። እስመ
መዓዛሁ ለክርስቶስ ንሕነ በኀበ እግዚ
አብሔር በእንተ እለ ይድኅኑ፤ ወእለሂ
ይትሐጐሉ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ የክር
ስቶስ መዓዛ እኛ ነንና ስለሚድኑት፤
የሚጠፉም አሉ። እስመ ቦ እለ ይደል
ዎሙ መዓዛ ሞት ለሞት፤ ወእለ ይደ
ልዎሙ መዓዛ ሕይወት ለሕይወት፤
ወመኑ ዘይደልዎ ዝንቱ። የሞት መዓዛ
የሚገባቸው ለሞት ናቸውና፤ የሕይወት
መዓዛ የሚገባቸው ለሕይወት ናቸውና፤
ይህ የሚገባው ማነው።» ብሏል።

እንዲሁም ሁሉ ስለሆነ ክርስቲያኖች
የክርስቶስን ብርሃንነት ለዓለሙ የሚያሳዩ
መቅረዞች፥ የመንግሥተ ሰማያት ከተማ
እንድትታይ አልያም እንድትሰወር የሚያ
ደርጉ ተራራዎች ናቸው። ከዚህ የተነሣ
ጌታችን ያስተማረውና ያዘዘው አንድ
ሰው ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበትን ሳይሆን
ለሌላውም የሚጠቅምበትንና ዋጋው
እጥፍ ድርብ የሚሆንበትን ነው። ለራሱ
ብቻ ጨው እንዲሆን ሳይሆን አልጫ
የሆነውን ሌላውንም እንዲያጣፍጥ በኃጢ
አት ዝገትና ብልሽት፥ በኃጢአት
መጥፎ መዓዛ እየተበላሸ ያለውን ከጥፋ
ትና ዝገት በማዳን እንዲጠነክርና እን
ዲጠብቅም ነው እንጂ። ክርስቲያኖች
ሌሎች የእግዚአብሔርን የቸርነት ጣዕም
እንዲቀምሱና ከአልጫ ሕይወት ነጻ እን
ዲወጡ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፥
ሌሎችም የእግዚአብሔርን ቸርነት ሊያዩ
የሚችሉት በክርስቲያኖች ሕይወት ነው።
ብርሃን ሆኖ ለራሱ ብቻ እንዲያበራ
ሳይሆን ለሌሎችም እንዲያበራና ከጨለ
ማ ሕይወት ነጻ ወጥተው ወደ ብርሃን
ክርስቶስ እንዲመጡ የማድረግ ኃላፊነት
ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። በዚህም ክር
ስቲያኖች ጨው ሆነው ሌላውን በማ
ጣፈጣቸው፥ ብርሃን ሆነው ለሌላው በማ
ብራታቸው የሚገኘውን ውጤት ሲገል
ጽ "በሰማያት ያለው አባታችሁን እንዲ
ያከብሩ" አለ። ማቴ.5÷14።

ሊታየን ሊታሰበን የሚገባው ጨው
ሆኖ የማጣፈጥ፥ ብርሃን ሆኖ ለሌላው
የማብራት ጉዳይ ክብደት ሳይሆን ከዚህ
የተነሣ የሚገኘው ነገር ነው። እግዚ
አብሔር ከእኛ የተነሣ እርሱን የ
ማያውቁና ከእርሱ ርቀው የነበሩ ሰዎች
እንዲያውቁትና እንዲያመሰግኑት ከሆነ
ከዚህ የበለጠ ምን ታላቅ ነገር አለ?
በመልካም ሕይወት በመኖሩ ራሱም
ይጠቀማል፥ ሌላውንም ይጠቅማል፥
እግዚአብሔርንም ያስመሰግናል፥ በዚህ
ሁሉ ዋጋው ይበዛለታል፥ ሌሎችን በሕ
ይወቱ አስተምሮአልና፥ ለሌሎች የእ
ግዚአብሔርን የቸርነት መዓዛ አድር
ሶአልና። ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖች
የእግዚአብሔርን የቸርነት መዓዛ ለሌ
ላው የሚያስተላልፉ መሆናቸውን ሲገል
ጽ እንዲህ ይላል፦ "በእኛም በየስፍራው
ሁሉ የዕውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአም
ላክ ምስጋና ይሁን፤ በሚድኑቱና በሚጠ
ፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር የክር ስቶስ
መዓዛ ነንና።" 2ቆሮ 2÷14-15።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ በወንጌል ያስተማረንና በተግ
ባር ሠርቶ ያሳየን ከዚህ አንጻር ነው።
አንዳንድ ሰዎች በወንጌል የታዘዙትንና
የተነገሩትን «ይህ የማይቻል ነው ፥ከባድ
ነው» ይላሉ፤ እንዲያውም «አንዳንዶቹ
ሊሆንና ሊፈጸም የማይችል ነገርን
ማዘዝ ትክክል አይደለም» ለማለት
የሚዳዳቸው አሉ። «ጠላትህን ውደድ፥
የሚረግሙህን መርቅ» የሚሉትን ሕግ
ጋትና ትእዛዛት በማየት ይህ የማይቻል
ስለሆነ ትክክል አይደለም፤ ሊፈጸም
አይቻልም ይላሉ። ነገር ግን ክርስቶስ
እንዲህ ያዘዘው ለምንድነው ብሎ መጠ
የቅ ተገቢ ይሆናል። እኛ ለምን እንዲህ
እንደታዘዝን ጌታ ሲናገር፦ «... እግዚ
አብሔርን ትመስሉ ዘንድ» አለ። ማቴ
5÷45፣48። ስለዚህ የትእዛዙ መሠረትና
ግብ ይህ ነው፤ እግዚአብሔርን በመም
ሰል የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን
ይህንኑ በሥራችን ማሳየትና መግለጥ
ይኖርብናል። ክርስቶስ ይህን ያዘዘውን
ሠርቶ አሳይቶናል፥ ሲሰድቡት መልሶ
አልተሳደበም፤ ፊቱን ለሚጸፉት፥ ጀርባ
ውን ለሚገርፉት ሰጥቶአል፥ ሞትን
ተቀብሎአል፥ ይህን ሁሉ መቀበል ብቻ
ሳይሆን እንዲህ ለበደሉት ሳይቀር
«አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁ
ምና ይቅር በላቸው» ብሎ ጸልዮላቸ
ዋል። ሉቃ.23÷34። የእኛ አኗኗርና
ድርጊት እንዲህ ባለ ሁኔታ ያዳነንን
ክርስቶስን የማይመስል ከሆነ የክርስ
ትናን ምንነትና የእግዚአብሔርን የቸ
ርነትና የማዳን ሥራ ለሌሎች በእርእ
ያነት ለማሳየት የማንበቃ እንሆናለን፤
ሌሎች በእኛ አማካይነት የእግዚአብሔ
ርን መዓዛ እንዲያሸቱና ወደ መዓዛው
ባለቤት ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ
የምናደርግ ሳይሆን በእኛ ምክንያት
ከእግዚአብሔር ቸርነት ከክርስትና ሕ
ይወት በአፍአ እንዲቀሩ የምናደርግ
እንሆናለን። ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር
ልጆች ስለሆኑ ይህንን የአባታቸውን
መልክ ለሌላው የሚያሳዩ መሆን ይገባ
ቸዋል። አባቱን የማይመስል ልጅ ሲ
ያዩት አባቱን እንዲያስታውሱት አያ
ደርግም። ስለዚህ ክርስቶስ በኃጢ
አት ጠፍቶ የነበረ እግዚአብሔርን የመ
ምሰል አርአያችንንና መልካችንን /Image
of God/ እንደመለሰልን እኛ ደግሞ ይህ
ንን ያላገኙ ሌሎች ከእኛ ሊያዩትና
እግዚአብሔርን በእኛ ሊያዩት ይገባል።
ጌታችን «ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዷችሁ
በእኔም ምክንያት በሐሰት ክፉውን
ሁሉ ሲናገሩባችሁ ደስ ይበላችሁ» በማ
ለት ማንኛውንም ነቀፌታና ስድብ እን
ዲሁም ስደት በሐሴት መቀበል እንደ
ሚገባ አስተምሮናል። በዚህ ብቻ አላበ
ቃም፥ የሚሳደቡትንና የሚነቅፉትን፥
የሚያሳድዱትንና መከራ የሚያመጡ
ትን ጠላቶች ሁሉ መውደድንም አዘዘ
እንጂ። በዚህም በግድ የመጣብህ ሳይ
ሆን ወድደህ የተቀበልከው መሆኑ
ይታወቃል። እንዲሁም ይህን ሁሉ የሚ
ያደርግብህን ጠላትህን ውደድ አለ፥ጠላ
ትን መውደድ መከራውን ታግሦ ከመ
ቀበል የበለጠ ይከብዳል፥ ውደድ በማ
ለት ብቻ አላበቃም፥ "ጸልይለት" አለ
እንጂ። ስለዚህ የሚያሰቃይህን ሰው
መከራውን ታግሠህ እንድትቀበል ብቻ
ሳይሆን እንዳትጠላው፥ እንድ ታፈቅ
ረው፥ ከዚያም በላይ ስለ እርሱ
ከክፋቱ እንዲመለስ ወደ እግዚአብሔር
እንድትጸልይ ነው።

ጌታ ይህንን ያዘዘው ለእኛ ፍጹም
የሚጠቅመን ስለሆነ ነው። ጉዳት የሚ
ደርስበት፥ የሚመታውና የሚገፋው
ሰው፥ መከራውንና ግፉን እንዲህ ሁሉ
ባለ ሁኔታ እንዲቀበለው ከተነገረው
የሚታየውና የሚታሰበው መጠቃቱና
መበደሉ ሳይሆን በዚህ ውስጥ የሚያ
ገኘው ክብር ነው። በሁኔታው የእግዚ
አብሔር ልጅነቱን በተግባር ለማስ
መስከር፥ እንደ ተሰጠው ወርቃማ ዕድ
ልና አጋጣሚ የሚቆጥረው ይሆናል።
ይህንን ዕድል በአግባቡ ተጠቅሞ የሰ
ማይ አባቱን ለመምሰልና የክርስቶስን
የሕይወት መዓዛ ለሌሎች ለመግለጥ
በሩጫው መስክ ለማሸነፍና ለመሸለም
እንደሚሮጥ ተወዳዳሪ /አትሌት/ ራሱን
ያጸናል፤ የሚታየው መከራው ሳይሆን
ክብሩና ዋጋው ነው። "የማይታየውን
እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል
የሆነው የጊዜው መከራችን የክብርን
የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ
ያደርግልናልና" እያለ በተጋድሎው ይ
ጸናል። 2ቆሮ.4÷17-18።

ጉዳት አድራሹና አጥቂውም ተበ
ዳዩ ሲታገሠው ከዚያም አልፎ ካሰበ
ውና ከጠበቀው በላይ ሲፈጽም ሲያየው
ልቡ ሊራራ ዕብሪቱም ሊሟሽሽ ይች
ላል። ተበዳዩ የሚደርስበትን በትዕ



www.eotcmk.org

ግሥትና በፍቅር ሆኖ ሲቀበል ከማየት የበለጠ ክፉ አድራጊዎችን የሚያስታግሥና የሚመልስ ነገር የለም:: እንዲያውም ክፉውን በመልካም ማሸነፍ ወዳጆች ያደርጋቸዋል:: ስለዚህ በተበዳዩ ትዕግሥት በዳዩም ተበዳዩም ይጠቀማሉ፥ በተበዳዩ ትዕግሥት የክርስቶስ ትዕግሥት ይገለጣል፥የክርስቶስ መከራ መቀበልና ለጠላቶቹ መጸለይ፥ ይገለጻል::

በሌላ አንጻር ግን ተበዳዩ ለበቀል ቢነሣና አጸፋውን ቢመልስ ውጤቱ ፍጹም የከፋና የተበላሸ ይሆናል:: ሁኔታው ሁለቱንም ያዋርዳቸዋል:: እንደ ጠገቡ በሬዎች እርስ በእርስ ሲታገሉ ይታያሉ:: በዚህም ሁለቱም በአካልም በመንፈስም ይጐዳሉ:: ጠላትነታቸው ይጨምራል፤ የዚህ ዓይነት ጠላትነት የሚያመራው ወደ ሞት ነው:: ያም መቋጫ ወደሌለው የብቀላና ደም መፋሰስ ዑደት ሊያመራ ይችላል:: ክፉ በክፉ ሊወገድ አይችልም:: ነገር ግን በተበዳዩ ትዕግሥት ይህ ሁሉ ቀርቶ ውጤቱ ለሁለቱም በሥጋም በነፍስም ጠቃሚ ይሆናል:: እንዲህ እየታገሡት የማይመለስ ቢኖር እግዚአብሔር ይበቀለዋል:: እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ዋጋውን ይሰጠዋልና፤ በቀል የእኔ ነው ብሏልና:: ስለ ተበዳይ እግዚአብሔር ይበቀላል:: አንተ ግን የሚገባህን አድርግ:: የክርስቶስን የሕይወት መዓዛ ግለጽ:: ይህንን የእግዚአብሔርን መዓዛ የማይጠቀምበት ቢኖር በራሱ ይጠየቅበታል::

የሕጉ አስደናቂነት ይህ ነው:: ለሁሉም የሚጠቅም ሕግ መሆኑ፤ ስለዚህ ሕጉ ከባድ ነው ማለት ሳይሆን የትእዛዙን ውጤትና ታላቅነት መረዳት ይገባል:: ሕጉ የሰላም ሕግ፤ የሕይወት ትእዛዝ ነው:: ይህንን ትዕግሥትና ፍቅር በሕይወትና በተግባር በመግለጥ ሌሎችን ወደ ንስሐና ሰላም ማምጣት የእግዚአብሔር መዓዛዎች በሆኑ ክርስቲያኖች ላይ የተጣለ ኃላፊነት ነው:: ቅዱስ እስጢፋኖስ ሲወገር ከክርስቶስ እንደ ተማረ «ይህን ከኃጢአት አትቁጠርባቸው፤ ይቅር በላቸው» /ግብ.ሐዋ.7÷60/ ብሎ በመጸለዩ አሳዳጁ ሳውል ተመልሶ መምህረ አሕዛብ ብርሃነ ዓለም ሆኖአል:: አውግስጢኖስ ይህንን ሲገልጽ «ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ እስጢፋኖስ ጸሎት ቅዱስ ጳውሎስን ያህል ሐዋርያ አገኘች» ብሏል:: በእስጢፋኖስ ሰማዕትነት የተገኘው ይህ ብቻ አይደለም፤ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ ተወስኖ የነበረው ክርስትና በክርስቲያኖች ስደት ሳቢያ በይሁዳና በሰማርያ አውራጃዎች ሁሉ ተስፋፍቷል:: የሐዋ.8÷1-5::

የሚጣላ፣ የሚሳደብ፣ የሚቀማ፣ የሚቆጣ ሌላውንም ክፉ ነገር የሚያደርግ ሰው ጤነኛ ሳይሆን በሽተኛ ስለሆነ ሊታዘንለት ይገባል:: ሐኪሞች አእምሮአቸውን በሳቱ በሽተኞች ሲሰደቡና ሲነቀፉ ቢሞቱም እንኳ የበለጠ ያዝናሉ እንጂ በሽተኛውን አይጣሉትም፣ ለመበቀልም አይነሡም:: ይልቁንም ያድኑትና ከስቃዩ ይፈውሱት፣ ወደ ቀድሞ ጤንነቱ ይመልሱት ዘንድ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ:: በጣም ካልታመመውና ደዌው ካልጸናበት በሽተኛ በበለጠ ይከባከቡታል:: የበሽተኛው ስድብና ድርጊት ከሕመሙ ጽናት የመነጨ እንደ ሆነ ያውቃሉና::

ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው እንዲህ ነው:: ጠላቶቹ ስንሆን በደላችንን ሳይቆጥር ይቅር አለን:: «እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለሙን ዋጅቶአልና፤ ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ በደላቸውንም ሳያስብ፤ የዕርቅ ቃሉንም በእኛ ላይ አደረገ፤ የይቅርታውን መልእክትም ሰጠን» 2ቆሮ.5÷19፤ «ጠላቶቹ ሳለን በደላችንን ሳይቆጥር ልጆቹ አደረገን» /ሮሜ 5÷10/፤ «የማንታዘዝ፣ የምንስት ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር...ሳለን እንደ ምሕረቱ መጠን አዳነን» ቲቶ 2÷3–5፤ «ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን» ኤፌ.22÷1:: ይህንን ለእኛ የተደረገውን እኛም በሕይወታችን ካልገለጽንና እግዚአብሔርን ካልመሰልን እንዴት ብለን የእርሱ መዓዛዎች እንሆናለን? የክር ስትናን ገጽታ የሚያጠቁር ታላቅ መጥፎ ነገር ቢኖር ክርስቲያን እየተባሉ ነገር ግን እግዚአብሔርን ሳይመስሉ መገኘት ነው::

ክርስቶስ የመጣውና ልጅነታችንን የመለሰልን፣ ጸጋውን የሰጠን «አልችልም» የሚለውን አሮጌውን ሰውነት ሊያስወግድልንና ኃይልን ሊያጎናጽፈን እርሱን ሊያስመስለን ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች ከሆንን እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋችን ድካም መመላለስ የለብንም:: ቅዱስ ጳውሎስ «አሮጌውን ሰው አስወግዱ፣ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፣ እግዚአብሔር ያደሰውን አዲሱን ሰውነት ልበሱት፤ በእውነት÷ በቅንነት÷ በንጽሕናም::» ያለው ለዚህ ነው:: ኤፌ.4÷23–24:: እንዲሁም የድሮው ደካማነትና አልችልም ማለት ተወግዶ አዲስ ኃይልና መንፈስ የተሰጠን መሆኑን ሲገልጽ፡– «ማንም ቢሆን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል» ይላል:: 2ቆሮ. 5÷17:: በክርስቶስ ኃይል ሁሉን እችላለሁ ማለትን ሰጥቶናል:: «እምነት ቢኖራችሁ... የሚሳናችሁም ነገር የለም::» ማቴ.17÷21:: ጌታችን በተለይም በማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ 5 እስከ 7 በሰፊው ያስተማረው ትምህርት ዓላማው እኛን እግዚአብሔርን ወደ መምሰል መምራትና ማድረስ ነው፤ የክርስትና ዓላማ እግዚአብሔርን መምሰል እርሱን ተዋሕዶ ከእርሱ ጋር ለዘላለም መኖር ነውና:: ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን በፊልጵስዩስ መልእክቱ በግልጽ ተናግሯል:: እንዲህ ሲል፡– «...ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ እፈጥናለሁ::» ፊልጵ.3÷1214::

ይህ ፍጹምነት፣ ይህ እግዚአብሔርን መምሰል ያለ ፈተናና ውጣ ውረድ አይገኝም:: ነገር ግን ከጸናንና ከእርሱ ጋር ከኖርን በመጨረሻ እናገኘዋለን:: እግዚአብሔርን ልንመስል ሲገባን ከቀራጮችና ከአሕዛብ ያልተሻለ ጽድቅ ይዘን ብንገኝ ምን ዓይነት አሳዛኝ ነገር ይሆን? የሚወዱትን ብቻ መውደድ የቀራጮች፣ የኃጥአንና የአሕዛብ ጠባይ ነውና:: የእግዚአብሔርንስ መንግሥት የምንወርሰው እንዴት አድርገን ነው? ጽድቃችሁ ከጻፎችና ፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አትገቡም ተብሏልና:: እግዚአብሔርን ልናስመስግንና ልናስከብረው ሲገባ በእኛ ምክንያት ስሙ በአሕዛብ ዘንድ እንዲሰደብ እያደረግን እንዴት አድርገን ሕይወትን እንወርሳለን!? «በአንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባል::» ተብሏልና:: ኢሳ.52÷5:: የእግዚአብሔርን መንግሥት እኛም እንዳንገባ ሆነን ሌሎችንም በእኛ መጥፎ የምግባር መዓዛ ምክንያት የምናርቅ ሁሉ ፍዳችን ዕጥፍ ድርብ ይሆናል:: በሕይወታችን እግዚአብሔርን ብንመስል እኛም ተጠቅመን ሌሎችንም እንደምንጠቅም ሁሉ እግዚአብሔርን ከመምሰል ወጥተን አሕዛብን ብንመስል ደግሞ በራሳችን ሕይወት መበላሸት እንጠየቃለን:: እንዲሁም ለሌሎች እንቅፋት በመሆናችንም እንጠየቃለን::

እርሱ ክርስቶስ የማይቻልና አስቸጋሪ ሕግ አልሠራብንም:: ይልቁንም የማይቻል የነበረውን ነገር ራሱ አምላክ ሲሆን ሰው በመሆን አሳይቶናል:: እርሱ ፍቅርን የገለጸው በሞቱ ሕይወትን እስከ መስጠት ድረስ ነው:: እኛም የሚወዱንን መውደድ ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችንንም ብንወድ÷ መውደድ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ እንደ ወደደን መጠን መውደድ÷ የሚረግሙንን መመረቅ ሌላውንም ሁሉ እንዲሁ እንደታዘዘ ብንፈጽም ለዓለም የአባታችን የእግዚአብሔር መዓዛዎች እንሆናለን::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



'

www.eotcmk.org

# ተዘክሮተ ሞት

**«ሞት መራራ ሆኖ በእኔ ዘንድ መሪር የምለው አይደለም፣ እርሱ እንደ እንቅልፍ ነው፤ ነገር ግን ስለ ኃጢአታችሁ በእናንተ ዘንድ መሪር ይሆንባችኋል፡፡»**

/ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ/

/ዲ.ያቆን ቃኘው ወልዴ/

አበው «ክርስቲያን አክብሮተ ሰንበትን ተዘክሮተ ሞትን መያዝ አለበት» በማለት ይመክራሉ፡፡ በዚህ ጽሑፍ ሞትን በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚያስተምሩት በመጠኑ ለማየት እንሞክራለን፡፡

1. *ትርጉም፡-* ሞት በቀጥተኛ ትርጉሙ መለየት÷ማጣት ማለት ሲሆን ሞተ ሥጋ፣ ሞተ ነፍስ፣ሞተ ኀሊና ተብሎ በሦስት ወገን ይገለጻል÷ይብራራል፡፡

ሀ/ <u>ሞት የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው</u> /ያዕ 2÷26/፡- ሰው በዚህ ዓለም እንዲኖር የተወሰነለት ዘመን ሲፈጸም ሞቶ ሥጋው ወደ መቃብር ይወርዳል፡፡ በነፍሱ ደግሞ ጽድቅ ወይም ኩነኔ እንደ ሥራው ይጠብቀዋል፡፡ «አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና» እንዳለ፡፡ መዝ. 61÷12፡፡ ቅዱስ አባ ማርቆስ «በሞት ከዚህ ዓለም በተለየን ጊዜ ያለማነው ካጠፋነው ጋር በፍትሐ እግዚአብሔር ይመዘናል፡፡ ያለማነው በልጦ ቢገኝ ይፈረድልናል፤ ያጠፋነው በልጦ ቢገኝ ይፈረድብናል» ብሏል፡፡ ሰው በዚህ ዓለም የሚኖርበት ዐረፍተ ዘመን ሲፈጸም ሞተ ይባላል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥረው የስሙ ቀዳሽ የክብሩ ወራሽ ሆኖ ለዘለዓለም እንዲኖር ነበር፡፡ ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር አባታችን አዳምን ዕውቀትን ሰጥቶ ሊጠብቀው የሚገባውንም ትእዛዝ አዘዘው፤ «ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፣ ከእርሱ በበላህ ቀን ትሞታለህ» አለው፡፡ ዘፍ.2÷17፡፡ ሰይጣን በእባብ አድሮ «እግዚአብሔር ከዚህ ዛፍ እንዳትበሉ የከለከላችሁ እርሱን በበላችሁ ጊዜ ዐይኖቻችሁ እንዲከፈቱ መልካምና ክፉን እንደምታውቁ ስለሚያውቅ ነው እንጂ አትሞቱም» የሚል የተንኰል ምክር አቀረበላቸው፡፡ አዳም ከፈጣሪዬ የተሰጠኝ ጸጋ ይበቃኛል ሳይል ከፈጣሪው ትእዛዝ ይልቅ የአታላዩን ምክር አምኖ የተሰጠውን የጸጋ ዕውቀቱን ለክዳትና ለስስት ተግባር በመለወጥ ያዋቂ አጥፊ ተብሎ በራሱ ላይ ሞትን አስፈረደ፡፡ ከፈጣሪው የተሰጠውን ዕውቀት ለጥፋት ሥራ በማዋል ከሕይወት ሞትን መረጠ፡፡ በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስና ሞተ ኀሊና ተፈረደበት፡፡ ሞተ ኀሊናም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከትንሣኤ ልቡና /ኀሊና/ ርቆ በኃጢአት ጸንቶ መኖር ነው፡፡ /ኤፌ.2÷2፤ ሉቃ. 15÷24.../፡፡ ሰው ከፍርድ በኋላ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም የሚወርድ ሆነ፡፡ አዳም ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ከኖረ በኋላ ነፍሱ ከሥጋው ተለይታለች፡፡ ዘፍ.5÷9፡፡ ሞተ ሥጋ ይህ ነው፡፡ ዕፀ በለስን በበላ ዕለት የሞተው ሞት ይህን ሳይሆን በኃጢአት መውደቁን ወይም ከእግዚአብሔር መለየቱን የሚያመለክት ነው፡፡ «በአንድ ሰው ምክንያት /በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት/ ሞት ወደ ዓለም ገባ» /ሮሜ.5÷6/ እንደ ተባለ አባታችን አዳም ከዕፀ በለስ ሰርቆ በመብላቱ ሞት በልጆቹና በልጅ ልጆቹ ላይ የታዘዘ ሆነ፡፡

ለ/ <u>ሞት ከእግዚአብሔር መለየት ነው፡-</u>

ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በኃጢአት ሥራ ጸንተው የሚመላለሱና እግዚአብሔርን በክፉ ሥራቸው የሚያሳዝኑ ከሆነ ሙታን ይባላሉ፡፡ ይኸውም ሊታወቅ ጌታችንን ከሕዝቡ አንዱ «አስቀድሜ ሔጄ አባቴን ልቅበር አሰናብተኝ» ቢለው «አንተስ ተከተለኝ» አለው፡፡ ለጊዜው በእግር ተከተለኝ ፍጻሜው በግብር ምሰለኝ ሲለው ነው፡፡ አያይዞም «ሙታንን ተዋቸው፤ ሙታኖቻቸውን ይቅበሩ፤ ወኅድኅሙ ለምውታን ይቅብሩ ምውታኒሆሙ» አለው፡፡ ማቴ. 8÷22፡፡ ሙተዋል ቢሉ ሙታን እናት አባትህን ሙታነ ኀሊና ዘመዶቻቸው ይቅበሯቸው፤ አልሞቱም ቢሉ ሙታነ ኀሊና እናት አባትህን ሙታነ ኀሊና ዘመዶቻቸው ይርዷቸው፤ ያጥቧቸው፡፡ አንድም ሙታነ ኀሊና እናት አባትህን ምውት ገንዘባቸው ይርዳቸው፣ ያጥባቸው፣ ሙት አለው ገንዘቡን የአንድ አንዱ ሲወስደው የእገሌ ነኝ አይልምና፡፡ ሟቹን የሚቀብሩት ዘመዶቹ በሕይወተ ሥጋ ያሉ ቢሆንም ከሕገ እግዚአብሔር ርቀው በኃጢአት የሚኖሩ በመሆቸው ሙታን ተብለዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት የመጀመሪያ መልእክቱ «ቅምጥሊቱ ግን በሕይወት ሳለች የሞተች ናት» በማለት በኃጢአት ስላለች ምንም ነፍሷ ከሥጋዋ ባይለይም የሞተች እንደ ሆነች ገልጿል፡፡ ተድላ ደስታ የምታደርገው÷ በወዲሁ አለሁ አለሁ ስትል በወዲያው ምውትናትና ይህን አለ፡፡ 1ጢሞ.5÷6፡፡ በተጨማሪም ለኤፌሶን ምእመናን «በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ» በማለት ቀድሞ በነበሩበት በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር አንድነት የተለዩ እንደ ነበር ተናግሯል፡፡ ኤፌ.2÷1፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በመጀመሪያዪቱ መልእክቱ እንዲህ አለ፡- «እኛስ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን /ከገሃነም ወደ መንግሥተ ሰማያት እንድንሔድ/ እናውቃለን፣ ወንድማችንን እንወዳለንና፤ ወንድሙን የማይወድ ግን በጨለማ፣ በድንቁርና፣ በገሃነም ይኖራል፡፡» ዮሐ. 3÷14፡፡ ኃጥአን በፍርድ ዕለት ከእግዚአብሔር ፊት በእሳት ባሕር ለዘለዓለም ይጣላሉ፡፡ ይህም ሁለተኛ ሞት ይባላል፡፡ /ራእይ 20÷13-14/፡፡

2. <u>የሞት አይቀሬነት /እርገጠኛነት/</u>፡ /መጽ.ጥበብ 2÷5/

·ሞተ ሥጋ ለሰው ሁሉ የታዘዘ ነው፡፡ ክቡር ወራዳ፣ ንጉሥ ጭሰኛ፣ ድሀ ሀብታም፣ ጭዋ ሊቅ፣ ደግ ክፉ ወዘተ ብሎ አይመርጥም፡፡ ወደ ብሔረ ሕያዋን የተሻገሩ እነ ሔኖክ፣ ኤልያስ ወዘተ በመጨረሻው ዘመን ሃይማኖታቸውን መስክረው ሞተ ሥጋን ይቀምሳሉ፡፡ ምክንያቱም «ተዘከር ከመ መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት፤ ከመሬት መገኘትህን ወደ መሬትም ልትመለስ እንዳለህ አስብ» የሚል አምላካዊ ቃል አለና፡፡ መፍቀሬ ሰብእ ሰሎሞን «ቀድሞ እንደ ነበረው ጊዜ መሬት ወደ መሬትነቱ ይመለሳል፣ ነፍስም ለሥጋ ሰጥቶት ወደ ነበር ወደ እግዚአብሔር ይመለሳል፡፡ በሥጋ በነ በረ ጊዜ ስለ ሠራው ሥራ ሁሉ ምላሽ ይሰጣል፡፡ ክፉውንም ቢሆን በጎውንም ቢሆን» ብሏል፡፡ መክ.12÷7፡፡ ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት እንዲሉ ኑሮ ኑሮ ሞት ይቆየዋል፡፡ ኋላም መቃብር ይከተለዋል፡፡ በምድራዊ አነዋወሩ÷ በዕውቀቱ፣ በሀብቱ የሚመካ ቢሆን ፍትወታተ ሥጋውን በመፈጸም መላ ዘመኑን በተድላ ሥጋ ያሳለፈ ቢሆን፣ በረኀብ ጅራፍ እየተገረፈ የኖረ ቢሆን የሙዓለ ሥጋዌው መጨረሻ ሞቶ በሣጥን ተከትቶ ወይም በሰሌን ተጠቅልሎ ወደ መቃብር መውረድ ነው፡፡ በሕይወተ ሥጋ ሳለ አስተዋይ ኑቱንና ብልህነቱን፣ ያማረች ሥርዓቱን፣ የተመሰገነች አካሔዱን፣ የቀና ንግግሩን እያነሡ ከእርሱ ወዲያ ሰው በማ





www.eotcmk.org

ለት ብዙዎች ያወሩለት የነበረ ሰው ከሞተ በኋላ የሚያስታውሰው የለም:: ምን አልባት ለተወሰኑ ዕለታት እገሌ እንጂ እንዲህ ዓይነት ሰው ነበረ በማለት የሚያወሩና ጥቅም ስለ ቀረባቸው የሚያዝኑ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል:: «ዋይ ሽሽ ተበላሽ» እያሉ ፊታቸውን እየነጩ፣ ለሰው ይምሰል የሚያለቅሱ፣ «እንባማ÷ አዛኝ ይበሉኝ፤ ምንኛ ይወደው ኖሯል ይበሉኝ፤» ብሎ ከዐይኑ ቅቤና የመሳሰሉትን በመጨመር የሚያለቅሱ የሟቹ የቅርብ ዘመዶችና ወዳጆች ስንኳ ከሣልስት በኋላ ስለ ሟቹ አሟሟት የሚያነሣባቸውን አይፈልጉም:: ከዚያ በኋላም የሟቹን ንብረት ወርሰው ከብረው ለመታየት በመጓጓት እርስ በርሳቸው ይገባኛል በማለት ይካሰሳሉ:: ለግድያም ይፈላለጋሉ:: እንዲህ እንዳደረጉ በሞታቸው ጊዜ ዘመዶቻቸው በእነርሱም እንዲሁ እንደሚያደርጉባቸው ግን አያስቡትም::

ሞት የማይቀር በመሆኑ ፈቃደ ሥጋን ማሸነፍና የጽድቅ ሥራን መሥራት እንዲገባ ያስተውሏል:: አንድ ብልህ ሰው «የምትሞት መሆንህ የተረጋገጠ ስለሆነ ከዛሬ ጀምሮ ራስህን እንደ ሞተ አድርገህ አስብ፤ በሕይወተ ሥጋ እስካለህ ድረስ አንድ ቀን መሞትህ እንደማይቀር ማሰብን አትዘንጋ» በማለት ተናገረ:: ሌላኛውም «የመርከብን መንገድ አቅንቶ የሚመራ ሰው በመርከቡ የፊተኛ ጫፍ እንደ ሚቆም እንደዚሁም ማንኛውም ሰው በጽድቅ ሥራ ለመመላለስና ከእግዚአብሔር አንድነት ላለመለየት ዘወትር ዕለተ ሞቱን ማሰብ ይገባዋል» ሲል ይመክራል:: እንኪያስ ከልጅነት እስከ ዕውቀት በማወቅ ባለማወቅ በድፍረት የተሠሩ ኃጣውእን በማሰብ ማልቀስና ከሞተ ነፍስ ለመዳን መፋጠን ይገባል:: የመዳንም ቀን ዛሬ ነውና::

መቃብራትን እየተዘዋወረ የተመለከተ አንድ ሰው እንዲህ እያለ በትሕትና ይናገር ነበር:: «እነዚህ ሙታን ነፍስ ከሥጋ ተዋሕዶላቸው መነሣት የሚቻላቸው ቢሆን ኖሮ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ምንኛ በተጉ ነበር፤ እኔ ግን ጊዜ ሳለልኝ ለነፍሴ ብዬ ምኑን አደርጋለሁ::» ምድራዊ ደስታ በሞት ይቋረጣል:: በዚህ ዓለም ታፍሮ ተከብሮ የሚኖር ሰው ከሞተ በኋላ ይናቃል፤ ይረገማል፤ ወደ መቃብር ወርዶ መረማመጃና የእግር መረገጫ ይሆናል:: ጢስ በፀሐይ ጨረር ፊት ከምድር ሲወጣ ለተመለከተው የሚያምርና ደስ የሚያሰኝ ቢሆንም ብዙ ሳይቆይ በትንሽ ነፋስ በንኖ ይጠፋል:: በሞት የደከሙበትን ትቶ መሔድ ግድ ነው:: ጻድቅ ኢዮብ «ከእናቴ ማኅፀን ራቁቴን እንደ ወጣሁ ራቁቴን እሔዳለሁ» ማለቱ ለዚህ ነው::

በወንጌልም «መዝገብን በዚህ ዓለም አትሰብስቡ፤ አታከማቹ» ተብሏል:: ማቴ 6÷19:: ሳላዲኖስ የሚባል ንጉሥ መሞቱ ቁርጥ በሆነበት ሰዓት «ሞቼ ሥጋዬን ወደ መቃብር ስትወስዱ የከፈን ጨርቅ በጦር አስራችሁ በአንድ ወታደር አስይዛችሁ ከበድኔ ፊት ለፊት እየሔደ በታላቅ ድምፅ ንጉሥ ከሀብቱ ሁሉ ወደ መቃብር ይዞት የሚወርደው ይህን ከፈን ብቻ ነው ይበል» ሲል አዘዘ:: የንጉሥ በድን ተቀብሮ ከፈረሰ በኋላ ድህም ይሁን ባዕለ ጸጋ ከሌላ ሰው ዐፅም መለያ የለውም:: ዲዮጌነስ የሚባል ፈላስፋ በመቃብራት መካከል ገብቶ እጅግ ተግቶ አንድን ነገር ሲፈልግ የተመለከተው ንጉሥ እስክንድር «በዚህ በሙታን ዐፅሞች ውስጥ ምን እየፈለግህ ነው» ብሎ በመደነቅ ቢጠይቀው:- «የአባትህን የፊልጶስን ራስ ቅል እየፈለግሁ ነው፤ ግን ማወቅ አልተቻለኝም፤ አንተ ማወቅ /መለየት/ ከተቻለህ እስኪ እባክህ አሳየኝ» አለው:: ሰዎች ሲወለዱ የተለያዩ ሆነው ነው፤ በሕይወተ ሥጋ ሳሉም እነዋወራቸው አንድ ዓይነት አይደለም፤ ወደ መቃብር በመውረድ ጊዜ ግን ትክክል ናቸው:: በመሆኑም ፈላስፋው «ሞት የነገሥታቱን ሉል ከማጭድ ጋር ያስተካክላል» በማለት ተናገረ::

ሞት የማይቀር የሰው ሁሉ ዕጣ ፈንታ መሆኑን የማያውቅ ሰው አለ ለማለት ያስቸግራል:: ሞቱን የሚዘከረው ሰው ግን በቁጥር አናሳ ነው:: ክቡር ዳዊት «የሰው ዕድሜ ቢበዛ ሰብዓ ሰማንያ ነው፤ ከዚያም ካለፈ መከራ ነው» ሲል ተናግሯል:: በቅዱስ መጽሐፍ የሰው ዕድሜ በሣር ተመስሎ ቀርቧል:: ሣር በክረምቱ ዝናም ይበቅላል፤ ይለመልማል፤ ያብባል:: ዐይንን እስኪማርክ አሸብርቆ ይታያል፣ በኋላም አበባው ይረግፋል፣ በፀሐይም ደርቆ ትቢያ ይሆንና በነፋስ ይወሰዳል:: የሰው ልጅ ዕድሜም እንዲሁ ነው:: ይወለዳል፣ ያድጋል፣ በኋላም በሕመም ፀሐይነት ደርቆ በሞት ነፋስነት ይወሰዳል:: በመሆኑም ሰው ከዕድሜው አንድ ቀን በጨመረ ቁጥር በዚህ መጠን ሞት ወደ እርሱ እርሱም ወደ ሞት ይቀርባል:: በክረምቱ ዝናም ከየጅረቱና ከየሸንተረሩ መንጭቶ ወደ ባሕር የሚወርድ /የሚገባ/ ውኃ ወደ ኋላው አይመለስም:: ውኃ ሙላት ያገኘውን እየጠራረገ ወደ ፊት ይጓዛል እንጂ ወደ ላይ አይፈስም:: የሰው ልጅም እንዲሁ ነው፤ ቀኖቹ እያለፉ ወደ ሞት ያቀርቡታልና:: ይህን ዓለም አልጠገብኩምና አልሞትም ማለት አይችልም::

ስለዚህ የተማርነውን ሃይማኖት የተቀበልነውን ልጅነት እንዳንተው መሆን ይገባናል:: ከሞት በኋላ ሕይወት ከመቃብር አጠገብ ትንሣኤ እንዳለ ማሰብ ይገባል:: ሃይማኖት ከምግባር አዋሕደን ብንይዝ ፍጻሜያችን ያማረ ይሆናል:: ፍሬ ምግባር ሳንይዝ ብንገኝ ግን እንደ በለሲቱ መወቀሳችን አይቀርም:: ሉቃ. 15÷6–7:: ምን ፍሬ አፈራን ብለን ራሳችንን ልንመረምር ይገባል:: ተክልን የተከለ ሰው መላልሶ መኮትኮቱ ውኃ ማጠጣቱና መድከሙ ከፍሬው ለመጠቀም እንጂ አበባና ቅጠሉን ለማየት ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔር አምላካችንም በመልካም ሥራ በልጽገን ትሩፋት ሠርተን እንድንገኝ እንጂ መልካም ምኞታችንንና ፈቃዳችንን ብቻ ማየት አያስደስተውም:: እግዚአብሔር ዓመታትን በቸርነቱ የሚያቀዳጀን /መዝ 64÷11/ ልንጠቀምበት÷ እርሱን የሚያስደስተውን መልካም ሥራ ልንሠራበት እንጂ ለከንቱ አይደለም:: ሳንዘጋጅ ሞት ድንገት ቢደርስብን ኀዘናችን የጸና ይሆናል:: አንድ ንጉሥ በጻዕረ ሞት ተይዞ ሳለ:- «ይህን ያህል ሁዳድ የማሳርስ፣ እጅግ ውብ የሆኑ እልፍኝ ከአዳራሾችን ያሠራሁ ስሆን በዚህች ሌሊት ነፍሴ ከሥጋዬ ብትለይ የምሔድበት ሠፈሬ አይታወቀኝም» ሲል ተናገረ ይላሉ:: እንግዲህ በወዲያኛው ዓለም የእኔ ዕጣ ፈንታ ጽዋዕ ተርታ ምን ይሆን? በማለት መፍራት፣ የኃጢአት ነቅዕ ከሚሆን ምክንያተኝነት በመውጣት ዘወትር ጸሎትን መያዝና ለምግባር ትሩፋት መፋጠን ይገባል::

አውጉስጢኖስ ሞት የማይቀር መሆኑን ሲገልጽ «የኋለኛችን ነገሩ መልካም ይሁን ክፉ ያልታወቀ ነው፤ በርግጠኝነት የታወቀ ሞት ነው» አለ:: ሰው በየትኛውም የዕድሜ ክልል ይሁን፣ ጤነኛ ይሁን ታማሚ አንድ ቀን በሞት ማጭድነት ታጭዶ ወደ መቃብር መውረዱ አይቀርም:: ከሞት የሚያመልጥ ማንም ኃያል የለም:: ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን ጸዋትወ መከራ ተቀብሎ መሞቱ መልካም ሞት /ዕረፍት/ እንድናገኝ ነው:: አውጉስጢኖስ «ሞትን የሚገታ ጉልበት የለም፤ ለእሳት፣ ለውኃ፣ ለገገርዎች ወዘተ ብርታት መቃወም ይቻላል:: ለሞት ግን መቃወም የማይቻል ነው» ብሏል:: ስለዚህ በዘመን ብዛት የማይሻረውንና ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖረውን ጽድቅ ያለበትን ሁሉ ማከማቸት ያስፈልጋል:: በዚህ ዓለም ባዕለ ጸጋ የመሆን ምኞት ሞትን ማስቀረት አያስችልም:: አንድ ንጉሥ በሞቱ ሰዓት:- «እነሆ ይህ ሁሉ ሥልጣን ሀብት ሳለኝ ሞቴን ለደቂቃ ስንኳ ማዘግየት አይቻለኝም» ያለው ለዚህ ነው::

በሣጥን ተከትቶ ወደ መቃብር የሚሔድ በድን «ዛሬ ለእኔ ነገ ደግሞ ለአንተ» ሲል ከሞት የሚያመልጥ ማንም አለመኖሩን ይናገራል:: ከዛሬ ነገ በማለት ሳይዘጋጁ ድንገት ሞት ለደረሰባቸው ወገኖች የምንደነግጥና የምናዝን ብንሆንም እኛም ባላወቅነው ሰዓት ልንሞት እንዳለን በመገንዘብ ተሰናድተንና ተጠንቅቀን ለመጠበቅ አንነሣሣም፤ አንደፍርም:: ሞት እንዳለበት ዘንግቶ በራሱ መንገድ የሚመላለሰው ሰው እጅግ ብዙ ነው:: ይህን



www.eotcmk.org

የተመለከተ አንድ ቅዱስ እንዲህ አለ፦«ምናልባትም ከሞት በኋላ መንግሥተ ሰማይ ወይም ገሃነም መግባት ባይኖር ኖሮ ሰው ሁሉ ሞትን ፈጽሞ በረሳው ነበር:: ዕለተ ሞቱን እየተዘከረ ሥራውን የሚሠራ ዝንና ራሱን የሚመረምር ሰው ፍጻሜው የከፋ አይሆንም:: ሥራዎቹን በአግባቡ ያከናውናልና፣ መምህራን «የዚህን ዓለም ፍጻሜ ቢመለከቱ በዓለም የሚወደድ ነገር ባልተገኘም ነበር» ይላሉ:: ቅዱሳን ዓለምንና ፍትወቱን ጥለው የሚሔዱት ምሬረ ገሃነመ እሳትን ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን ዐውቀው ነው:: የሞትን ርግጠኝነት የተገነዘበ አንድ ሰው፦ «ሞት እንዳለብህ አስብ» የሚል ቃል በጣት ቀለበቱ ላይ አስቀርጾ ይኖር እንደ ነበር ይነገራል:: አንድ ባሕታዊ በሞቱ ጊዜ ደስ ተሰኝቶ የተመለከቱ፦ «ይህን ያህል የሚያስደስትህ ምንድን ነው?» ቢሉት «ሞትን ዘወትር በፊቴ አኖርኋት፥ አሁንም ስትመጣ ጊዜ እንግዳ ነገር ሆና አልታየችኝም» ብሎ መለሰ::

### 3.የሞት መምጪያ ሰዓት አለመታወቁ

ከሕግ በላይ የሆኑ ቅዱሳን /የሕጉን ፈጽመው ሲያበቁ በገድል ተቀጥቅጠው የሚኖሩ ዕለተ ዕረፍታቸው ይነገራቸዋል:: አንድም በጸጋ እግዚአብሔር ያውቁታል::

እኛ ግን የመሞቻችንን ጊዜ አናውቀውም:: «አልቦ ጥዩቅ ከመ ሞት፡ ባሕቱ አልቦ ምንትኒ ኢጥዩቅ ከመ ሰዓተ ምጽአቱ» እንደ ተባለ መሞታችን በርግጥ የታወቀ ቢሆንም ዓመቱ፣ ወሩ፣ ዕለቱና ሰዓቱ ግን ከቶ አይታወቅም:: ስለዚህም ነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ድልዋኒክሙ ሀልዉ፡ እስመ በጊዜ ኢትአምሩ ይመጽእ ወልደ እጓለ እመሕያው» በማለት በአባትነት ፍቅሩ የመከረን:: ማቴ.24÷44:: ሞት እንደ ሌባ ባልተጠበቀ ሰዓት በስውር ይመጣብናል:: ባለቤት ሌባ የሚመጣበትን ጊዜ ቢያውቅ ተግቶ በጠበቀ ነበር:: ግድግዳውን ምሰው ግምቡን አፍርሰው ይሰርቁት ዘንድ ቸል ባላለም ነበር:: ሉቃ.12÷59:: እግዚአብሔር የሞታችንን ጊዜ ከእኛ መሰወሩ ሁል ጊዜ ሞት እንዳለብን በማሰብ ተዘጋጅተን እንድንጠባበቅና ለትሩፋት ተግተን እንድንኖር ነው:: ጥንተ ጠላታችን ሰይጣን ግን እንዳንዘጋጅ ያዘገየናል:: ስለዚህ አበው እንዲህ በማለት ይመክራሉ:: «ሰይጣን ነገ ትናዘዛለህ፣ ዛሬ ይህን ፈጽም በማለት ኃጢአት ለማሠራት ግድ ቢልህ የዕድሜዬ መጨረሻ ዛሬ ቢሆን ማን ያውቃል?» ብለህ መልስለት:: «ከእግዚአብሔር አንድነት የምለይበት ይህ ክፉ ጊዜ ምን አልባት ነፍሴ ከሥጋዬ የሚለይበት ቢሆን፥ በንስሐ ኃጢአቴን የማጥብበት ዕድል ባላገኝስ ለዘለዓለም ምን ሆኜ እቀራለሁ» በለው:: «ይህ አንተ የምትለው ክፉ ነገር በድንገት የሚደርስብህ አይደለም::» በማለት በቁልምጫ ቃል ቢያባብልህና ግድ ቢልህም «ቢደርስ ብኝስ ለዘለዓለም ምን እሆናለሁ? ወግድ!!» በለው::

እግዚአብሔር የሰውን ድኅነቱን እንጂ ጥፋቱን ስለማይሻ መዓቱን በምሕረት ቁጣውን በትዕግሥት መመለስ ያበዛል:: ቸርነቱን አይተን አነዋወራችንን እናስተካክል ዘንድ ይፈልጋል:: በንስሐ አማካይነት ኃጢአታችንን ይደመስስልናል:: በንስሐ እንደ በረድ እንደ ፀምር እንነጻለን:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ አለ:: «በጭቃ እድፍ የተያዘ ሰው በውኃ ቢታጠብ ከእድፉ ይለያል:: የቀደመ መልኩም ይመለሳል:: በጽኑ ኃጢአት የተያዘ፥ በኃጢአት የተዳደፈ ሰው ግን በውኃ መታጠብ ከኃጢአት አይለየውም:: ጽኑ ንስሐ ብዙ ልቅሶ ያስፈልገዋል እንጂ፡ ለዘመዶቹ ለወዳጆቹ ከሚያለቅሰው ልቅሶ ይልቅ እያለቀሰ ትሩፋት መሥራት ያሻዋል እንጂ::» በጭቃ እድፍ የተያዘ ሰው በውጭ ያለ ስለሆነ ፈጥኖ ይነጻለታል:: ኃጢአት ግን ከውስጥ የምትነቃ ስለሆነ በብዙ ድካም ትርቃለች::

ሞት ድንገት ሊመጣ የሚችል ከሆነ ዘንዳ ንስሐን ለነገ ለከርሞ በማለት ማዘግየት አይገባም:: ሞት ሲወስድ ከሚቹ ፈቃድ አይጠይቅም:: ስለዚህ አውጉስጢኖስ «እመጣለሁ ተጠንቀቅ የሚል የመግደል ፈቃድ የለውም» አለ:: ከዘለዓለም ፍርድ ለመዳን ኃጢአት ከመሥራት መታቀብ ያስፈልጋል:: ዕለተ ሞቴ ሲደርስ ንስሐ እገባለሁ ማለት አይመችም:: እምቢ ለኃጢአት፥ ብለው ከሕገ እግዚአብሔር ርቀው በኃጢአት ለኖሩ እምቢተኞች ሞት የበቀል እንጂ የምሕረት አይደለምና:: ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን ሞትን ተዘጋጅታችሁ ተሰናድታችሁ ጠብቁት እንጂ ሞት ሲደርስ ተሰናዱ አላለንም:: አውጉስጢኖስ፦ «ሲቻለው ራሱን ማዳን ያልፈለገው ሰው በኋላ ሲፈቅደው አለመቻሉ የተገባ የቅጣቱ ፍርድ ነው» ካለ በኋላ «በቀኖቹ ሁሉ ተዘጋጅተን ሞትን እንጠባበቅ ዘንድ እግዚአብሔር መጨረሻውን ቀን ይሠውርብናል» በማለት ተናግሯል:: በሕይወተ ሥጋ ሳለን በምግባር አጊጠን ብንኖር ከሞት በኋላ የሚኖረው የነፍሳችን ደስታ ታላቅ ይሆናል::

### 4. የኃጥእ ሰው ሞት

ክቡር ዳዊት «ሞቱ ለኃጥእ ፀዋግ፡ የኃጥእ ሞቱ ክፉ ነው» በማለት ኃጢአተኞችን ክፋት እንደ ሚያጠፋቸው ገልጿል:: መዝ.33÷21:: ኃጥእ ሰው ከዛሬ ነገ ከዘንድሮ ከርሞ፣ ኃጢአቴን ተናዝዤ ንስሐ ገብቼ የወዳያ ዓለም ቤቴን ሠርቼ ከፈጣሪዬ ጋር ታርቄ እሞታለሁ ሲል ንስሐ ገብቶ ከፈጣሪው ሳይታረቅ ይሞታል:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚያደርግለትን ተግሣጽ እያቃለለ የሚኖር ስለሆነ ተስፋንና ሃይማኖትን አጥፍቷልና ተስፋ ቢያደርግም ቅጣቱን አያቀልለትም:: ኃጥእ ሰው ሞትን ይፈራል:: በአንጻሩ በክፉ አነዋወር ጸንቶ መመላለስ አያስፈራውም:: አውጉስጢኖስ የኖረበትን ክፉ ጠባይዕ ለማስወገድ ዐሥራ ሁለት ዓመት ተጋድሏል:: እንግዲህ መላ ዘመኑን በኃጢአት ያሳለፈ ሰው በሞቱ ጊዜ ጣዕር በዝቶበት የሞት ግርማ ተጭኖት ሲዘባርቅ ይሰማል:: በነፍሱ ላይ ዲያብሎስ ጽሉም ገጹን ሕሡም ራእዩን ይለውጥባታል፡ ትደነግጣለች:: ጠላት ሰይጣን ኃጥኡን «በሕይወት ዘመንኽ ሁሉ ቃለ እግዚአብሔርን በመስማት ነፍስህን ከመመገብ ቸል ብለህ ተዘልለህ ኑረህ አሁን እግዚአብሔር ይምርሕ ይመስልሃልን?» በማለት ያስደነግጠዋል::

ኃጥእ ሰውን የበደሉ ብዛት ይጫነዋል:: አንድ ጸሐፊ «ኃጥኡ የፈጸማቸው ክፉ ሥራዎች እንደ ክባቢ ሐራ /ወታደር/ ዙሪያውን ከበው በወዲያው ዓለም ተከትለንህ እንሔዳለን:: በፍርድ ቀንም በፈራጅ ዳኛ ፊት አብረንህ እንገኛለን ይሉታል» ሲል ገልጿል:: ይህ ሰው ከመኰነን ለማምለጥ ቢሞክርም እስከ ዕለተ ሞቱ ኃጢአትን ወድዷልና አይቻለውም:: በወደደው አነዋወሩ ይጠፋል:: መልካም ፍጻሜ አይሆንለትም:: ልቡ እንደ ደንጊያ ለደነደነ እንደ አንጥረኛ መስፍ ለጠና ሰው የእግዚአብሔርን ጥሪ አቃልሏልና በሞቱ ጊዜ ፍዳን ይቀበላል:: አውጉስጢኖስ «እርሱ ራሱ ሳይተዋቸው ኃጢአቶቹ የሚተዉት ኃጥእ ሰው በሞቱ ሰዓት የሚፈጽመው ሁሉ በግድ ይፈጽማልና እንደ አገባቡ ኃጢአቶቹን ሊጸየፍ ያስቸግረዋል» ብሏል::

ምሕረት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ እግዚአብሔር ኃጥኡ በኃጢአቱ እንዲሞት አይፈልግም:: በንስሐ ይመለስ ዘንድ ዕድሜ ይሰጣል:: ዛሬ ነገ ማለት ግን አያዋጣም:: የመዘግየትን ጉዳት ለማመልከት «አሜሃ ይዬውኡኒ ወኢያጸምእ፡ እኔን የሚጠሩበት ጊዜ ይመጣል፣ እኔም አልሰማቸውም» ብሏልና:: እግዚአብሔር ፍርዱ ርቱዕ በመሆኑ በደለኛውን ይበቀለዋል:: ኃጢአተኛው ከክፉ ሥራው ካልተመለሰ እንደሚጠፋ ተናግሯልና:: ሉቃ.13÷3፣ ሕዝ.33÷11::

ኃጢአተኛው ከክፉ ሥራው ቢመለስና ንስሐ ቢገባ የቀደመ ኃጢአቱን እንደማያስብበት እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷል:: ኃጥኡ በሞቱ ጊዜ እንደ ሚመለስና ይቅርታንም እንዲያገኝ ግን አልተነገረም:: ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ መሆኑ የንስሐን ዕድል በመስጠቱ ይታወቃል:: ንስሐ ባንገባ በኃጢአታችን እንደምንሞት ሲገልጽ «ትመውቱ በኃጢአትክሙ» በማ



www.eotcmk.org

ለት መላልሶ ገልጿል:: ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ጊዜ ብቻ እግዚአብሔርን የሚፈልግን ሰው እንዳይሰማው «ትፈልጉኛላችሁ ግን አታገኙኝም» በማለት አስረድቷል:: ያም ከሆነ በቅዱስ መጽሐፍ እንደ ተነገረ ቀርቦ ሳለ እግዚአብሔርን መጥራትና በመገኛው ጊዜ መፈለግ ያስፈልጋል::

በጣዕረ ሞት ካልተያዘ በቀር ኃጢአትን ጠልቶ ምረረ ገሃነመ እሳትን ዐውቆ ንስሐ መግባት የማይፈቅድ ሰው አለ:: በሞት አፋፍ ሳሉ ኃጢአትን አስታውሶ መጸጸት ትርፉ ምንድን ነው? ይህን በማስመልከት አውጉስጢኖስ:- «እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ እግዚአብሔር አምላኩን ረስቶ የኖረ ሰው በሞቱ ራሱንም ቢረሳ የተገባ ቅጣቱ ነው» አለ:: ቅዱስ ጳውሎስም ሁሉም የዘራውን እንደሚያጭድ ተናግሯል:: ዓለምን ወድዶ ፈቅዶ ሥጋውን ሲከውን የኖረ ሰው በሞቱ ክፉኛ ይጐዳል:: መበስበስንና መከራን የዘለዓለምንም ሞት ይሰበስባል:: እንኪያስ በተሰጠን ጊዜ ልንጠቀምበት ይገባል:: እግዚአብሔር በምሕረቱ የዛሬዋን ዕለት የሰጠን የመጨረሻዪቱ እንደ ሆነች አናውቅምና ሞትን አለማሰብ እብደት ነው:: ሞትን እያሰቡ አለመዘጋጀት ደግሞ የከፋ ስንፍና ነው:: አንድ የንጉሥ አገልጋይ የነበረ ሰው ዓለምን ትቶ ለመመነን ወስኖ ከንጉሡ ቀርቦ ሲሰናበት ንጉሡ «ከቤተ መንግሥት ወጥተህ መሔድህ ለምንድን ነው?» በማለት ቢጠይቀው «በማይመች አካሔድ በሔዱበት ባለፈ ጊዜና በሞት መካከል የንስሓ ጊዜ የግድ ያስፈልጋል ብሎ ነው» በማለት መለሰለት ይላሉ:: አንድ ባዕለ ጸጋ መልአከ ሞት ነፍሱን ከሥጋው ለይቶ ሊወስድ ሲመጣ አጋንንት ነፍሱን ለመንጠቅ በዙሪያው ከበው ተመልክቶ:- «እባካችሁ ለአንዲት ቀን እንኳ ተዉኝ» በማለት አምርሮ ጮኸ:: በዚህ ጊዜ «ብዙ ዘመን ተሰጥቶህ ሳትጠቀምበት በኃጢአት አሳለፍከው፣ ከእንግዲህ ወዲህ ግን ተጨማሪ ዕድሜ አይሰጥህም፤ በቃህ!» አሉት:: ርዳታ ሽቶ ቢጮህም መልካም ሥራ አልተገኘበትም ነበርና ሊረዳው የሚችል አላገኘም:: በቀቢጸ ተስፋ ተይዞ እየቃተተም ነፍሱ ወጣች::

ክቡር ዳዊት «ወፍኖቶሙሰ ለኃጥአን ትጠፍእ፤ የክፉዎች መንገድ /የኃጥአን ተድላ ደስታቸው/ ትጠፋለች» ይላል:: መዝ.1÷6:: እግዚአብሔር የክፉዎችን ሥራ አይወድም:: ዋጋ በማስጠት÷ አብነት በመሆን ጸንታ አትኖርምና:: ከተፈተለ ገመድ፣ ከተተከለ ግንድ፣ ከተቆፈረ ጉድጓድ አድርሳቸው በፍዳ አትያዝም፤ እሳት ገለባን ይዞት እንዲጠፋ ይዛቸው ትጠፋለች:: ቅድመ ዓለም ለጻድቃን ተብሎ በልበ ሥላሴ በተዘጋጀ በመንግሥተ ሰማያት ኃጥአን አይኖሩም:: ጠቢቡ ሰሎሞንም «ክፉ ሥራ÷ የኃጥእ ሰው ሰውነት÷ ሥራውም ሠሪውም መከራ በታዘዘበት ቀን ይጠፋሉ» ብሏል:: መጽሐፈ ተግሣጽ1÷19:: የኃጢአት ክፋት የበረታ መሆኑን አውጉስጢኖስ ሲገልጽ «እኩይ ዘኢየኀልቅ- የማያልቅ ክፋት» ብሏል:: ሞት ለኃጥአን ከመከራ ወደ ጽኑ መከራና ቃይ የሚሸጋገሩበት /የሚገቡበት/ ነው:: ለዚህም ነው ኃጥአን የሆኑት ሄሮድስ፣ ሐናንያና ሰጲራ ወዘተ ሞቱ የተባሉት:: ማቴ.2÷19፤ ሥራ.5÷5፤ 12÷23::

በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተነገረ በመላ ዘመናቸውን ከሕገ እግዚአብሔር ርቀው በኃጢአት ወድቀው የሚኖሩ ሁሉ በሥጋቸው ወደ መቃብር ሲወርዱ በነፍሳቸው «ዕፄሁ ዘኢይነውም እሳቱ ዘኢይጠፍእ፤ ትሉ ወደ ማያንቀላፋ እሳቱ ወደማይጠፋ ወደተባለለት መካን ይወርዳሉና፤ ሞታቸው አስጨናቂ ነው::

## 5. የጻድቃን ሞት

«ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር» እንዲል ሞት ለቅዱሳን ክብር፣ ዕረፍት፣ እንቅልፍ ነው:: 1ኛተሰ.4÷14፤ ሮሜ.14÷9:: የጻድቃን ነፍስ የምትለይ በመዓዛ ገነት፣ በይባቤ መላእክት፣ በመዝሙረ ዳዊት ነው:: ከድካም፣ ከፃዕር የሚያርፉበት፣ ወደ ዘላለም ደስታ የሚገቡበት ነው:: እንዲህ ስለሆነም ሞት በቅዱሳን ዘንድ ይናፈቃል:: በዚህ ምድር ረጅም ዘመን መኖር ስቃይንና መከራን ከማብዛት ያለፈ ፍሬ አይለቀምበትም፤ ሰው በሕይወተ ሥጋ የሚኖርበት ዘመን የዕረፍት ሳይሆን ለዘለዓለማዊ ሕይወት ለመብቃት በብዙ የሚደከምበት ነውና:: እጅግ አድካሚ የሆነ ሥራን አከናውነው ወደ ዘለዓለም ዕረፍት ይሔዳሉና ሞት ለቅዱሳን የተመሰገነች ናት:: አንድ ፈላስፋ «ረጅም ዕድሜን የሚለምኑ የዚህ ዓለም ወዳጆች ብዙ መከራንና ስቃይን ካልሆነ ምኑን ይለምናሉ!» አለ::

በሞት ጊዜ ቅዱሳን ጭንቅ ስቃይ የለባቸውም፤ «ግብኢ ነፍስየ ውስተ ዕረፍትኪ» እንዲል ክቡር ዳዊት «ሑሪ ነፍስ ክርስቲያናዊት ፃኢ እምዝ ዓለም» የሚለው ገጸ ንባብ አያስፈራቸውም:: ምክንያቱም «ነፍሱን ሊያገኛት የሚሻ ይተዋት» የሚለውን ሰንቀው በመያዝ ከዚህ ዓለም ነገር ራሳቸውን ለይተው ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ባለመውደድ ኖረዋልና:: የዚህ ዓለም ባዕለ ጸግነት፣ ሀብት ንብረት በእነርሱ ዘንድ እንደምናምን የሚቆጠር ስለሆነ ነፍሳቸው ከሥጋቸው በክብር ስትለይ አያዝኑም:: በሞታቸው ጊዜ «አምላኪየ ወኩለንታየ» ከማለት በቀር መቄርቄር፣ ማዘን፣ መተከዝ የለባቸውም:: «በሰላም ቦቱ እስክብ ወእነውም» የሚለውን በመዘመር ያርፋሉ:: ዓለምን ትተው እርሱን ብቻ አገልግለውታልና እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳቸውን ወደ ዘለዓለም ዕረፍት ያስገባል:: ጥበብ 4÷7::

ሞት ለጻድቃን ከጨለማ አበጋዝ ከዲያብሎስ ጾር፣ ከዚህ ዓለም ሁከት የሚሸጋገሩበት ስለሆነ ደስታ ነው:: ድል የማድረጊያ ጊዜ ነው:: የጻድቅ ሰው ነፍስ ከሥጋው ተለይታ በይባቤ መላእክት ወደ ፈጣሪዋ ስታርግ ሲያይ ዲያብሎስ «አመለጥከኝ» በማለት ቁጭቱን መግለጡ ሞት የዕረፍት፣ የክብር፣ ድል የማድረጊያ ድልድይ በመሆኑ ነው:: አንድ አረጋዊ በሞቱ ሰዓት ሊለያቸው መሆኑን አይተው በአጠገቡ የነበሩ ሁሉ ሲያለቅሱለት ተመልክቶ ሳቀባቸው:: ስለምን ትስቃለህ ቢሉት «እኔ ከመከራ ከጻዕር ወደ ዕረፍት እሔዳለሁ፣ እናንተ ግን ታለቅሳላችሁና ስለዚህ ነው» በማለት መለሰላቸው:: ማልቀስ የሚገባም በሕይወቱ ሳለ በኃጢአት ባሕር ጠልቆ ለሚዋኝ አብድ ነው:: ሞት ለቅዱሳን ከኀዘን ወደ ደስታ ቦታ የሚሔዱበት በመሆኑ ደስታቸው ወሰን የለውም::

ሥጋና ነፍስ ተዋሕደው ሰውን ያስገኙ ቢሆንም በፈቃድ ስለሚለያዩ በሰው ሕይወት ውስጥ የተለያዩ ፈተናዎች ይፈጠራሉ:: «ሥጋ ነፍስ ልትሠራው የማትወደውን ይወዳል፣ ነፍስም ሥጋ ሊሠራው የማይወደውን ትወዳለች:: ስለዚህ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ::» ገላ.5÷16–17:: በዚህ ውጊያ ፈቃደ ሥጋ አይሎ ፈቃደ ነፍስን ድል ቢያደርግ ሥጋን ማርኮ ለሰይጣን ያስገዛዋል፣ ፈቃዱንም ያስፈጽመዋል፤ የእንስሳትን ሥራ ያሠራዋል:: ፈቃደ ነፍስ ከአሸነፈች ሥጋን ለእግዚአብሔር ታስገዛዋለች፤ ፈቃደ እግዚአብሔርን በመፈጸም እንዲጸና ታደርገዋለች:: ገላ.5÷22:: ቅዱሳን መላእክትን ታስመስለዋለች፤ በቅዱሳን መላእክት ግብር ታኖረዋለች:: በዚህ ጊዜ ፈቃደ ነፍስ ፈቃደ ሥጋን የመግዛት ኃይልን ታገኛለች:: በውጊያው ፈቃደ ሥጋ ያየለ እንደ ሆነ የነፍስ ፈቃዷ ትደክምና ለፈቃደ ሥጋ ተገዥ ትሆናለች:: ሮሜ.7÷9–11:: ቅዱሳን በጾም፣በጸሎት፣ በስጊድና በመሳሰሉት የጽድቅ ሥራዎች ጸንተው በጽድቅ ጎዳና ተጉዘው ጠርነቱን ያሸነፉ ስለሆነ ከዚህ ውጊያ ወደ ጸጥታ ቦታ የሚሸጋገሩበትን ሞታቸውን ይናፍቃሉ:: ከዕድሜያቸው አንዲት ዕለት ባለፈች ቁጥር ይህ የውጊያ ጊዜ በአንድ ቀን መቀነሱን እያሰቡ ደስ ይላቸዋል:: ንዋይ ኅሩይ ቅዱስ ጳውሎስ «እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ:: በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና÷ ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ:: እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» በማለት ተናገረ:: ሮሜ.8÷21–24::

እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ «ልሔድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤



www.eotcmk.org

ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻለው ነውና» በማለት ዕለተ ዕረፍቱን እንደሚመኝም ገልጿል:: ምክንያቱም ከሞት በኋላ ወሰን የሌለው ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዳለ ያውቃልና:: ፊልጵ.1÷23:: በባሕር የሚጓዝ ሰው ስለ ደኅንነቱ እርግጠኛ የሚሆነው ማዕበል ሞገድ ሳይነሣበት በሰላም ሊደርስ ካሰበበት ወደብ ከደረሰ ብቻ ነው:: እንደዚሁም በባሕር በተመሰለ በዚህ ዓለም ስንኖር ብዙ የኃጢአት ማዕበል ያማታናል:: የቅዱሳን ነፍስ የተመሰገነች መባሏ በምግባር፣ በትሩፋት ጽምድት ሆና /ተጠምዳ/ ባሕረ ኃጢአትን በእግዚአብሔር ቸርነት በመሻገሯ ነው:: መንገደኛ መንገዱን ፈጽሞ ያሰበበት ቦታ ሲደርስ ደስ እንደሚለው ጻድቁም በጽድቅ መንገድ ተጉዞ በሞት አማካይነት ከእግዚአብሔር ዋጋውን ይቀበላልና ይህን በማሰብ ደስ ይለዋል:: ሞት እግዚአብሔርን ከመበደል የሚላቀቁበት ነው:: ጥበብ 4÷14:: እንዲያም ከሆነ ሞት የክፉ ሥራ መቀበሪያ ነው ማለት ነው:: አነዋወሩን ከእግዚአብሔር አንድነት ያልለየ ሰው ሲሞት ኃጢአት የመሥራት ዕውቀት ወደ ሌለበት አዲስ ሕይወት የሚገባ ስለሆነ ደስ ይለዋል:: ዕለተ ሞቱን በማሰብ ይኖር የነበረ አንድ ሰው «በምሞትበት ሰዓት ኃጢአት ከሚሠራበት ከዚህ ዓለም የምትሔድበትና እግዚአብሔርን የማትበድልበት ጊዜ እነሆ ደርሶልሃልና ደስ ይበልህ» በሉኝ ሲል ለቤተ ሰዎቹ ነግሮ እንደ ነበር ይነገራል::

ሞት ለቅዱሳን «ተፍጻሜተ ጻዕር» ብቻ ሳይሆን ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡበት ኖኅት ነው:: ለዚህም ነው ቅዱሳን ሞትን «በሩን አንቺ ካልከፈትሽልኝ ፈጣሪዬን ለማየት አይቻለኝም» በማለት ናፍቆታቸውን የሚገልጹት:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እንዲህ አለ፤ «ንጉሥ አንድ ምስኪን ሰው ይኖርበት ዘንድ ለራሱ ያሠራውን አዳራሽ ሸላልሞ ቢያዘጋጅለት ዳሩ ግን እስከዚያ ዕለት ድህውን ሽታና ክርፋት ባለበት በከብቶች በረት እንዲሰነብት ቢያደርገው ድህው ወደ ንጉሡ አዳራሽ ለመግባት ምንኛ በቸኮለ ነበር::» እንደዚሁም ቅዱሳን በሞቅኅ /ወኅኒ/ ከተመሰለ ከዚህ ዓለም ወጥተው ወደ ዘለዓለማዊ እልፍኝ በመሔድ ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ ቅዱስ እያሉ ከመላእክት ጋር እንደ መላእክት ባለ ማረፍ ምስጋናውን ለማመስገን ይጣደፋሉ:: ከሥጋ ማሰሪያ ተፈትተው ከፈጣሪ ጋር ለመኖር አብዝተው ይናፍቃሉ እንደ ስምዖን አረጋዊ:: ይህ ቅዱስ፣ ደግ፣ ቅን፣ ኀዳጌ በቀል ሲሆን የእሥራኤልን ደኅንነት ያይ ዘንድ ተስፋ በማድረግ በኢየሩሳሌም ይኖር ነበር:: የክርስቶስን መወለድ ሲጠባበቅ ከአልጋ ተጣብቆ ይኖር ነበር:: በአራቱ እንደ ታዘዘ ጌታችን፣ እመ ቤታችንና ቅዱስ ዮሴፍ ወደ ቤተ መቅደስ በገቡ ጊዜ ስምያንንም መንፈስ ቅዱስ አነሣስቶ አጽናንቶ ወደ ምኩራብ ወስዶት ነበር:: በዚያም ተቀብሎ አቀፈው:: ከዚህ ጊዜ ያደረስከኝ ከደዌዬ የፈወስከኝ ብሎ ካመሰገነው በኋላ ከዚህ ዓለም ጣዕር ጋር ያወጣው ዘንድ «ይእዜ ትስዕሮ ለገብርከ፣ ባሪያህን ዛሬ በሞት ታሰናብተዋለህ» በማለት ሞቱን ለመነ:: ሉቃ.2÷25–30:: እንግዲህ የቅዱሳን ሞት ልደት እንጂ ሞት አይባልም:: ወደ ዘለዓለም ብፁዓዊ ሕይወት መረማመጃ ነውና:: ስለዚህ «ሞት ሆይ÷ የጉዳት ሁሉ ፍጻሜ የፃርና የጋዕር መሰናበቻ÷ የዕረፍት ፈለማ ስለ ሆንህ አንተን የማይሻና የማይናፍቅ ማን ነው» በማለት አውጉስጢኖስ ተናገረ:: እንኪያስ ቅዱሳን እግዚአብሔርን ያዩ ዘንድ እንደ መልካም ስጦታ ሞትን በብርቱ መለመናቸው ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን ዐውቀው ነው::

ሞት ወደ ሚሻለው አነዋወር የሚሻገሩበት ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን «ሰውነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደች ሆናለችና በጥቂት ዘመንም ቢሞት ብዙ ዘመን ጨረሰ» በማለት ገልጿል:: መጽ. ጥበብ 4÷13:: አንድ ልጅ ብቻ የነበረው ሰው ብዙ ምጽዋት በመያዝ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ለአባቱ ረጅም ዕድሜ እንዲሰጠው ለልጄ ይለምኑለት በማለት አደራ አስጠበቀ:: ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን ልጁ አረፈ:: በዚያም ያ ሰው መሪር ኀዘን አዘነ:: እግዚአብሔር የዚያን ሰው መሪር ልቅሶ ተመለከተ፤ መልአኩንም ወደ እርሱ ላከ:: መልአኩም ለልጅህ ረጅም ዕድሜን ለመንከ፣ ትንሽ ሲለ ምኑት ብዙ የሚሰጥ አምላክም አንተ ከለመንከለት ይልቅ ዘለዓለማዊ ሕይወትን እንደ ሰጠው ዕወቅ በማለት አጽናንቶታል» ይላሉ:: ቅዱሳን ሰማዕታት ሊገድሏቸውና መከራ ሊያጸኑባቸው ሲወስዷቸው ወደ ሕይወት የሚሔዱ መሆናቸውን በመረዳት ደስ እያላቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይሔዱ ነበር:: ሞትን መፍራት የለባቸውም:: እግዚአብሔርን የሚወዱና ሊያዩት የሚናፍቁት ስለሆነ ሞት ለቅዱሳን ደስታ ነው:: እነርሱ ቅሉ ኃጢአትን እንጂ ሞትን አይፈሩም::

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን እንዲህ አለ:- «የጻድቃን ነፍስ ግን በእግዚአብሔር እጅ ናት:: ስቃየ ገሃነምም አላገኛቸውም:: ላላዋቆች ዐይኖች ግን ሞት ያገኛቸው መሰላቸው:: በሞትም ከዚህ ዓለም መውጣታቸው ክፉት እንዳለባቸው ተቈጠረ:: በሞትም መሔዳቸው ጥፋት መሰለ:: እነርሱ ግን በደስታ በተድላ አሉ:: በሰው ፊት ሞቱ ቢባል አለኝታቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ሞት የሌለባት ፍጽምት ሕይወት ናት:: ጥቂት መከራ ተቀብለው ለብዙ ጸጋና ክብር ይዘጋጃሉ:: እግዚአብሔር በመከራ ፈትኗቸዋልና ለእርሱ የተዘጋጁ /የተገቡ/ ሆነው አገኛቸው...:: በጸጋ በክብር በሚጐበኙበት ወራት እንደ ፀሐይ ያበራሉ:: በብር የተፈናጠረ የብረት ፍንጣሪ እየሰፉ እንዲሔድ በክብር እየሰፉ ይሔዳሉ:: ሕዝቡን አሕዛቡን ይገዛሉ /በነፍስ እንደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት÷ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ/ እግዚአብሔርም ለዘለዓለም ይነግሥላቸዋል::» መጽ.ጥበብ 3÷1–8:: በዚህም ሞት ለቅዱሳን ዋጋ የሚያገኙበት እንደ ሆነ እንረዳለን:: ሞት እንደ ቅጣት በመታየቱ ታዝን የነበረች አንዲት እናት «የተወደደህ ሞት ሆይ÷ ብዙ ሰው የሚያረክስህ /የሚጠላህ/ ሲሆን በመዓልት በሌሊት አክብሬ ስጠራህ ወደ እኔ አለመምጣትህ ስለ ምንድን ነው?» በማለት ሞትን ትመኝ ነበር ይላሉ::

በአጠቃላይ ሞት ለቅዱሳን ዕረፍት ነው:: በእንቅልፍ ይመሰላል:: ለምሳሌ ቅዱስ እስጢፋኖስ፣ አልዓዛር፣ ክቡር ዳዊትና ሌሎችም አንቀላፉ ተብለዋል:: ሥራ. 7÷60፤ ዮሐ.1111፤ 1ኛነገ.2÷10፤ ማቴ.27÷53÷9፤ 1ኛቆሮ.15÷6:: ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅም «ሞት መራራ ሆኖ እኔ መራራ የምለው አይደለሁም:: ስለ ኃጢአታችሁ መሪር ይሆንባችኋል እንጂ. እርሱስ እንደ እንቅልፍ ነው» ብሏል::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር


በታል ያለው እንዲደረሳ !!!

«ሐሳይማን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ»

ሐመርና ስምዐ ጽድቅ በልዩ ልዩ ጊዜ ለምእመናን ካቀረቧቸው ሥራዎች መካከል የተውጣጡትን የተለያዩ መጣጥፎች፣ ግጥሞች፣ አባባሎች፣ ምሳሌዎች፣ወ.ዘ.ተ. በተለያዩ እትሞች ተበታትነው ቀርበው ከነበሩት መካከል የተወሰኑት በዚህ መጽሐፍ ተሰባስበው ቀርበዋል:: በተመሳሳይ ከዚህ በፊት ምሥጢሬን ላካፍላችሁ አንደኛና ሁለተኛ መጽሐፍ እንዲሁም ቬነሲያን የመሳሰሉ ተመሳሳይ ዝግጅቶችን ማቅረባችን ይታወሳል::

በሁሉም የሐመር መጽሔት እና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎቻችን ውስጥ ያገኟቸዋል !!
ስልክ- 23-45-29/23-45-30/22-86-01




www.eotcmk.org

# ምሥጢረ ሥጋዌ በውዳሴ ማርያም

*መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው*

ውዳሴ «ምስጋና፣ ክብር፣ ምርቃት፣ አገልግሎት፣ መሥዋዕት» የሚል ትርጓሜ አለው:: ይኸውም ልዑል እግዚአብሔርንና ሌሎች ፍጥረታትን ከፍ የሚያደርግ፣ የሚያወድስና የሚያከብር ቃል ነው:: ምስጋና የባሕርይና የጸጋ በሚል በሁለት ይከፈላል:: ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ምስጋና የባሕርይ ሲሆን ለፍጡራን የሚቀርበው ግን የጸጋ ነው:: አፈጻጸሙም አስቀድሞ በተደረገ ጉዳይ ላይ አጽንዖት በመስጠት ሊከወን ይችላል:: ለምሳሌ አሳብና ምኞት ሲፈጸም ስእለት ሲደርስ ለፈጻሚው አካል በሚያስደስት ቃል በነቢብ፣ በዜማ፣ በግጥም፣ በሥነ ጽሑፍ ሊቀርብ ይችላል::

## የውዳሴ ማርያም የትመጣ (origin)

ብሩና ፍቀው ቀለም በጥብጠው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸውን የምስጋና መጻሕፍት ከደረሱ ቅዱሳን አባቶች መካከል ታላቁ የነገረ መለኮት ምሁር ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም አንዱ ነው:: ቅዱስ ኤፍሬም በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን /306 ዓ.ም/ ንጽቢን በምትባል አገር ተወለደ:: የንጽቢን ሊቀ ጳጳስና ከሠልስቱ ምእት ወገን ከሆነው ከአባ ያዕቆብ ዘንጽቢን ዘንድ ነገረ ሃይማኖትን አጥንቷል:: ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነገረ መለኮት ምሁራን መካከል ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬም በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል::

ቅዱስ ኤፍሬም በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ ውዳሴ ማርያምን ደርሷል:: ሲደርስም ደራስያን አውጥተው አውርደው ተጨንቀው እንደሚደርሱት አልነበረም:: በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ከዳር እስከ ዳር ሰተት አድርጎ ሊደርስ ችሏል:: የሐዲስ ኪዳን መተርጉማን አደራረሱን እንዲህ ይገልጹታል:: «ከዕለታት በአንድ ቀን ዕለቱ ሰኑይ /ሰኞ/ ጊዜው ነግህ ነው:: /አባ ኤፍሬም/ የነግህ ተግባሩን አድርሶ ከመካነ ግብሩ /ከሥራው ቦታ/ ተቀምጦ ሳለ እመቤታችን ትመጣለች:: የብርሃን ምንጣፍ ይነጠፋል፣ የብርሃን ድባብ ይዘረጋል፣ ከዚያም ላይ ሁና 'ሰላመ ለከ ኦ ፍቁርየ አፍሬም፣ ወዳጄ ኤፍሬም ሆይ÷ሰላም ለአንተ ይሁን' ትለዋለች፣ እርሱም ፈጥኖ እጅ ነስቶ ይቆማል:: 'ወድሰኒ፣ አመስግነኝ' ትለዋለች፣ ' እፎ እክል ወድሶተኪ ዘኢይክሉ ሰማያውያን ወምድራውያን፣ ምድራውያን ጻድቃን ፣ሰማዕታት ሰማያውያን መላእክት አንቺን ማመስገን የማይቻላቸው ለእኔ እንደምን ይቻለኛል አሳት:: 'በከመ አለበወከ መንፈስ ቅዱስ፣መንፈስ ቅዱስ እንደ ገለጸልህ' ተናገር አለችው:: በተረቱበት መርታት ልማድ ነውና፣ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበሥራት 'እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ፣ ወንድ ሳላውቅ ይህ እንደምን ይሆንልኛል' ብትለው መልአኩ መንፈስ እግዚአብሔር ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ' ብሏት ነበርና እርሷም 'የእግዚአብሔር 'መንፈስ የገለጠልህን ተናገር' በማለት ቅዱስ ኤፍሬምን ረታዋለች:: ከዚህ በኋላ 'ባርክኒ' ይላታል፣ «በረከተ ወልድየ ወአቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ይኀድር በላዕሌከ»፣ የልጇ በረከት የባሕርይ አባቱ የአብና የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ በረከት በአንተ ላይ ይሁን» ትለዋለች፣ ተባርኮ ምስጋናዋን ይጀምራል:: 'ሲያመሰግናት ደቀ መዝሙር ቅኔ ቆጥሮ እንዲቀኝ ድርሰት አስቦ እንዲያጽፍ አይደለም:: ብልህ ደቀ መዝሙር ያጠናውን ቀለም ከመምህሩ ፊት ሰተት አድርጎ እንዲያደርስ እንደዚያ ነው::» /ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው÷ 1963 ዓ.ም.::

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ 13ኛው–15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ወቅት «ወርቃማው የኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ዘመን» ተብሎ ይጠራል:: በዚያን ዘመን ውዳሴ ማርያም ከዐረብኛ ወደ ግእዝ ተተርጉሟል:: በዚያን ወቅት ከውዳሴ ማርያም ጋር በርካታ የጸሎትና የሥርዓት መጻሕፍት ፣ የተለያዩ ገድላትና ድርሳናት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉመው ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቀርበዋል:: ይህም በመሆኑ ነው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመራማሪዎች ወቅቱን *«ወርቃማው የኢትዮጵያ የግእዝ የሥነ ጽሑፍ ዘመን»* የሚሉት::

ዛሬ ለምእመናን መማፀኛ ከፍተኛ አገልግሎት ከሚሰጡ የጸሎት መጻሕፍት መካከል ውዳሴ ማርያም አንዱ ነው:: ውዳሴ ማርያም ሁለት ቃላት የተዛረፉበት ሐረግ ሲሆን «ውዳሴ» ተዛራፊ «ማርያም» ዘርፍ ነው:: ትርጉሙም *የማርያም ምስጋና* ማለት ነው:: በአራቱ ማዕዘን የሚገኙ የተዋሕዶ ልጆች እመቤታችንን «ሰአሊ ለነ ቅድስት፣ ቅድስት ሆይ ለምኝልን» ሳይሏት አይውሉም፣ አያድሩም:: በነግህና በሠርክ በመጸለይ እመቤታችን ከልጇ እንድታማልዳቸው ይማፀኑበታል:: ለጸሎት እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ ባሻገር ለትምህርትም ጠቃሚ የሆኑ ምሥጢራትን ስለ ያዘ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በጾመ ፍልሰታ በመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት መሠረትነት የተደረሰውን ይህን የምስጋና የጸሎት መጽሐፍ ትርጓሜውን በመተርጎም ምሥጢሩን በማመስጠር ለምእመናን ከኀሊና የማይፋቅ ደገኛ ትምህርት ይሰጡበታል::

በአጠቃላይ ውዳሴ ማርያም በሰባቱ ዕለታት የተከፋፈለ የምስጋና መጽሐፍ ሲሆን እንደየ ምሥጢሩ ሁኔታ የየዕለቱ ምስጋና እያንዳንዱ ንዑስ ክፍል አጭርና ረጅም ነው:: በተጨማሪ በቁጥር የበዛና ያነሰ አለው:: ንዑስ ቁጥሩ በጠቅላላ ሲደመር ግን በእመቤታችን ዕድሜ መጠን 64 ይሆናል:: ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው::

1/ የሰኞ ውዳሴ ማርያም– 9 ክፍል
2/የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም–15 ክፍል
3/ የረቡዕ ውዳሴ ማርያም –8 ክፍል
4/ የሐሙስ ውዳሴ ማርያም–7 ክፍል
5/ የዓርብ ውዳሴ ማርያም–10 ክፍል
6/ የቅዳሜ ውዳሴ ማርያም–10 ክፍል
7/ የእሑድ ውዳሴ ማርያም–9 ክፍል ናቸው::

በዜማ ትምህርት ቤት የዜማ ትምህርት የሚማሩ ደቀ መዛሙርት ማታ ማታ በየዕለቱ በዋዜማው /ለምሳሌ የሰኞ ውዳሴ ማርያም እሑድ ማታ/ በዜማ ያደርሳሉ /ይጸልያሉ/:: ዜማው ሁለት ዓይነት አደራረስ አለው:: ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያለው አራራይ ሲባል የእሑድ ደግሞ ዕዝል ይሰኛል::

በቅኔና በትርጓሜ መጻሕፍት ቤት ውዳሴ ማርያም የሚደረሰው በንባብ ሲሆን የሚደርሱት ደቀ መዛሙርት በጣም ካሳነሱ የሰባቱ ዕለታት ውዳሴ ማርያም ሙሉ በሙሉ ይደገማል:: ይኸውም እያንዳንዱ ንዑስ ክፍል በአንድ አዳይ /አከፋፋይ/ አማካይነት ይታደላል:: ይህም በንባብም ይሁን በዜማ የጸሎት አዳራረስ ማስታኮት ይባላል::

የሐዲስ ኪዳን መተርጉማን ከምን አንጻር በሰባቱ ዕለታት እንደ ተከፈለ እንዲህ በማለት ያመሰጥራሉ:: «በሰባቱ ዕለታት መመስገን ፈቃዷ ቢሆን አንድም ሰባቱ ዕለታት ምሳሌዋ ናቸው::» ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በሰባቱ ዕለታት የተፈጠሩትን ፍጥረታት ከምሥጢረ ሥጋዌ ጋር በማነጻጸር የራቀውን አቅርበው የረቀቀውን አጉልተው ተርጉመዋል:: ሰባቱ ዕለታት እንዴት ተመስጥረው እንደ ተብራሩ የውዳሴ ማርያም ትርጓሜን ይመልከቱ::



www.eotcmk.org

ቅዱስ ኤፍሬም የአምላክ የምስጢር መዝገብ ለሆነችው ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ልዩ ፍቅር ነበረው:: ከፍቅሩ ጽናት የተነሣ «ሲ.መጸውትም በሥላሴ፣በመላእክት፣ በጻድቃን፣በሰማዕታት ስም አይመጸውትም፤ በእመቤታችን ስም ይመጸውት ነበር:: ንቋቸው አጥቅቷቸው ነውን? ቢሉ አይደለም:: የእመቤታችን ፍቅር ባያደርሰው ነው፤ የእመቤቴ ምስጋናዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት፣ እንደ ምድር አሸዋ በዝቶልኝ እንደ ልብስ ለብሼው እንደ ምግብ ተመግቤው ጠግቤው እያለ ይመኝ ነበር::» እግዚአብሔር ጥቂት ሲለምኑት አብዝቶ መስጠት ልማዱ ነው:: ቅዱስ ኤፍሬም ከለመነው በላይ ተሰጠው:: የተሰጠው ጸጋ ቢበዛበት «አኃዝ እግዚእ መዋግደ ጸጋከ፤ የጸጋህን ማዕበል ገትተህ ያዝልኝ» ብሏል:: «እግዚአብሔር ጸጋውን ሰፍሮ አይሰጥም» እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ የሰው ስጦታ በመጠንና በጊዜ የተገደበ ነው:: የእግዚአብሔር ስጦታ ግን ገደብ የለውም:: በንጹሕ ልቡና በትሑት ሰብእና የለመኑትን የሚሰጥ እግዚአብሔር ልቡናውን ብሩህ አድርጎለት እጅግ ብዙ የሆኑ /ዐሥራ አራት ሺ/ ድርሳናትንና ተግሣጻትን ደርሷል:: ከእነዚህም ውስጥ በመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት ላይ ያተኮሩት የትርጓሜ መጻሕፍት፣ ለመናፍቃን መልስ የተሰጠባቸው የተግሣጽ መጻሕፍቱ፣ በእመቤታችን ቅድስናና ዘላለማዊ ድንግልና በጌታችንና በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ዙሪያ በቁ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መዝሙራቱና ድርሳናቱ ተጠቃሽ ናቸው:: በዚህ ጽሑፍ ስር ቅዱስ ኤፍሬም ከደረሳቸው መጻሕፍት አንዱ የሆነውን ከ«ውዳሴ ማርያም» ምሥጢረ ሥጋዌ የተነገረበትን የምስጋና አንቀጾች እንዴት ምሥጢረ ሥጋዌ እንደ ተሰበከባቸው ለመቃኘት እንሞክራለን::

## «ፈቀደ እግዚእ ያግዕዞ ለአዳም ኅዙነ ወትኩዘ ልብ፤ ያዘነ የተከዘ አዳምን ሊያድነው ወደደ»

ቅዱስ ኤፍሬም የደረሰው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የምስጋና መጽሐፍ የሚጀምረው በዚህ ዐረፍተ ነገር /ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ዘር ይሉታል/ ነው:: በዐረፍተ ነገሩ ለመረዳት እንደሚቻለው የድርሰቱ መጀመሪያ *«ኅዙነ አዳም»* ነው:: ኅዘነ አዳም ደግሞ ለአምላክ ሰው መሆን መሠረታዊው ምክንያት ነው:: እኛም በዚህ እትም የኅዘነ አዳምን ምክንያቶች በአጭሩ ከዳሰስን በኋላ፤ ይህንን ኀዘኑን የተመለከተው አምላክ አዳምን ሊያድነው እንደ ፈቀደ በአጭሩ እንመለከታለን::

### 1. ኅዘነ አዳም

አባታችን አዳም የገጠመው ኀዘን የቤተ ፊት ኀዘን አይደለም:: ቤተ ፊት /አግኝቶ ያጣ ሰው/ የሥጋውን ምቾት እያስታወሰ ያዝናል፤ ይተክዛልም:: በዚህ ወር ይህን አድርግ ነበር ዛሬ ግን ያሁሉ ቀረ በማለት ይቆጫል:: አባታችን አዳም እየዋለ እያደረ እንደ እግር እሳት ይለበልበው የነበረው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሶ ለሰይጣን ጆሮውን ያዋሰበትን ዕለት ነው:: «ፈጣሪዬ አትብላ ያለኝን ዕፀ በለስ በልቼ ከፈጣሪ ትእዛዝ ወጣሁ» እያለ ያለቅስ ነበር:: መሪር የሆነውን አዳምን ኀዘን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት እንዲህ በማለት ይገልጹታል:: «አልቦቱ ካልዕ ኀሊና ለአዳም ዘእንበለ ብካይ ላዕለ ኃጢአቱ» ለአዳም ኃጢአቱን እያሰበ ከማዘን በስተቀር ሌላ አሳብ አስተሳሰብ አልነበረውም:: ኃጢአቱ ያስተከዘውን አዳምን እግዚአብሔር በምሕረት ዐይን ዓይቶ ሊያድነው ወደደ:: ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር ብለው የሚያዝኑት ኀዘን ምላሹ የዘ ላለም ሕይወት ነውና:: 2ቆሮ.7÷10:: ለመሆኑ አዳም ለምን አዘነ?

### ልጅነቱን ስለ አጣ

የአዳም ልጅነት በነጻነት ያዚህ ዓለም ገዥ ሁኖ እንዲኖር በእግዚአብሔር አርአያና መልክ በክብር መፈጠሩ ነው:: «ሰውን በመልካችን እንፍጠር የባሕር ዓሣዎችን የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትን፣ ምድርን ሁሉ በምድር የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዛ» ዘፍ. 1÷21:: እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው የልጅነት ሥልጣን በሥነ ፍጥረቱ አልቆ በአርአያውና በአምሳሉ ፈጥሮ ከእርሱ በታች በሰጠው የገዥነት ሥልጣን ይታወቃል:: ይህን ልጅነቱን ከውድቀት በኋላ አጥቷል::

አዳም ከውድቀቱ በኋላ ከእግዚአብሔር አምላኩ ፊት ሸሽቷል:: አንድ ልጅ አባቱን ከሰረቀ የሰውነቱ ጠባይ ተለውጦ ሌላ ዓመል ያወጣል:: አባታችን አዳምም ሲወድቅ እግዚአብሔርን ፈርቶ በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት አፍሯል:: «በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ ዕራቁቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ፤ ተሸሸግሁም» /ዘፍ. 3÷10/ በማለት ከጸጋ እግዚአብሔር በታች መሆኑን በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ለመረዳት ይቻላል:: አዳም ገነትን ሲለቅ በገነት የነበረውንም ክብር አጥቷል:: በገነት የነበረው ክብር የእግዚአብሔር ልጅነት ነው::

### ከገነት ስለ ተባረረ

አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ ከተፈጠሩበት ዕለት አንሥቶ ለሰባት ድፍን ዓመታት ኑረዋል:: በቆይታቸው ወቅት በዚህ ዓለም ሰውን ከሰውነት ተራ አውጥቶ የሚያጐሳቁለው ረሃብና ጥም አያውቃቸውም:: በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2÷8–17 እንደ ተመለከተው እግዚአብሔር በምሥራቅ አቅጣጫ በምትገኘው የዔደን ገነት ዕፅዋትን ተክሎ የፈጠረውን ሰው እዚያ እንዲኖር እንዳስገባው ተገልጾአል:: ይህንንም ካደረገ በኋላ ለአዳምና ሔዋን መመሪያ ሲሰጣቸው ደጉንና ክፉውን ለይታ ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ በስተቀር በኤደን ገነት የሚገኙትን የዛፍ ፍሬዎች ሁሉ እንዲበሉ ፈቅዶላቸዋል:: «ደጉንና ክፉውን ለይታ ከምታስታውቀው የዛፍ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ ሞትን ትሞታላችሁ» ብሎ አስጠነቀቃቸው:: አዳምና ሔዋን ግን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጣስ የሰይጣንን ምክር ሰምተው የተከለከለውን ፍሬ በበሉ ጊዜ ጸጋቸው ተገፎ ከገነት እንዲወጡ ተደርገዋል:: ዘፍ.3÷23::

ከገነት ሲባረሩ በወዛቸው ጥረው ግረው እንዲኖሩ በፍትሐ እግዚአብሔር ተበይኖባቸዋል:: «ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ::» ዘፍ.3÷19::

ይህንን የአዳምን ፍጹመ ኀዘን የተመለከተው አምላክም ሰው ሆኖ ሊያድነው መፍቀዱን «ፈቀደ እግዚእ ያግእዞ ለአዳም» በማለት ይኸው የቅዱስ ኤፍሬም ድርሰት ከጅምሩ ይገልጻል:: ለመሆኑ ወልደ እጓለ እመሕያው ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን አዳምን ሊያድነው ወደደ?

### ሰው ወዳጅ በመሆኑ

እግዚአብሔር ያዘነ የተከዘ ሰውን ለማዳን የወደደው የሰው ልጅ ለድኅነት የሚያበቃ ሥራ ሠርቶ አይደለም:: እግዚአብሔር ፍቅር በመሆኑ ነው፤ «እግዚአብሔር አንድያ ልጅን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና» ዮሐ.3÷16:: «እንዲሁ ወዷልና» የሚለው ቃል እግዚአብሔር ፍቅሩ ከፍቅር በላይ እንደሆነ ያጠይቃል:: ከማንኛውም ነገር የጸዳ ንጹሕ ፍቅር የእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስም የተለየ ፍቅሩን ሲገልጽ እንዲህ ይላል:– «ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና፤ ስለ ጻድቅ የሚሞት ከጭንቅ ይገኛል:: ስለ ቸር ሰው ግን ሊሞት እንኳን የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል:: ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያስረዳል::» ሮሜ. 5÷6–9:: ይኸውም እግዚአብሔር የፍቅር ሁሉ ምንጭ ሲሆን የፍቅሩ ዓይነትም ፍጡር ካለው ፍቅር የተለየ ነው:: የሰዎች ፍቅር ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር ሊወዳደር አይችልም:: ሰው ጠላቱን ይገድ ሳል እንጂ ስለ ጠላቱ አይሞትም፤ «ወሶበ እንዘ ፀሩ ንሕነ ለእግዚአብሔር ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ፤ እግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንኾን በልጁ ሞት ብናምን ይቅር አለን::» ሮሜ.5÷10:: እግዚአብሔር ግን ስለ ጠላቶቹ ሞቷል:: ይህም ሰው ወዳጅነቱ ገደብ የማይጣልበት ፍጹምነት ካለው ከእርሱ ከራሱ የተገኘ ነው:: ከራሱ ዐልፎ ወደ ሰው ህልውና የሚያመራው ፍቅሩ በመስቀል ተገልጿል:: እግዚአብሔር ሰውን በማዳኑ ከሰው የሚያገኘው ጥቅም የለም:: ወደፊትም አይኖርም:: ምክንያቱም የሰው ህልውና በእግዚአብሔር ቸርነትና መግቦት ላይ የተመሠረተ ነው:: እግዚአብሔር ያለ ሰው መኖር ይችላል:: የሰው ልጅ ግን ያለ እግዚአብሔር መኖር አይችልም::

/ወደ ገጽ ፴፱ ዞሯል/





www.eotcmk.org

# ሰባኪ ሕይወት

/እመቤት ተፈራ/

ሂሜን አለቃዋ በእርሷ ቢሮ በኩል መውጣት መግባቱን ስለተወ ምን አጥፍቼ ይሆን በሚል ግራ ተጋብታለች:: ሁለት ዓመት ስትሠራ አንድ ቀን መጥፎ ፊት አሳይቷት የማያውቀው አለቃዋ ሰሞኑን ለወጥ ብሎ ባታል:: ዛሬ የሚያስደስተውን ነገር ይዛ ልታናግረው መምጣቱን እየተጠባበቀች ነው:: እንደ ሰሞኑ ዛሬም የራሱን በር ከፍቶ ገባ:: ሂሜንም እንዳሰበችው በሚያምር ባዝ ላይ ያደረገችውን ጽጌረዳ አበባ ከጠረጴዛዋ ላይ አንሥታ ከአለቃዋ ቢሮ ጋር የሚገናኘውን በር አንኳኳታ ዘለቀች:: እና «ደኅና አደርክ አቶ አሻግሬ? ዛሬ በጣም የምታምር አበባ አመጣሁልህ» አለችው:: መለስ ብሎ ሳይመለከታት «አመሰግናለሁ» ሲላት «የስብከት ቪዲዮ ካሴትም አምጥቻለሁ፤ በምሳ ሰዓት ከኛ ጋር ታያለህ? ወይስ አሁን ይሻልሃል?» አለችው በመለማመጥ፤ አቶ አሻግሬ ግን በፍጹም አልተበገረም:: ፊቱን እንዳዞረ «ጊዜ የለኝም» አለ:: ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ ትችላለች? ኩምሽሽ ብላ ወደ ቢሮዋ ተመለሰች::

ሂሜን ኮምፒውተሩን ከፋፍታ ለመሥራት ብትታገልም አልተሣካላትም:: የአለቃዋ ሁኔታ ስላሳሰባት «ለዚህ ይሆን ለካ» እያለች ዐሥሩን ነገር ታወጣና ታወርድ ጀመር:: «ምን አጋጥሞት ይሆን? እኔ የማላውቀው የሥራ ጉዳይ ይኖርበት ይሆን?» እያለች ስትብሰለሰል ብትቆይም ምንም ፈለግ ለማግኘት ባለመቻሏ «አጅሬ ሰላሜን ሊያደፈርስብኝ ይሆን?» አለች በአሳቧ:: እስከ ዛሬ የምትሠራበት ቦታ ለክርስትና ሕይወቷ ስለ ተመቻት እግዚአብሔርን ሳታመሰግን ውላ አድራ አታውቅም:: አልፋ ተርፋ በየጉባኤው የምትሰማውን ቃለ እግዚአብሔር ምክርና ተግሣጽ ለባልደረቦቿም በማስማት ብዙ የራቁ ክርስቲያኖችን እያቀረበች ስለሆነ በሥራ ቦታዋ ከማንም በላይ ደስተኛ ነች::

በተፈጥሮዋ አዛኝና ሰው ወዳድ የሆነችው ሂሜን እንኳን ለእርሷም ለሌላውም ጥሩ የሆነው አለቃዋ ቀርቶ ማንም ሰው ቢሆን ከፍቶት ካየች ይከፋታል:: ካዘነው ጋር ከተቸገረው ጋር ተቸግራ÷ ያላትን አካፍላ ቢሆንላት ችግሩን አቅልላ ባይሆንላት የእግዚአብሔርን ቃል እየጠቃቀሰች ለማረጋጋት ሳትሞክር አታልፍም:: ስለዚህ በደመ ነፍስ የምታከናውነውን ጅምር ሥራ በቶሎ ጨራርሳ እንደምንም አግባብታ ልታነጋግረው ወሰነች::

አቶ አሻግሬ ግን ባታናግረው እንደውም ወደ ቢሮው ዝር ባትል ፈቃዱ ነው:: ላለማየት የሚሸሻት አስቀይማው ወይም መጥፎ አመሏ አስጠልቶት አይደለም:: እንደውም ያስጨነቀው በሁሉ ነገር ጥሩ መሆንዋ ነው:: ሥራ ላይ ጎበዝና ታማኝ ጠባይዋም እጅግ መልካም ነው:: እንዲያው ቀልቤ ጠልፏታል እንዳይል ቀልቡ ወዷታል ልክ እሱ ጠባይዋ እንደ ወደዳት «የኮተቤ አምላኩም» ወዷታል:: የኮተቤው ዐዋቂ ሂሜንን አምጣልኝ ካሉ ሰንብተዋል:: በመለማመን አሳባቸውን ለማስቀየር ቢሞክርም አልሆነለትም:: ሂሜን «ዐዋቂ» ቤት የሚባል ነገር እንደማትወድ ያውቃል:: እንኳን እርሷ ልትሄድለት የእሱን መሔድ ብታውቅ እንደ ምታዝንበት ምናልባትም ሥራውን ለቅቃ ልትሔድ እንደምትችል ስለ ሚያውቅ ምንም እንዳታውቅ አድርጎ ነበር የቆየው:: ከእርሳቸው ግን እሷን መደበቅ አልቻለም፤ ዐወቋት:: ዐውቀው አልተውአትም፤ ትምጣ አሉ:: የሰሞኑ ጭንቀቱ የሂሜንን ዓይን የሚያሸሸው ይኼ ነው:: ዛሬ በተለይ ባለቤቱ «የእርሳቸው ቀጠሮ ለነገ ስለሆነ በዘዴ ይዘናት እንሔዳለን፤ እንድትነግራት» ብላ ስላስጠነቀቀችው ቁርጡን ቀን ማለፍ ባለመቻሉ ከራሱ ጋር ሙግት ይዟል:: እንደትላንት እንደ ቀድሞው ሕይወቱ ቢሆን እንዲህ ያለው ትእዛዟ ብዙም አያስጨንቀውም ነበር:: ዛሬ በሂሜን ሕይወት ተሰብኳል:: በሂሜን የክርስትና ሕይወት ራሱን ለመለወጥ ሲሞክር መጀመሪያ የተወው ዘመናዊነትን ነበር:: ሂሜንን ያመጣለት ጓደኛው ነው:: ጎበዝና ታማኝ ልጅ አለች ብሎ ትሠራበት ከነበረችበት ቦታ አፈናቅሎ ሲያመጣት መጀመሪያ የተመኛት ዘማዊ ልቡ ነበር:: ግን አልሆነለትም:: የሂሜን የተገራ አንደበት፣ ርጋታና አጠቃላይ ሁኔታዋ ድፍረት ስላሳጣው ቆይ ትንሽ ትሰነባብት እያለ ስሜቱን ደብቆ ነበር የተጣጋት:: መሰንበቻው ደግሞ ማንነቷን እንዳያውቅ ሲያደርገው ሐሳቡን ቀይሮ ሥራዋን ብቻ ይከታተል ጀመር:: ቀስ በቀስ ሕይወቷ ቀና ምግባሯ እየሰበከው ሲመጣ ቅርበታቸው ከአለቃና ምንዝርነት አልፎ ወደ ጓደኝነት ተለወጠ:: አሁን አሁንማ ደቀ መዝሙሯ ልታደርገው ምንም አልቀራት:: ከምታስደምጠው የስብከት ካሴቶችና መዝሙሮች አልፎ «አቤት በዚህ ቀን እዚህ ቤተ ክርስቲያን እንዴት ያለ ጉባኤ አለ መሰለህ፤ የመናፍቃን ምላሽ ስለሆነ አያምልጥህ» እያለች በየጉባኤው ስትወስደው ለመናፍቃን ብቻ ሳይሆን ለራሱ ውስጣዊ ጥያቄ መልስ እያገኘ እንዲመጣ አድርጋዋለች:: በተለይም እሷና እዚያው ድርጅት ውስጥ ያሉ መሰሎቿ ባቋቋሙት ጽዋ ማኅበር ላይ እንዲገኝ እየጋበዙ እንደ ለመደው ጠበል ጸዲቅ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል እየመገቡ ሲመልሱት ስለ ሃይማኖቱ ብዙ ዐውቋል::

እንደውም የእርሱ ክርስቲያንነት ምን ድረስ እንደሆነ ያወቀው ከእዚያ ወዲህ ነው እንጂ ቀደም ሲልማ ከእርሱ በላይ ክርስቲያን ያለ አይመስለውም ነበር:: ምክንያቱም የታወቁትን አጽዋማት ይጾማል:: በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ የልማት ሥራ አንደኛ ተሳታፊ ነው፤ በገዳማቱና በየንግሡ አይቀርም:: መሔድ ብቻ ሳይሆን በእጁታ ስሙ ሳይጠራ አይመለስም:: ለነዳያንም ይመጸውታል:: ታዲያ ከአንድ ጥሩ ክርስቲያን ሌላ ምን ይጠበቃል:: ይኸው ብቻ ይመስለው ነበር:: የኮተቤውን ጉዳይ ሲያስብም በባዕድ አምልኮነቱ ከመቀበል ይልቅ «እግዚአብሔር በሰጣቸው ዕውቀት የሰጠኝን ሀብት ለእግዚአብሔር ቤት እያዋልኩት ነው» እያለ ራሱን የሚደልል ነበር:: አሁን ግን ዐዋቂ ለሚላቸው ሰው መስገድ ቀርቶ በሀብት፣ በወገን፣ በዕውቀት፣ መመካት እንኳ ሳይቀር እንደ ባዕድ አምልኮ መቆጠሩን እየተማረ ዐውቋል:: የከበደው መተግበሩ ነው:: በተለይ ከኮተቤው መላቀቅ ይፈራል:: በዚያ ላይ እስከ ዛሬ የከፋ ነገር አዝዘውት አያውቁም:: ዝም ብሎ ክርስቲያናዊነቱንም ያኛውንም ይዞ አለሳልሶ እንዳያልፍ ዛሬ ከበድ ያለ ነገር ገጠመው:: ሂሜንን አምጧት ባይሉ ምን ነበር? እንዳሉት «የድርጅቱ ግንባር ስለሆነች ቱፍታ ተቀብላና ተባርካ ድርጅቱን ብር በብር እንድታደርገው» ይሆን? አሻሚ ምርጫ ያለው ፈተና እንደቀረበለት ነው የቆጠረው:: በቤቱም በቢሮውም በሐሳብ መናወዝ ሆኗል ሥራው:: ዛሬም ጠረጴዛው ላይ ተኝቶ ይሄንኑ ሲያወጣና ሲያወርድ ያለበትን ቦታ ያወቀው የቀጥታ መስመር ስልኩ ሲያንባርቅበት ነው:: በድንጋጤ የመነጋገሪያውን እጀታ አንሥቶ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ አደረገው:: ማንንም ማናገር አልፈለገም:: ወዲያው ሞባይሉ ጮኸ:: ፈላጊውን ቁጥር ሲመለከት የባለቤቱ ነው:: መልስ መስጫውን ተጭኖ ሃሎ! ሲል «ለምን አንሥተህ ዘጋህብኝ» ብላ ተቆጣችው:: «አንቺ መሆንሽን አላወቅሁም:: ሥራ..... በዝቶብኝ..... ከማለቱ አቋርጣው «ነገርካት?» አለችው «አልነገርኳትም እምነቷ እንደማይፈቅድና እሺ እንደማትል እያወኩ......» ሲላት «እዚያ ነው በላት ማን አለህ? እንዴት እንደ ምትነግራት ተነጋግረን አልነበረም» አለችው የወጠኑት የማታለያ ዘዴ ሂሜንን እንደሚያሸንፍ ስለ ዐወቀ:: «ግን እስቲ ይህቺ ልጅ አንድ ነገር ብትሆን ብዬ ፈራሁ:: እንዴት ያለች የእግዚአብሔር ሰው መሰለችሽ?» ከማለቱ ከአፉ ነጥቃ «እሳቸውስ የእግዚአብሔር አይደሉም? ያሠሩትን ቤተ ክርስቲያን አይተህ የለም? ደግሞስ በየወሩ ለሚካኤልና ለገብርኤል የሚዘክሩትስ? ዛሬ አዲስ የምትሆነው ምን ለማለት ፈልገህ ነው? እንደውም ተወው በቃ እኔ እነግራታለሁ» አለችና ስልኩን ጆሮው ላይ ጠረቀመችበት::

አሻግሬ ባለቤቱን ስለሚወዳትና ስለሚፈራት የምትለውን ሁሉ ይሰማል:: ልቡ ባይደርስም ይቀበላታል:: ድሮም ቢሆን የኮተቤውን «ዐዋቂ» የጎበኘው በሷው ግፊት ነው:: የድርጅቱ ወረት እያቆለቆለ ሔዶ ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቆ የባንክና የየሰው ብድር ራሱን ባዞረው ወቅት አይዞህ ያለችውና ይህንን መላ አምጥታ ከውድቀት ያዳነችው እርሷ ነች:: «መለኛ ነች» ይላታል፤ አልገባ ያላት የክርስትና ጉዳይ ብቻ ነው:: የእሱን ልብ የሸረሸረው የሂሜን ሕይወት የእርሷንም እንዲያንኳኳ ከሂሜን ጋር ቢያቀራርባትም አልተበገረችላትም:: ጭራሽ የእሱንና የሂሜንን ግንኙነት በጥርጣሬ መመልከት ከጀመረች ቆይታለች::



www.eotcmk.org

«ጤና ይስጥልኝ÷ አሹ ካምፓኒ» አለች ገና ከማስቀመጧ ያቃጨለውን ስልክ አንሥታ:: ነገር ግን እንደ ገመተችው የሥራ ጉዳይ ሳይሆን «ሃይ ሄሚቲ!» የሚል ቤተሰባዊ ሰላምታ ተከተለ:: የአሻግሬ ባለቤት ነች:: «ውይ አቲላ እንዴት ነሽ» አለች ሄሜንም ልክ እንደ ልጆቿ አጠራር:: አስቴር ሰላምታውን ብዙም ሳትገፋ «ባክሽ ችግር ላይ ነኝ፤ የአሹ አባት በጣም ታመዋል ተብሎ ተላከብን» አለቻት «ውይ በስመ አብ.... ምን አገኛቸው?»

«አላወኩም:: መልእክተኛውን አላገኘሁትም:: አባትየው ያለበት አገር ደግሞ የቅርብ ሩቅ ነው:: ስልክ የለውም፤ የግድ መሔድ አለብኝ»::

«ከማን ጋር ልትሔጂ?»

«ብቻዬን ነዋ! ከቻልሽ ብታካሒጂኝ ጥሩ ነው:: ለገዳዲ ሊደርስ ወደ ግራ ታጥፎ ወደ ውስጥ ይገባል እንጂ ቅርብ ነው:: እባክሽ ሄሚቲ አካሒጅኝ!»

«ብቻሽን ከምትሔጂ እኔም ብሔድ ደስ ይለኛል፤ ግን ሥራውስ?»

«እርሱማ አያሳስብም:: ምክንያት ፈልጌ እነግርልሻለሁ:: ደግሞ ከኔ ጋር መሆንሽን ስለሚፈልግ ምንም አይልም::»

ሄሜን ተቸገርኩ ላላት ሁሉ መድረስ ደስታዋ ስለሆነ ፈቃደኝነቷን ገልጻላት በማግሥቱ ሊጓዙ ተቀጣጥረው ስልኩ ተዘጋ::

አቶ አሻግሬ የሄሜንን ዓይን ሲሸሽ ጭራሽ ያጋጠመህን ንገረኝ ብላ በጥያቄ ስለ ወጠረችው ቢሮውን ጥሎ ከወጣ ቆይቷል:: ቤተ ክርስቲያን ሔዶ ሲጸልይ ሲያለቅስ ነው የዋለው:: የአስቴር ዕቅድ እንዲከሽፍ ተስሎ የእርሱም ልብ ድፍረት እንዲያገኝ ተማፅኖ ወደ ቤት ሲገባ ግን ባለቤቱ ሄሜንን እንዳሳመነቻትና ለመሔድ ተስማምታ ለጉዞ መቀጣጠራቸውን በመስማቱ ተስፋ ቆረጠ::

«ያቺን የመሰለች ልጅ ተበላሽታ ስትቀር አታሳዝንሽም?» አላት በቁጣ፤

«ለምን ታሳዝነኛለች? ለመመረቅ በመመረጧ እንደውም ዕድለኛ ነች»

«እንደቀዘባሽ እዛው በያስቀሯትስ? የትትደርሳለች የተባለች ልጅ ቡና ካዳሚ ሆና ሆነ ነው የቀረችው»

«ምነው ያኔ አልተከራከርካት? ቀዘባህ የኔ እኅት ስለሆነች ዝም ብለህ ሰደድካት:: ለዚህች ትሚገትላታህ፤ የአንተ.... እንትን......ስለሆነች ነው?»

«የኔ ምን አስቱ? ኧረ ተይ እመኝኝ፤ ተይ .... ሌላው ቢቀር ሄሜንን በማጣቱ ሥራችን እንደ ሚጎዳ አይታወቅሽም?»

« ለድርጅቱ መርቄ ቀባብቼ እልካታለሁ ነው ያሉት፤ ለምን ያጣታል?»

«እኔ አልመሰለኝም አስቱ÷ በፈጠረሽ ተለመኝኝ»

«ኧ...አልመሰለኝም፤ ከመቼ ወዲህ ነው ላሳቸውን መጠራጠር የጀመርከው?»

«ቀዘባሽንስ የወሰድሻት ዓይነ ጥላዋን ለማስወገድ አልነበረም»

«ነበር ግን አውሊያው ወደዳታ፣ ሰውዬ ጤነኛ አይደለህም»

«እኔ የፈለግሽውን በይኝ ደውዬ እነግራታለሁ»

«እናያለ....ኧ...እንዲች ብለህ አንድ ነገር ተንፍስና ይለይልናል»

ስትል ስሜቷ በል ብሎ በመንደዱ ከጣራ በላይ እየጮኸች «ብች ልህ ብችልህ አልቻል አልከኝ የማላውቅህ መስለህ......ወይ አንደኛህን ጠቅለሃት አትቀመጥም?» አለችና የታመቀ ብሶቷን አፈነዳችው:: ለማስተባበል የሚያወጣቸውን ቃላትም በቅጡ ስለማትሰማቸው የበ ለጠ እያጋጋሉአት ጩኸቱና ስድቡ አልበቃ ስለ አላት ጎሮሮውን ልታንቅ ሞከረች:: ይቅርታ ጠይቆ «እንደ ፈለግሽ አድርጊ» ቢላትም እንኳ ልትበርድ አልቻለችም:: «አንተም ሔደህ እውነቱ መውጣት አለበት» በሚል ሌላ ጭቅጭቅና አምባጓሮ ፈጥራ በአሳቧ መስማማቱን በመሐላ ካጸናላት በኋላ ነው በረድ ያለችው:: በማግሥቱ ሄሜን ከእንቅልፏ ሳትነቃ ነው የአስቴር መኪና ቤቷ በር ላይ ቆሞ ጡርንባውን ያንደቀደቀው:: ድንገት አሳቡን ቀይሮ እንዳይነግራት ስለ ፈራች ነው በማለዳ የሔደችው:: የዋኋ ሄሜን ግን እውነት ችግር ላይ ያለች ስለ መሰላት ያለ ጥርጣሬ ወጥመዱዋ ውስጥ ገባችላት:: ቀድማ ባለመነሣቷ ይቅርታ ጠይቃ መኪናው ላይ የወጣ ችው ጡሩንባውን በሰማች በአምስት ደቂቃ ውስጥ ነበር:: እንዳሰበችው ግን ጉዞው ወዲያው አልተጀመረም:: ለዘመዶቹ ይገፔ የምሔደውን ታጋኘኛለሽ በሚል ሰበብ ወዲያ ወዲህ ሲሉ ከከተማው ሳይወጡ ዋሉ:: አስቴር ለገዳዲ ድረስ ለመሔድ ያሰበችው ኮተቤ ከሆነ ትጠረጥረኛለች ብላ ነው:: እንዳሰበ ችውም አመሻሹ ላይ ተነሥተው እያዘ ገሙና በሰበብ አስባቡ እየቆሙ ለገዳዲ የደረሱት ከጨለመ በኋላ ነበር:: በአንድ የኮረኮንች መንገድ ትንሽ ከሄዱ በኋላ መኪናውን አዙራ ወደ አስፋልቱ ስትገባና ወደ አዲስ አበባ አቅጣጫ ስታቀና ሄሜን መመለሳቸው በስሕተት መስሏት ጠይቃ ነበር፤ እንዳልተመለ ሱና ለገዳዲን አለፍ ብሎ የሚገኘውን መታጠፊያ በመፈለግ ላይ እንዳለች ስትነግራት እንኳን በጭለማ በቀንም አካባቢውን በደንብ ስለማታውቀው እሺ ብላት ወደ ሚታረድበት ቄራ እንደ ሚነዳ በሬ በጸጥታ ወደ ኮተቤ ተጓዙ:: ወደ ከተማው ብትገባ በደንብ ትለየው ነበር:: ግን ገና ኬላ ሳይደርሱ ባለው የኮረኮንች መንገድ ስለታጠፉ ቅንጣት ያህል ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸውን አልጠረጠረችም:: አስቴር ግን አካባቢውን በጣም ስለ ለመደችው ውስጥ ለውስጥ እያቆራረጠች የምትፈልገው ቦታ አደረሰቻት::

ሌሊቱን በጭንቀት እንቅልፍ ያጣውና ሽለብ ሲያደርገው በአስፈሪ ቅዠት ሲባንን ያደረው አሻግሬ ንጋት ላይ ስለ ተጫጫነው አልጋውን የለቀቀው አረፋፍዶ ነው:: እንደ ተነሣ ወደ ቢሮው ስልክ ደውሎ ሄሜን አለ መግባቷን ካረጋገጠ በኋላ መቼም ጉዞው ከሰዓት ነው ብሎ መኖሪያ ቤቷ ሞከረ:: በማለዳ ከአስቴር ጋር መሔዳቸው ሲነገረው ሳይቀድማት መቅደሟ እንደሆነ በማመን ዳተኝነቱን ከረገመ በኋላ «ያቺን የዋህ ልጅ ለሰይጣን ራት አደረግኋት፤ ገበርኳት፤ አምላኬ ሆይ÷ አድንልኝ፤ ከዘላለም ጸጸት አውጣኝ» እያለ ያነባጀመር:: ከዚህ ውጭ በሱ በኩል ምንም ማድረግ አይችልምና እግዚአብሔር ተአምሩን እንዲያሳየው ተማፅኖ ወደ ቢሮው ሊያዘግም ሲዘገጃጅ ቅርብ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረት ላይ ሲነገር የሰማው ተአምር ትዝ አለው:: መስ ካሪው ባለጋራኘ ነበሩ:: ሥራቸው እየቀዘቀዘ ሲመጣና ሲከስሩ ሳዎች ዐዋቂ ቤት እንዲሔዱ ይመክሯቸውና በሰው ግፊት ይሔዳሉ:: መስካሪው እንደ ሚሉት ገና የተባለው ቦታ እንደ ደረሱ መንፈሱ «ተቃጠልኩኝ:: ኪስህ ውስጥ የያዝከው ነገር አቃጠለኝ:: ወይ ሒድልኝ ወይ አውጣና ጣልልኝ» ይላቸዋል:: ይሄኔ በሸሚዝ ኪሳቸው የያዙት ምንጊዜም የማይለያቸውን ሰኔ ጎልጎታ መጽሐፍ መሆኑን ሲረዱ «አውጥቼማ አልጥልም» ብለው እንደ መጡ ይቀሩና በዚሁ የመንፈሱን ርኩስነት በማረጋገጣቸው ሒድ ሒድ ይሏ ቸው የነበሩትን ወዳጆቻቸውን አሳፍረው ችግራቸው ሁሉ በጠበል እንደተፈታ ወረታ ቸውም እንደ ተመለሰ የመሰከሩት ቁልጭ ብሎ ሲታየው ልቡ ተረጋጋ:: ሄሜንም መጽሐፍ እንደ ማይለያት ያውቃላ!! «ተመስገን ለሰበብ ካዘዛት በዚሁ ትድናለች» ብሎ ራሱን ዘና አደረገ::


የኮተቤው «ዐዋቂ» ቤት ግቢው ሰፊ ቢሆንም መኪና ማስገባት ክልክል ነው:: ስለዚህ አስቴር ወደ አጥሩ ጥግ መኪናዋን አዙራ ከአቆመች በኋላ ለመውረድ እየተዘገጃጀች በሰላም በመግባቷ «ተመስገን በአንተው መጀን» ስትል ሄሜን ደግሞ «እግዚአብሔር ይመስገን፤ ጨለማው አስፈርቶኝ ነበር::» እያለች ዳዊቷንና ሌሎች የጸሎት መጻሕፍቷን የያዘ ቦርሳዋን ብድግ ስታደርግ አስቴር «ለቅሶ ቤት ቦርሳ ይዘሽ ልትገቢ ነው?» ብላ ከእጇ መንጭቃ ወደ መኪናው ኋላ ወረወረችው:: ሄሜን ክፋቱ ባይታያትም የአስቴር ፊት መለዋወጥና ቁጣ ስላስደነገጣት በታዘዘችው መሠረት የለበሰችውን ጠቆር ዠጕርጕር ያለ ሻርፕ ተከናንባ ወረደች:: የግቢውን በር ከረገጠች በኋላ ፀጥታው ከበዳት፤ የአተስተናባሪዎቹ ብዛትና ወደ አስቴር እየተጠጉ የሚንሾካሾኩት ነገር ግራ አጋባት:: ለማንኛውም የአስቴርን ዕቃ ተቀብሎ የሚመራቸውን ሰው የምትከተለውን አስቴርን ለጥቃ እየተራመደች መሔድ ብቻ ነበር ምርጫዋ:: የቤቱ በር ላይ ሲደርሱ መሪያቸው እንዲገቡ ጋብዟቸው ወደ ኋላ ቀረ:: ክፍሉ ሰፋ ያለ ሆኖ ከደጁ ጨለማ ብዙም በማይለይ የደበዘዘ ብርሃን የተዋጠ በመሆኑ የምትቀመጥበት ቦታ ላይ ጎት ተው ያሳረፉአት ከብዙ መደነባበር በኋላ ነው:: ቦታቸውን እንደ ያዙ ሄሜን «አቲላ ምንድነው ነገሩ?» አለች የለቅሶ ቤቱ ነገር ተዘበራርቆባት:: «ሰውየው አልሞቱም፤ ግን ውቃቢአቸው ተነሥቶባቸው እየተለማመኑላቸው ነው:: ከአሁኑ በኋላ ዝም ብለሽ የሚደረገውን ማየትና ማዳመጥ ነው ያለብሽ፤ አለበለዚያ ትቀሰፊያለሽ» አለቻት በጣም ዝቅ ባለ የለሆሳስ ድምፅ:: ሄሜን መቅሰፍቱን እንኳ አልፈራችም:: ግን ላለመረበሽ ትንሽ ልታገሥ ብላ ዝም እንዳለች የአስቴር ሞባይል በመጮኹ መጣሁ ብላት ወጣች::

ይቆየን፤



www.eotcmk.org

# የአባ ሀደራ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት የወንዶች ገዳም



የመቐለ ከተማ ከአዲስ አበባ 783 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን ከመቐለ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ የሃላ መንደር ድረስ 40 ኪ.ሜ ያህል በመኪና ተጉዘው አባ ሀደራ ገዳም ለመድረስ የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ይጓዛሉ፣ ወይም 50 ኪ.ሜ ከመቐለ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ወደ ሀገረ ሰላም ከተማ ተጉዘው አባ ሀደራ ገዳም ለመድረስ የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ይጓዛሉ። በሁለቱም አቅጣጫ ከፊት ለፊት ሰንሰለታማ የሆነውን የሰገነት ተራራን እየተመለከቱ ቁልቁለታማ የሆነውን መንገድ አንዳንድ ጊዜ በእጅ መሬቱን እየተደገፉ አንዳንድ ጊዜ እየተንፏቀቁ መጓዝ የግድ ነው። ነገር ግን ከገዳሙ ሲመለሱ ቀጥ ያለውን ድንጋያማ ተራራ ከ4:00 – 4:30 ባለው ጊዜ ውስጥ ጨርሰው ሀገረ ሰላም ይደርሳሉ።

በገዳሙ 25 ወንድ መነኮሳት እና ወደ 25 የሚጠጉ የአብነት /የፈለገ ሕይወት /ትምህርት የሚማሩና በዕድሜ የገፉትን መነኮሳት የሚያግዙ /አርድእት/ ይገኛሉ። የፈለገ ሕይወት ትምህርቱ የሚሰጠው በአንድ የመዝገብና የጾመ ድጓ መምህር ብቻ ነው። አሁን በገዳሙ የሚገኙትና በዕድሜ የገፉት መነኮሳት አእዋፈ ሰማይን የሚመግብ ጌታ ይመግበናል በሚል ፍጹም ክርስቲያናዊ ተስፋ ያለባቸውን የምግብና የዘወትር ልብስ ችግር በመቋቋም በእነ ዐፄ ዮሐንስ፣ በእንልዕልተ ዐጸደ አስፋው፣ በእነ ራስ ሥዩም መንገሻ፣ በእነ ራስ ጉግሳ አርአያ፣ በእነ ደጅ አዝማች ግርማይ መንገሻ ወዘተ የተበረከቱ ታሪካዊና ጥንታውያት ቅርሶችን በትጋት በመጠበቅና በመንፈሳዊ ትጋት በበኣታቸው ጸንተው ይገኛሉ ።

ገዳሙ በመቐለ ከተማ ከሚያከራያቸው አምስት ክፍል ቤቶችና ወደ ጠበሉ ከሚመጡት ሰዎች ከሚሰጠው ብስጭት ውጭ ሌላ መተዳደሪያ የሌለው በመሆኑ ገዳማውያኑ መቸገራቸውንና በገዳሙ የሚመነኩሱ፣ የሚማሩም ሆነ የሚያስተምሩ መምህራን የሉም ለማለት በሚቻልበት ደረጃ የደረሰ ይመስላል። ይህም የተተኪ አባቶችን ቁጥርና በገዳሙ ያሉትን ቅርሶች ሕልውና ጥያቄ ላይ የሚከት ይሆናል።

አሁን የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ያለበት ቦታ መሥዋዕተ ኦሪት ይሠዋበት እንደ ነበረና በኋላም በዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ [1674–1698 ዓ.ም] ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ የቅዱስ ሚካኤል ታቦት ገብቶበት አገልግሎት መስጠት እንደ ጀመረ ይነገራል። ምንም እንኳን መጀመሪያ በዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ቢመሠረትም 12 ርስት ጉልት በመስጠት አንድ ታላቅ ደጀ ሰላም በማሠራት ለመምህራን ደሞዝና የዘወትር ልብስ በመስጠት ያደራጁት ዐፄ ዮሐንስ አራተኛ ናቸው። በወቅቱ ቁጥራቸው ይህን ያህል ማለት ባይቻልም እጅግ ብዙ መነኮሳት የንባብ፣ የቅኔ፣ የድጓ ፣የጾመ ድጓ፣ የዜማ፣ የምዕራፍ፣ የመዝገብ፣ የደብረ ዓባይና የሰደድ ኩላ ቅዳሴ ወዘተ የሚያስተምሩና የሚማሩ የነበሩ ሲሆን በአንድ የትምህርት ዓይነትም እስከ 150 የሚደርሱ ተማሪዎች ይማሩ ነበር።

የቅዱስ ሚካኤል ታቦት በአንድ ወቅት ገዳሙ ውስጥ ሾልከው በገቡ የቅብዐት መነኮሳት ተሰርቆ ወደ ጎንደር የተወሰደ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኑ ያገለግሉ የነበሩት ቄስ ወልደ ክርስቶስ ታቦቱ ወደ ጎንደር መሔዱን ሰምተው ለጎንደር ንጉሥ አቤት ለማለት ወደ ጎንደር ተጉዘዋል። ነገር ግን ወደ ንጉሡ የሚያደርሳቸው በማጣት ሦስት ዓመት ደጅ እየጠኑ ቆይተዋል። ባለቤታቸውም ዓመተ ኢየሱስ የባለቤታቸውን ወደ ቤት አለመመለስ ለምን እንደ ሆነ እግዚአብሔር ይገልጥላቸው ዘንድ ወደ ዔካ በመግባት ሱባኤ ይዘዋል።

ከሦስት ዓመታት በኋላ የቄሱን ደጅ ጥናት የተመለከቱ አንድ ባሕታዊ ወደ ቄሱ ዘንድ መጥተው ለምን እንደ መጡ ምን እንደሚፈልጉ ጠየቋቸው። እሳቸውም ሁሉንም በዝርዝር ካስረዱአቸው በኋላ ባሕታዊው «በዚህ ሁኔታማ ማንም ወደ ጃንሆይ ሊያቀርቦት አይችልም፤ ነገር ግን ወይባ ቆሮንጮ ለብሰው ጃንሆይ ሲወጡ ወይም ሲገቡ ይጠብቋቸው» ብለው ስለ መከሯቸው በዚህ ሁኔታ ወደ ንጉሡ ቀርበው የመጡበትን አስረዱ። ጥያቄአቸውም ተቀባይነትን አግኝቶ ታቦቱ ተፈልጎ በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ከሦስት ዓመታት በኋላ ወደ ቀድሞ መንበሩ ተመልሶአል ።

የቄሱ ባለቤትም የባለቤታቸውና የታቦተ ሚካኤልን በሰላም መመለስ ሰምተው ሱባኤያቸውን ጨርሰው ወጥተዋል።

ከዚህ በኋላ ከእነዚህ ደጋግ ክርስቲያኖች አባ ሀደራ ተወልደዋል። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወላጆቻቸው በገዳሙ ካሉት የድጓ መምህር ይማሩ ዘንድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደዋቸዋል። አባ ሀደራም ከትምህርታቸው በተጨማሪ በጾምና በጸሎት እየተጉ የተለያዩ መንፈሳዊ ሥራዎችን ይሠሩ ነበር። ሌሊት ሌሊት ተምረው ሲጨርሱ ሌሎች ተማሪዎች ሲተኙ እርሳቸው ግን በገዳሙ አካባቢ በሚገኘው ወንዝ ውስጥ እየገቡ ይጸልዩ ነበር። ተማሪዎቹም «እርሱ ቤቱ ቅርብ ስለሆነ እየሔደ ያድራል» ብለው ያሙአቸው ነበር። ይህንንም ሔደው ለመምህራቸው ነግረዋቸዋል። መምህሩም ሌላ ጊዜ በተማሪዎቹ ጥቆማ አባ ሀደራ ወደ መጸለያ ስፍራቸው ሲሔዱ የእግራቸውን ዱካ ተከትለው ቢሔዱ አባ ሀደራ እንደ ብርሃን እያበሩ ዙሪያቸው በብርሃን



www.eotcmk.org

ተከቦ ሲጸልዩ ተመልክተዋል:: በጥዋቱ አባ ሀደራ እግር ስር ወድቀው «ይቅር በለኝ ሳላውቅ በድዬሃለሁ» ቢላቸው አባ ሀደራም «መምህሬ ምን በደሉኝና ነው ይቅርታ የሚጠይቁኝ» አሏቸው:: መምህሩም «እኔ ያየሁትን አላየህምና ዝም ብለህ ይቅር በለኝ» ስላሏቸው ይቅር ብለዋቸዋል:: ያ ስፍራ እስከ አሁን «ምጽላየ አባ ሀደራ» ተብሎ ይጠራል:: ከዚያ በኋላ አባ ሀደራ «ለካ ታውቄአለሁ» ሲሉ ቦታውን ትተው ወደ ጎንደር ተጉዘዋል:: እዚያም አባ ቶማስ ከሚባሉ የበቁ መነኩሴ ጋር ተገናኝተዋል:: አባ ቶማስም አባ ሀደራን እንግድነት ከተቀበሉ በኋላ «ሒድ አንተ ቦታህ እዚህ አይደለም፤ የአንተ ቦታ ተንቤን ነው፤ በዚያ ስፍራ ከአንተ የተነሣ ብዙ ሰዎች ይድናሉ፤ እኔም በአረፍሁ ሰዓት በዚያ እንድትቀብረኝ ወደ አንተ እመጣለሁ» ብለው ወደ ቀድሞ በአታቸው አሰናብተዋቸዋል::

አባ ሀደራም ከጎንደር ተመልሰው ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከፍ ብለው በታላላቆቹ የድንጋይ ቋጥኞች ስር ሆነው ሲጸልዩ በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የአካባቢው ምእመናን ወንዶችም ሴቶችም ይገለገሉበት ስለነበር ሌላ የወንዶች ገዳም ለመመሥረት ዘወትር ያስቡ ነበር:: እግዚአብሔርም ይህን አሳባቸውን ዐውቆ ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንና እርሳቸው ከሚጸልዩበት መካከል አንዲት ነጭ ጥጃ ስትዘል አሳይቶአቸዋል:: እርሳቸውም «በአካባቢው ከብት የለ፤ ይህች ጥጃ ከየት መጣች?» ብለው ለማየት ቢወርዱ ጥጃዋ ትሰወርባቸዋለች፤ ይህንን ሦስት ጊዜ ተመልክተዋል:: በኋላ ምናልባት ያሰብኩት ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ እግዚአብሔር የፈቀደው ቦታ ይህ ነው ብለው ቤተሰቦቻቸውንና የአካባቢውን ኅብረተሰብ አስተባብረው ቤተ ክርስቲያን አሠርተው የቅድስት ኪዳነ ምሕረትን ታቦት አስገብተው ቢታል:: ይህ ቤተ ክርስቲያን ከድንጋያማው ተራራ ስር ያለ ሲሆን ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከ10–15 ደቂቃ ያህል ያስኬዳል:: ቤተ ክርስቲያኑም በ1994 ዓ.ም ለአገልግሎት ተለኩሶ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በተረሳ ጧፍ አማካይነት ሙሉ ለሙሉ የተቃጠለ ሲሆን ታቦቱና ከቃጠሎው የተረፉ ንዋየ ቅዱሳት ዐፄ ዮሐንስ ባሠሩት ደጀ ሰላም ውስጥ ገብተው ለጊዜው በዚያ አገልግሎት እየተሰጠባቸው ይገኛሉ::

ቤተ ክርስቲያኑ በተቃጠለበት ቦታ አንድ የጣሊያን ዜግነት ባለውና ከጠበሉ ፈውስ ባገኘ ሰው እና በሌሎች በጎ አድራጊዎች አማካይነት አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን እየተሠራበት ይገኛል:: አባ ሀደራ ጎንደር ያገኙአቸው አባት÷ አባ ቶማስ ባረፉ ጊዜ አባ ቀለሜንጦስ ገብረ ሚካኤል የተባሉ ረድአቸው ዐፅማቸውን በአህያ ጭኖ ወደ አባ ሀደራ ተጉዞአል:: ከረዥም ጉዞ በኋላ ገብረ ሚካኤል አግቤ ቆላ ተንቤን ሲደርስ አህያው ወድቆ አልነሣም ስላለ አባ ቀለሜንጦስ ቦታው እዚህ ይሆናል ብሎ ሊቀብራቸው ሲያስብ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጾ ቦታው እዚህ አይደለምና እንዳትቀብራቸው ስላለው እንደገና ጉዞአቸውን ቀጥለው ወደ ገዳሙ ሔደዋል:: አባ ሀደራም በራእይ የጻድቁ ዐፅም ወደ ገዳሙ መመጣቱ ተገልጦላቸው በተለያየ ቦታ ወደሚኖሩ ታላላቅ ገዳማትና መነኮሳት አንድ ታላቅ እንግዳ እየመጣብኝ ነውና ወጥታችሁ እንድትቀበሉልኝ በማለት መልእክት ይልካሉ:: ከእነዚህም ውስጥ በዘንዶና በአንበሳ ይሔዱ የነበሩት አቡነ ዘሥላሴ፣ ገባ መድኃኔዓለም ገዳም የሚገኙት አቡነ ዝክረ ማርያም፣ ርዋክሳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም የሚገኙት አቡነ ተላዊ ክርስቶስ ዋነኞቹ ናቸው:: መነኮሳቱም የአቡነ ቶማስን ዐጽም ለመቀበል ሲመጡ ብዛታቸው እንደ ጽፈቀተ •ሮማን፣ እንደ ከዋክብተ ሰማይ ነበር::

አባ ቀለሜንጦስ ወደ አባ ሀደራ ገዳም ታኅሣሥ 12 ቀን በደረሱ ጊዜ መነኮሳቱ ተቀብለው ጸሎተ ፍትሐቱን ካደረሱ በኋላ «ከሩቅ አገር የመጡ ጻድቅ አባት ናቸው:: በቤተ መቅደስ ውስጥ ይቀበሩ» ብለው በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀብረዋቸው ተለያይተዋል:: ነገር ግን በማግሥቱ ጥዋት ሰሞነኛው ካህን ለአገልግሎት ሊገባ ሲል አካባቢው በተለይም ቤተ መቅደሱ በውኃ ተጥለቅልቆ አላስገባ ሲላቸው ነገሩን ለአባ ሀደራ ይነግሯቸዋል:: አባ ሀደራም ውኃውን ከተመለከቱ በኋላ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ የነበሩትን መነኮሳት በድጋሚ ጠርተዋል:: እነርሱም በኅብረት ጸሎት በሚያደርጉበት ሰዓት ከቤተ ክርስቲያኑ በስተደቡብ አቅጣጫ በተወሰነ ሜትር/ እስከ 50 ሜትር/ ርቀት ቀስተ ደመና ተተክሎ ተመልክተዋል:: ዕጣን ሲያጤሱ የእጣኑ ጢስ በቀስተ ደመናው መሬት ከነካበት ቦታ ላይ ዐርፏል:: አሁን ያሉትና በዕድሜ የገፉት መነኮሳት እንደሚናገሩት በዚያ ሰዓት በተጨማሪ ቅዱስ ሚካኤል ሁለት የወርቅ ማጥን ይዞ በመምጣት ተገልጾላቸዋል:: ይህንን የተመለከቱት መነኮሳት የጻድቁን ዐፅም አውጥተው ቅዱስ ሚካኤል ከሰጣቸው ሁለት ብርሌ ጋር የዕጣኑ ጢስ ባረፈበት እና ቀስተ ደመናው በታየበት ቦታ ላይ ቀብረዋቸዋል:: በጻድቁ የመቃብር ስፍራም ታላቅ ጠበል ፈልቋል:: ጠበሉ እስከ ዛሬ ድረስ በሽተኞች እየተፈወሱበት ይገኛል::

ገብረ ሚካኤል የተባለውና የአቡነ ቶማስን ዐፅም ይዞ የመጣው አህያ ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት ወደ ድንጋይነት ተለውጧል:: ያ ድንጋይ አሁን ከቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት በዕፅዋት ተከቦ ይገኛል:: አባ ቀለሜንጦስ ግን በገዳሙ ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ እዚያው ዐርፈዋል::

የገዳሙ መተዳደሪያ የነበረው 12 የሚሆኑ ርስትና ጉልት የቀድሞው ሥርዓተ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ የቀረ ቢሆንም ከመቐለ ሰሜን ምሥራቅ በአፋር ክልል ከሚገኘው ከበረሃ ዓለም ከሚገኘው የጨው ቀረጥ 1/3ኛ እየተባለ 1200 ብር ይሰጣቸው ነበር:: አሁን ደግሞ ለገዳሙ ምንም መሬት አያስፈልገውም ተብሎ ገዳሙ ያለምንም መሬት ቀርቷል:: በቀድሞው ሥርዓተ መንግሥት ይደጎም የነበረውም 1200 ብር ተቋርጧል:: ነገር ግን ለመነኮሳቱ ለሁለት መነኮሳት /እንደ ባልና ሚስት እያደረጉ/ በመሬት ክፍፍሉ ወቅት አንድ ጥማድ መሬት ከገዳሙ ፊት ለፊት ተሰጥቷቸዋል::

ከ1971 ዓ.ም ጀምሮ ምንም እንኳን በቅዱስ ዮሐንስ / በርእሰ ዐውደ ዓመት/፣ በልደት፣ በጥምቀት፣ በትንሣኤ፣ በጾመ ሐዋርያት በፍልሰታና በመሳሰሉት ታላላቅ በዓላት ላይ ቤት የሚዘጋጅ የአንድነት ማዕድ ቢኖርም ገዳሙ ሙሉ በሙሉ የአንድነት ገዳም ነው ለማለት አያስደፍርም::

በገዳሙ ዙሪያ የተለያዩ ዕፅዋት ያሉ ሲሆን ዓመቱን ሙሉ የማይቋረጥ ወንዝ ከገዳሙ መሬት ስር ይገኛል:: ይህም ገዳሙ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን እንዲያከናውን ይረዳዋል::

ጻድቁ ኣባ ቶማስ ከተቀበሩበት ስፍራ በፈለቀ ጠበል በመጠመቅና ከጠበሉ ተወስዶ ለአባ ሀደራ በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መሠረት የአባ ሀደራ ገድል እየተነበበ ጸሎተ ዕጣን እየተደረገበት ከሚቀየው ጠበል በመጠጣት ከተለያየ ደዌ የተፈወሱ ሰዎች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው:: በብዙ ሰዎች ተይዘው ለብዙ ሰዎች አስቸግረው ወደ ጠበሉ የሚመጡ አካባቢው ላይ ከደረሱ በኋላ ግን ያለምንም ማንገራገርና ያለማንም ርዳታ ወደ ጠበሉ በመግባት የያዛቸው ርኩስ መንፈስ እስኪወጣ ድረስ ለአንድ ሰዓት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ጠበሉ ውስጥ በተለያየ ቋንቋ እየተናገሩ ይቆያሉ:: በገዳሙ ኅዳር 12 ቀን የሊቀ መልአኩ የቅዱስ ሚካኤል በዓል፣ ታኅሣሥ 12 ቀን የአባ ቶማስ ዐፅም ወደ ገዳሙ የገባበት፣ የካቲት 16 ቀን የቅድስት ኪዳነ ምሕረት፣ ሚያዝያ 21 ቀን የአባ ሀደራ ዕረፍት ይከበራል:: የቅዱሱ የአባ ሀደራ ጸሎትና በረከት ከሁላችን ጋር ይሁን:: አሜን::

# ታላቁ ቅዱስ አርሳንዮስ

/ወልደ አረጋዊ/

በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዓመት የግብፅን በረሃ በንጽሕናና በተጋድሎ ባሸበረቁ መነኰሳትና ባሕታውያን የሞሉት ከግብፅ አካባቢ የተገኙ ብቻ አልነበሩም፤ ከተለያየ የዓለም ክፍል የተገኙም እንጂ:: ከሮም÷ ከቁስጥንጥንያ÷ ከኢትዮጵያ÷ ከኢየሩሳሌም /ከፍልስጥኤም ምድር/ ወዘተ. የመጡ ነበሩ:: ከእነዚህም በሮማውያንና በግሪካውያን ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ከደረሱትና ወደ ግብፅ ሔደው በተባሕትዎ ታላቅ ተጋድሎ ከፈጸሙት አንዱና አንጋፋው ታላቁ ቅዱስ አርሳንዮስ ነው::

ቅዱስ አርሳንዮስ ባዕለ ጸጋና ደጋግ ከነበሩ ወላጆቹ በ350 ዓ.ም በሮም ተወለደ:: ወላጆቹ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲማር አደረጉ:: በተጨማሪም በዘመኑ የነበረውን የግሪካውያንና የሮማውያንን ትምህርት እስከ መጨረሻው ድረስ የተማረና በጣም ዐዋቂ ነበር:: አርሳንዮስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ የሚወድ በመሆኑ በሮም ጳጳስ ዲቁና ተሾመ:: አባትና እናቱ ከሞቱም በኋላ ያወረሱትን ሀብት በሙሉ ለድኾች ሰጥቶ ብቻውን መኖር ጀመረ:: እርሱም ስለ ጽድቅ ሥራውና ስለ ጥበቡ የታወቀ ሆነ::

ታላቁ ንጉሥ ቴዎዶስዮስም ሁለቱን ልጆቹን አርቃዴዎስንና አኖሬዎስን የሚያስተምርለት ሰው በፈለገ ጊዜ የሮም ጳጳስ በመንፈሳዊና በዓለማዊ ዕውቀት የተካነውን አርሳንዮስን ስለ ጠቆመው ወደ ቁስጥንጥንያ ሔዶ እነርሱን ማስተማር ጀመረ:: አንድ ጊዜ ንጉሡ:- ቅዱስ አርሳንዮስ ልጆቹን ሲያስተምር ለማየት ሲመጣ አርሳንዮስ ቆሞ ሲያስተምር ልጆቹ ደግሞ ተቀምጠው ሲማሩ ዐየ:: በዚህን ጊዜ እነርሱ ቁመው እንዲማሩ አርሳንዮስ ግን ተቀምጦ እንዲያስተምራቸው አደረገ:: በዚህ ሁኔታ ወደ ዐሥር ዓመት ገደማ ከቆየ በኋላ ያለበት ቦታ ቤተ መንግሥት በመሆኑ አጠቃላይ ሁኔታው ደስ አላሰኘውም:: ጌታ በወንጌል «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ካጣ ምን ይጠቅመዋል?» ያለውን ነገር እያሰላሰለ ፈጣሪውን «የምድንበትን መንገድ አሳየኝ» ሲል ጸለየ:: በዚህም ጊዜ «አርሳንዮስ ከሰው ተለይተህ ሒድ ትድናለህ» የሚል ቃል መጣለት:: በዚህ ጊዜ ቁስጥንጥንያን ትቶ በእስክንድርያ አድርጎ ወደ አስቄጥስ ገዳም ወደ አባ መቃርዮስ ሔደ:: አባ መቃርዮስም ለዮሐንስ ሐፂር ፈትኖ እንዲቀበለው ሰጠው:: ማታ መነኰሳቱ ሁሉ የዕለት መቁነናቸውን ሲወስዱ ሳለ ዮሐንስ አርሳንዮስን ከመሀል እንደ ቆመ ሳይሰጠው ዝም አለው:: ከዚያም ቅዱስ ዮሐንስ መቁነኑን ከፈለገ እንዲበላ በሚገልጽ ሁኔታ ከአርሳንዮስ ፊት ጣለለት:: አርሳንዮስ ደስ እያለው ተቀምጦ ተመገበ:: ቅዱስ ዮሐንስ ሐፂር በአርሳንዮስ ሁኔታ ተደስቶ ሌላ ፈተና ሳይፈትነው «ይህ ሰው መነኩሴ ይሆናል» ብሎ ተቀበለው:: አርሳንዮስም ተጋድሎውን ጀመረ::

ቅዱስ አርሳንዮስ በሌላው የሚደረገውን የእኔ ነው ብሎ የሚወስድ ነበር:: አንድ ጊዜ የተቀቀለ ጥሬ ገለፈቱን ሲልጥ ዐይተውት ስለሚያከብሩት በቀጥታ አልነገሩትም:: ነገር ግን ሌላ ሰው በአጠገቡ ተቀምጦ ልክ እንደ አርሳንዮስ እንዲያደርግና እርሱን እንዲገሥጹት ተመካክረው መጡ:: ያም ሰው ከአርሳንዮስ አጠገብ ሆኖ እየጠረጠረ ሲመገብ ሌላው መጥቶ በጥፊ መታውና «በገዳም ለምን እንዲህ ታደርጋለህ?» አለው:: አርሳንዮስም ተግሣጹ ለእርሱ መሆኑ ገብቶት «ዝጽፍአት ዘአርሳኒ ውእቱ፤ ይህ ጥፊ የእኔ ነው» ብሎ ያን ልማድ ተወ::

በአስቄጥስ በረሃ ሲኖር ታምሞ ከሰው ምጽዋት ስለ ተቀበለ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ÷ ስለ ስምህ ምጽዋት ከሰው እቀበል ዘንድ አብቅተኸኛልና አመሰግንሃለሁ» አለ:: በሌላም ጊዜ በሲሃት በረሃ እያለ ታሞ ደዌው ስለ ጸናበት ወደ ቤተ ክርስቲያን አምጥተውት በትንሽ ምንጣፍ ላይ ትራስ አድርገው አስተኙት:: ከአረጋውያን አንዱ ሊያየው መጥቶ እንዲያ ባየው ጊዜ እንዲህ የሚጸናው አርሳንዮስ «ይህ በምንጣፍ ላይ ተኝቶ ያለው ነውን?» ብሎ ስለ እርሱ ታላቅነት ተጠራጠረ:: በዚህ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ካህን ይህንን አረጋዊ «በሀገርህ ሳለህ ሥራህና አነዋወርህ እንዴት ነበር?» አለው፤ እርሱም የበግ ጠባቂ ነበርኩ ኑሮዬም በብዙ ድካምና ውጣ ውረድ ነበር አለው::

ከዚያም «በዚህ በገዳምስ እንዴት ነው?» አለው÷ እርሱም «በዚህስ በበኣቴ ተወስኜ በዓለም ከነበረብኝ ድካም በጸጋ እግዚአብሔር ዐርፌያለሁ» አለ:: «አርሳንዮስን በዓለም ሳለ ታውቀዋለህ?» ሲለው «አላውቀውም» አለ:: «አርሳንዮስ የንጉሥ ልጆች መምህር ነበር÷ ለእነርሱ ብዙ አገልጋዮችና ታዛዦች ነበሩት÷ ወርቅና ብር ሌላውም ሀብት አይቆጠርም ነበር÷ የተማረና የተከበረ የቤተ መንግሥት ሰው ነበር፤ አንተ በዓለም ሳለህ የነበረህን ያህል ሀብትና ምቾት እንኳ አርሳንዮስ በዚህ ገዳም በሕመም ጊዜ አላገኘም፤ አንተ በገዳም ለኑሮህም ተሽሎህ ዐርፈሃል÷ እርሱ ግን ያን ሁሉ ክብርና ብዕል ትቶ መጣ» አለው:: በዚህ ጊዜ ተጸጽቶ አርሳንዮስን «አባቴ ሆይ÷ ይቅር በለኝ፤ አንተ ወደ ድህነትና ትሕትና መጣህ÷የእኔ ግን ከድካም ወደ ዕረፍት ነው» ብሎ ሰግዶለት ሔደ::

ቅዱስ አርሳንዮስ ስለ ራሱና ስለ ዓለም ሁኔታ ሁል ጊዜ ሲያለቅስ ከመኖሩ የተነሣ በደረቱ መካከል እንባው የሚወርድበት ቦታ ጐርፍ እንደ ሚሔድበት መሬት ለይቶ ይታይ ነበር:: ስሌን በመታታት ሲኖር የሚያርስበትን ውኃ አይቀይርም ነበርና አንዱ «ለምን ይህን በጣም የቆሸሸና የሚሸት ውኃ አትቀይረውም?» ሲለው «በዓለም ሳለሁ ለጠጣሁት ያማረና መልካም ውኃ በዚህ ልቀጣ ብዬ ነው» አለው:: ቅዳሜ ማታ ፊቱን ወደ ምሥራቅ... አድርጎ ፀሐይ ጀርባውን ስትመታው እጆቹን ዘርግቶ ለጸሎት ይቆምና የሚቀመጠው እሑድ ጧት ፀሐይ ፊቱን ስትመታው ነው:: «ንሳዕ መክፈልተከ ኦ ሐካይ ሥጋ፤ ደካማ ሥጋ ሆይ÷ ያውልህ ዕረፍ ብሎ ያርፋል:: አንድ ምንም ትምህርት ያልተማረን መነኩሴ አርሳንዮስ ምክር ሲጠይቅ አይተው «አንተ ፈጽሞ የተማርክ ስትሆን እንዴት ይህንን ትጠይቃለህ?» አሉት:: እርሱ ግን ሲጠይቁት «አዎ÷ የግሪክንና የሮማውያንን ትምህርት ተምሬአለሁ÷ የቅዱሳንን ሕይወት ግን ገና ፊደሉንም አልቆጠርኩም» አላቸው::

ቅዱስ አርሳንዮስ ተባሕትዎን ፈጽሞ ከመውደዱ የተነሣ ከሰው መገናኘት አይወድም ነበር:: አንድ ቀን ቅዱስ አባ መቃርስ «አርሳንዮስ ሆይ÷ ከእኛ ለምን ትሸሻለህ? እኛንም ዓለማውያን አድርገኸን ነውን?» ሲለው «ፈጽሞ እንድወዳችሁ እግዚአብሔር ያውቃል÷ ነገር ግን ከሰውና ከእግዚአብሔር ጋር መሆን አልችልም፤ እግዚአብሔርንም ትቼ ከሰው ጋር መሆን ስለማልችል ነው» አለው:: ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባም በዓምዱ ይሰወር ነበር::

በአንድ ወቅት ከሮም ቤተ መንግሥት የሆነች እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ልታየው ፈልጋ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ቴዎፍሎስ ለአርሳንዮስ ይነግርላት ዘንድ ለመነችው:: ሊቀ ጳጳሳቱ ይህንን ለአርሳንዮስ ሊነግረው ፈቃደኛ አልሆነም:: ለንግሥቲቱም እንደማይቀበላት ሲነገራት «እኔ ተራ ሰውን ሳይሆን ታላቁን ቅዱስ አርሳንዮስን ላይ መጥቻለሁና እንደማየውና በረከቱን እንደምቀበል በእግዚአብሔር አምናለሁ» ብላ ከብዙ አጃቢና ሠራዊት ጋር ሆና ብትሔድ አርሳንዮስን ከበኣቱ በር ላይ አገኘችው:: እርሷም ሔዳ ከእግሩ ስር ወደቀች፤ እርሱም «ለምን እዚህ ድረስ መጣሽ? ሮም ሔደሽ አርሳንዮስን ዐየሁት እያልሽ ልታወሪና የሀገሩ ሴቶች ሁሉ እንዲመጡ መንገድ ልታሳይ ነውን?» አላት:: እርሷ ደግሞ «እግዚአብሔር ካልፈቀደ ማንም ወደዚህ ሊመጣ አይችልም፤ ነገር ግን እኔ ሁልጊዜ በጸሎትህ ታስበኝ ዘንድ እሻለሁ::» አለችው::

አርሳንዮስ «አነ አኀሥሥ እምእግዚእከመ ይጥፋእ ዝክርኪ እምልብየ፤ እኔስ ፈጣሪዬን የምለምነው መታሰብሽን ከልቤ እንዲያጠፋልኝ ነው» አላት::

/ወደ ገጽ ፵ ዞሯል/



www.eotcmk.org

# ወጣትነት እንደ ዮሴፍ

ሐተታዊ ጥንቅር

*/በዲ/ን ፋሲል አስረስ/*

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የሰው ልጅ ዕድሜ እየጨመረ የሚሔድ ሲሆን ከልጅነት እስከ ወጣትነት ባለው ዕድሜ አካል የሚጠነክርበት የአእምሮ አስተሳሰብ ብስለት እያደገ ክፉና ደጉን ከመለየት ጀምሮ ወደፊት ስላለው በማሰብ ለቀጣይ የኑሮ ዘመን መሠረት የሚጣልበት ነው።

የሁሉም ነገር መሠረት በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በወጣትነት ዘመናቸው በጐም ሆነ ክፉ ሥራ የሠሩ የተለያዩ ሰዎችን ሕይወት የሚያሳይ ታሪክ የተጻፈ ሲሆን አሁን ያለው ወጣት ከሕይወታቸው በመማር ሕይወቱን ባፋጭ ማድረግ ይጠበቅበታል። መንፈሳዊነት ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አድርጎ ተስፋ የምትደረገውን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ከማስጠት ባሻገር በምድር በምንኖርበት ዘመን ሰላምን፣ ፍቅርን፣ መረጋጋትን ታማኝነትን የሚያጐናጽፍ ሀብት ነው። ማንም ሰው በዚህ ሕይወት ውስጥ ቢኖር አንዳች የሚያጣው ነገር የለም። መንፈሳዊ ሰው በቀናች ሃይማኖት ጸንቶ በሚፈጽመው መልካም ምግባርና ባለው የሚረካ በሌለው ነገር የማይበሳጭ የራሱን የሚያካፍል የሌላውን የማይመኝ ነው።

ወጣትነት ደግሞ ትኩስ ኃይል ያለበት የወደፊት የኑሮ ዕጣ ፈንታ የሚወሰንበት የዕድሜ ክልል ነው። በዚሁ ወቅት በተለያዩ የሥራ መስኮች የሚገኘው ወጣት ነገ የእርሱ አለመሆኑን በመገንዘብ ዛሬ የለውጥ ሐዋርያ መሆን ይጠበቅበታል። ይህ ከወጣቱ የሚጠበቀው ተግባር እውን እንዲሆን መንፈሳዊነት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። በዚህ እትም ከሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን አገዘ ጋር ቆይታ አድርገን ያጠናቀርነውን ጽሑፍ ይዘን ቀርበናል።

በቅዱሳት መጻሕፍት ታሪካቸው ጐልቶ ሥነ ምግባራቸው አምሮና ተውቦ ከሚነበቡትና ከሚታወቁት የዛሬ አባቶች የጥንት ወጣቶች ውስጥ አንዱ ዮሴፍ ነው።

ዮሴፍ የስሙ ትርጉም «ይጨምር» ማለት ሲሆን የያዕቆብ ዐሥራ አንደኛ ወንድ ልጅ የራሔልም የበኩር ልጅ ነው። ዘፍ.30÷22-24። በዘመነ አበው የሕገ አበው ፈጻሚና ተጠቃሚ የነበረው ዮሴፍ በወጣትነቱ እያሌ ሥራዎችን ሠርቷል። ብዙ ፈተናዎች ደርሰውበታል። እነኝህንም የተወጣቸው በድል አድራጊነት ነው። ወጣትነት ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ አንዱ የሆነው እሳትነት የሚያይልበት ዘመን ሲሆን ዮሴፍ የእሳትነት ዘመኑ ሳያሸንፈው የፈተና ቀንበርን ድል አድርጎ መገኘቱ አሁን ላለው ወጣት አርአያና ምሳሌ እንዲሆን አድርጎታል።

አበ ብፁዓን ዮሴፍ የመጨረሻ ልጅ በመሆኑና ጸጋ እግዚአብሔር የነበረው በመሆኑ አባቱ ይወደው ስለነበር በወጣትነት ጊዜው በፈተና ውስጥ እንዲገባ የመጀመሪያው ምክንያት ሁኖበታል። በአባቱ ዘንድ በመወደዱ ሩቅ ሳይሔድ የገዛ ወንድሞቹ ጠሉት። በእርሱም ላይ ተነሣሱ። በጉድጓድ ውስጥም ጣሉት። በመጨረሻም ልብሱን ገፈው ለነጋዴዎች ሸጡት። ይህ ከሥጋዊውም ሆነ ከመንፈሳዊ ዝምድና የማይጠበቅ ሲሆን ነገር ግን በዮሴፍ ላይ ተፈጸመ።

ዮሴፍን አባቱ ይወደው ነበር ሲባል ከወንድሞቹ የተለየ አባቱ ያደርግለት ነበር ማለት ነው። የዮሴፍ ልብስ የአባቱ ፍቅር መገለጫ፣ ገጸ በረከት፣ አባቱ እንደሚወደው ምልክት ነው። ወንድሞቹ ሲጠሉት የወሰዱት ርምጃ የአባቱን ስጦታ መግፈፍ ማስጣል ነበር። ልብስ የበረከት፣ የጸጋ፣ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ምሳሌ ነው፤ ልብስ የመልካም ባሕል፣ የሀገርና የአባቶች ቅርስ ነው። አባቶቻችን ለእግዚአብሔርና ለሰው የነበራቸውን ፍቅር የሚገልጡት የነበራቸውን ነገር በማስቀመጥና ለልጆች በማውረስ ነው።

ዮሴፍ የአባቱን ስጦታ ወንድሞቹ እንደገፈፉት ሁሉ ይህ የዘመኑ ወጣት ሃይማኖቱን ባሕሉን የሀገርና የአባቶቹን ቅርስ እንዳይነጠቅ ሊጠነቀቅ ግድ ይለዋል። የዮሴፍ ወንድሞች ልብሱን በመግፈፍ አላቆሙም ለአባቱ ልጅህ ሞቷል ብለው የበጐቹን ደም አስነክተው ልብሱን መልሰው አባቱን አርድተውታል።

በአሁኑ ወቅት አባቶቻችን ያቆዩልንን ለመንጠቅ ከእግዚአብሔር ለመለየትና በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንድንሞት የሚደረጉት ጥረቶች ሁሉ አባቶቻችንን ስለሚያሳዝን ያለንን አጥብቀን በመያዝ በእምነታችን ልንጸና ያስፈልጋል።

ምንም እንኳን ዮሴፍ የተለያዩ ፈተናዎች ቢገጥሙትም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር መልካም ሥራውን አላቋረጠም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሰው ሥራው ሁሉ ይከናወንለታልና። ተሽጦ በሰው ሀገር ቢሔድም እግዚአብሔር ሹመት አዘጋጅቶ ጠበቀው። ዘፍ.39÷1-6። በእርሱም ምክንያት እግዚአብሔር የግብፃውያኑን ቤት ባረከ። ዮሴፍ ወጣት ነው፤ እግዚአብሔር ሰውን አይንቅም። የወጣቶችን ሥራ አገልግሎት ይባርካል። ጲጥፋራ በዮሴፍ ሥራና ውስጥ እግዚአብሔር እንዳለ ዐውቋል። የቤቱን ሀብት ንብረት ሁሉ ለዮሴፍ እንዲያዝበት ሰጥቷል። ወጣቶች ለሥራ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የወጣቶችን ሥራ እግዚአብሔር ይባርካል ብሎ የሚያምን አባት ሊኖር ይገባል። ወጣቱም እግዚአብሔር ሥራ የሚያሠራው ሁኖ መገኘት አለበት።

ሌላኛው የዮሴፍ ፈተና የጌታው ሚስት ዓይኗን በእርሱ ላይ መጣሏና ለዝሙት መጠየቋ ነው። «ሰው መልካም ሲሠራ በፈተናዎች መካከል እየሔደ መሆኑን ማመን አለበት። አንዱን ፈተና ማለፋችን ከሌላ ፈተና ነጻ ነን ማለት አይደለም። ጉዞው ሁሉ በፈተና የተሞላ ሁኖ ከዚህ የደረሰው ዮሴፍ በሚያባብል ንግግርም ሆነ በሥልጣን ጫና በማድረግ ፈቃዷን እንዲፈጽም ለጠየቀችው ሴት የሰጣት መልስ «ጌታዬ ሚስቱ ስለሆንሽ ከአንቺ በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም። ስለዚህ ይህን አላደርገውም» ነበር። የዕድሜውን ሁኔታ ስንመለከት «ይህ ከወጣቶች እንዴት ይወጣል?» ሊባል ይችል ይሆናል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሰው ግን ይናገረዋል፤ ይተገብረዋል። ዛሬ ወጣቱ ቢቻል በአካል አልያም በደብዳቤ፣ በስልክ ካልሆነም በሽማግሌ የእርሱ ያልሆነውን የእርሱ ለማድረግ ሲጥር እንደሚታየው ይህች ሴትም ዕለት ዕለት ፈቃዷን እንዲፈጽም ትጨቀጭቀው ነበር። ቆራጥ ልቡና የነበረው ዮሴፍ ሊቀበላት ባለመቻሉ በሐሰት ከስሳ ወደ እስር እንዲጣል አድርጋዋለች። ዘፍ.39። ዮሴፍ እስር ቤት ቢገባም ከግዞት ቤት አለቃ በታች የእስር ቤት ኃላፊ ሆኖ ተሹሟል። «እግዚአብሔር በወጀብና በአውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው» /ናሆ.1÷3/ እንዳለው በችግርና በመከራ በፈተናና በስቃይ ጊዜ እግዚአብሔር ልጆቹን ይመለከታል። ዮሴፍ ለእግዚአብሔር የተመቸ በመሆኑ በፈተናዎች ውስጥ ጽናትንና ክብርን ሰጥቶታል። የዛሬዎቹ ወጣቶችስ ከዮሴፍ ሕይወት ምን እንማራለን፡-

## 1ኛ. ታዛዥነትን

ቅዱስ ጳውሎስ «ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ» /1ኛተሰ.5÷15/ እንደሚለው ዮሴፍ ለወላጆቹም ለእግዚአብሔርም ታዛዥ ነበር። ለአባቱ ታዘዘ አባቱ ወደደው፤ በዚህ ምክንያት ወንድሞቹ ቀኑበት÷ ጠሉት። እግዚአብሔር ግን ከፍ ከፍ አደረገው። /ዘፍ.39÷1/።

ይስሐቅ እስከ ሞት ድረስ ለአባቱ ታዘዘ፤ እግዚአብሔር ከሞት ታደገው፤ አባቱንም እግዚአብሔርንም አስደሰቷልና /ዘፍ.22÷10/ ስሙ ሲጠቀስ ይኖራል። አበ ብዙኀን አብርሃም እግዚአብሔር ልጁን እንዲሠዋለት ሲጠይቀው በመታዘዝ ልጁን ለመሠዋት ተዘጋጀ። ይስሐቅም የሚሠዋበትን እንጨት ተሸክሞ ወደሚሠዋበት ቦታ የአባቱን ትእዛዝ በማክበር ተጓዘ። የአብርሃምን ቆራጥነት የይስሐቅን ታዛዥነት የተመለከተ እግዚአብሔር «አንድ ልጅህን አልከለከልከኝምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን ዐውቄአለሁ» በማለት አንድ በግ ተዘጋጅቶ በይስሐቅ ፈንታ ቀርቦለት እርሱን ሠውቷል።

*አብርሃም በልጁ በይስሐቅ*



www.eotcmk.org

# ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?

## "በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው::" ያዕ. 1÷12

መምህር ደጀኔ ሽፈራው

በመንፈሳዊ ጉዞ አያሌ ፈተናዎች ሲያጋጥሙን እንደሚችሉ ከጥንት ጀምሮ የተጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ያስተምሩናል:: በመሆኑም ከሁሉ አስቀድሞ ችግሮች ከየትና እንዴት ሊመጡ ቻሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት መሞከር አለብን:: ሰዎች:- ባለማወቅ፣ በሰው ተገፋፍተው፣ በዲያብሎስ አሽክላ ተይዘው፣ በሥጋ ፍላጐት ተታለው፤ በዐይን አምሮት ተማርከው በየዋህነትና በቅንነት፣ እውነት መስለው በሚቀርቡ ሐሰቶች፣ ትክክል መስለው በሚቀርቡ ስሕተቶች ተሳስተው በመታለል፤ በትዕቢትና በእልከኝነት የተነሣ፤ ክፉ ምክርን ከመስማት፤ ከቅንጦት፣ ከድሎት፣ ዐቅምን ካለማወቅና በአጉል ፍልስፍና በመራቀቅ ሊሳሳቱ በእነዚህም ሳቢያ ችግር ሊገጥማቸውና ሊፈተኑ ይችላሉ:: ዋናው ነገር ችግር ለምን ይኖራል አይደለም:: የሰው ልጅ ጉዞ ከችግር ተለይቶ አያውቅም:: ትልቁ ነጥብ ችግሩን ለምን ለመፍታት አልቻልንም ነው? እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው ችግሩን የሚፈታበት ራሱን የሚያይበትና ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመለስበት ጊዜና ጥበብ ይሰጠዋል:: እንዲህም ስለ ሆነ ከወዴት በኩል እንደ ወደቁ መመርመር እንጂ ጠቅልለው ራሳቸውን /ዕድላቸውን/፣ ባልንጀራቸውን ወይም ከፍ ብለው እግዚአብሔርን መኰነንና ማማረር አይገባቸውም::

ከላይ እንደ ተገለጸው ሰውና ፈተና ተለያይተው አያውቁም:: ሁል ጊዜ አብረው ይኖራሉ:: ኑሮአቸውም የፍቅር ሳይሆን የጠብ÷ የሰላም ሳይሆን የጦርነት ነው:: በመሆኑም ሰው ፈተናን ለማለፍ መከራን ይታገሣል፤ ይጋደላል:: ፈተናም ሰውን ለመጣል መከራ ያጸናል:: ይህ ሒደት የሰው ልጅ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ ዚያኛው ዓለም እስኪጓዝ ድረስ የሚቀጥል ነው፤ አያቋርጥም:: አንዱን ፈተና ሲያልፍ ሌላው ይተካል:: አንዱን ተወጣሁት ሲል ሌላው ደግሞ ጓዙን ጠቅልሎ ይመጣል:: የፈተና መምጫ መንገዱ÷ መግቢያ በሩ÷ መሹለኪያ ቀዳዳው÷ መሸጋገሪያ ድልድዩ÷ መወጣጫ መሰላሉ ብዙ ነው:: ስለዚህ በፈተና ሳለመውደቅ

ማንንም በክፉ አይፈትንም:: ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ "ማንም ሲፈተን:- በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና፤ እርሱ ራሱ ማንንም አይፈትንም::" ያለው:: ያዕ.1÷13:: ምናልባት እዚህ ላይ "ምነው፤ እግዚአብሔር ወዳጁን አብርሃምን ፈትኖት የለ?" እንል ይሆናል:: በርግጥ በጥሬ ንባብ ሲመለከቱት ይመስላል:: "ምነው ባልጠፋ ፈተና በልጁ ይፈትነዋል? ለምን እስከዚህ ድረስ ያስጨንቀዋል? አብርሃም በዚህ ነገር ባይታዘዝ ይፈረድበታል?" ያሰኛል:: ይኼ ሰው ሰውኛውን ሲያስበው፣ ሰውኛውን ሲመለከቱት ነው:: ትርጓሜውን ሲመለከቱት ግን ምሥጢሩ ሌላ ነው:: ይህም ምሥጢር ፈተናው ከሰው ባላጋራ ከሰይጣን መሆኑን ያስገነዝበናል::

አበ ብዙኃን አብርሃም የሃይማኖትም የምግባርም አብነት ነው:: አምልኮተ ጣዖት በሰፋበት በዚያ በጨለማ ዘመን ብርሃን እግዚአብሔርን ፈልጐ ማግኘቱ÷ ባገኘውም ጊዜ ድምፁን ሰምቶ በእርሱ ማመኑና መታመኑ ሃይማኖት ነው:: የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ከዘመዶቹ ተለይቶ÷ ከአገሩ ወጥቶ እግዚአብሔር ወደ ሚያውቃት፣ እርሱ ግን ወደ ማያውቃት አገር መጓዙ መታመን ነው:: ከዚህም ጋር በእንግድነት አገር ያውም በድንኳን ተቀምጦ በእግዚአብሔር ስም እንግዶቹን መቀበሉ (የተራቡትን ማብላቱ÷ የተጠሙትን ማጠጣቱ÷ የመሸባቸውን ማሳደሩ÷ ስንቅ ሰጥቶ መሸኘቱ) ምግባረ ብሉይ ብቻ ሳይሆን ምግባረ ሐዲስም ነው:: በየጊዜውም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያሳርግ ነበር:: ከዚህ የተነሣ በክብር ላይ ክብር እየተጨመረለት ሔደ:: ቅዱሳን መላእክትም "አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ፤" እያሉ ጧት ማታ ያመሰግኑት ይሰግዱለት ነበር::

የበጐ ምግባር ጠላት÷ የቅዱሳን ከሳሽ የሆነ ሰይጣን ይኽንን የአብርሃምን የቅድስና ሕይወት እያየ ይቀና ነበር::

ሳል:: ሰይጣን ነውር÷ ነቀፋ የሚሆን ምክንያተ ኃጢአት ከአብርሃም በማጣቱ በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ:- "እግዚአብሔር ሆይ÷ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ÷ እባርክሃለሁ÷ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ÷ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ:: ብለህ በክብር ከፍ ከፍ ያደረግኸው÷ ከአንተም አልፈህ በምስጋናና በስግደት በቅዱሳን መላእክት ያስከበርከው ይኼ አብርሃምኮ:- በስተእርጅና ያገኘኸውን የቃል ኪዳን ልጅህን ይስሐቅን እረድልኝ÷ ብትለው አያርድልህም፤ በሌላ ይታዘዝህ እንጂ በዚህ አይታዘዝህም::" እያለ ይከስሰው ጀመር::

እግዚአብሐር ልብን እና ኩላሊትን የሚመረምር (ልብ ያሰበውን ኩላሊት ያጤሰውን የሚያውቅ) አምላክ ነው:: መዝ.7»9:: ስለ ሰው ማንም እንዲነግረው አይፈልግም÷ እርሱ ራሱ ፈጥሮ የሚገዛቸውን ሰዎች ያውቃል:: "ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር÷ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና፤ ... ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበር፤" እንዲል:: ዮሐ. 1÷25:: በመሆኑም እግዚአብሔር በአብርሃም ልብ ያለውን ጽኑዕ እምነት ያውቃል÷ነጋሪ አያስፈልገውም:: ሰይጣንንም እስከነ ግብሩ ያውቀዋል:: ነገር ግን ሰይጣን በቅዱሳን ላይ ምክንያት እንዳይኖረው ለማድረግ÷ የሰይጣንን ክህደቱንና ሐሰቱን÷ የአብርሃምን ደግሞ እምነቱን፣ እውነቱንና ምግባሩን ለመግለጥ እግዚአብሔር አብርሃምን "ልጅህን ሠዋልኝ፤" አለው:: በዚህን ጊዜ አብርሃም ለእግዚአብሔር ያለውን እምነት ሳያጉድል÷ የእግዚአብሔርን ፍቅር በልጅ ፍቅር ሳይለውጥ «ጥንቱንስ የሰጠኝ እርሱ አይደል?» ብሎ ምትክ የሌለውን ልጁን ይስሐቅን:- እጅ እግሩን አስሮ በመሠዊያ ላይ አጋደመው:: እግዚአብሔር ለአብርሃም ያለውን ታማኝነት ላያ

በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል፤» እንዲል:: ሮሜ.16÷19::

ሰይጣን ቅዱሳንን ለመፈተን የቅዱሳን ከሳሽ እንደ ሆነ በጻድቁ በኢዮብ ሕይወትም ታውቋል:: የአምላክ ልጆች (ቅዱሳን መላእክት) በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም በመጡ ጊዜ ሰይጣን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም በመካከላቸው መጣ:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን:- «ከወዴት መጣህ?» አለው:: ሰይጣንም:- «በምድር ላይ ዞርሁ÷ በእርስዋም ተመላለስሁ፤» ብሎ ለእግዚአብሔር መለሰ:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን:- «በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም፤» አለው:: ከዚህ የምንማረው:- እግዚአብሔርን አብነት አድርገን ስለ ቅዱሳን መመስከር እንደሚገባ ነው:: ቅዱሳንን መክሰስ የሰይጣንና የመልእክተኞቹ ነውና:: ሰይጣንም ሳያፍር:- «በውኑ ኢዮብ እግዚአብሔርን የሚፈራ በከንቱ ነውን? እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን? የእጁን ሥራ ባርከህ ለታል÷ ከብቱም በምድር ላይ በዝቶአል:: ነገር ግን እጅህን ስደድና ያለውን ሁሉ ዳብስ፤ (አጥፋ)፤ በእውነት በፊትህ ይሰድብሃል፤» ሲል ለእግዚአብሔር ተናገረ::

ሰይጣን ዝም ብሎ ይደክማል እንጂ እግዚአብሔር ወዳጆቹን ያውቃቸዋል÷ እንደሚያምኑት ያምናቸዋል፤ «ሰይጣን በሚያመጣው ፈተና ምን መከራ ቢጸናባቸው አይክዱኝም፤» የሚል እምነት በቅዱሳን ላይ አለው:: የቅዱሳንን እና የእግዚአብሔርን ወዳጅነት ልዩ የሚያደርገው ይኼ ነው:: ከላይ እንደገለጥነው ሰይጣን አስቦት ሳይፈጽመው የሚቀረው ክፋት ስለሌለ በጻድቁ በኢዮብ ፈተና አበዛበት:: የኢዮብ ዐሥር ልጆች በአንድ ቀን አለቁ÷ እሳት ከሰማይ ወርዶ ሰባት ሺህ በጎቹ ከነጠባቂዎቻቸው ተቃጠሉ÷ አንድ ሺህ በሬዎቹንና አምስት መቶ እንስት አህዮቹን የሳባ ሰዎች አደጋ ጥለው ወሰዷቸው፤ የሚጠብቁትን ብላቴኖችንም በሰይፍ ገደሏቸው:: ሦስት ሺህ ግመሎቹን ደግሞ ከለዳውያን ወሰዷቸው:: ጻድቁ ኢዮብ ይኸንን ሁሉ መርዶ በአንድ ጊዜ በተከታታይ በሰማ ጊዜ መጐናጸፊያውን ቀደደ:: እንዲህ ማድረግ የኀዘን ምልክት ነው:: ፀጉሩንም ተላጭቶ በምድር ላይ በግንባሩ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ሰገደ:: «ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፤ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ፤ እግዚአብሔር ሰጠ÷ እግዚአብሔርም ነሳ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ (የተመሰገነ) ይሁን::» አለ:: በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም:: ኢዮ.1÷1-22::

ሰይጣን÷ ልክስክስ ውሻና ሌባ መለስ ቀለስ ያበዛሉ:: ሰይጣን በአንድ ፈተና ብቻ አይተወንም÷ በአንድ በኩል ድል ስናደርገው በሌላ በኩል ይመጣል:: እስከ መጨረሻው ይታገለናል:: ለዚህም ነው ዳግመኛ በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የደፈረው:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን «ከወዴት መጣህ?» ብሎ ዳግመኛ ጠየቀው:: ሰይጣንም እንደ ልማዱ «በምድር ላይ ዞርሁ÷ በእርስዋም ተመላለስሁ፤» ብሎ መለሰ:: እግዚአብሔርም ሰይጣንን:- «በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትኸውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን÷ እግዚአብሔርንም የሚፈራ÷ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም፤ በከንቱም አጠፋው ዘንድ አንተ በእርሱ ላይ ምንም ብታንቀሳቅሰኝ እስከ አሁን ፍጹምነቱን ይዞአል::» አለው:: ሰይጣንም «ኢዮብ ጤናውን ቢያጣ ይክድሃል፤» ሲል መልሶ ተናገረ:: እግዚአብሔር ግን ኢዮብ ምንም ይሁን ምን እንደማይክደው ያውቃል:: ይሁን እንጂ በምግባር በምት ገለጥ በኢዮብ ሃይማኖት ሰይጣን ያፍር ዘንድ ፈተናው መጣ:: ኢዮብ ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ በቁስል ተመታ÷ በትል ተበላ÷ መግል ፈሰሰው÷ ሸተተ÷ አመድ ላይ ተኛ:: በዚህ ሁሉ ኢዮብ አልበደለም:: ኢዮ.2÷1-9:: በዚህም የትዕግሥት አብነት ሆኗል:: ይኸንን በተመለከተ:- ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ:- «እንግዲህ÷ ወንድሞች ሆይ÷ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ:: እነሆ÷ ገበሬው የፊተኛውንም የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል:: እናንተ ደግሞ ታገሡ÷ ልባችሁንም አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀር ቦአልና:: ወንድሞች ሆይ÷ እንዳይፈረድ ባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፤ እነሆ ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል:: ወንድሞች ሆይ÷ የመከራ እና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ:: እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል÷ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤» ብሏል:: ያዕ. 5÷7-11::

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ የምንማረው÷ ሰይጣን:- እንኳን ከእኛ ምክንያት አግኝቶ÷ ባያገኝ እንኳን ሰውን ከመፈተን እንደ ማያርፍ ነው:: እንኳን የሥጋ ፍላጐታችንን እና የዐይን አምሮታችንን እንደ በር ከፍተንለት ቀርቶ÷ ፈቃደ ሥጋችንን ለፈቃደ ነፍሳችን አስገዝተን መግቢያ ቀዳዳ÷ መምጪያ መንገድ ብናሳጣው እንኳ እርሱ ሰውን ከመፈተን ወደ ኋላ አይልም:: ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ:- «እንግዲህ በጊዜው ከፍ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኀይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና፤ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት÷ በመጠን ኑሩ÷ ንቁም÷ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደ ሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል÷ ያጸናችሁማል÷ ያበረታችሁማል::» ያለው:: 1ኛጴጥ.5÷6-10:: ስለዚህ ሐዋርያው እንደ ተናገረው÷ ቅዱስ ያዕቆብም በመልእክቱ «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤» /ያዕ.4÷6/ ባለው መሠረት:- በጾም÷ በጸሎት÷ በስግደትና በምጽዋት ተወስነን በዙሪያችን የሚልከሰከሰውን ጠላት እስከ መጨረሻው ልንቃወመው ይገባል:: ምክንያቱም እርሱ የሚሸሸው ለጊዜው ነው:: በኋላ ግን ኃይሉን አጠናክሮ ይመለሳል:: ጌታ በወንጌል:- «ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ÷ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያል ፋል÷ አያገኝምም:: በዚያን ጊዜም:- ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመ ጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል:: ከዚያ ወዲያ ይሔድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት (ፍጹም ኃጢአት የሚያሠሩትን) ከእርሱ ጋር ይወስዳል÷ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል:: ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲህ ይሆንበታል::» ያለው ለዚህ ነው:: ማቴ. 12÷43-45:: በዚህ ትምህርት የተጠረገ ባዶ ቤት የተባለው ከጾም÷ ከጸሎት÷ ከስግደትና ከምጽዋት ባዶ የሆነ የሰው ሕይወት ነው:: ያ ሰው ትቶት ወደ ነበረው ክፉ ምግባር ሲመለስ በበጐ ምግባር ኃይል ሸሽቶ የነበረ ሰይጣን ከእርሱ የከፉ ሌሎች አጋንንትን አስከትሎ ወደዚያ ሰው ይ መለሳል:: «ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል፤» የተባለው ደግሞ የፊተኛው ከምግባር ነው የለየው÷ የኋለኞቹ ግን ከሃይማኖት ይለዩታል ማለት ነው::

የተወደዳችሁ አንባብያን:- ከዚህ ተነሥተን÷ በዚህ ተመሥርተን ነው:– «ፈተና የሚመጣው ከየት ነው?» የሚለውን በዝርዝር የምንመለከተው:: ይህም ለሕይወታችን እጅግ ጠቃሚ ነው:: ምክንያቱም ለመጠንቀቅም ለመጠበቅም ይረዳል:: የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን::

*ይቆየን::*


**ዜና መጽሐፍ**

**መሥዋዕተ ወንጌል**

ስለ ምሥጢረ ቁርባን ሰፊ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥ÷ ግልጽ በሆነ አቀራረብ÷ ማራኪ ቅደም ተከተል ባላቸው ስድስት ምዕራፎች የተዘጋጀ አዲስ መጽሐፍ እነሆ ለምእመናን ተበረከተ::

*አዘጋጅ:– ያዕቆብ ሰንደቁ*

**ይህ መጽሐፍ**

- ለመቁረብ እየፈለጉ በተለያየ ምክንያት ለዘገዩ መፍትሔ የሚሰጥ::
- ቅዱስ ቁርባን በመቀበል የሚገኘውን መንፈሳዊ ጸጋና በረከት በምላት የሚያስረዳ::
- ጋብቻቸውን በቅዱስ ቁርባን ለመፈጸም የሚያስፈልገውን ቅድመ ዝግጅት የሚጠቁም ::
- ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል እንዴት እንደምንዘጋጅ የሚመክር::
- ቅዱስ ቁርባን በተቀበልንበት ዕለት የምናደርገውን ጥንቃቄ የሚያስረዳ::

**መጽሐፉን ለማግኘት**

✝ በሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ማከፋፈያዎች
✝ አርያም መዝሙር ቤት አውቶብስ ተራ
✝ መርካቶ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት በሚገኙት የመጽሐፍት መደብሮች

E-mail: yakobzz@yahoo.com ☎ 20-04-38 09-63-63-93

ከዚህ በፊት ከአዘጋጁ የቀረበ መጽሐፍ «እናታችን ጽዮን»




www.eotcmk.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኅትመት መገናኛ ብዙኃን አጠቃላይ ዳሰሳ

/መስፍን ነጋሽና አሉላ ጥላሁን/

በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል አዘጋጅነት የሐመር መጽሔትንና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣን የ10 ዓመት ጉዞ በመቃኘት «ዝክረ ሐመረ ጽድቅ» ዐውደ ጥናት የካቲት 20 ቀን 1996 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ማዕከል አዳራሽ ተካሒዶ ነበር። በዐውደ ጥናቱ ላይ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ኃላፊዎች፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣የቤተ ክርስቲያኒቷ ኅትመት ሚዲያ /ጋዜጣ፣መጽሔት/አዘጋጆች ፣ የመንግሥትና የግሉ ፕሬስ ባለሞያዎች ተገኝተዋል። በዚህ እትማችን በዕለቱ ቀርበው ከነበሩት የጥናት ጽሑፎች መካከል በአቶ መስፍን ነጋሽና አቶ አሉላ ጥላሁን ተዘጋጅቶ የነበረውን አንዱን ጥናት በዚህ እትም አቅርበናል።

1.መግቢያ

የኅትመት መገናኛ ብዙኃን/ለዚህ ጽሑፍ ዓላማ መደበኛ ጊዜያቸውን ጠብቀው በተከታታይ የሚወጡትን ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ብቻ የሚመለከት ነው/ በአገራችን ረጅም ታሪክ ያለው ክስተት አይደለም። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፣ በእርስዋም በኩል ኢትዮጵያ ረጅም የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ቢኖራትም በኅትመት መገናኛ ብዙኃን በኩል አጀማመሯም ሆነ የደረሰችበት ደረጃ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር እንኳን የሚመጣጠን አይደለም። የሥነ ጽሑፍ ታሪካችን ለኅትመት መገናኛ ብዙኃን ተጠቃሚነት ያላበቃን ምናልባትም የኅትመት ሚዲያውን ግድ የሚሉና የሚያበረታቱ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ሳይፈጠሩ በመቆየታቸው ሊሆን ይችላል።

በአገራችን የመጀመሪያው የማተሚያ መሣሪያ ምጽዋ ላይ የተተከለው በ1863 /እ.ኤ.አ/ ነው። ማተሚያውንም ያስመጣው የላዛሪስት ሚሲዮን መምህር የነበረው ሎሬንዞ ቢያንቺሪ ነው። በ1885 ዓ.ም እንዲሁ የስዊድን ኢቫንጀሊካል ሚሽን በማንኩሎ /ምጽዋ አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ/ አነስተኛ የማተሚያ ቤት ለመክፈት በቅቶ ነበር። የፍራንሲስካውያን ሚስዮኖች አባት የነበረው በርናንድ በ1896 ስለ ሥጋ ደዌ በሽታ የሚያስተምር በአማርኛና በፈረንሳይኛ የሚጻፍ ሳምንታዊ ጋዜጣ ማሳተሙ በታሪክ ተመዝግቧል። /ሽመልስ፣ 2000፡6/።

በርናንድ በ1905 «Le Semanic d' Ethiopie» በሚል ስያሜ ሐረር ውስጥ ያወጣው የነበረውን ሳምንታዊ ጋዜጣ ለአገራችን ወቅቱን ጠብቆ በተከታታይ የሚወጣ የመጀመሪያ ኅትመት /Periodical/ አድርገው የሚያስቀምጡ አሉ። በሌላ በኩል ብላታ ገብረ እግዚአብሔር በእጃቸው እየጻፉ በየሳምንቱ አዲስ አበባ ውስጥ ያከፋፍሉት የነበረውን «ጋዜጣ» የመጀመሪያ የሚሉ አሉ። በ1896 ዓ.ም. ገደማ በከንቲባ ደስታ እየተዘጋጀ ይሠራጭ የነበረውን «የብዕር ድምፅ» ጋዜጣ የመጀመሪያ የሚያደርጉ ጸሐፊዎችም አሉ። /ተድባበ፣ 1990/።

ከዚህም ጉን በተመሳሳይ ወቅት ማለትም ከ1900 በፊት በነበሩት ዓመታት መውጣት የጀመረውን «አእምሮ» የተሰኘውን «ጋዜጣ» የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃውን የጠበቀ ጋዜጣ የሚሉት ጸሐፊዎች አሉ። /ፓንክረስት፣1962/። በመጨረሻም በርካታ የዘመናችን ጸሐፊዎች ደግሞ የመጨረሻው ማለትም «አእምሮ» የመጀመሪያው ጋዜጣ በመሆኑ ይስማማሉ። ለጋዜጣው «አእምሮ» የሚለውን ስያሜ የሰጡት ዐፄ ምኒልክ መሆናቸው ይነገራል። የ«አእምሮ» የሥርጭት ብዛት በእጅ እየተጻፈ በሚሠራጭበት ወቅት 24 ቅጂዎች የነበሩ ሲሆን የማተሚያ መሣሪያ ከመጣ በኋላ ወደ 200 አድጓል።/ ሽመልስ፣ 2000፣7/።

ከዚያ በኋላ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ በ1917 /ሳምንታዊ/፣ በጣልያን ወረራ ወቅት ደግሞ «ባንዲራችን» /በኋላ ሰንደቅ ዓላማችን ተብሏል/ ፋና ወጊዎች ነበሩ። ከነጻነት መመለስ በኋላ በመንግሥት የተቋቋሙት ሳምንታዊዎቹ« አዲስ ዘመን» /1941 እ.ኤ.አ/ እና«ዘኢትዮጵያን ሄራልድ» /1943 እ.ኤ.አ/ ከታኅሣሥ 1950 ጀምሮ ዕለታዊ በመሆን እስከ ዛሬ ዘልቀዋል። «የዛሬይቱ ኢትዮጵያ» ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ ሲታተም ቆይቷል። በዚህ ታሪክ ውስጥ የልዩ ልዩ እምነት ድርጅቶች ጋዜጦችም ታትመው ይወጡ ነበር። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን «ተክለ ሃይማኖት» የተባለ ጋዜጣ ከ1938 ዓ.ም ጀምሮ ይወጣ ነበር።

ተከትሎ በመጣው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሥርዓተ መንግሥት በአገሪቱ ከመንግሥትና ከፓርቲ ውጭ የነበሩ አብዛኞቹ ጋዜጦች መታተም ቢያቆሙም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋዜጦችና መጽሔቶች ሲታተሙ መቆየታቸውን እናስታውሳለን። ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ በአገሪቱ የተከሰተው ለውጥ ለበርካታ የኅትመት ውጤቶች መነበብ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩ ጋር በተያያዘም በቤተ ክርስቲያን አካባቢ በቁጥርም በዓይነትም የበዙ የኅትመት ውጤቶችን ለማየት ተችሏል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካላት የሥነ ጽሑፍ ሀብት፣ የምእመናን ብዛትና በአገሪቱ ውስጥ ከነበራት ሁነኛ ድርሻ አኳያ በጋዜጣና በመጽሔት ኅትመት በኩል በቂ ርቀት ተጉዛለች ማለት ግን ፈጽሞ የማይቻል ነው።

## 2. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፕሬስ ውጤቶች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የፕሬስ ውጤቶች / ጋዜጦችና መጽሔቶች/ በተመለከተ የተደረገ ይህ ነው የሚባል ጥናት ለማግኘት አልተቻለም። በመሆኑም ለዚህ ጥናት ከየቦታው በተሰባሰቡ መረጃዎችና ከግለሰቦች በተገኙ የቃል አስረጂዎች ላይ መመሥረት የግድ ሆኗል።

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደ ተሞከረው የቤተ ክርስቲያኒቱ የፕሬስ ውጤቶች ታሪክ ቢበዛ ከ60 ዓመት ያለፈ አይደለም። በዚያውም ላይ የፕሬስ ውጤቶቹ በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ በተደረገው ጥረት ለጥቂት ጊዜያት ወጥተው የተቋረጡ በርካታ ኅትመቶች መኖራቸውን ብንረዳም የአንዳንዶችን ቅጂ እንኳ በቀላሉ ለማግኘት አልተቻለም። ይህም ቢሆን ግን የኅትመት ውጤቶቹን በጣም ከሚታወቁት ጋዜጦችና መጽሔቶች ጋር በማያያዝ በሦስት ዘመናት ከፍሎ ለማየት ተሞክሯል። በዚህ ትንተና የዋና ዋና የፕሬስ ውጤቶችን ታሪክ ብቻ ሳይሆን በየዘመኑ ያሳዩትንም አጠቃላይ ባሕርይ በንጽጽር ለመዳሰስ ተሞክሯል።

ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው በዚህ የዳሰሳ ጥናት ዝግጅት ወቅት ከፍተኛ የመረጃ ምንጭ እጥረት አጋጥሟል። በመሆኑም ጥናቱ በአጠቃላይ ዳሰሳና ንጽጽር ላይ አተኩሮ ለሌሎች ዝርዝርና ሰፊ ጥናቶች መነሻ እንዲሆን ማድረግ የተሻለ ሆኖ አግኝተነዋል። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያንን የኅትመት ውጤቶች ታሪክ በሦስት ክፍለ ዘመናት በመከፋፈል በየዘመናቱ የታዩትን ሁኔታዎች ከተወሰኑ ማሳያዎች አኳያ ለመዳሰስ ተሞክሯል። ከዚሁም ጉን ለጉን ለጊዜው የተሻለ መረጃ የተገኘላቸውንና ዋና ዋና ያልናቸውን የኅትመት ውጤቶች ነባራዊና ወቅታዊ ሁኔታ በጣም በአጭሩ እንዲቀርብ ተደርጓል። በዚህ ጥናት ያልተጠቀሱ ወይም ታሪካቸው በበቂ ሁኔታ ያልሰፈረ የኅትመት ውጤቶች ቢገኙ ይህ የሆነው በመረጃ እጥረት አለበለዚያም ከጥናቱ የምልከታ ውስንነት ብቻ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን። ይህ የዳሰሳ ጥናት የቤተ ክርስቲያናችን የኅትመት ውጤቶች ሰፊ ጥናት ሊደረግባቸው እንደሚገባ ለማመልከትና ለመነሻ የቀረበ እንደ መሆኑም በአመዛኙ ከአጠቃላይ ባሕርያትና በንጽጽር ላይ ያተኮረ ሆኗል።

በጥናቱ ለንጽጽር የቀረቡት የኅትመት ውጤቶች የተመረጡት አዘጋጆቹ ባገኙት መረጃና በግል አመለካከታቸው ላይ ብቻ በመመሥረት ነው። የጥናቱ አዘጋጆች በዚህ ጥናት ያልተጠቀሱ ወይም በንጽጽር ታሪካቸው በአጭሩ የተገለጡ ኅትመቶች ከሌሎቹ ያነሱ ናቸው የሚል እምነት የላቸውም። ይልቁንም የነበሩትንም ሆነ ያሉትን ኅትመቶቻችንን በተናጠልም ሆነ በጋራ በስፋት በማጥናት ቤተ ክርስቲያን የጠንካራ የኅትመት ውጤቶች ባለቤት የምትሆንበትን መንገድ በጋራ መመልከት እንደሚገባ የዳሰሳችን ውጤት ያሳያል። በዚህ ዐውደ ጥናት የሚነሡት አሳቦች የዳሰሳ ጥናታችንን እንደሚያበለጽጉትና ጥሩ የመነሻ ጥናት እንደሚያደርጉት ተስፋ እናደርጋለን። በመጨረሻም በዚህ የዳሰሳ ጥናት የቀረቡት መረጃዎችም ሆኑ ትንታኔያቸው የጥናት አድራጊዎቹ ብቻ መሆናቸውን እናስታውሳለን። ለጥናታችን መሳካት መረጃ በመስጠት የተባበሩንን ሁሉ በእጅጉ እናመሰግናለን።

### 1. ከ1935 - 1966 ዓ.ም.

ለዚህ ጥናት ካነጋገርናቸው ሰዎች ለመረዳት እንደ ተቻለው በዘመናዊ መልኩ ለቤተ ክርስቲያናችን የመጀመሪያው ጋዜጣ የታተመው በ1938 ዓ.ም. ነው። ይህም «ተክለ ሃይማኖት» የተባለው በየ15 ቀኑ ይወጣ የነበረ ጋዜጣ ነው። /መጋቤ ምሥጢር



www.eotcmk.org

ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ፣የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 1996 ዓ.ም./:: በሁለተኛነት የሚነሣው «ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ» ሲሆን በ1940 ዓ.ም. መታተም ጀምሯል:: ወደ ኋላ «ተክለ ሃይማኖት» እና «ዜና ቤተ ክርስቲያን» ጋዜጦች በየ15 ቀኑ መውጣታቸው ቀርቶ ሁለቱም ወደ አንድ ጋዜጣነት ተጣምረው በየሳምንቱ እሑድ እንዲወጡ ተደርጓል:: በዚህም ይመስላል ለቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ዘመናዊ ጋዜጣ «ዜና ቤተ ክርስቲያን» ወይም «ተክለ ሃይማኖት» ስለ መሆኑ የተለያዩ አስተያየቶች የሚሰሙት:: /«ዜና ቤተ ክርስቲያን ዘኢትዮጵያ» ለተወሰነ ጊዜ «ዜና ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊት» ይባል ነበር::/ በዚህ ዳሰሳዊ ጥናት ሒደት «ተክለ ሃይማኖት» ጋዜጣ «ዕለታዊም ሆኖ ነበር» የሚል የቃል መረጃ አጋጥሟል::

«ተክለ ሃይማኖት » ጋዜጣ በትምህርተ ሃይማኖት ላይ ያተኮረ ሲሆን «ዜና ቤተ ክርስቲያን» ደግሞ ለዜናና ለታሪኮች የበለጠ ትኩረት ይሰጥ ነበር:: እነዚህ ሁለት ጋዜጦች በኋለኛው ስም ከተጠቃለሉና ሳምንታዊ ከሆኑ በኋላ ከፍተኛ ተነባቢነትን አግኝተው እንደ ነበረ የቃል አስረጂዎች ያሳያሉ:: /ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ÷ የሊቃውንት ጉባኤ አባል÷ ቃለ መጠይቅ÷ 1996 ዓ.ም/:: ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንቅስቃሴና አስተምህሮ በየጊዜው በጋዜጣ መረጃ ለመስጠት በመቻሉ የጋዜጣው ተቀባይነት ብዙ የሚያስገርም አይደለም:: ዜና ቤተ ክርስቲያን በዚህ ወቅት እስከ 5000 ኮፒ ለመታተም ደርሶ ነበር::

ተከትሎ የመጣውና ከፍተኛ ዕውቅና ያገኘው «ትንሣኤ» መጽሔት ነው:: መሠረቱን በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ባደረገው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት አሳታሚነት በግንቦት 1959 ዓ.ም. መታተም የጀመረው ይህ መጽሔት እስከ የካቲት ወር 1971 ዓ.ም ድረስ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ፤ ከመጋቢት ወር 1971 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በየወሩ እስከ 1985 ዓ.ም. ድረስ ሲታተም ቆይቷል:: መጽሔቱ መጀመሪያ በዓመት ስድስት ጊዜ ሲታተም ቢቆይም በ1969 ዓ.ም. ከብሥራተ ወንጌል የሬድዮ ጣቢያ መዘጋት ጋር በተያያዘ ወርኃዊ እንዲሆን ተደርጓል:: «ትንሣኤ» በይዘቱም ሆነ በአደረጃጀቱ ጠንካራ ነበር ለማለት ይቻላል:: ለምሳሌ በይዘቱ በጤና፣ በሴቶች፣ በልማት፣በፍልስፍና፣ በሥነ ልቡና፣ በሥነ ጽሑፍና በሌሎችም መስኮች የተለያዩ ጽሑፎችን ያቀርብ ነበር:: ከሃይማኖታዊ ትምህርቱ ጐን ለጐን እነዚህን መሰል ጉዳዮች በብዛት የማቅረቡ አስፈላጊነት የሚያነጋግር ቢሆንም በተለይ ከመጽሔቱ የሥርጭት አድማስ ስፋትና ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ የሚመሰገን እንጅ የሚነቀፍ አይሆንም:: እነዚህን ጽሑፎች በባለሞያዎች ለማዘጋጀት ለጸሐፊዎቹ /Freelancers/ በጽሑፍ 50 ብር ይከፈል ነበር:: ከ7,000-12,000 ኮፒ ይታተም የነበረው ይህ መጽሔት በሐዋርያዊ ድርጅት ስር ሲመራ ቆይቶ ከአብዮቱ በኋላ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ተጠቃሏል::

«ትንሣኤ» መጽሔት ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን አጣጥሞ ለምእመናን በማቅረብ ለቤተ ክርስቲያን ፕሬሶች /ጋዜጣና መጽሔት/ ፋና ወጊ ሆኗል ማለት ይቻላል:: ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው ማኅበራዊ ጉዳዮች ሌላ የቤተ ክርስቲያንን ቅዱሳን፣ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ፣ የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት ወዘተ... ማንጸባረቅ የመጽሔቱ ዋነኛ ተግባር ነበር:: መጽሔቱ የአገራችንን ገዳማትና አድባራት በማስተዋ ወቅም ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: ይህንኑ እየተዘዋወሩ የሚዘግቡ አባ ቸርነት ጋሻው በዛ የተበሉ መነኮስ ሪፖርተርም ነበሩት::

«ትንሣኤ» መጽሔት ከአዘጋጆቹ በተጨማሪ ጽሑፎችን የሚያበረክቱለት ከ30 ያላነሱ የስብከተ ወንጌል መምሪያ ሠራተኞችም ነበሩት:: ይህም በርካታ ርእስ ጉዳዮችን በተለያየ አቀራረብ ለማዘጋጀት ሳይረዳው አልቀረም:: ከመጽሔቱ ቋሚ ዓምዶች መካከል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፣ የሃይማኖት ትምህርት፣ ማኅበራዊ ኑሮ፣ የግብርና በረከት፣ የጤና ዓምድ፣ ሴቶች በሃይማኖት እና የወጣቶች ዓምድ የሚጠቀሱ ናቸው::

በ1956 ዓ.ም. በሐዋርያዊ ድርጅት ስር መታተም የጀመረው «ድምፀ ተዋሕዶ» ጋዜጣም ለኅትመት በበቃባቸው ዓመታት ከፍተኛ ተነባቢነትን አግኝቶ ነበር:: ይህ በየ15 ቀኑ ይወጣ የነበረ ጋዜጣ ለልጆችና ለተማሪዎች /ለወጣቶች/ የተለዩ ዓምዶችን ከመክፈቱም በተጨማሪ ለለውጥና ለውይይት የሚጋብዙ አስተያየቶችን በማቅረብ ይታወቃል:: ቀድመውት ከነበሩት ከነዜና ቤተ ክርስቲያን ጋር በመወዳደር ምእመናን የንባብ አማራጭ እንዲያገኙም አድርጓል:: በዓምድ ደረጃ የልጆች ፣ የሴቶች ፣ የጤና፣ የስብከት፣ የወጣቶች/የተማሪዎች/ ፣የቅዱሳት መካናት፣ የቅዱሳን ሰዎች እና የዜና ዓምዶች ነበሩት:: «ድምፀ ተዋሕዶ» በኅትመት ብዛት እስከ 15,000 የደረሰበት ጊዜ ነበረ:: / ሊቀ ልሳናት ንቅዓ ጥበብ ወንድም፡ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ የነበሩ፡ ቃለ መጠይቅ፣ ኅዳር 1996 ዓ.ም./::

በዚህ በመጀመሪያው ዘመን / 1938 - 1966 ዓ.ም/ ሲታተሙ የነበሩት እነዚህ ብቻ አይደሉም:: ለዚህ ጥናት ዓላማ ሲባል የዘመኑን ፕሬሶች ገጽታ ለማሳየት ያህል ቀደም ሲል የተጠቀሱት ተነሡ እንጂ በርካታ የኅትመት ውጤቶች እንደ ነበሩ የተለያዩ ማስረጃዎች ይጠቁማሉ:: ከእነዚህም መካከል ሦስቱን እዚህ ላይ ማንሣቱ በዘመኑ የነበረውን ጠንካራ ጅምር ያሳየናል:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ድርጅት ስር ከሚታተሙት መካከል የምእመናን አስተያየትና ድምፅ ብቻ የሚስተናገድበት /በአጥቢያ ደረጃ የሚዘጋጅ/ «ድምፀ ምእመናን» የተባለ ጋዜጣ ነበር:: በተመሳሳይ መልኩም የካህናት ጉዳዮች ብቻ የሚስተናገዱበት «ግብረ ልዑካን» የሚባል ጋዜጣ ሲታተም ነበር:: «ድምፀ ምእመናን» በምእመናን የዕለት ከዕለት ሕይወትና በቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው የሚያጋጥሙዋቸውን ችግሮች፣ እንዲሁም ስለ መንፈሳዊ ሕይወታቸው ምእመናን ራሳቸው ይወያዩበት ነበር:: ከዚህም በተጨማሪ በየጊዜው በጥምቀት፣በሕያዋንና በሙታን መዝገብ የሚገቡ ምእመናን ዝርዝር በዚሁ ጋዜጣ ይወጣ ነበረ:: ይህ ከስድሳ ዓመት በፊት የነበረ ጅምር ቀጥሎ ቢሆን አሁን ለቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆቿን በዝርዝር እንድታውቅ ያስችላት እንደ ነበረ አያጠራጥርም:: ሌላው አስገራሚ ጅምር «ትንሣኤ» መጽሔት በግእዝ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎችም እንዲወጣ መደረጉ ነው:: በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ሰባክያነ ወንጌል በወር አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ስለ ግእዝ ቋንቋ ውይይት ካደረጉ በኋላ የውይይቱ ፍሬ ነገሮች በግእዝ ቋንቋ ተጽፈው እንዲታተሙ ሲደረግ ነበር:: በእንግሊዘኛም እንዲሁ የተለየዩ ኅትመቶች በተለይም በማዕዶት መጽሔት ለንባብ እንዲበቁ ተደርጓል:: /መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ፣ የሊቃውንት ጉባኤ አባል፣ ቃለ መጠይቅ፣ ኅዳር 1996 ዓ.ም./::

ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የምታወጣቸውን ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ለሕዝብ ለማዳረስ መውጣት ጀምራ የነበረችው «ቃለ ዓዋዲ» የተሰኘችው ጋዜጣም በዚህ አጋጣሚ መጠቀስ ይኖርባታል:: ይህች ጋዜጣ እንደ መንግሥት የነጋሪት ጋዜጣ እንድታገለግል ታስባ ነበር:: በዚህ ዘመን የወጡትን በተለይም ለዚህ ጥናት ዓላማ የተመረጡት የኅትመት ውጤቶች በይዘትም ሆነ በአቀራረብ አምስት ባሕርያት ይንጸባረቅባቸዋል::

*ሀ. የኤዲቶሪያል ነጻነት*

የኅትመት ውጤቶቻችን በየገጾቻቸው በሚያቀርቧቸው ጽሑፎችና አስተያየቶች አቅም በፈቀደ መጠን በየአካባቢው በሚካሔዱ የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ላይ ተገቢ ነው ያሉትን ነጻ አስተያየት ይሰጡ ነበር:: እንዲያውም አንዳንዶቹ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መዋቅራዊ አሠራር ላይ ሳይቀር የሰላ ሂስ ይሰነዝሩ ነበር:: እነዚህ አስተያየቶች በወቅቱ ያመጡት ለውጥ ስለ መኖሩ ወይም ስላለመኖሩ ማረጋገጥ ቢያስቸግርም አስተያየቶቹ በነጻነት መስተናገዳቸው በራሱ በጠንካራ ጐንነቱ የሚጠቀስ ነው::

*ለ. ሁሉን ዓቀፍ የመሆን አዝማሚያ*

የፕሬስ ውጤቶቻችን ከመንፈሳዊ ትምህርትና ታሪክ በተጨማሪ በወቅታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አገራዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎችን አቅርበዋል:: በተለይም በግብርና፣ በጤናና በሴቶች ጉዳይ ያለማሰለስ ያቀረቧቸው ጽሑፎች አዘጋጆቹ ኅትመቶቻቸው በሁሉም ዜጋ እንዲነበቡ የማድረግ፣ ተልእኳቸውም ቤተ ክርስቲያናዊ ብቻ ሳይሆን አገራዊም እንዲሆን መፈለጋቸውን ያለ ጥርጥር የሚያሳይ ነው::

ኅትመቶቹ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልሳኖች እንደ መሆናቸው በመንፈሳዊው ጉዳይ ላይ ብቻ መወሰን ነበረባቸው የሚል አሳብ ሊሰነዘር ይችላል:: በዚህ ጥናት አቅራቢዎች እምነት በመርህ ደረጃ የተባለው ትክክል የሚሆንበት አጋጣሚ ቢኖርም በአገራችን ባለውና በነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ሌላው ጉዳይ/ ልማት፣ጤና፣ ሥነ ጾታ ..../ ባለቤት ስላለው እኛ ልንነካው አይገባም የሚባል አይደለም::

ከዚሁም ጋር አሁን አሁን ፈጽሞ በማይታይ ሁኔታ ለሌሎች እምነት ድርጅቶች /ካቶሊክና ፕሮቴስታንት/ ቀና አመለካከት የሚንጸባረቅባቸው ዘገባዎችና ጽሑፎች ይቀርቡ ነበር:: ይኼ በአመዛኙ በወቅቱ የቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች አጥብቀው ይደግፉት ከነበረው የኢኩሜኒካል እንቅስቃሴ /የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት/ ጋር የተያያዘ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያስቸግርም::

## *ሐ.ጊዜውን የመዋጀት ፍላጐት*
## */Dynamism/*

ይህ ነጥብ ቀደም ሲል ከተነሣው ጋር የተጣመረ ነው:: የኅትመት ውጤቶች ለየጊዜው የሚነሡ አገራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳዮችን ከቤተ ክርስቲያንና ከምእመናን ጋር በማያያዝ መረጃና ትንታኔዎችን ይሰጡ ነበር:: ለዚህ ጥናት በተደረገ ዳሰሳ



www.eotcmk.org

እንደ ታየው የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶች ሳይቀሩ በሃይማኖታዊ እይታ ተዘግበዋል፡፡ ዓለም አቀፋዊና አገራዊ ጉባኤያትን፣ በተለይም በሃይማኖት ዙሪያ የሚያጠነጥኑቱን በስፋት ይዘግቡ ነበር፡፡ ቀደም ባለው ነጥብ ላይ የሚሰነዘረው አስተያየት እዚህም ሊቀርብ ይችላል፡፡ ይሁንና ኅትመቶቹ በየወቅቱ የሚነሡ ጉዳዮችን ከቤተ ክርስቲያን አንጻር ሆኖ ለመከታተል መሞከራቸው የማንኛውም ሚዲያ ጠንካራ ጐን በመሆኑ አካሔዱ የሚተች አይመስለኝም፤ ባይሆን በአቀራረባቸው ላይ ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ፡፡

### መ. መንግሥትን መደገፍ

በወቅቱ የነበሩት ኅትመቶች አንዱ ዋነኛ ባሕርይ የነበረው መንግሥት ደጋፊዎች መሆናቸው ነው፡፡ ቤተ ክህነቱና ቤተ መንግሥቱ ከነበራቸው ጥብቅ ግንኙነት አኳያ ይኼ የሚጠበቅ ነው፡፡

### ሠ. ሞያዊና ተቋማዊ አቅም

በተቋም ደረጃ በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ስር ሲታተሙ የነበሩት ኅትመቶች ጠንካራ እንደ ነበሩ መረዳት ይቻላል፡፡ የራሳቸው ቢሮና አዘጋጆች ነበሩዋቸው፡ በርካታ የጽሑፍ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ /በነጻም በክፍያም/ ጸሐፊዎችም ነበሩ፡፡ ሌሎቹ ከዚህ ጋር ሲነጻጸር ደከም ያለ ተቋማዊ ጥንካሬ ነበራቸው፤ በካፒታልም በሰው ኃይልም፡፡

ሞያዊ ብቃትን በተመለከተ አብዛኞቹ /እንዲያውም ሁሉም ማለት ይቻላል/ ጸሐፊዎች በቂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የነበራቸው ናቸው፡፡ ይሁንና የጋዜጠኝነት ሞያን የተማሩት በጣም ጥቂቶቹ ብቻ እንደ ነበሩ በዚህ ጥናት ተጠቁሟል፡፡ / መምህር ካህሣይ ገብረ እግዚአብሔር፣ የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ም/ዋና አዘጋጅና የፈለገ ጥበብ መጽሔት ዋና አዘጋጅ፤ ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም፣ የልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት ዋና አዘጋጅ፤ መሪጌታ መንክር ዋሴ፣ በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያ ተልእኮ መምሪያ የሥርጭት ክፍል አባልና ጽሑፍ አቅራቢ የነበሩ፣ ቃለ መጠይቅ፣ ኅዳር 1996 ዓ.ም./፡፡

ይህም ቢሆን ግን በወቅቱ በመንግሥት ይታተሙ ከነበሩት ጋዜጦች ጋር ብዙም ልዩነት አልነበራቸውም፡፡ ልዩነቱ እየጐላ የመጣው እየቆየ መሆኑን ጋዜጦቹን በማስተያየት በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በተውጣጡ መምህራን ከስብከት ዘዴ ሥልጠና ጋር የጋዜጠኝነት ሞያ ትምህርት መሰጠቱን በወቅቱ የነበሩ ባለሞያዎች ገልጸዋል፡፡

ለማጠቃለል በዚህ ዘመን /1938-1966 ዓ.ም./ የወጡት የቤተ ክርስቲያኒቱ ጋዜጦችና መጽሔቶች በወቅቱ ከነበረው የአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ጥሩ ጅምሮች ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ በኅትመት ብዛትም ሆነ በዓይነት በቂ ነበሩ ማለት ባይቻልም ከነበረው የአንባቢ ብዛትና የሥራው ልምድ ጋር ሲተያይ ወቅቱ ለትልቅ ርእይና ሥራ መሠረት የተጣለበት ነበር፡፡ በዚህ በኩል የኅትመት ዝግጅቶቹን ሲመሩና በጽሑፍ እንዲሁም በመረጃ አስተዋፅዖ ሲሳተፉ የነበሩ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

### 2 .ከ1966 - 1983 ዓ.ም

ይህ ወቅት ቀደም ባለው ዘመን ማብብ ጀምሮ የነበረው የአገሪቱ የኅትመት ሚዲያ የታፈነበት ነበር፡፡ ከቤተ ክርስቲያንም አንጻር ፀረ ሃይማኖት መንግሥት ሥልጣን የያዘበትና ቤተ ክርስቲያኒቱ ፈርጀ ብዙ ፈተናዎችን የተጋፈጠችበት ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱ የፕሬስ ውጤቶች በአብዛኛው መቀጠል ችለው ነበር፡፡ ከአብዮቱ በፊት በቤተ ክርስቲያን ሲታተሙ የነበሩት ጋዜጦችና መጽሔቶች በዚህም ዘመን ሥራቸውን መቀጠላቸው እንዳለ ሆኖ ከኅትመት የወጡትም በአብዛኛው በውስጣዊ የቤተ ክርስቲያኒቱ የአስተዳዳር ውሳኔዎች ነው፡፡ /ቃለ መጠይቆች/፡፡

ለምሳሌ፡- «ትንሣኤ» መጽሔትና «ድምፀ ተዋሕዶ» ጋዜጣ እስከ 1975 ዓ.ም. በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ስር ሲሠሩ ቆይተው በዚህ ዓመት ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ስር በመምጣት እስከ 1984 ዓ.ም. ድረስ ዘልቀዋል፡፡ በ1986 ዓ.ም. አንድ ጋዜጣና አንድ መጽሔት ወደ ማዘጋጀት በማዘንበል በተሰጠው ውሳኔ «ትንሣኤ» እና «ማዕዶት» ተጣምረው «ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» በሚል ስያሜ፣ ከ«ድምፀ ተዋሕዶ» እና ከ«ዜና ቤተ ክርስቲያን» ደግሞ ዜና ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡

በዚህ ዘመን አዲስ ከተጀመሩት ኅትመቶች ዋነኛው «ማዕዶት» መጽሔት ነው፡፡ በዓመት አራት ጊዜ ይወጣ የነበረውና በመስከረም 1972 ዓ.ም. መታተም የጀመረው ይህ መጽሔት በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ይታተም ነበር፡፡ /መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ ፣ የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ፣ ቃለ መጠይቅ፣ 1996 ዓ.ም/፡፡ በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ስር ሲታተም ቆይቶ በ1986 ከትንሣኤ ጋር ተዳብሎ ስሙም ተቀይሯል፡፡ /«ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ» የተባለው «ማዕዶት» ራሱ ነው፣ የለም «ትንሣኤ» ነው የሚሉ የተለያዩ አስተያየቶች አሉ፡፡ /ቃለ መጠይቆች/፡፡

ይህ ዘመን እየተበራከቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ጋዜጦችና መጽሔቶች ዕድገታቸውን ገትተው ቁጥራቸው ወደ ሁለት / አንድ ጋዜጣ፣ አንድ መጽሔት / እንዲወሰን የሆነበት ነው፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የኤዲቶሪያል ነጻነትም በወቅቱ ከነበረው ርዕዮተ ዓለም አንጻር እንዲቃኝ ግድ ሆኗል፡፡ ለዚህም በጠቅላይ ቤተ ክህነት እና በማስታወቂያ ሚኒስቴር የተሰየሙ ሁለት የሳንሱር ኮሚቴዎች / የማስታወቂያ ሚኒስቴሩ ኮሚቴ የበላይ ነው/ ጽሑፎቹን እንዲገመግሙ ተደርጓል፡፡ ኅትመቶቹ ከቀድሞው በባሰ መልኩ የመንግሥት ደጋፊዎች በመሆን ቤተ ክርስቲያኒቱንና መሪዎቿን የሚዘልፉ ጽሑፎችንም ለማስተናገድ ተገደው ነበር፡፡ ይሁንና ቀደም ሲል የተጀመረው በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች / ጤና ፣ ልማት፣ ሴቶች ፣ ሥነ ጽሑፍ ወዘተ.../ ላይ የሚያተኩሩ ጽሑፎች ቀጥለው ነበር፡፡

የቀደመው ዘመን ኅትመቶች የእኅት አብያተ ክርስቲያናትንና የሌሎች እምነቶች ድርጅቶችን /በተለይ የካቶሊክ/ እንቅስቃሴ ያለ ጥላቻ መንፈስ ሲዘግቡ እንደ ቆዩት ሁሉ በዚህ ዘመን ደግሞ ለሶሻሊስት አገሮች አብያተ ክርስቲያናት /ሩሲያ፣ ሮማንያ፣ቡልጋሪያ.../ የተለየ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ይህም በአንድ በኩል የኤዲቶሪያል ነጻነቱን መገፈፍ ሲያሳይ በሌላ ገጹ ግን የሌሎችን የእምነት ድርጅቶች እንቅስቃሴ የመዘገቡ አቅጣጫ መቀጠሉን ያሳያል፡፡ በሞያዊና በተቋማዊ አቅም አንጻር የነበረው ጠንካራ ጐን እየሳሳ የሔደበት ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

የዚህ ዘመን የኅትመት ውጤቶች ከወቅቱ የመንግሥት ርዕዮተ ዓለም አንጻር ከመቃኘታቸው በስተቀር ከሞላ ጐደል በመጀመሪያው ዘመን /1938-1966 ዓ.ም./ የታዩትን አምስት መገለጫዎች/ሀ-ሠ/ እንደ ያዙ ቆይተዋል፡፡

### 3. ከ1983 - እስከ አሁን

በ1983 ዓ.ም የተደረገው የመንግሥት ለውጥ በአገሪቱ ካስከተላቸው መሠረታዊ ለውጦች አንዱ የፕሬስ ነጻነት በሕግ መረጋገጡ (ዐዋጅ ቁጥር 34/1985 ዓ.ም፣ ስለ ፕሬስ ነጻነት የወጣ ዐዋጅ) ነው፡፡ ይህ ለውጥ በአገሪቱ የነጻ ፕሬስ እንደ ገና እንዲያንሰራራ ከማድረጉ ጋር ቤተ ክርስቲያንንም ሳይነካ አላለፈም፡፡

በቤተ ክርስቲያኒቱ በኩል ቀድመው የነበሩት ኅትመቶች ከመቀጠላቸው በተጨማሪ «ፈለገ ጥበብ» የተሰኘው መጽሔት በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ስር ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ መታተም ጀምሯል፡፡ (መጽሔቱ በ1969 ዓ.ም አንድ ጊዜ ታትሞ ቆሞ የነበረ ነው፡፡) ከፕሬስ ነጻነቱ ጋር በተያያዘ በየአድባራቱ ለጥቂት ጊዜ ታትመው የቀሩትን ትተን በሁለት ሰንበት ት/ቤቶች በዓመት አራት ጊዜ የሚወጡ ሁለት መጽሔቶችን (ኤፍራታ እና ቢታንያ) ለማንበብ በቅተናል፡፡ ሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ፣ እንዲሁም መለከትና አኮቴት መጽሔቶችም የዚሁ ዘመን ውጤቶች ናቸው፡፡

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በነበሩት ዓመታት በግለሰቦች (በድርጅቶች) አሳታሚነት ለንባብ የበቁ ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱ የሃይማኖት ጋዜጦች መኖራቸው ወቅቱን ከቀዳሚዎቹ ሁለት ዘመናት ይለየዋል፡፡ ከዐዋጁ ጋር በተያያዘም ሁሉም የኅትመት ውጤቶች ከመንግሥት ቀጥተኛ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው ለመንቀሳቀስ ችለዋል፡፡ የዚህን ዘመን አጠቃላይ ገጽታዎች፣ ድክመትና ጥንካሬዎች ይወክላሉ በሚል በጥናቱ የተዳሰሱትን ጋዜጦችና መጽሔቶችን በዚህ ክፍል እንቃኛለን፡፡

ባለፉት 12 ዓመታት በቋሚነት መውጣት ጀምረው ከተቋረጡት ጋዜጦች በተጨማሪ በየአጥቢያዎቹና በየሰንበት ት/ቤቶች አማካይነት፣እንዲሁም ከሕንፃ ማሠራት ወይም ጥገና ጋር በተያያዘ በርካታ መጽሔቶች ወጥተዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ሦስተኛውን ዘመን (1983 ዓ.ም ወዲህ ያለውን) ከቀደሙት የተለየ ቢያደርገውም ኅትመቶቹ ቀጣይ ባለመሆናቸው የዚህ ዳሰሳ አካል አልተደረጉም፡፡ ከቀደሙት ሁለት ዘመናት በተለየ የዚህን ወቅት ኅትመቶች አጠቃላይ መስያ (አቅጣጫ) ለማንሣት የተፈለገው ድክመቶቹንም እግረ መንገድ ለመጠቆምና ለመማማር በማሰብ ነው፡፡

ለዚህ ዳሰሳ በማሳያነት የተመረጡት ስድስት ኅትመቶች (ሦስት ጋዜጦች ፣ ሦስት መጽሔቶች) የሚከተሉት ናቸው፤

1. ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ፡- በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ፣ ኅዳር 1938 ዓ.ም የተጀመረ፣ ወርኃዊ ጋዜጣ፣ ባለ 12 ገጽ

2. ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ፡- በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል፣ ጳጉሜን 1985 ዓ.ም የተጀመረ፣ ወርኃዊ ጋዜጣ፣ ባለ 16 ገጽ

3. ቢታንያ ጋዜጣ፡- በጎፋ መካነ


www.eotcmk.org

ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሰንበት ት/ቤት፣ሐምሌ 1994 ዓ.ም የተጀመረ፣ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚወጣ (በየ4 ወሩ)፣ ባለ 8 ገጽ

4. ፈለገ ጥበብ መጽሔት:- በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ፣ በ1991 ዓ.ም የተጀመረ፣ በየሦስት ወሩ የሚታተም መጽሔት፣ ባለ 32 ገጽ

5. ሐመር መጽሔት:- በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል፣ በ1985 ዓ.ም ጥር ወር የተጀመረ፣ በየሁለት ወሩ የሚወጣ ባለ 40 ገጽ

6. መለከት መጽሔት:- በዋኖስ የኅትመትና ማስታወቂያ ድርጅት (የግል)፣ ኅዳር 1985 ዓ.ም የተጀመረ፣ ወርኃዊ መጽሔት፣ ባለ 32 ገጽ

የእነዚህን ስድስት ኅትመቶች ዝርዝር ሁኔታ መመዘን የዚህ ዳሰሳ ዓላማ ባለመሆኑ አጠቃላይ አቅጣጫውን ከሚያመለክቱ መመዘኛዎች አኳያ በአጭሩ እንደሚከተለው ልንቃኛቸው እንችላለን::

## 1.ጋዜጦች

በመላው ዓለም በተለመደው አሠራር ጋዜጣ የሚባለው በዋነኛነት ዜናዎችን የያዘና በየዕለቱ ቢዘገይ በየሳምንቱ የሚወጣ ኅትመት ነው:: ይህን ትርጓሜ በቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች ላይ እንከተለው ብንል ከጋዜጣነት ምድብ መውጣታቸው አይቀርም:: ይሁንና ለዚህ ዳሰሳ ዓላማ ትርጓሜውን በማስተካከል በጋዜጣነት ተወስደዋል::

የጋዜጣ ዋነኛ መለያ ዜና እንደመሆኑ ሦስቱም ጋዜጦች ዜናዎችን ይዘው ይቀር ባሉ:: የዜናዎቻቸው አመራረጥ ግን በእጅጉ የተለያየ ነው:: «ዜና ቤተ ክርስቲያን» የሚያቀርባቸው ዜናዎች በአብዛኛው ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው:: ይህንን ድምዳሜ የሚያጠናክረው ደግሞ ከዚህ ውጭ ያሉት «ዜናዎች» በአብዛኛው የሚቀርቡት በዜና ሐተታ መልክ መሆኑ ነው:: በጋዜጣው ትምህርትና ስብከቶች ቢቀርቡም የሚሰጣቸው ቦታ በአንጻራዊነት አነስተኛ ነው:: በርግጥ ከጋዜጣ ዜናን በዋነኛነት የማቅረብ ዓላማ አንጻር ለዜና ዘገባዎች ትኩረት መስጠቱ የሚያስመሰግን ነው::

ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በቤተ ክርስቲያን የኅትመት ሚዲያዎች ታሪክም ትልቅ ሥፍራ እንደ ሚይዝ አያጠራጥርም:: ዜና ቤተ ክርስቲያን በረጅም ታሪኩ በርካታ ዓምዶችን በመክፈት የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች በስፋት ሲያስተናግድ ቆይቷል:: ጋዜጣው ተነባቢነትን ያገኘበት አንዱ ምክንያትም ይኼ ነው ማለት ይቻላል:: ይሁንና አሁን ጋዜጣው የሚያስተናግዳቸው ዓምዶች በጣም ጥቂት ሆነዋል:: ጋዜጣው የአህጉረ ስብከት እንቅስቃሴዎችን፣ እንዲሁም የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን ወቅታዊ ሁኔታ መዘገቡ በጠንካራ ጐንነት ሊጠቀስ የሚገባው ነው::

የጋዜጣው የዜና አመራረጥ አቅጣጫ በአብዛኛው ከቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች እና አስተዳዳሪዎች እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል:: ይሁንና ሌሎች ዓምዶች አንሰዋል ማለት ይቻል ይሆናል እንጂ ይህ የዜና አቀራረብ አቅጣጫ የተለመደ መሆኑን ማስታወስ ይገባል:: በተለይ በውጭው ዓለም የትልልቅ ተቋማት፣ የክልል መንግሥታትና የከተማ ማዘጋጃ ቤት ልሳን /Muncipal Newspapers/ የሆኑ ጋዜጦች ዜናዎቻቸውን በዋነኛነት የሚዘግቡት ከመሪዎቻቸው ጉዞ ጋር እያይዘው ነው:: ስለዚህም የዜና ቤተ ክርስቲያን የዜና አመራረጥ አቅ ጣጫ የሚነቀፍ አይሆንም::

«ስምዐ ጽድቅ» ጋዜጣ የተሻለ የዜና አቀራረብም ሆነ ሽፋን አለው ማለት ይቻላል፤ በአህጉረ ስብከቶችም በባሕር ማዶም:: ቋሚ የዜና ገጾችን ሰጥቶ መሥራቱም የሚጠቀስ ጥንካሬ ነው:: በውስጥ ገጾች ይዘትም ቢሆን ከተቀሩት ጋዜጦችም ሆነ መጽሔቶች በተለየ መልኩ ምእመናን አሳባቸውን እንዲገልጹ የሚያስችሉ ሁለት ዓምዶችን በመክፈቱ የተለየ አቅጣጫ የተከተለ ይመስላል:: በየወቅቱ አከራካሪ/አወያይ ሊባሉ የሚችሉ ዘገባዎችንና አስተያየቶችን በማቅረብም ጋዜጣው የተሻለ አቋም አለው:: ቋሚ የትምህርት/ ስብከት እና አበውን ከማስተዋወቁ አኳያ የተሻለ አቀራረብ አለው::

«ቢታንያ» ጋዜጣን ስንመለከት ገና ጀማሪ እንደ መሆኑ የዓምዶቹ ብዛት ጥቂት ነው:: ቢሆንም በአጥቢያ እንደሚዘጋጅ ጋዜጣ ሳይሆን ዜናዎችን ለማቅረብ ይሞክራል:: ቋሚ የትምህርት /የስብከት ገጾችም አሉት:: «ቢታንያ» ከሌሎቹ ኅትመቶች በተለየ ሁኔታ የተለያዩ የንግድ ማስታወቂያዎች ማስተናገዱ ከሌሎቹ ይለየዋል:: ጋዜጣው በትርፍ ጊዜ አገልጋዮች በአጥቢያ ደረጃ የሚዘጋጅ እንደ መሆኑም ጥሩ ጅምር ነው ለማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ የጋዜጦቹን ይዘት ስንገመግም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ስፋትና እንቅስቃሴ አኳያ በሚፈለገው የጊዜ ርቀት በቂ ዜናዎችን እያቀረቡ ነው ለማለት አያስደፍርም:: ምእመናን ስለ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ለማወቅ ካላቸው ፍላጎትና ዜና በመረጃ ምንጭነቱ ከሚሰጠው ጥቅም አንጻር ከብዛትም ከሽፋንም አኳያ ብዙ ሊሠራበት የሚገባ ይመስለናል:: ከዚህም ሌላ በስምዐ ጽድቅ የተጀመረው የምእመናንን አሳብ የማቅረብ ሁኔታ በሌሎችም መቀጠል ይኖርበታል::

## 2. መጽሔቶች

መጽሔቶች ከጋዜጦች በተለየ ስፋትና ጠለቅ ላሉ ትንታኔዎች (ትምህርቶችና አስተያየቶች) የበለጠ ትኩረት መስጠት እንዳለባቸው ይታመናል:: በአንድ ጉዳይ ላይ ሰፊ (በአንጻራዊ እይታ) ትንታኔና አሳቦችን ለማስተናገድም መጽሔቶች የተሻሉ አማራጮች ናቸው::

«ፈለገ ጥበብ» መጽሔት የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራው ሃይማኖትንና ታሪክን ለወጣቶች በማስተማር ላይ ነው:: ስለዚህም ከዚህ ውጭ ላሉት ማኅበራዊ ጉዳዮች የሚሰጠው ቦታ በጣም አነስተኛ ነው::

«ሐመር» መጽሔትም በተመሳሳይ ሁኔታ ለትምህርተ ሃይማኖትና ለታሪክ (ቅዱሳት መካናትና ቅዱሳን ሰዎች) የበለጠ ትኩረት ቢሰጥም ማኅበራዊ ጉዳዮችንም በቋሚነት ያስተናግዳል:: ከወቅታዊ ጉዳዮች ጋር በተያየዘ የተለያዩ ጥናት ነክ ጽሑፎችን ማቅረቡም ሊጠቀስ ይገባዋል::

«መለከት» መጽሔት በቅርብ ጊዜ ካደረጋቸው ለውጦች በተጨማሪ ሙሉ በሙሉ በዶግማና በቀኖና እንዲሁም በክርስቲያናዊ ትውፊት /ታሪክ/ ትምህርት ላይ ያተኮረ ሆኖ ቆይቷል:: መጽሔቱ በተቋቋመበት ጊዜ ከነበረው ችግር አኳያም ይመስላል በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አንባብያንን ከመናፍቃን ቅሰጣ የመጠበቅ አካሔድ ጎልቶ ይታያል:: ለዚህም ይመስላል የሚቀርቡት ጽሑፎች በቋንቋም ሆነ በአሳብ ጠጣር ያሉት::

### ለ. ሥርጭት

በሥርጭት ሽፋን አኳያ ሁሉም ቋሚ የቤተ ክርስቲያኒቱ የኅትመት ውጤቶች በአዲስ አበባ የሚዘጋጁና ሥርጭታቸውም በጣም አነስተኛ መሆኑ ይታያል::

እነዚህን በማሳያነት ያነሣናቸውን ጋዜጦችና መጽሔቶች የኅትመት ብዛት በምሳሌነት ብንወስድ:-

ዜና ቤተ ክርስቲያን 5,000(በወር)፣ ስምዐ ጽድቅ ከ13,000-14,000 (በየወሩ )፣ ቢታንያ ከ2,000-5,000 /በ4 ወር/፣ ፈለገ ጥበብ ከ5,000–12,000 /በየ3 ወሩ/፣ ሐመር ከ30,000-35,000 (በ2 ወር) እና መለከት ከ3,000-10,000 ገደማ (በወር) ነው:: ከፍተኛዎቹን የኅትመት ብዛቶች ወስደን ብንደምረው የምናገኘው ቁጥር 81,000 ገደማ ነው:: ለዚያውም በወርም በአራት ወርም የሚታተሙትን አብረን ደምረን ነው:: በዚህ ንጽጽር ያልተካተቱት የኅትመት ውጤቶቻችንን ታሳቢ ተደርገው በድምሩ 20,000 ድረስ ይታተማሉ ብንል አጠቃላይ ድምሩ በወር 100,000 ይሆናል:: ይህን ቁጥር በ40 ሚልዮን ለሚገመቱት የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ማካፈሉን ትተን በአዲስ አበባ ብቻ ላሉት ምእመናን ለማዳረስ ብንሞክር እንኳ በጣም አነስተኛ ነው::

በማሠራጫ መንገድ በኩልም ሰንበት ት/ቤቶች፣ ሰበካ ጉባኤያትና አህጉረ ስብከት ጥሩ መንገዶች ሊሆኑ ቢችሉም በሚገባ ጥቅም ላይ አልዋሉም:: እነዚህን ተቋማት በተሻለ መልኩ በማሠራጫነት የመጠቀም ሒደት የሚታየው በዜና ቤተ ክርስቲያን እና በልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት በኩል ቢሆንም አሠራሩ በኮታ ከመስጠት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ብዙ ለውጥ ማምጣቱ አልታየም:: ሐመርና ስምዐ ጽድቅ በማኅበረ ቅዱሳን ንዑሳን ማዕከላት ባሉዋቸው ማከፋፈያዎች አማካይነት የተሻለ የሥርጭት ዕድል አግኝተዋል:: መለከት መጽሔትም በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ማከፋፈያዎች፣ የንዑሳንና የወረዳ ማዕከላት ይጠቀማል::

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ያሉትን የቤተ ክርስቲያን ኅትመቶች በጋራ የሚንጸባረቅባቸውን ገጽታ በሚከተሉት ነጥቦች አኳያ አጠቃሎ ማስቀመጥ ይቻላል:: እነዚህ ነጥቦች ከቀደሙት ሁለት ዘመናት ሁነኛ ባሕርያት ጋር ሊነጻጸሩ የሚችሉ ናቸው::

### ሀ. የኤዲቶሪያል ነጻነት

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ያለው አጠቃላይ የአገሪቱ ሁኔታ የኅትመት ውጤቶቹን በሙሉ ከማንኛውም መንግሥታዊ ኤዲቶሪያል ጫና ነጻ አድርጓቸዋል:: ይሁንና አሁን ለንባብ የሚበቁት የቤተ ክርስቲያኒቱ ኅትመቶች በአብዛኛው በራሳቸው ላይ የጫኑት የኤዲቶሪያል ገደብ እንዳለ በቀላሉ ማየት ይቻላል:: ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ላይ ችግሮች መኖራቸውን ቢያውቁም ሞያዊ ሂስ የመሰንዘር ድፍረት ያገኙባቸው አጋጣሚዎች በጣም ጥቂት ናቸው:: በመጀመሪያው ዘመን (1938-1966 ዓ.ም) የነበሩት ኅትመቶች አሁን ከሚታየው በተሻለ መልኩ በየደረጃው የሚታዩ የአሠራርና የአስተዳደር ግድፈቶች እንዲታረሙ ምእመናን አሳባቸውን እንዲሰጡ ያበረታቱ ነበር:: በአሁኖቹ ኅትመቶች በዚህ ዙሪያ አስተያየት ቢሰጥ እንኳ የሚስተናገዱት እንደ ጋዜጣና መጽሔት አሠራር በቀጥታ ሳይሆን ከስብከት ባልተለየና መልእክቱን በሚያደበዝዝ መንገድ ነው:: የመስተናገድ ዕድል የሚያገኙ የአንባብያን አሳቦችም በአብዛኛው ስብከትና ትምህርት አሊያም ባለቤት የሌላቸው÷ «መደረግ አለበት» የሚሉ ምክር መሰል መልእክቶች





www.eotcmk.org

ብቻ ሆኖ ይታያል፡፡

ይህ በራስ ላይ የተጣለ ሳንሱር /Self censorship/ የአሁኖቹ ኅትመቶች በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ላሉ ችግሮች ዋነኛው ተጠያቂ ጥፋተኛ ምእመኑ የሆነ የሚያስመስል አቅጣጫ እንዲከተሉ አስገድዷቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ማንኛውም ኅትመት የራሱ የኤዲቶሪያል ፖሊሲ በማዘጋጀት አቅጣጫውን ከመወሰኑ አሠራር ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ በእርግጠኝነት ማቅረብ ያስቸግራል፡፡ ይህ አስተያየት በጣም አልፎ አልፎ የታዩትን የኤዲቶሪያል ነጻነትን የሚያንጸባርቁ ርእሰ አንቀጾችንና ጽሑፎችን የሚመለከት አይደለም፡፡

## ለ. በትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነት፣ የቅዱሳን መካናትና ሰዎች ታሪክ ላይ ማተኮር

በንባብ ላይ የሚገኙት ኅትመቶች አብዛኛውን ገጾቻቸውን የሰጡት ለሃይማኖትና ለታሪክ ትምህርቶች ነው፡፡ ለማኅበራዊ ችግሮች ቦታ በመስጠት የሚያስተናግዱ ቢሆንም የሚሰጡት ሽፋን እጅግ አነስተኛ ሆኖ ይታያል፡፡ ከማኅበራዊ ጉዳዮች ባለፈ ቤተ ክርስቲያኒቱና አገሪቱ ከሚጋሩዋቸው ችግሮች አኳያ ለአገራዊ ጉዳዮች የሰጡት ቦታም ኢምንት ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡ ይልቁንም በአትኩሮት ለሚመዝናቸው አገራዊ ጉዳዮች አያገቡንም የሚል አቋም እንደ ያዙ ያስገምታል፡፡ ይህንን ከመጀመሪያው ዘመን ጋር ስናነጻጽርም ሰፊ የአቅጣጫ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ምናልባትም የሁለቱ ዘመናት ኅትመቶች ሁለት ጽንፈኛ ዳር ሳይዙ አልቀሩም፡፡ የመጀመሪያዎቹ ዋነኛ ኃላፊነታቸው ከሆነው ሃይማኖታዊ ትምህርት ባልተናነሰ ለማኅበራዊና ለአገራዊ ጉዳዮች ትኩረት ሲሰጡ፣ የአሁኖቹ ደግሞ ጠቅላላውን በሃይማኖት ትምህርት ላይ ብቻ በማተኮር ማኅበራዊ ጉዳዮችን ችላ ብለዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ሊነሣ የሚገባው ሌላው ነጥብ የአሁኖቹ ኅትመቶች ስለ ሌሎች የእምነት ድርጅቶች (ካቶሊክና ፕሮቴስታንት) ጠንካራ ጥላቻን የሚያንጸባርቁ መሆናቸው ነው፡፡ ስለ እኅት አብያተ ክርስቲያናትም የሚዘገበው በጣም ጥቂት ነው፡፡ ይህም በጣም እየቀዘቀዘ ከመጣው የኢኩሜኒዝም አመለካከት ጋር በአንድ በኩል፤ ሌሎች የእምነት ድርጅቶች ምእመናንን እየሰበኩ ለመውሰድ ከመጣደፋቸው አኳያ ለዚሁ ቀድሞ ትምህርት መስጠት የግድ ማስፈለጉ በሌላ ወገን በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የእኅት አብያተ ክርስቲያናቱ ግንኙነት መቀዝቀዙም በራሱ ለዚህ አስተዋፅዖ ሳያደርግ አይቀርም፡፡

### ሐ. ጊዜውን የመዋጀት ፍላጎት

ይኼ ካለፈው ነጥብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ ከአሁኖቹ ኅትመቶች አንዳንዶቹ በየጊዜው ከሚነሡት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አንዳንዴም ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አኳያ ምእመናን ወቅታዊና ተገቢ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ሲሞክሩ ይታያሉ (ለምሳሌ፡- ኤች.አይ ቪ/ኤድስ፣ ተዝካር፣ የሥራ ባሕል፣ ድህነት ቅነሳ፣ የበዓላት አከባበር…)፡፡ በአጠቃላይ ስናየው ግን በሃይማኖታዊና ታሪካዊ ጉዳዮች መዋጣቸው ለአዳዲስ ችግሮች አዳዲስ መፍትሔዎችን እንዳያፈላልጉ፣ ምእመናንን እንዳያወያዩ አድርጓቸዋል፡፡ በርግጥ ይኼ ቀደም ሲል ከተነሣው የኤዲቶሪያል ነጻነትም ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

ከዚህ ላይ ግን ወቅታዊ ጉዳዮችን ከክርስቲያኖች አኗኗርና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር አያይዞ ማቅረብን የመን ፈሳዊነት እጦት አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ መኖሩ ለዚህ አስተዋፅዖ ማድረጉን ማስታወስ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ግን ኅትመቶቻችን የአንባቢዎቻቸውን ፍጥነት በሚመጥን መልኩ ወደፊት እየተራመዱ ነው ማለት አይቻልም፡፡ በዚህም የተነሣ በአብዛኛውም በጣም ተነባቢ የሚሆኑት በአዲስ አንባብያን አካባቢ መሆኑን መናገር ይቻላል፡፡ የኅትመት ሚዲያዎች አንባቢዎቻቸውን የሚይዙበት ዋናው መሣሪያ የሚያነሡት ጭብጥ ወቅታዊነትና ጥልቀት ከመሆኑ አኳያ ኅትመቶቹ ተገቢ ትኩረት ሊሰጡበት ይገባል፡፡

### መ. ሞያዊና ተቋማዊ አቅም

በሞያ በኩል አሁን ባሉት ኅትመቶቻችን ዘንድ በአንድ በኩል በቂ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ያላቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተሻለ ሞያዊ ብቃት የያዙ ጋዜጠኞች አሉ፡፡ ብዙዎቹ በሁለት አዘጋጆች ብቻ የሚሠሩ ናቸው፡፡

በተቋም ደረጃም በጣም ደካማ ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡ በአደረጃጀታቸውም ሆነ በሚሰጡት ክፍያም ገና ናቸው፡፡ በቂ የሰው ኃይልም የላቸውም፡፡ ከውጭ እየከፈሉ ለማጻፍም አቅማቸው አይፈቅድላቸውም፡፡ ምናልባትም የመጀመሪያው ዘመን ኅትመቶች ከአሁኑ የተሻለ አስተዳደራዊ ድጋፍ ነበራቸው፤ ስለዚህም በወቅቱ መመዘኛ የተሻለ አቋም ነበራቸው ማለት ይቻላል፡፡

## የይሁንታ ሐሳቦች

### 1. ኅትመቶች በአህጉረ ስብከት ደረጃ በተለያዩ ቋንቋዎች ቢዘጋጁ

አሁን ያሉት ኅትመቶች በቁጥር በጣም አነስተኛ መሆናቸውን፣ በቋንቋም በአማርኛ ብቻ እንደሚጻፉ ቀደም ሲል ጠቁመናል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት አንዱ አማራጭ እያንዳንዱ አገረ ስብከት ቢያንስ አንድ ቋሚ ኅትመት (ጋዜጣ/መጽሔት) እንዲኖረው ማድረግ ነው፡፡ ይኽ ከምእመናን ብዛት አኳያ ጥሩ መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለያዩ ቋንቋዎች የሚጻፉ ኅትመቶችን ለማዘጋጀትም የቋንቋው ተናጋሪዎች በብዛት ካሉበት አህጉረ ስብከት የተሻለ አካል አይኖርም፡፡ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አሳታሚነት የተጀመረው «ኖኅተ ጥበብ» ጋዜጣ ለዚህ መልካም አርአያ ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

በቋንቋ በኩልም በሌሎች የአገራችን ቋንቋዎችና ቢያንስ በእንግሊዝኛ የሚታተሙ ኅትመቶች መኖር የግድ አስፈላጊ መሆኑን እንደገና ማጤንና ተግባራዊ ርምጃ መወሰድ ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም በጥናት መደገፍ ይገባል፡፡

### 2. ሞያዊ ሥልጠናዎች

በኅትመቶች አካባቢ ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ለማቃለል በሁለት አቅጣጫ ሥልጠና ያስፈልጋል፡፡ በቂ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ላላቸው የጋዜጠኝነት ሥልጠና፣ የጋዜጠኝነት ዕውቀት ላላቸው ደግሞ ለኅትመት ሥራው የሚያግዝ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሥልጠና በተከታታይ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህም በተለይ አሁን በኅትመቶቹ ላይ ጎልቶ የሚታየውን የጋዜጠኝነት ሞያ ጉድለት ይፈታል፡፡ በዚህ በኩል በማኅበረ ቅዱሳን ኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል የተጀመረው ሥልጠና እያደገና እየሰፋ መሔድ ይገባዋል፡፡ ይህም የቤተ ክርስቲያናችን ኅትመቶች እየተደጋገፉና እየተመጋገቡ እንዲያድጉ አንድ መነሻ ሊሆን ይችላል ብለን እናምናለን፡፡

### 3. የምእመናን ተሳትፎ

እስካሁን በቆየው አሠራር ምእመናን የኅትመቶቹ አንባቢ ብቻ ሆነው ቆይተዋል፡፡ ይኽ ደግሞ በዚህ ተወስኖ መቀጠል አይኖርበትም፡፡ ምእመናን በዝግጅትም ሆነ በባለቤትነት በኅትመቶቹ እንቅስቃሴ መሳተፍ አለባቸው፡፡ ለዚህም ያሉትን በገንዘብ በመደጎምም ሆነ በዕውቀት /በየሞያቸው ዘርፍ/ አስተዋፅዖ በማድረግ ምእመናን ወደ ኅትመቶቹ ቀጥተኛ ባለቤትነት የሚሸጋገሩበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ ኅትመቶቹ የምእመናንንም ድምፅ እንዲያንጸባርቁ ማድረግ ለዚህ ቀዳሚው ርምጃ ይመስለናል፡፡ ይህም ማለት በአንድ አቅጣጫ ብቻ ይፈስ የነበረው መልእክትና መረጃ ወደ ሁለት ማደግ ይኖርበታል ማለታችን ነው፡፡

### ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያናችን ካላት የዕውቀትና ታሪክ ሀብት እንዲሁም ከልጆቿ ብዛትና አቅም አንጻር አሁን ካሉት በብዛትም ሆነ በጥራት የበለጡ የኅትመት ውጤቶች ያስፈልጓታል፡፡ በሦስቱም ዘመናት ለማየት እንደ ሞከርነው ኅትመቶቹ በጣም ጠቃሚ ሚና ተጫውተዋል፡፡ አሁን ያሉትን በተለየ ስንመለከታቸውም ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያውቁ በማድረግ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ በትምህርትም በሰው ኃይልም አንዳች የሌላት የሚመስላቸውንም እውነታውን እንዲረዱት በማድረግ ታሪክ የማይረሳው ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ይሁንና በማንኛውም መመዘኛ ኅትመቶቹ በቂ ናቸው ማለት፣ የተሟሉ ነበሩ ማለትም አይቻልም፡፡

የቤተ ክርስቲያኒቱ የኅትመት ውጤቶች ባለፉት 50 እና 60 ዓመታት እያደጉ የመጡበት ገጽታ እንዳለ ሁሉ የጫጨበት ሁኔታም አልታጣም፡፡ ካለፈውም ሆነ አሁን ካለው ተሞክሮ በመማር የተሻለ ለመሥራት ማቀድ ደግሞ ከሁሉም በላይ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና በዚሁ ሥራ ላይ የተሠማሩ አሳታሚዎችና ባለሞያዎች ኃላፊነት ነው፡፡

በዚህ አጭር ዳሰሳ ለማየት እንደ ተቻለውም የቤተ ክርስቲያኒቱ የኅትመት ውጤቶች ከሌሎች የአገራችን የኅትመት ውጤቶች አኳያ እንኳን ብዙ ርቀት መሔድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ አሁን እንደ ተደረገው ሁሉ ኅትመቶቹን በጋራ በመገምገም አቅጣጫና ስልት በማስቀመጥ ተቀራርቦ መሥራት የሚመረጥ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው የዚህ ጥናት ማጠቃለያ ዐረፍተ ነገር የኅትመት ውጤቶቹ አሳታሚዎችና አዘጋጆች ተቀራርበው እንዲሠሩ፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ አቅጣጫ እንዲከተሉ፣ ተደጋጋሚ ሥራ ከመሥራት ይልቅ ተመካክረው እንዲሠማሩ ጥሪ የሚያደርገው፡፡ ይህ ከሆነ በምንገኝበት የመረጃ ዘመን በብዙ የአፍሪካ አገሮች እንደታየው ሁሉ የተሻለች አገርና የነቃ ዜጋ ለመመሥረት በሚደረገው ጥረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የኅትመት ውጤቶች የቀዳሚነቱን ሚና ሊወስዱ እንደሚችሉ ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡

### ስምዐት

Shimelis, Bonsa.2000. Survey of The Private Press in Ethiopia. Forum For Social Sutdies-Monograph series 1, Addis Ababa, Image printing press.

Pankhurst, Richard. 1962. "The Foundation of Education, Printing, Newspapers, Book production, Libraries and Literacy in Ethiopia."
In Ethiopian Observer. Addis Ababa: Vol.6,No. 3.

### ቃለ መጠይቆች

ክንፈ ገብርኤል አልታዬ /ሊቀ ካህናት/፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አባል

ነቅዓ ጥበብ ወንድም /ሊቀ ልሳናት/፣ የልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት ዋና አዘጋጅ

ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ /መጋቤ ምሥጢር/፣ የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

ካህሣይ ገብረ እግዚአብሔር፣ የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ም/ዋና አዘጋጅና የፈለገ ጥበብ መጽሔት ዋና አዘጋጅ

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ /መጋቤ ብሉይ/፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ አባል

መንክር ዋሴ /መሪ ጌታ/፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የኅትመት ሥርጭት ክፍል ባልደረባ እንዲሁም ጽሑፍ አቅራቢ የነበሩ

### መዛግብት

ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ /ሊቀ ካህናት/፣ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ኃላፊ፣ ለ22ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የቀረበ ሪፖርት፣ 1996 ዓ.ም. ✦



www.eotcmk.org

## «ጥናቱ ለቀጣይ እንቅስቃሴያችን ጥሩ መሠረት ነው»

የጥናት አቅራቢዎቹ አዘጋጅተው ስላቀረቡልን ጥናት አመሰግናለሁ:: ብዙ ነገሮችን ሰምተናል። ብዙዎቻችን የማናውቃቸውን ነጥቦች ተምረናል:: አገልግሎታቸው በምን መልኩ እንደ ነበረ፣ በጥንካሬ በድክመት የተጓዙባቸውን ሒደቶች አስተምረውናል:: አሁን እየተዘነጋ የመጣው የኅትመቶቻችን ማኅበራዊ አገልግሎት እንዴት እንደ ነበረ ነግረውናል:: በዚህም ጤናን፣ ልማትን፣ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት ላይ ባልተመሠረተ ሁኔታ አላግባብ የምትወቀስበትን ሥርዓተ ጾታን፣ የኤዲቶሪያል ነጻነታቸውንና የሴቶች ጉዳይን አካትተዋል:: ካለን የምእመናን ብዛት አኳያ የኅትመቶቻችን ዓይነትና ሥርጭት ብዙ እንደሚቀራቸውም አሳስበውናል:: ይህ በርግጥ የቤተ ክርስቲያናችን ትልቁ ችግር ነው:: ሞያዊና ተቋማዊ ብቃታችንን አሳድገን በአህጉረ ስብከቶቻችን ደረጃ በሚገኙት መዋቅሮቻችን ኅትመቶቻችን በተለያዩ ቋንቋዎች መዘጋጀት እንዳለባቸው ተምረናል:: እንግዲህ የኅደለውን ሞልተን ጥናቱን ማጠናከር፣ ሒሱን ተቀብለን ድክመታችንን ማረም የእኛ የአባቶች ድርሻ ነው:: ወጣቶችም በበኩላችሁ ማወቅ የምትፈልጉትን በግልጽ መጠየቅ ይገባችኋል:: በአጠቃላይ የቀረበልን ጥናት ለቀጣይ እንቅስቃሴያችን ጥሩ መሠረት ነው::

*/ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ ኃላፊ/*

## «ጥናቱ ለጥናት የሚጋብዝ ነው»

ከምንም ተነሥቶ አንዳንድ ሰዎችን በቃል አነጋግሮ፣ ሰነድ ሳያገኝ በማቅረቡ የሚመሰገን ጥናት ነው:: በእውነት ባለፈው በጋዜጦችም ሆነ በመጽሔቶች የተሰጡት አገልግሎቶች ወይም የገጠሙት ችግሮች የጥናት መነሻ ነው የምለው:: ልጆች አባቶቻቸውን ይጠቁማሉ:: ምን እንደ ጐደለን ነግረውናል:: ወደፊት ሰፊ ዐውደ ጥናት ያስፈልገዋል:: ጥናቱ ብዙዎችን አካተተ አላካተተ የሚለውን ትተን ጥናቱ ለጥናት የሚጋብዝ ነው ብዬ ነው የምወስደው:: ብዙ ዕድሎች አሉን በሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ:: አሁን ይኸ ጥናት በመጨረሻ ሦስት ጥያቄዎችን አቅርቦልናል:: ከእነዚህ ተነሥተን በእነዚያ ላይ አዳብረን ለጥናት ብናቀርባቸው:: ጐደለ በሚባለው ላይ ወደፊት ስብከተ ወንጌል አስቦበት የሚቀናጁ ድርጅቶችም እንዳሉ ከሰበካ ጉባኤ መምሪያ፣ ከሰንበት ት/ቤቶችም ጋር ይቀናጅ እንደ ሆን አብረው ከሠሩት ጋር ተቀናጅቶ ሰፊ ጥናት እንዲቀርብ:: እንዲሁ ከምንም ተነሥተው ልጆቻችን ወጣቶቹ ይኸን በማቅረብ እኛን ለማስደንገጥ ወቀሱን ለማለት ሳይሆን ኅሊናችንን የሚወቅስ ነገር ለማቅረብ ችለዋል::

ስለዚህ ይህን እንደ ጥያቄ ቆጥረን ወደፊት ለመዘጋጀት ስለምንችል ዕድሉ ሳለን አሁን ሦስት ጥያቄዎች ቀርበዋል:: የቀረቡትም:-

☞ የሥነ ጽሑፍ ሞያዊ ሥልጠና እንዲኖር፣ የጋዜጦችና የመጽሔቶች ክፍሉን በቻለ መልኩ እንዲደራጅ፣ ነጻ በሆነ መልክ ምንም ሳይኖርባቸው እንዲቀጥሉ የሚሉ ናቸው:: ሁሉንም ነካ ነካ አድርገውታል:: እነዚህን ሐሳቦች ማጠናከር አለብን::

☞ ሌላው በየክፍለ ሃገሩ በየአህጉረ ስብከቱ የቤተ ክርስቲያን ትምህርቷን ዜናዋን የሚገልጹ በተለያዩ ቋንቋዎች እትሞች ቢኖሩ፣ አሁንም በተጨማሪ የምእመናን ተሳትፎ ጉልህ ሥፍራ እንዲኖረው የሚል ነው:: እነዚህን ተግባራዊ ለማድረግ ምናልባት አቅም ያንሰናል:: ማኅበረ ቅዱሳን ከልጅነትም አንጻር፣ ወጣት ዕድሜ ያለው እንደ መሆኑ መጠን፣ እንደገና ወጣቶቹ ሁለገብ ከመሆናቸው አንጻር፣ ለዘመናዊውም ዕውቀት እንግዳ ካለመሆናቸው አንጻር፣ በልጅነት ሁሉ ስለሚያምር፣ ምናልባት ባቋቋሙት ንዑስ ማዕከል በየደረጃው ያሉት ተግባራዊ ለማድረግ አያቅታቸውም ማለት ይቻላል::

በእኛ በኩል ግን፣ ተቀናጅተን እንሥራ ለማለት በዐውደ ጥናት ላይ ወሳኝ የሆኑት አካላት መገኘት አለባቸው:: ከሊቃነ ጳጳሳት ጀምሮ ይህንን ችግራቸውን ማወቅ አለባቸው:: ለዚህ ደግሞ ማወቅ የሚያስችለው በአጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የሥነ ጽሑፍ መወያያ ተዘጋጅቶ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ ሊቃነ ጳጳሳት ባሉበት የተወሰነ እንደሆነ ተግባራዊ ለማድረግ ያመቻል፣ ይኼ መንደርደሪያ ነው::

ወደ ኋላ ተመልሰን ያለፍንበትን ችግር የሠራነውን እየገለጽን ጊዜ ከማባከን በእነዚህ በሦስቱ ጥያቄዎች ላይ አዳብረን ለአጠቃላይ ጉባኤ ጥናቱ ቀርቦ፣ ለሥነ ጽሑፍ ጉባኤ ተሰጥቶ በውሳኔ ቢያልፍና እነዚህ ነገሮች ቢዳብሩ ጥሩ ነው:: በቋንቋ ይታተሙ ከሚለው አስቀድሞ ይህን ለመተግበር በጣም ይከብዳል:: ግን ቢከብድም በተግባር ላይ መዋሉ አይቀርም:: መጀመሪያ ሥርጭት ቢጨመር:: ሥርጭቶች እንዴት እንደሚደርሱ፣ ምእመናኖቻችን በቋንቋ አትሙልን አላሉም በሙሉ አማርኛውን ይናገራሉ:: ያንን በትክክል ማግኘት ግን አልቻሉም:: የእኛ ጋዜጣ ከሚያነበው የማያነበው ነው የሚበልጠው፣ ሐመርና ስምዐ ጽድቅ ግን ሊሠራጩ ይችላሉ::

ሥርጭቱ ተጨምሮ እንዴት እናድርስ፣ እንዴት እናቀናጃቸው እናት የሆነው «ዜና ቤተ ክርስቲያን» ነባር ጋዜጣ እንዴት ይድረስ የሚለውን፣ ሁሉንም አንጻጽረን ብናነብ እና ሥርጭቱ ተጨምሮ ለአጠቃላይ ጉባኤ መንደርደሪያ ብናደርጋችው::

ማኅበሩ በነካ እጁ ቅዱስነታቸውን አስፈቅዶ አባቶች በአሉበት ቢካሔድ:: በአጠቃላይ ጉባኤ የማኅበረ ቅዱሳን ሥራ የሌለበት ሪፖርት ሊቀርብ አልቻለም፣ ይኼ ታላቅ ደስታ ነው:: እራት እየበላን ቅኔ መስጠትም ጀምረናል፤ ለማኅበረ ቅዱሳን:: ሥራው እየገፋ መጥቶ የማኅበረ ቅዱሳን እርዳታ እጅ የሌለበት ሀገረ ስብከት ስላልተገኘ በአማዳፊ ሁኔታ ጥሪ ተደርጎ ጥናቱ መንደርደሪያ ሆኖ በዚህ በጥናቱ ያልተካተቱ ብዙ ነገሮች ስላሉ ሰፊ ጥናት ቢቀርብ:: ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር ተቀናጅተው ጥናቱን አዘጋጅተው ጥሪ ያድርጉና ቅዱስነታቸው ባሉበት ቢቀርብ ተግባራዊ ለማድረግም ይቻላል::

*/የ«ዜና ቤተ ክርስቲያን» ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ/*

## «ለፊደላትና ለቃላት አጠቃቀም ጥንቃቄ ይደረግ»

በእውነቱ ጥናቱ በጣም ጠቃሚ ከመሆኑም በላይ ደስ በሚያሰኝ ገለጻ የቀረበ ነው:: ሁሉም ተነግሯል፣ ለመጨመር የፈለግኹት፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነታችን ረዘም ያለ ዕድሜ ያላቸው ተክለ ሃይማኖትና ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች እንደ ኾኑ ተጠቁሟል:: በተለይ ዜና ቤተ ክርስቲያንን አስመልክቶ የ25ኛ ዓመቱን ኢዮቤልዩ ያከበረ ጋዜጣ መኾኑን አስታውሳለሁ:: 50ኛ ዓመቱ ግን ሳይከበር ተዘሏል:: ለምን እንዳልተከበረ አላውቅም:: አሁን እንግዲህ ዕድሜው ወደ 60 ዘመን እየደረሰ ነው:: ስለ ይዘቱ የተነገረው ጥሩ ነው፣ ትክክል ነው:: ይሁንና ከተክለ ሃይማኖትና ከዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጦች ባሻገር መጽሔቶችም ይወጡ እንደ ነበር አልተጠቆመም:: ይኸውም በዓላትን አስመልክተው የሚወጡ መጽሔቶች ነበሩ:: ለምሳሌ፡ ሰሙነ ሕማማትንና ትንሣኤን በማስመልከት፣ ሌላም ከዚህ ጋር የተቀራረበ ትምህርት ይወጣ ነበር:: በተለይም ለቀዳም ስዑር በዓል የሚታደል መጽሔት ነበር:: የዘመን መለወጫንና የዐፄ መስቀል በዓላትን የተመለከቱ ጽሑፎችን ይዘው የሚወጡ ጋዜጦችም ነበሩ::...

ከግብፃውያን ጋር የነበረውን የክህነት ግንኙነትና ክህነቱን ከግብፅ ለማምጣት የነበረውን ክርክር አስመልክቶ በየዓመቱ በፓትርያርኮች በዓለ ሢመት ቀን የሚወጡ ጋዜጦችና መጽሔቶችም ነበሩ፣ ለሕዝብ በተለያየ ጊዜ ይታደሉ ነበር:: የእነዚህ ቅጅዎች በጠቅላይ ቤተ ክህነት ቤተ መጻሕፍት ይገኛሉ:: እናንተ አላገኛችኋቸው ይሆናል:: የዜና ቤተ ክርስቲያንና የተክለ ሃይማኖት ጋዜጦች ጥራዝም በቤተ መጻሕፍት አሉ::

በሳንሱር ተጽዕኖ ሳቢያ በተለይ የማይገለጹ የሕዝብ አስተያየቶች እንደ ነበሩ ተጠቁሟል፣ ይህ ግን በየዘመናቱ አለ፣ የማይካድ ነው:: በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደርም ኾነ መዋቅር ዘንድ ኩርኩም ስላለ ትችት ለመስጠት አልተመቸም:: ... በአስተዳደር ላይ የተለያዩ ሒሶችን ስንሰጥ ወቀሳ ይደርስብን ነበር:: በገንዘብ ተቀጣ የሚባል ባይሆንም ወቀሳዎች ነበሩ::...

ሐመርና ስምዐ ጽድቅ ባሳለፍነው 10 ዓመት ውስጥ ለቤተ ክርስቲያን ጠበቃ ኾነው የቆሙ ኅትመቶች ናቸው:: ከመንግሥተ እግዚአብሔር ውጭ ያሉትን እየተቃወሙ ተገቢ ትምህርትና ለጥያቄዎችም በቂ ምላሽ እየሰጡ ናቸው፣ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይም የቤተ ክርስቲያናችንን አቋም በመግለጽ ላይ ናቸው::

አእምሮ፣ ብርሃንና ሰላም፣ ሰንደቅ ዓላማችን ይባሉ የነበሩት መንግሥታዊ ጋዜጦች አዘጋጆች የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ነበሩ፣ አርታዒያኑም እንዲሁ:: ለምሳሌ እነ ብላታ ወልደ ጊዮርጊስ በዘመናችን የደረስንባቸው ሊቆች ነበሩ:: አሁን ግን ለቃላትና ለፊደላት አጠቃቀም ጥንቃቄ አይደረግም:: ይህም ቤተ ክርስቲያናችን ለቋንቋና ለፊደላት አጠቃቀም የነበራትን መምህርነት የለቀቀች አስመስሏታል፣ «ካህን እንደ ሕዝብ ኾነ» እንዲል የቤተ ክርስቲያንም ሰዎች እንደ ሕዝብ ኾነናል:: እኛ ነበርን ትክክለኛውን ለሕዝብ ማስተማር የነበረብን:: በቀድሞው ሥርዓተ መንግሥት «ከኅብረት ወደ ውህደት» የሚል ንግግር ነበር:: «ውህደት» ማለት ግን ለእነርሱ እንደ መሰላቸው ኅብረት፣ አንድነት ማለት ሳይሆን «ጉድለት» ማለት ነው:: «ታዳጊ አገር» ይላሉ፣ «አዳጊ አገር» ያሉ እየመሰላቸው:: «ዘርዐ ዮሐንስ» ማለት ሲገባቸው «ዘርዓ ዮሐንስ» ይላሉ፣ ስሕተት ነው:: መጥፎው ነገር የቤተ ክርስቲያኒቱ ኅትመቶች የሚጽፉት የተሳሳተ ፊደል አብነት ኾኖ መውጣቱ ነው፣ ለምን እኮ፣ በዚህ ረገድ ሥልጠና ለመውሰድ ችግሩ

www.eotcmk.org

ምንድን ነው? በሌላ በኩል ሥርጭትን አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያናችን ጋዜጦች የሚገፉት በአንዳንድ የራሳችን ሰዎች ነው:: ኅትመቶች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን የተሸጡ እንደ ኾነ ከሕዝቡ የምናገኘው ገቢ ይቀንሳል ብለው:: ለምሳሌ ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በአጥቢያቸው እንዳይሸጥ የሚቃወሙ አሉ:: እንግዲህ ጋዜጣው የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ የጠቅላይ ቤተ ክህነቱን ዜና ይዞ የሚወጣ ኾኖ ሳለ ለምን ይገፋል? የደብር አለቆችና ካህናት የኅትመቶችን ጥቅም እንዲያውቁ ተመሳሳይ ዐውደ ጥናት ያስፈልጋቸዋል:: ይህ ካልኾነ የእኛ ድካም የቅንድብ ጠጉር ነው የሚኾነው፤ አያድግም:: ለዚህ ተፈጻሚነት ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች ይዘን መወያየት ይገባናል::

*/ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ÷*
*የሊቃውንት ጉባኤ አባል/*

## «ቤተ ክርስቲያናችን በመጽሔትና በጋዜጣ ኅትመት የቆየ ታሪክ አላት»

ኅትመቶች በአህጉረ ስብከት፣ በግለ ሰቦችና በማኅበራት ደረጃ ይስፋፉ ስንል በዚያ መልኩ ተዘጋጅተው የሚታተሙ መጽሔቶች ጋዜጦች ከቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ እምነት ውጭ ወጥተው ስሕተት እንዳይሠራባቸው÷ ጥፋት እንዳይፈጽምባቸው ቁጥጥሩ የሚደረግበት ሁኔታና ለዚህም ኃላፊነቱ የሚሰጠው ወገን ሊኖር ይገባል:: በቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጁቱ ጽሑፎች እንደ ዓለማዊ ጽሑፎች ሳይሆን በሚገባ መታየት ያለባቸው ስለሆኑ የቅድመ ኅትመት ምርመራ ጉዳይን አስፈላጊነት ልናጤነው ያስፈልጋል::... ሥነ ጽሑፍ /በተለይ የአማርኛ/ ከ17ኛው መ.ክ.ዘ ጀምሮ የነበረ ነው:: ጋዜጣና መጽሔት በቅርብ ጊዜ ነው የተጀመረ የሚባለውን አልቀበለውም፤ ማለትም ቤተ ክርስቲያናችን በመጽሔትና በጋዜጣ ኅትመቶችን ከጀመረች ገና 60 ዓመትዋ ነው የሚባለው ትክክል አይደለም:: ... በሌላ በኩል በቤተ ክርስቲያናችን ኅትመቶች ላይ ሂስ አለ/ይኖራል ሲባል ጽርፈት፣ ወቀሳና ሌሎችን ማጥላላት ባይኖር ደስ ይለኛል::

*/መሪጌታ ኤፍሬም በየነ÷*
*የልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ*
*መጽሔት ም/ዋና አዘጋጅ/*

## «ኅትመቶቻችንን ለማሳደግ ለተግባር የሚያነሣሣ ጥናት፣ በምሁራን ደረጃ የሚቀርብ ጽሑፍ፣ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ማዘጋጀትና የንባብ ልምድን ማዳበር ይጠበቅብናል::»

የጽሑፎቻችን ዕድሜ፣ በየዘመኑ የነበራቸው አጠቃላይ ባሕርይ፣ የኤዲቶሪያል ነጻነታቸው፣ የኅትመት ብዛት፣ የሞያ ብቃት፣ የምእመናን ተሳትፎ፣ የሥርጭት አድማስና የወደፊት ርእይ መነሣቱ በጣም ጥሩ ነው:: ያለፈው መነሣቱ፣ ጠንካራና ደካማ ጎን መታየቱ፤ በጠንካራ ጐኑ እንዲህ መሠራት አለበት እንድንል÷ በቁጭት እንድን ነሣሣ ነው:: በደካማ ጐኑ ደግሞ እንዲህ መሠራት የለበትም÷ ወደፊትም አይደገምም እንላለን:: ጥናቱ የጥናት መነሻ ነው የሚለውን እኔም እጋራዋለሁ፤ በተለይም ካሳለፍነው ታሪክ አንጻር ወዴት÷ እንዴት እንሒድ የሚለው መነሣቱ አስፈላጊ ነው፤ ወደ ተግባር የሚመራን ዋነኛ ነገር ነውና::

በቀጣይም በየቦታው ያለነውን አሳታሚዎችና አዘጋጆች አሰባስቦ ለአንድ ዓላማ የሚያስተባብረን ተግባራዊ ጥናት ያስፈልገናል:: ለዚህም በተናጠልም በማዕከልም በሥራው ላይ ያሉት ተቋማት ሁሉ ለአንድ ዓላማ በዚህ መሰል ጥናት መነሻነት የጋራ ውይይትና ግንኙነት ያስፈልገናል:: ተቋማትን አጠናክሮ አንድ ዓይነት መልእክት ለሚመለከታቸው ክፍሎች ሁሉ ለማስተላለፍ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ተገኝተው ፍላጐታቸውን የሚገልጹበት፣ መመሪያና ቡራኬ የሚሰጡበት መድረክ ያስፈልጋቸዋል::

በተለያየ ምክንያት ብዙዎቹን ኅትመቶቻችንን የማግኘት ዕድላቸው ጠባብ የኾነባቸው አሉ:: በመሆኑም የጋዜጣና የመጽሔት ኅትመቶቻችንን እንደ አንድ የማስተማሪያ አማራጭ በመውሰድ ተቋማዊ አቅማቸውን ማጠናከር ላይ ማተኮር አለብን:: በቤታችን ያለው ጉድለት የኅትመቶቻችንን 95% ጥንካሬ የማበረታታት ሳይሆን 5% ድክመት ላይ መረባረባችን ነው:: በደካማ ጐናቸው ላይ ከመረባረብ ይልቅ ለጠንካራ ጐናቸው አስተዋፅዖ መደረግ አለበት:: በተለይ በተቋዋም ደረጃ ላሉት በየአህጉረ ስብከቱ በመሪነት ደረጃ የተቀመጡቱ መተባበር አለባቸው:: ቤተ ክርስቲያኒቱን በሁሉም መስክ ሊረዳ የሚችል የሥነ ጽሑፍ ተቅዋም እንዲኖር መታመን አለበት:: ...ያለፈው እንዳለፈው ተሠርቷል:: የወደፊቱን ነው የምናየው:: በመሆኑም የሥነ ጽሑፎቻችን ይዘትና መልእክት የቤተ ክርስቲያናችንን ትምህርት፣ ሥርዓትና ትውፊት ከማስተማር፣ የጊዜውንም ሁኔታ ከመዳሰስ አኳያ መሥራት አለባቸው:: ዘመኑን መስሎ በቀላል አቀራረብ ትውልዱን መመለስ፣ ለአራሹም፣ ለነጋዴውም፣ ለሐኪሙም፣ ለካህናትም የሚመጥን ይዘትና የአቀራረብ ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል:: «ግብረ ልዑካን» ለካህናት ታስባ ትዘጋጅ እንደ ነበረው ሁሉ «መርሐ ምእመናን» የምትባል ብዙ ተከታታይ ጽሑፎችን ለምእመናን ይዛ የምትወጣ መጽሔት ነበረች:: ከጸታም፣ ከሞያም አኳያ እየገባን መሥራት አለብን፤ የሞያ ቃል ኪዳንን የመካድ የጊዜያችን ደዌ አለና÷ ቃልና ተግባር የተለያዩበት ሁኔታ ሰፍኗልና:: ኀሊናን የመሸጥ፣ ወገንን የመጥላት፣ ራስን የመውደድ (self centeredness, ego centerism) ይታያልና ልናስብበት ይገባል:: ወደዚህ ሞያዊ ብቃት ለመድረስ በምሁራን ደረጃ የሚቀርብ ጽሑፍ ያስፈልገናል:: በጥንቶቹ ኅትመቶች ምሁራን ነበሩበት:: መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን፣ አፈ ሊቀ ሊቃውንት አክሊሉ ገብረ ኪሮስን፣ አለቃ ይትባረክ መርሻን፣ መምህር ዓምደ ጽዮንን፣ መምህር ወልደ ኢየሱስን፣ መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈን የመሳሰሉ ነበሩ፤ የሰውን ኀሊና ይተረጉሙ ነበር፤ መጽሐፍ አከል ነበር ጽሑፋቸው:: ዛሬ ግን በእነርሱ ቦታ እነርሱን የሚተካ÷ እነርሱን የሚወክል ሰው በቤቱ የለም:: ዛሬ ጥልቅ የቤተ ክርስቲያን ዕውቀትና የዘመናዊ ሥልጣኔ ትምህርት ያላቸው ባለሞያዎች ያስፈልጉናል::

የሥርጭት የአላላክ ጉዳይ ብቻ አይደለም ኅትመቶቻችንን የሚያሳድገው:: ዋናው አንባቢ ማግኘት ላይ ነው:: ለዚህ ደግሞ ምእመናን የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: አበው ካህናትስ ምን ያህል ፍላጐት /የንባብ ልምድ/ አላቸው? ምን ያህል ጊዜያቸውን ለንባብ ይሰጣሉ:: ለኅትመቶቻችን ባለቤት የመስጠት ሁኔታ እንጂ እያንዳንዳቸውን አንብቦ ትምህርት ማግኘትና አስተያየት መስጠት የለም:: በእውነቱ ኅትመቶቻችንን ካህናት ጥሚቸው ከአነበቡ ምእመናንን ይስባሉ፤ በግፊት፣ በማስታወቂያ፣በማባበልም አይደለም፤ በራሱ ጊዜ እፈልገዋለሁ የሚል አንባቢ ያስፈልገናል:: ለዚህም ከንባብ ልምድ ጋር የጽሑፉ ዝግጅትና ይዘት ወሳኝ ነው:: አንድምታ የተቀላቀለበት መጽሓፋዊ ብቻ መሆን የለበትም:: ቀኖናን የማያፋልስ፣ ማንንም የማይጎዳና የማይበድል፣ ነጻ አንደበት፣ ነጻ ብዕር ለማስተናገድ የሚያስችልም ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ያስፈልገናል:: እርግጥ የውስጥ ዝግጅት ነው፤ በእኛ ጊዜ በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሠራተኞች ይህ በሽፍት ነበር የሚሠራው:: ለሁለትና ለሦስት ወራት አንዱ አራሚ ሌላው ጸሐፊ ኾኖ በወር ተራ ይሠራ ነበር:: በአጠቃላይ ለወደፊቱ ለተግባር የሚያነሣሣ ጥናት ይኑር እላለሁ::

*/መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን÷*
*የቅርሳ ቅርስ መምሪያ ኃላፊ/*

## «በየቦታው ኅትመት ይኑር÷ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በአማካሪነት ይመደቡ»

በቅድሚያ መድረኩን ያዘጋጀውን ማኅበረ ቅዱሳንንና የጥናት ወረቀቱን አቅራቢዎች በእጅጉ አመሰግናለሁ:: ጥሩ መነሻ ነው:: ይህ ዘመናዊ የአሠራር ሒደት ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን ተግባራዊ ልታደርገው የሚገባት ነው:: ራስን ገምግሞ የኋላን እያሰቡ ለወደፊቱ መዘጋጀት÷ ለዚህም ጊዜን መሥዋዕት ማድረግ በጣም አስደናቂ አሠራር ነው::

ጋዜጣ የሥነ ጽሑፍ አካል ነው:: አገራችን ኢትዮጵያ ጋዜጣ የሚለው ሥነ ጽሑፍ ከመጀመሩ በፊት ጽሑፍ ሳይሆን ጋዜጣዊ ሥነ ጽሑፍ አልነበራትም ወይ? በሌላ አገላለጽ ማተሚያ ቤት ባልነበረበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን መልእክት ታስተላልፍ ነበር:: ይህ አሳብ ለቀረበው ጥናት መነሻ ቢሆን ጥሩ ነበር:: ጋዜጣ ትላንት ከውጭ የወረስነው ወይም ከዘመኑ ዕድገት አንጻር የደረስንበት ነበር:: ይኸውም ነገሥታቱ የየዕለት ውሏቸውን የሚመዘግቡ /ዜና መዋዕል የሚጽፉ/ ጸሐፊዎች ነበሯቸው:: የእረኛ÷ የአዝማሪ ጋዜጠኛ እኮ ነበር፤ ደባትር ጋዜጠኞች ነበሩ:: «እረኛ÷ አዝማሪ ምን አለ?» ይባላል:: ጊዜው ስለ ማይፈቅድ በጋዜጣ ቅጽ ባያትሙትም ያዩትን ነገር ነገር በመጽሐፍ መልክ ያወጡት ነበር::...

ከጋዜጣ በፊት ጋዜጣዊ የሕዝብ መገናኛ መንገድ ነበር:: በዚያም ወደ ዘመናዊ ሥነ ጽሑፍ ስለ መሸጋገራችን ጥናቱ ቢያካትት መልካም ነው:: ቤተ ክርስቲያናችን በዘርፉ የቆየችበትን ያህል በሚገባ አላሳደገችውም እንጂ ለመንግሥት ሚዲያዎችም መሠረት ጥላለች÷ ተርፋለች:: .... የጽሑፍ ማዕከላዊነት ካለ ሥራ ሊሠራ አይችልም:: ቤተ ክርስቲያን የራስዋ ትምህርተ ሃይማኖትና ሥርዓተ እምነት አላት:: ከዚህ አኳያ በየቦታው ኅትመቶች ይኑሩ:: ማዕከላዊነት ቢሮክራሲያዊ ማነቆን ያመጣል:: የጽሑፍ ውበትና ጥንካሬ ይቀጭጫል:: በማዕከል መደረግ ያለበት እገዛ /ድጋፍ/ መስጠት ብቻ ቢሆን መልካም ነው:: ኅትመቶች በጋዜጣና በመጽሔት መልክ ባይዘጋጁ እንኳ በኮምፒዩተር ተጽፈው በትምህርታዊ ጽሑፍ መልክ ይሠራጩ ዘንድ ግፊቱ እንዲኖር

ይህ መድረክ በውሳኔ አሳብነት ቢይዘው እላለሁ።... በሥነ ጽሑፍ ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ እያገዘ ነው። የኅትመት ውጤቶቹ በዓለም እየዞሩ እያስተማሩ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ በሰጠችው መድረክ ሕዝቡን እያገለገለ ነው። አውስትራሊያ ሳለሁ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደርሶኛል፤ ይህም የቤተ ክርስቲያናችንን ዕድገት ያሳያል። በእውነቱ ለዚህ አድናቆት አለኝ፤ አመሰግናለሁ። ዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣና ልሳነ ተዋሕዶ ዘኦርቶዶክስ መጽሔት ግን አልደረሰኝም፤ ይህም ሊታሰብበት ይገባል።

*/መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን÷*
*የሊቃውንት ጉባኤ አባል/*

## «ሌሎችም ነበሩ...»

በጥናቱ ውስጥ እንደ ተወሳው ተጀምረው ከተቋረጡት የቤተ ክርስቲያናችን ኅትመቶች በተጨማሪ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል /ማኅበረ ክርስቶስ/ ይዘጋጁ የነበሩቱ መታወስ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ስለ ግእዝ ቋንቋ /ትንሣኤ ግእዝ/፣ በተባዕት ምእመናን /ወጣት ወንዶች/ ዙሪያ «እስጢፋኖስ»፣ በእንስት ምእመናት /ወጣት ሴቶች/ ዙሪያ «የሴት ልጅ ዕድገት በሃይማኖት» ይሰኙ የነበሩ ኅትመቶች ይጠቀሳሉ። እነዚህን ይዞ በጥናቱ የታወሱት ሰባት ኅትመቶች /ትንሣኤ መጽሔት በግእዝ፣ በአማርኛና በእንግሊዘኛ፣ እስጢፋኖስ፣ የሴት ልጅ ዕድገት በሃይማኖት፣ ግብረ ልዑካን፣ ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ/ ሊቋረጡ የቻሉት በቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔ ሳይሆን በግለሰቦች ግፊትና መጎናተል ነው። ይኼ ቢያንስ አሁን ባሉቱ ዘንድ መደገም የለበትም። ጸጸት ነው ትርፉ። በሌላ በኩል ለኅትመት መገናኛ ብዙኃን ውጤቶቻችን መጠናከር በተለይ ካህናቱን ጠርተን መድረክ ፈጥረን ገለጻ መስጠት አለብን እላለሁ።

*/መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ÷*
*በጠቅላይ ቤተ ክህነት*
*የሕግ አገልግሎት ኃላፊ/*

ከአዘጋጁ፡- መሪጌታ ተስፋ ጥሩነህ በዐውደ ጥናቱ ወቅት ለዕይታ የቀረቡቱን የነበሩና ያሉ የቤተ ክርስቲያናችንን ጋዜጦችና መጽሔቶች በመመልከት እርሳቸውም የበኩላቸውን ጠቃሚ ሰነድ በስጦታ መልክ አበርክተዋል። ይህም ቀደም ሲል በብሥራተ ወንጌል ሬድዮ ጣቢያ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ሰባክያነ ወንጌል ያስተላለፏቸው ትምህርቶች ነበሩ። ይህም በዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ዘንድ አድናቆትን አትርፎላቸዋል። የዝግጅት ክፍላችንም ከፍ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል።

## «ኅትመት መገናኛ ብዙኀን ኃይልና ጉልበት ነው»

ማኅበረ ቅዱሳን ዛሬ በሚገኝበት ደረጃ ላይ ሊደርስ የቻለው አገልግሎቱን በመጽሔትና በጋዜጣ ኅትመት ስለ ጀመረ ነው። በሌላ ቢጀምር አንድ ቦታ የሚያቆም የነበረ ይመስለኛል። አሁንም ኃይል አግኝቷል፤ ጉልበቱ፣ ኃይሉ፣ መውጊያው ይኸው መጽሔትና ጋዜጣ ስለ ኾነ ሌሎች ቋንቋዎችን ጨምሮ በዚሁ መበርታት አለበት። የኅትመት መገናኛ ብዙኀን ባለሞያዎችና አሳታሚዎች ቅንጅት አስፈላጊ ቢሆንም ምክክር÷ ውይይት ካልኾነ በቀር ሁሉም በያሉበት ኾነው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርትና ሥርዓት ጠብቀው ቢሠሩ መልካም ነው።

*/መምህር ገብር ሚካኤል ድፈር÷*
*የሊቃውንት ጉባኤ አባል/*

## «የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያው ለእምነት ተቋማት ባልተፈቀደበት ሁኔታ የኅትመት ሚዲያውን ከማጠናከር ውጭ አማራጭ የለንም።»

ሚድያ ከኒውክሊየር የበለጠ ኃይል እየያዘ ነው። በእኛ በኩል የኅትመት መገናኛ ብዙኀንን ልናተኩርበት ይገባል። ቤተ ክርስቲያናችን ከእኅት አብያተ ክርስቲያናት መገናኛ ብዙኃን አቅም አንጻር ስናስተያያት ወደ ኋላ ነች። በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ሌሎች እያውቋትምና በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚዘጋጅ ጋዜጣና መጽሔት ሊታሰብበት ይገባል። ያሳተምንባቸው አጋጣሚዎች ቢኖሩም በቂ አይደሉም። ስትራቴጂ የሚወጣበት፣ አቅጣጫ የሚሰጥበት፣ ሁሉንም የኅትመት መገናኛ ብዙኀን አሠራርና ዕድገት እያየ አመራርና ድጋፍ የሚሰጥ ማዕከላዊ አመራር ያስፈልገናል። ሳንሱር ይኑር ማለቴ አይደለም። ራሱን የቻለ መዋቅር /የሰው ኃይል/፣ በቂ በጀትና ጠንካራ የሕዝብ ግንኙነት ተግባር መኖር አለበት። የስብከተ ወንጌልና ሐዋርዊ ተልእኮ መምሪያም በሰው ኃይል /በባለሞያ/ እና በሥልጠና መጠናከር አለበት። የአገራችን የብሮድካስት ሕግ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያውን ለእምነት ተቋማት በማይፈቅድበት ሁኔታ የኅትመት ሚዲያውን ከማጠናከር ውጭ አማራጭ የለንም።

*/መምህር ካህሣይ ገብረ እግዚአብሔር÷*
*የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ም/ዋና አዘጋጅና*
*የፈለገ ጥበብ መጽሔት ዋና አዘጋጅ/*

## «በማዕከል ደረጃ ለፕሬሶቻችን ዕውቅና የሚሰጥ አካል ይኑር»

በኅትመት መገናኛ ብዙኀን ረገድ የሆሄያት አጠቃቀምን ያካተተ ሞያዊ የጋዜጠኝነት ሥልጠና መስጠት አለበት። ለሞያዊ ዕድገት ስለሚጠቅም የኅትመት መገናኛ ብዙኀን ባለሞያዎችና አሳታሚዎች የሚገናኙበት የጋራ መድረክ ያስፈልጋቸዋል። በየደረጃው ለሚያብቡት ፕሬሶቻችን ዕውቅና የሚሰጥ አካል በማዕከል ደረጃ መቋቋም አለበት። ይህ የፕሬሶቹን ዕድገት ይጨምራል÷ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል። በብዙ ቋንቋዎች በየአህጉረ ስብከቱ የሚ ታተሙ ፕሬሶች ያስፈልጉናል። በቤተ ክርስቲያናችን የኅትመት መገናኛ ብዙኀን ጠቅላላ ሁኔታ ዙሪያ የሚነጋገር÷ ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች የሚገኙበት መድረክ ይዘጋጅ።

*ዲያቆን ደቅስዮስ ሽብሩ*
*የመለከት መጽሔት ዋና አዘጋጅ*

## «ቤተ ክርስቲያናችን የሥነ ጽሑፍ ማሠልጠኛ ተቋም፣ የትርጉም አገልግሎት ክፍል፣ በርካታና ዘመናዊ ማተሚያ ቤቶች ይኑሯት»

ቤተ ክርስቲያናችን በኅትመት መገናኛ ብዙኀን ወደ ኋላ እንጂ ወደፊት አልተራመደችም። ለመራመድ፥ ለመሻሻል ግን ፈቃደኝነቱ አለ። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችን በማዕከል ደረጃ የሥነ ጽሑፍ ማሠልጠኛ ተቋም ሊኖራት ይገባል። ፊደልን ጨምሮ በግእዝም ይሁን በሌሎች የአገርና የውጭ ቋንቋዎች አንጻር የትርጉም አገልግሎት ክፍል ያስፈልገናል፤ አሁን በመጠኑ ቢኖርም የተደራጀ ግን አይደለም። ይህም በሊቃውንት ጉባኤ ስር ኾኖ፣ ራሱን ችሎ፣ በበጀት ተጠናክሮ ሊቋቋም ይችላል። የምንዘምርባቸው፣ የምንጽፍባቸው፣ የምንተችባቸው ቋንቋዎች መጨመር አለባቸው። የእኛን ተግባር ሌሎች እየወሰዱት ነው። አማርኛ ቋንቋን ብቻ ይዘን የትም ልንደርስ አንችልም። ከዚህም ባሻገር የተሻሻሉ የኅትመት መሣሪያዎች ያስፈልጉናል። የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅትና የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት በሰው ኃይል፣ በበጀት፣ በማቴሪያል መጠናከር አለባቸው። ይህም ብቻ ሳይሆን ሌሎች በርካታ ማተሚያ ቤቶች ሊኖሩን ይገባል። የብሮድካስት ሕጉ የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ እንዳይኖረን ቢያግደንም ገፍተን መጠየቅ ይኖርብናል፤ ሌሎች የመረጃ ቴክኖሎጂዎችንም /ኢንተርኔት፣ ዌብ ሳይት/ መጠቀም አለብን። እንደ ዋኖስ አሳታሚ ድርጅትና ማኅበረ ቅዱሳንን የመሳሰሉ አካላትም መበረታታት ይገባቸዋል።

*/መምህር ዕንቁ ባሕርይ ተከስተ÷*
*የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ*
*ም/ኃላፊ/*

## «የኅትመቶቻችንን አቅም ለመደጎም የማስታወቂያ አጠቃቀማችን መጨመር አለበት»

የኅትመት መገናኛ ብዙኀን /ጋዜጠኝነት/ «አራተኛው መንግሥት» ይባላል። ይህም አጠራር የዘርፉን አስፈላጊነትና ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳየናል። የቤተ ክርስቲያናችንን የኅትመት መገናኛ ብዙኀን እንደ አማራጭ የስብከተ ወንጌል መንገድ ልናየው ይገባል፤ በተለይ በዳር አገርና በባሕር ማዶ ላሉ ምእመናን። ስለሆነም አንድም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ኅትመቶችን ማዘጋጀት አልያም ደግሞ ባሉት የኅትመት ውጤቶች ይዘት ውስጥ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን የምንጠቀምበት ሁኔታ ሊተኮርበት ይገባል። ይህም በርካታ ወገኖችን ለማስተማር ከመጥቀሙም በላይ አላግባብ ቤተ ክርስቲያናችንን የአንድ ብሔር ብቻ አድርገው የሚፈርጁትን ወገኖች አሳብ የሚያስተባብል ይሆናል። በመጨረሻም የኅትመቶቻችንን አቅም ለመደጎም የማስታወቂያ አጠቃቀም ሁኔታ መጤን ይኖርበታል እላለሁ።

*አንዱ ዓለም በድሉ*
*የቢታንያ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ*
*/ጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል*
*ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት/*



www.eotcmk.org

# ዝክረ ቴዎፍሎስ፣ ጴጥሮስ ወሚካኤል

*ባለፈው እትማችን የሁለተኛውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዜና ሕይወትና ሰማዕትነት እንዴት እንደ ተቀበሉ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ ከቅዱስነታቸው 43 ዓመታት በፊት በፋሺስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የሰማዕትነት አክሊል የተቀዳጁትን የሰማዕቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ ዜና ሕይወትና የሰማዕትነት ታሪክ እናቀርባለን።*

## የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቀዳማዊ ዜና ሕይወትና ሰማዕትነት

- በ1875 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ አገረ ስብከት ሰላሌ አውራጃ ፍቼ ከተማ ተወለዱ።
- ወላጆቻቸው ዕድሜያቸው ገና በወግ ለትምህርት ሳይደርስ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመውሰድ ባሕታዊ ተድላ ለተባሉ መምህር አደራ ሰጧቸው።
- በዚያው ገዳም የንባብ ቤቱንና የዜማውን የትምህርት ደረጃዎች በሚያስገርም ሁኔታ በአጭር ጊዜ አቀላጥፈው በመጨረስ ገና በልጅነት የዕድሜ ደረጃቸው ሦስተኛውን የቅኔ ትምህርት ጀምረው በአጭር ጊዜ ሙሉ ቤት ተቀኙ። ይህንኑ የቅኔ ትምህርት ለማስፋፋት በምዕራብ ጎጃም አገረ ስብከት ወደ ሚገኘው የቅኔ ትምህርት ማዕከል ዋሸራ ተሻግረው ለመምህርነት የሚያበቃውን ትምህርት ፈጽመው አስመሰከሩ።
- ከዚያም ከቅኔው ዐውድማ ጎጃም ወደ ዜማው አዝመራ ጎንደር ተሻገሩ። በዚያም እንደ ቅኔው ሁሉ እስከ ማስመስከር ባይደርሱም የዜማውን ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ ቀጸሉ።
- ከጎንደርም በወቅቱ ወሎ ቦሩ ሜዳ ከተባለው ቦታ ላይ ወንበር ዘርግተው የመጻሕፍትን ምሥጢር በየዓይነቱ ሲመግቡ ወደ ነበሩት ስመ ጥሩው መምህር አካለ ወልድ ዘንድ በመሔድ ዋና ዋናዎቹን የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርቶች ማለትም ብሉያትን፣ሐዲሳትንና ሊቃውንትን በብቃት አሔዱ።
- ከዚህ በኋላ ልክ በ1900 ዓ.ም. እዚያው ወሎ አማራ ሳይንት በተባለው ቦታ ወደ ሚገኘው ምስካበ ቅዱሳን ገዳም በመሔድ ወንበር ዘረጉ። በዚያው ቦታ ለዘጠኝ ዓመታት ያህል ቅኔንና መጻሕፍትን አስተማሩ።
- በዚህ ዓይነት በመማርና በማስተማር ራሳቸውን በእግዚአብሔር ቃል በሚገባ ከኰሰሙ በኋላ በ1909 ዓ.ም. ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በመሔድ ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጸሙ። ብዙም ሳይቆዩ መዓረገ ቅስናን ተቀብለው ከወንበሩ አገልግሎት ጋር የቤተ መቅደሱን ተልእኮም ደርበው ያዙ።
- በ1910 ዓ.ም. መምህር ኃይለ ማርያም ተብለው በወላይታ ሰዶ በሚገኘው ደብረ መንክራት ምሁር ኢየሱስ ገዳም ተሾሙ።
- በ1916 ዓ.ም. እንደገና በዝዋይ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም በመምህርነት ተሾሙ።
- በ1919 ዓ.ም. ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ማርቆስ መምህርና በቤተ መንግሥት የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አበ ንስሐ ሆኑ።
- የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ሺ ስድስት መቶ ዓመታት በኋላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዕውቀት መንፈሳዊ ከእርስዋ ተወልደው በዕቅፏ ውስጥ ባደጉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት እንድትመራ ፈቃዷን ስትገልጽ ከተመረጡት አባቶች አንዱ በመሆን ግንቦት 18 ቀን 1921 ዓ.ም. በእስክንድርያው መንበረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መዓረገ ጵጵስናን ተቀበሉ።
- ከዓመት በኋላም "አቡነ ጴጥሮስ ጳጳስ ዘምሥራቀ ኢትዮጵያ ተላዌ አሠሩ ለአቡነ ኢየሱስ ሞዓ" ተብለው በያኔው መንዝና ወሎ አገረ ስብከት ተሾሙ።
- በ1928 ዓ.ም. አረመኔው የኢጣልያ ፋሺስት በግፍ አገራችንን ለመውረር ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት በማለት ውቅያኖስ አቋርጦ በመምጣት ኢትዮጵያን ሲወርና ሕዝቧን፣ ሊቃውንቷን፣ ገዳማቷንና አድባራቷን በግፍ ሲጨፈጭፍ ያዩት ብፁዕነታቸው ወራሪውን ኃይል ከኢትዮጵያውያኑ አርበኞች ጋር በመሆን በጸሎት ሊዋጉት ቀረቡ።
- የወቅቱ የአገሪቱ መሪ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ከአረመኔው ፋሺስት ጦር ጋር በመፋለም ላይ የነበረውን አርበኛ ለማበረታታት ወደ ማይጨው በሔዱ ጊዜ ብፁዕነታቸው ተከትለው ሔዱ።
- ከዚያ እንደ ተመለሱም በታላቁ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ተሰባስበው የቤተ ክርስቲያን አምላክ በኢትዮጵያውያን ላይ የመጣውን ችግር እንዲያሥታግስ በጸሎት እየተጉ ወደ ነበሩት አባቶችና አርበኞች በመሔድ ለአገርና ለነጻነት መሞት ቅዱስ ተግባር መሆኑን በመስበክ ሁሉም እንዲጋደሉ ማሳሰብ እና ማትጋት ጀመሩ።
- ኋላም የገዳሙ መነኮሳትና የሰላሌ አርበኞች ይባሉ የነበሩት አርበኞች ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ወራሪውን ኃይል ሲወጉ አብረው በመምጣት ተሳታፊ ሆኑ። ከዚያም አርበኞቹ የቻሉትን ሁሉ አድርገው ወደ ሰላሌ ሲመለሱ ብፁዕነታቸው አዲስ አበባ ቀሩ። ብዙም ሳይቆዩ በጠላት እጅ ተያዙ።

ብፁዕነታቸው በተጠቀሰው ቀን በጠላት እጅ ከወደቁበት ቀን ጀምሮ በፋሽስት ጣልያን የጥይት እሩምታ በሰማዕትነት እስካለፉበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሒደት የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጋዜጠኞችና የታሪክ ጸሐፍት እንደሚከተለው ዘግበውታል።

"በኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ፤ ተከታዮቼን ግን አትንኩ" የሚለውን ቃለ ምዕዳን ለገዳዮቻቸው ፋሺስቶች ያስተላለፉት ስለ አገር ነጻነት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ክብር፣ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ሲሉ በሰማዕትነት ያረፉት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ናቸው።

ይህንንም የተናገሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዓለም ድኅነት ሕይወቱን ለመስጠት በዚያች በመከራ ሌሊት ሊይዙትና ሊገድሉት ለመጡት ለሮማውያን ጭፍሮች "ማንን ትፈልጋላችሁ? እኔ እንደ ሆንኩ አለሁላችሁ። እነሱን ግን ተዉዋቸው ይሒዱ" /ዮሐ.18÷8/ ሲል በተከታዮቹ ላይ መከራ እንዳይፈጽሙባቸው የተናገረውን ቃል ለሕይወታቸው መመሪያ በማድረግ፣ መስቀሉንም ተሸክመው በኋላ ለመከተልና ፍኖተ መስቀሉንም ተጉዘው የሰ





www.eotcmk.org

ማዕትነት አክሊል ለመቀዳጀት ነበር። ቆመው ሞትን በሚጠባበቁበት ጊዜ የዛሬ 68 ዓመት ሐምሌ 22 ቀን 1928 ዓ.ም. ነበር።

እ.ኤ.አ ሰኔ 15 ቀን 1936 ዓ.ም. አዲስ አበባ የገባው ቺሮ ፓጃሊ "ኮሪያሬ ዴስራ" የተባለው ጋዜጣ ወኪልና የምሥራቅ አፍሪካ ዜና መዋዕል አዘጋጅ የነበረ ሲሆን ስለ አቡነ ጴጥሮስ የተሰጠውን ፍርድና የተፈጸመውን ግድያ ባየውና በተመለከተው መንገድ እንደሚከተለው ጽፎ ነበር።

«ሐምሌ 22 ቀን 1928 አቡነ ጴጥሮስ ተይዘው ወደ ግራዝያኒ ቀረቡ። በዚህ ጊዜ አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊው ጳጳስ ቀርበው ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታስማ በአቡነ ጴጥሮስ ላይ አንዳች ነገር ማድረግ አይገባህም ሲሉ ለግራዝያኒ ነገሩት። ምክንያቱም ይላሉ አቡነ ቄርሎስ፡ አቡነ ጴጥሮስ ታላቅ ሰው ናቸው። በመሠረቱ ሊያዙ ባልተገባ ነበር። ከተያዙም ደግሞ ልትገድላቸው ትችላለህ። ነገር ግን በርሳቸው ላይ የምታደርገውን ነገር ሁሉ ለእስክንድርያው መንበረ ፓትርያርክ ምክር ቤት ሳታስማ ምንም ማድረግ አይገባህም አሉት።

አቡነ ቄርሎስ ይህን ማለታቸው በዲፕሎማቲክ ደረጃ ለዓለም ለማስማትና የአቡነ ጴጥሮስን ሕይወት ለማትረፍ አስበው እንደ ነበር ግልጥ ነው። ነገር ግን ግራዝያኒ ይህ የአቡነ ጴጥሮስ የሞት ፍርድ እንኳንስ እስከ ግብፅ ከአዲስ አበባ ውጭ እንኳ ከመስማቱ በፊት በግማሽ ቀን እንዲፈጸም ትእዛዝ አስተላለፈ።

ጸሐፊው ሲገልጥ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ቁመታቸው ረዘም፣ ፊታቸውም ዘለግ ያለ፣ መልካቸው ጠየም ያለ ዐዋቂነታቸውና ትሕናቸው ከገጻቸው የሚነበብ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለብሰውት የነበረው ልብሰ ጵጵስና ጥቁር ካባ ያውም በጭቃ የተበከለ ነበር። በዚህ ሁኔታ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ወደ ችሎት ቀረቡ። ለፍርድም የተሰየሙት ዳኞች ሦስት ሲሆኑ እነዚህም ጣሊያኖችና የጦር ሹማምንት ናቸው። የመካከለኛው ዳኛ ኮሎኔል ነበር። የቀረበባቸውም ወንጀል ሕዝብ ቀስቅሰዋል፣ ራስዎም ዐምፀዋል፣ ሌሎችንም እንዲያምፁ አድርገዋል የሚል ነበር። ዳኛውም «ካህናቱም ሆኑ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስም የኢጣሊያንን መንግሥት ገዥነት አምነው አሜን ብለው ሲቀበሉ እርስዎ ለምን ዐመፁ? ለምን ብቻዎን አፈንጋጭ ሆኑ?» ሲል ጠየቃቸው።

አቡነ ጴጥሮስም የሚከተለውን መለሱ። "አቡነ ቄርሎስ ግብፃዊ ናቸው፤ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚገዳቸው ነገር የለም። እኔ ግን ኢትዮጵያዊ ነኝ። ኃላፊነትም ያለብኝ የቤተ ክርስቲያን አባት ነኝ። ስለዚህ ስለ አገሬና ስለ ቤተ ክርስቲያኔ እቆረቆራለሁ። ከዚህ በቀር ለእናንተ ችሎት የማቀርበው ነገር የለኝም። ለፈጣሪዬ ብቻ የምናገረውን እናገራለሁ። እኔን ለመግደል እንደ ወሰናችሁ ዐውቃለሁ። ስለዚህ በእኔ ላይ የፈለጋችሁትን አድርጉ። ግን ተከታዮቼን አትንኩ" አሉ።

ኢጣሊያዊው ጋዜጠኛ ቺሮ ፓጃሊ «እኒህ ጳጳስ ሐቀኛ ነበሩ። ነገር ግን ለኢጣሊያ ለጋስዮን ታዝዞ የመጣው አስተርጓሚ ዳኞች የሚሉትን ብቻ ከማስተርጐም በቀር ጳጳሱ የሚናገሩትን ሐቀኛ ንግግር አላስተረጐመም። እኔ እንኳን የሰማሁት በአዲስ አበባ ለሠላሳ ዓመት የኖረው የእቴጌ ሆቴል ኃላፊ የነበረው የግሪክ ዜጋ ማንድራኮስ አጠገቤ ተቀምጦ ስለ ነበር የተናገሩትን ሁሉ ስለ ገለጠልኝ ነው። እኔ እንደ ሰማሁት ፍርዱን ለመስማት በብዛት የተሰበሰቡት ጣሊያኖችና ታዝዞ የወጣው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሐቀኛ የሆነውን ንግግራቸውን ቢሰሙ ኖሮ ልባቸው ይነካ ነበር» ይላል።

ሆኖም አስተርጓሚው በጳጳሱ ላይ ተጽዕኖ ስላሳደረባቸው እውነተኛ ንግግራቸው ሳይገለጥ እንደ ቀረ ይጽፋል። ቀጥሎም ብፁዕነታቸው በፍርድ ችሎት ላይ እንዳሉ ሕዝቡ ሁሉ ስለ ርሳቸው እያዘነ ሳለ መስቀላቸውን አውጥተው እየጸለዩ ሕዝቡን ባረኩ። ወዲያው የሞታቸው ፍርድ ሲሰማ ሕዝቡ በኢጣልያ የእጅ ሰላምታ ዓይነት እጁን እንዲያነሣ ታዘዘ። በዚያን ጊዜ አቡነ ጴጥሮስ የሞታቸው ሰዓት መድረሱን ዐውቀው ሰዓታቸውን ከኪሳቸው አውጥተው ተመለከቱ። በዚህ ጊዜ ሁሉ ምንም ፍርሃት አይታይባቸውም ነበር። የሞታቸውን ፍርድ ያነብ የነበረው ኢጣሊያዊ ዳኛ ግን ይንቀጠቀጥ ነበር። ታላቅ ፍርሃትም በፊቱ ላይ ይታይ ነበር።

«ይሙት በቃ» የተፈረደባቸው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በችሎት ፊት ለብዙ ሰዓታት ቆመው ስለ ዋሉና ደክሞአቸው ስለ ነበር ለመቀመጥ ፈልገው ዳኛውን በትሕትናና በፈገግታ ጠየቁት። እንዲቀመጡም ፈቀዱላቸው። በመጨረሻም የሞታቸው ፍርድ ከተነበበ በኋላ የፈረዱባቸውን ዳኞች ጸልየው በመስቀላቸው ባረኩዋቸው። ብፁዕነታቸው እስከ መቃብር አፋፍ ድረስ የፍርሃትና የድንጋጤ ምልክት ያይደለ ከልብ የሆነ ፍጹም የክብር ትሕትና ይታይባቸው ነበር።

የአገራቸው በጠላት መወረር፣ የሕዝባቸው መገደልና መታሰር፣ የቤተ ክርስቲያናቸው መደፈር እስከ ሞት ያደረሳቸውን እኒህን እውነተኛ ጳጳስ ለመግደል ሲወስዱ ጥይት አልፎ ሌላ ሰው እንዳይጐዳ ግንብ ይፈልግ ጀመር። ሩቅ ባለመሔድ ከመካነ ፍትሑ 10 ሜትር ርቆ ግንብ ያለው መግደያ ቦታ ተገኘና ወደዚያ ተወሰዱ። ከገዳዮቹም አንዱ «ፊትዎን ለመሸፈን ይፈልጋሉን?» ሲል ጠየቃቸው። «ይህ የአንተ ሥራ ነው» ሲሉ ብፁዕነታቸው መለሱ። ከመግደያውም ቦታ እንደ ደረሱ ወንበር ቀረበላቸውና ፊታቸውን ወደ ግንቡ ጀርባቸውን ወደ ሕዝቡ አድርገው እንዲቀመጡ ሆኑ።

ከዚያ በኋላ ስምንት ወታደሮች በስተ ጀርባቸው ሃያ ርምጃ ርቀው ተንበርክከው በተጠንቀቅ ቆሙ። ወዲያው አዛዡ «ተኩስ» በማለት ትእዛዝ ሲሰጥ ስምንቱም ተኩሰው መቱዋቸው። ግን በስምንት ጥይት ሳይሞቱ ቀሩ። መሞታቸውንና አለመሞታቸውን ለማረጋገጥ ዶክተር ተጠራ። ዶክተሩም እንዳልሞቱ አረጋገጠ። ከዚያም ሌላ ወታደር በሦስት የሽጉጥ ጥይት ራስ ቅላቸውን መትቶ ገደላቸው።

የብፁዕነታቸው አስከሬን ማንም እንዳይወስደው በአስቸኳይ ከአዲስ አበባ ውጭ ማንም በማያውቀው ቦታ በምሥጢር እንዲቀበር ተደረገ። በዚያች ሌሊት በአዲስ አበባ ውስጥ በየቤቱ ልቅሶና ዋይታ ሆነ» ሲል ጽሑፉን ይደመድማል። ይህም ጠላት የሰጠው ምስክርነት በካቶሊካዊው ፓፓ ቡራኬ አገራችንን የወረረውን የፋሽስት ጣሊያንን ጦር አረመኔነትና በአንጻሩ የታየውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጀግንነት ሲያረጋግጥ ይኖራል።

በተጨማሪም ደራሲና ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ «አቡነ ጴጥሮስ እንዴት ሞቱ?» ሲል ሙሴ ፓይላክን ጠይቆአቸው እርሳቸውም የሚከተለውን ተናግረዋል። «አቡነ ጴጥሮስ የተገደሉ ዕለት እዚያው ነበርኩ። መጀመሪያ በእጃቸው ይዘውት የነበረውን መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ተሳለሙት። ቀጥለውም የያዙትን መስቀል አማትበው ሕዝቡን ባረኩ። የኪሳቸውንም ሰዓት አውጥተው ካዩ በኋላ መልሰው ከኪሳቸው ከተቱት። ወዲያው ወታደሮች በሩምታ ተኩሰው ገደሉዋቸው። ይህ እንደ ሆነ አስገዳዩ ኮሎኔል ተመልካቹን ሕዝብ አጨብጭቡ ብሎ አዘዘና ተጨበጨበ።

ማታ ከአስገዳዩ ኮሎኔል ጋር ተገናኝተን ስንጫወት «በዚህ ቄስ መገደል እኮ ሕዝቡ ተደስቷል» አለኝ። «እንዴት?» ብለው አላየህም ሲያጨበጭብ አለኝ። እኔም «ባታውቀው ነው እንጂ የሕዝቡ ባሕል ሲናደድም ያጨበጭባል» አልኩት። «እንዴት?» ቢለኝ እጄን እያጨበጨብኩ አሳየሁት። እሱም አሳየኝ። «ከዚህ በኋላ የሆነው ቢሆን እኔ ትልቅ ማስታወሻ አግኝቼአለሁ» ብሎ አቡነ ጴጥሮስ ሲገደሉ ይዘውት የነበረውን መስቀልና መጽሐፍ ቅዱስ፣ የኪስ ሰዓታቸውን ጭምር አሳየኝ። መጽሐፍ ቅዱሱ መሐል ለመሐል በጥይት ተሰንጥቋል። መስቀሉም ልክ በመሐከሉ ላይ ጥይት በስቶት ወጥቷል። የኪስ ሰዓታቸውንም እንዳየሁት እንደዚሁ ጥይት በስቶታል» ብለው ያዩትን መስክረዋል።» /ትንሣኤ፣ ቁጥር 58፣ 1978 ዓ.ም./

የብፁዕነታቸውን አኩሪ ታሪክ ትውልድ ሲያዘክርላቸው እንዲኖር መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ ሐምሌ 16 ቀን 1938 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ እምብርት ሐውልት ቆሞላቸዋል። የተጋዳዩና ሰማዕቱ አባታችን በረከት ይደርብን። አሜን።



www.eotcmk.org

# «የጽሕፈት ቋንቋ የሆነውን የግእዝ ፊደላችንን ማወቅ ሕዝባችንን የበለጠ ያቀራርበዋል።»

*ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ /Ph.D.,D.H.L. (hon.)/*

ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ይባላሉ፡፡ የተወለዱት በኢትዮጵያ የቀድሞው ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ነጆ ከተማ [በዛሬው ምዕራብ ወለጋ ዞን] ግንቦት 21 ቀን 1929 ዓ.ም ነው፡፡ ፕሮፌሰር ኤፍሬም አሁን የ67 ዓመት አዛውንት ናቸው፡፡ ወላጅ አባታቸው እሥራኤላዊ /የየመን ይሁዲ/፣ እናታቸው ኢትዮጵያዊት ናቸው፡፡ በሞያቸው አንጥረኛ የነበሩት አባታቸው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ለጥቂት ጊዜ ከኖሩበት ድሬዳዋ ጓዛቸውን ይዘው ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ነጆ ከገቡ በኋላ ነበር እናታቸውን አግብተው እርሳቸውን የወለዱት፡፡ ወላጆቻቸውን ጨምሮ ገሚሱ የቤተሰባቸው አባላት ይሁዲ ሲኾኑ የተቀሩት ደግሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባልና ቤተ ሰብእ ናቸው፡፡ እንዲያውም በአንድ ገዳም የሚኖሩ መነኩሲት እኅት አለቻቸው፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ተወልደው ባደጉበት በነጆ፥ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተከታትለዋል፡፡ በፍልስፍና፣ በኬሚስ ትሪና በሙዚቃ ዲግሪዎች አሏቸው፡፡ በምሥራቅ ቋንቋዎች በተለይም ደግሞ በግእዝ ሥነ ጽሑፍ ላይ በሠሩት ጥናት ከሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል፡፡ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ እ.አ.አ ከ1968 እስከ 1977 ድረስ በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ በአፍሮ አሜሪካን ዲፓርትመንት የመጀመሪያው አፍሪካዊ ፕሮፌሰር በመኾን በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ በዚህም ወቅት «የዓመቱ ምርጥ መምህር» በመባል በዲፓርትመንቶችና በተማሪዎቻቸው ተመርጠዋል፡፡ በዚህም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ናቸው፡፡ በልዩ ልዩ ዘርፎችም እያሌ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን ተቀብለዋል፡፡ ከ1998 እ.ኤ.አ. ጀምሮም በአፍሪካ ጥናትና ምርምር ላደረገ የነጻ ትምህርት ዕድል የሚሰጥ ተቋም በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ በስማቸው ተመሥርቷል፡፡ በሂብሩ፣ በፕሪስተን፣ በሀዋርድ... በሌሎችም ከፍተኛ ዩኒቨርስቲዎች ተጋብዘው በሂብሩ መጽሐፍ ቅዱስ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ፣ በባርነትና በአፍሪካ ሥልጣኔ ወዘተ... ርእስ ጉዳዮች ዙሪያ ትምህርት ሰጥተዋል፡፡ በ21 ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥም ግልጋሎት ይሰጣሉ፡፡ የሥራ ባሕርያቸው ከኢትዮጵያ፣ ከአሜሪካ፣ ከእሥራኤል፣ ሕንድና የመን... ጋር ያገናኛቸዋል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተካሔደው የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ መሥራችና ርዳታ አሰባሳቢ ኾነው ሠርተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በአፍሪካ ቀንድ የሰላምና የልማት ድርጅት የቦርድ ሊቀ መንበር ናቸው፡፡



ፕሮፌሰር ኤፍሬም በግእዝ ቋንቋና ፊደል፡ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ቅዱሳት መጻሕፍትዋ ላይ የጻፏቸውን ጨምሮ የእያሌ መጣጥፎችና መጻሕፍት ደራሲ ናቸው፡፡ በርካታ መጻሕፍትን ተርጉመዋል፡ አሳትመዋል፡፡ እኒህን እንደበተ ርቱዕ፣ ግልጽ፣ ትሑትና አስተዋይ የኾኑ ምሁር ያገኘናቸው ሚያዝያ 20 ቀን 1996 ዓ.ም. "The Alphabet as Technology: Its Origin and Development" በሚል ርእስ በግእዝ ፊደላትና ሥነ ጽሑፍ የት መጣና ዕድገት ላይ ያተኮረ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ባቀረቡበት ወቅት ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከግእዝ ቋንቋ፣ ፊደላትና ሥነ ጽሑፍ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከእሉላ ጥላሁንና ተስፋዬ ሽብሩ ጋር ውይይት አድርገዋል፡፡ በእጅጉ ከተጣበበው ፕሮግራማቸው ጋር አጣጥመው በፈቀዱልን የ40 ደቂቃ ያህል ጊዜ ውስጥ ያደረግነውን ቆይታና በሌሎች ተዛማጅ ምንጮች ውስጥ በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የሰጧቸውን አሳቦች አጠናቅረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ከዚያ በፊት ግን ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅን ምን ያህል ቋንቋ እንደሚናገሩ በጠየቅናቸው ወቅት እግረ መንገዳቸውን በሚገባ በሚችሏቸውም ኾነ ለአካዳሚክስ ያህል በሚያውቋቸው ቋንቋዎች ሁሉ ለእናንተ ለአንባቢዎቻችን ሰላምታ እንዲያቀርቡ ጠይቀናቸው ነበር፡፡ እርሳቸውም «ሰላም ለክሙ» ብለው በግእዝ ቋንቋ በመጀመር፣ በአማርኛ፣ በትግርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በጉራጊኛ፣ በዕብራይስጥ፣ በግሪክኛ፣ በላቲን፣ በፈረንሳይኛ፣ በጀርመንኛ፣ በዐረብኛ፣ በስዊድንኛ፣ በመስኮብኛ፣ በደች፣ በጃፓን፣ በቻይናና በኮሪያ ቋንቋዎች «ጤና ይስጥልኝ፣ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን» ብለ



www.eotcmk.org

ዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስላል አንድ የውጭ አገር ጋዜጣ፡- «እኒህ ሰው የዓለም አስገራሚ ሰው ናቸው፡፡ የቋንቋ ክሂላቸው፣ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጥናቶቻቸው፤ የሁሉም ነገር ዕውቀታ ቸው፣ ለሰላም ያላቸው ጽኑ እምነትና ለዚህም የሚከፍሉት መሥዋዕትነት ወደር የለውም፡፡» ያለው፡፡ በቀጠሮችን መሠረት ወዳረፉበት ሒልተን ሆቴል ሔደን ስንገናኝ የጥያቄውን ቅድሚያ የወሰዱት እርሳቸው ነበሩ፤ «የት አለ ነጭ ልብስ የለበሳችሁት?» አሉን፡፡ ድንገተኛ ጥያቄ ነበርና ከመገረም በቀር ለጊዜው መልስ አልነበረንም፡፡ ይሁንና አጋጣሚው ውይይታችንን አለባበሳቸውን አስመልክቶ ከተናገሩት እንድንጀምር መንገድ ከፈተልን፡፡

## አለባበስ

### «ራሴን መሆኔ የሚሰማኝ አካሌን በአገሬ ሸማ ውስጥ ሳገኘው ነው፡፡»

በ1960ዎቹ አሜሪካኖች ስለ ኢትዮጵያ ብዙም አያውቁም ነበር፡፡ እኔ ንግግር እንዳደርግላቸው ጋበዙኝ፡፡ ዓላማው በአለባበሳችን፣ በምንበላው፣ በምንጠጣው እንዲሁም በባሕልና ወጋችን ላይ ያለኝን ዕውቀት እንዳጋራቸው ነበር፡፡ እንደሚታወቀው የምበላውን ወስጄ ለበርካታ ሰዎች ማሳየቱ አስቸጋሪ ነው፡፡ የምለብሰውን ግን ላደርገው እችላለሁ ብዬ የአገር ባሕል ልብሶችን መልበስ ጀመርኩኝ፡፡

በበርካታ መድረኮች ንግግር እንዳደርግ እጋበዛለሁ፡፡ አለባበሴም ባሕላዊ ሆነ፡፡ በእውነቱ በጣም ምቹ የሆነ አለባበስ እንዳለን ያወቅኹት ተግባራዊ ካደረግኹት በኋላ ነው፡፡ የኋላ ታሪኬን ስመለከት ትንሽ ልጅ ሆኜ እንደ ማንኛውም የባላገር ልጅ ነው አለባበሴ፡፡ የአውሮፓውያንን ሱፍ መልበስ የጀመርኩት ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪ ሆኜ ነው፡፡ የፈረንጅ ልብስ ምቾት አይሰጠኝም፡፡ የአሜሪካን ጉዞዬ ወደ ራሴ ቱባና ኦሪጅናል ባሕል እንድመለስ አደረገኝ፡፡

መቼም አንድ ሁለት ሱፍ ልብስ አላጣም፡፡ ግን እርሱን ስለብስ ራሴን የሆንኩ አይመስለኝም፡፡ በበርካታ ቦታዎችና በአያሌ ዩኒቨርስቲዎች እየተዘዋወርኩ ሳስተምርና ገለጻ ሳደርግ ይህንኑ ሸማችንን ለብሼ ነው መድረክ ላይ የምወጣው፡፡ ራሴን መሆኔ የሚሰማኝ አካሌን በአገሬ ሸማ ውስጥ ሳገኘው ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ እ.ኤ.አ በ1967 ለነበረው ትውልድ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ሰፊ ቃለ ምልልስ አድርጌያለሁ፡፡

ከአለባበሳችን ሳልወጣ በቆይታ የተረዳሁትን ልጨምር፡፡ ባሕላዊ የአበሻ ልብሳችን ነጭ ነው፡፡ ቶሎ ቶሎ ያድፋል፡፡ በዚህም እኔም ንጽሕናዬን መጠበቅ ስለሚያስደስተኝ ቶሎ ቶሎ አጥበዋለሁ፡፡ የሱፍ ልብስ ደግሞ ብዙ ጊዜ ቀለሙ ጥቁር ነው፡፡ ያድፋል፡፡ ለጤናም ጥሩ አይደለም፡፡ ስለዚህ ለጤናዬ የሚበጀው የአገሬ ሸማ ስለሆነ ምርጫዬ አድርጌዋለሁ፡፡ በአገራችን የምናዘወትረው የሱፍ ልብስ ከአውስትራሊያና ከእን ግሊዝ ነው የሚመጣው፡፡ ይህንን ሱፍ ልብስ በገዛሁ ቀጥር ገንዘቡ ገቢ የሚሆነው ለውጭ አገር ነጋዴዎች ነው፡፡ የአገሬን ሸማ ስለብስ ግን የአገሬን ሸማኔ የጠቀምኩት ያህል ይሰማኛል፡፡ ከምጣኔ ሀብት አኳያም በትንሹም ቢሆን አገሬን ደጐምኳት ማለት ነው፡፡ በዚያ ላይ ውብ ነው፡፡

አለባበሳችንን ልብ ብለን ስናስተውለው ፍልስፍናና ሳይንስ የሚሆንበትም ጊዜ አለ፡፡ እንደሚታወቀው አገራችን በምድር ወገብ አካባቢ ነው የምትገኘው፡፡ ስለዚህ የአገራችን ሰማይ ነጭ በመሆኑ የፀሐይ ብርሃንን ያንጸባርቃል፡፡ ሱፍ የምለብስ ከሆነ የፀሐይ ሙቀት ስለሚስብ እሰቃያለሁ፡፡ በዚህም ምቾቴን አጣለሁ፡፡ ሸማ ግን ፀሐይን ከማንጸባርቅ በተጨማሪ ብርድ ቢሆንብኝ ኩታዬን፣ ጋቢዬን፣ ከቻልኩም ቡሉኮዬን እከናነብና ቅዝቃዜውን እቋቋማለሁ፡፡ ይህንን አለባበስ ቤቴ በምውልበት ጊዜ አልጠቀምበትም፡፡ ቤቴን ስጠርግ አልያም አንዳንድ ሥራዎችን ስሠራ ሌላ ቀለል ያለ አለባበስ እመርጣለሁ፡፡ በማስተምርበት ወቅት ግን ሙሉ በሙሉ የምለብሰው የአገራችንን ሸማ ነው፡፡

አሁን አሁን ግን አሜሪካ ውስጥ እንዲህ ለብሶ መሔድ ትንሽ ያስፈራል፡፡ ከመስከረም አንዱ የኒውዮርክ አደጋ በኋላ ነገሮች ተወሳስበዋል፡፡ እንደምታውቁት እ.ኤ.አ 2001 መስከረም 11 ቀን በአሜሪካን አሸባሪዎች ችግር ፈጥረው ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ከቢንላደን ጋር አመሳሰሉኝ፡፡ ወዳጆቼም «በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ቀን ሥርዓተ ጸሎታቸውን አድርሰው ሲመለሱ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ተደብድበዋል፡፡ አንተም ተጠንቀቅ አትልበስ» አሉኝ፡፡ ለክፉም ለደጉም ብዬ አንድ ሁለት ሱፍ ልብሶችን ገዛሁ፡፡ ይሁን እንጂ አሁንም ሱፍ ስለብስ ምቾት አይሰማኝም፡፡ ሁኔታው እንደ ተረጋጋም እየተጠነቀቅሁ ቢሆንም ከዓመት በኋላ ወደ ራሴ የአለባበስ ባሕል ተመልሻለሁ፡፡ ከዚህ የወዳጆቼ ማስጠንቀቂያ በቀር እስካሁን በአለባበሴ ምክንያት ከባድ እክል ገጥሞኝ አያውቅም፡፡

## ሐበሻና ኢትዮጵያዊነት

### «የጽሕፈት ቋንቋ የሆነውን የግእዝ ፊደላችንን ማወቅ ሕዝባችንን የበለጠ ያቀራርበዋል፡፡»

ሊቃውንት «አበሻ» የሚለው ቃል ሐበሻት ከሚል ቃል ነው የመጣው ይላሉ፡፡ «ሐበሻ» የሚለው ቃል በሳባ ቋንቋ በተጻፈ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ ይገኛል፡፡ ሐበሻት በጥንቱ የሳባውያን ቋንቋ ሲፈታ «ባዕለ ጸጋ ሕዝብ» /Wealthy people/ ብለው ይተረጉሙታል፡፡ አንድ ኢርባን የተባለ ጸሐፊ እንደ ተናገረው «ሐበሻት የቦታ ስም ነው፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ነው፤ በደቡብ ዐረቢያ ኢንስክሪፕሽን ላይ ሲያዩ ያገኙት ነው» ይላል፡፡ እኔም በልጅነቴ የሊቃውንቱን መጻሕፍት ሳነብ «ድብልቅ ሕዝብ» የሚል ትርጉም እንደ ሰጡት ተገንዝቤያለሁ፡፡ አበሻ ከሚለው ቃል ነው «አቢሲኒያ» የሚለው ስያሜ የመጣው፡፡ በሴማውያን ቋንቋም «ሐበሻ» የተለመደ ቃል ነው፡፡ በኢየሩሳሌም ከተማ በዚህ ቃል የተሰየመ አንድ መንገድ ነበር፡፡ «ረኮቨ ያ ሓበሺ» ይሉታል፡፡ «የአቢሲኒያ መንገድ» ማለት ነው፡፡ በኋለኛው ዘመን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት መጠሪያው ይቀየር ብሎ «የኢትዮጵያ መንገድ» (Ethiopian Street) ተብሏል፡፡ ይህ ለእኔ ትልቅ ስሕተት ነው፡፡ ሐበሻት ጥሩ ቃል ነው፤ እንዲያውም እኔ የሚመስለኝ የነገድም ይሁን አይሁን «ሓበሻ» «ሀብታም ሕዝብ» ወይም «አሸናፊ ሕዝብ» ማለት ነው፡፡

ይህ የበለጠ መጠናትም ይኖርበታል፡፡ አብዛኛው ትርጓሜው ግን «ድብልቅ» እንደ ማለት ነው፡፡ ዐረቦች እኛን «ሓበሻ» ነው የሚሉን፡፡ በእኔ እምነት ታሪክን ለሚመረምር ይህ ስያሜ መጥፎ ገጽታ የለውም፡፡

ኢትዮጵያን በተመለከተ ደግሞ መጥቀስ እችላለሁ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጐመው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ284 ዓመት ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ግሪኮች ኩሽ የሚሉት በዕብራይስጥ ጥቁር ማለት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ «ኩሽ»ን ኢትዮጵያ እያሉ ተረጐሙት፡፡ እንደሚባለው ከሆሜር ጊዜ ጀምሮ ኢትኦፕስ ብለው ነው የሚጽፉት፤ ኢትዮጵያ ማለት ነው፡፡ «ኢት» አቃጠለ ማለት ሲሆን «ኦፕስ» ደግሞ ፊት ማለት ነው፡፡ የቃላቱን ትርጉም ስናጣምረው «የተቃጠለ ፊት» ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አገራችን መጥቶ ሲተረጎም ኢትዮጵያ ተባለ፡፡ በእርግጠኛነት ከዐሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያ በሚለው ጸና፡፡ በሌላ ገጽ ደግሞ ኢትዮጵያ «ጥቁር ሕዝብ» ማለት ነው፡፡ እኔ በዚህ ጉዳይ የሰበሰብኳቸው በርካታ ማስረጃዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ማስረጃዎቼ በአንድ ቅጽ የሰበሰብኳቸው ማፖች /ካርታዎች/ ናቸው፡፡ ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ መላውን አፍሪካ - ኢትዮጵያ፤ አትላንቲክ ውቅያኖስን - የኢትዮጵያ ውቅያኖስ፤ ምዕራብ አፍሪካን /ኢትዮጵያን/ ደግሞ ሪክሰን ዴታሌ ይለዋል፡፡ ወደ አሁኑ ጊዜ ላይ ስንመጣ አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ… ሕዝቦችን እናገኛለን፡፡ የሁሉም ፊት ጥቁር ነው፡፡ ሕዝቡም በባሕል፣ በእምነት፣ በአመለካከትና በሥነ ልቡናው ተመሳሳይ ነው፡፡ እናም ሕዝቡ አንድ ነው፤ ኢትዮጵያ ጥሩ ስም ነው፡፡ ይህ ለእኔ ኩራት እንዲሰማኝ ያደርገኛል፡፡

በተለይ በፊደላችን ልዩ ነን፡፡ በአግባቡ እየተጠቀምን እንድናሳድገው እመክራለሁ፡፡ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ይራመድ በነበረው አስተሳሰብ ፈረንጆች አፍሪካውያንን «ታሪክ የላቸውም» ብለው የሚናገሩት፣ «የጽሕፈት ቋንቋ የላቸውም» [Only cultures that have writings have history] ከሚል በመነሣት ነው፡፡ ስለዚህ የእኛ ፊደል ለመላው አፍሪካ ኩራት ሊሆን የሚገባው ነውና ሁሉም ሰው ይህንን ፊደል ማወቅ አለበት፡፡ ሕዝባችንንም በበለጠ ያቀራርበዋል፡፡ በእውነቱ የተለያየ ባሕል ያለው ሕዝብ የሚገኝበት በመሆኑ ልንኮራበት ይገባናል፡፡ የዓለማችን ችግር ሕዝቦች በቋንቋ፣ በዘርና



www.eotcmk.org

በባሕል መለያየታቸው አይደለም:: እንዲያውም ጸጋዋ ነው:: ትልቁ ችግር ራስን የተለየ አድርጎ ከማየቱ ነው የሚነሣው:: ሁሉም ሰው አንድ ዓይነት ቢሆን ኖሮ ሕይወት በጣም አታካች ይሆን ነበር:: አመጋገባችንንም እንደዚያው ልንወስደው እንችላለን:: በየዕለቱ ገብስ ብቻ ብንመገብ አታካችና አሰልቺ እንደሚሆን አያከራክርም::

## «ኢትዮጵያ 'ሞዛይክ' አገር ናት»

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ ዲ.ዐውደ ፖኤዝ የተባለ ፖርቱጋላዊ 'Fide Religio Morisco Ethiopi' - የኢትዮጵያ ሃይማኖትና የኢትዮጵያ ባሕል- በሚል ርእስ መጽሐፍ ጽፎ ነበር:: እዚያ ላይ «ኢትዮጵያ የምትባል አገር አለች:: የጥንት ክርስቲያን አገር ናት:: ነገር ግን እስላምም አለ፤ ይሁዲም አለ፤ ሕዝቡ በመከባበር፣ በሰላምና በፍቅር የሚኖርባት አገር ናት:: ብዙ ቋንቋዎችም ይነገራሉ:: እኛ አውሮፓውያን ግን በሰላም መኖር አልቻልንም:: ምንድን ነው÷ እዚህ አውሮፓ ውስጥ ፍቅር አልባ ነን::» በማለት ኢትዮጵያን እያመሰገነ፣ የአህጉሩን ሰዎች ደግሞ እየወቀሰ ጽፏል:: እንዲያውም በወቅቱ የሮማ ካቶሊክ «መጽሐፉ እኛን ይሰድባል» ብለው 'ኢንዴክስ' ላይ አስቀመጡት:: እንደምታውቁት በሮም ካቶሊክ ዘንድ 'ኢንዴክስ' ማለት «እንዳይነበቡ የተከለከሉ» ማለት ነው:: ቆይቶ አንድ እንግሊዛዊ ሰው /ሳሙኤል ጆንሰን ይመስለኛል/ ከላቲን ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተርጉሞታል::

የመጽሐፉ ደራሲ በዚያ መልኩ ስለ ኢትዮጵያ ለመጻፍ አሳቡን ያገኘው እንዲህ ነው:- በ1441 ዓ.ም በጣሊያን ፍሎረንስ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በተካሔደበት ወቅት በኢየሩሳሌም የዴር ሡልጣን ገዳም የነበሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ተገኝተው ነበር:: ከዚያ ወዲህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ወደ አውሮፓ ይሔዱ ነበር:: ለምሳሌ አንዱ ተስፋ ጽዮን ይባላል:: እርሱ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ግእዝ ቋንቋ በርካታ አውሮፓውያንን አስተምሯል:: በመሆኑም ደራሲው ተስፋ ጽዮንን የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያንን እየጠየቀ ስለ ኢትዮጵያ ሲመራመር የደረሰበት ድምዳሜ ምንድን ነው? «ኢትዮጵያ በእውነቱ <Mosaic> አገር ናት፤ በተለይ በእምነት በሃይማኖት እየተከባበሩ ነው የሚኖሩት::» የሚል ነው:: አሁንም እንግዲህ እኛም ቢዚህ መልኩ መቀጠል አለብን:: ለጊዜው በመካከላችን ችግር ተፈጥሮ ይሆናል:: በተለይ በቀድሞው ሥርዓተ መንግሥት ማኦኢስት፣ማርክሲስት፣ ሌኒንስት ብለን አገራችንንና ባሕላችንን አጥፍተናል:: እኔ እንዳመዛዘንኩት መቻቻል የሌለው በእኔ ጊዜ ትውልድ ውስጥ ነው:: የኔ ትውልድ አሁንም በጣም ያሳዝነኛል፤ ገና አልገባውም:: በዘርና በተለያዩ ምክንያቶች የሚጣላው እርሱ ነው፤ አይግባባም:: አዲሱ ትውልድ ግን ከዚህ ሕመም ነጻ የወጣ ትውልድ ነው:: እዚህ ትውልድ ላይ ተስፋ አለኝ:: ስለ ግጭት ስታወራለት አይፈልግም፤ ያለ መቻቻል በሽታ የለውም:: አሜሪካ ያሉት የኢትዮጵያ ወጣቶች በአገራቸው ታሪክ፣ ባሕል፣ ቋንቋ ላይ ነው ትኩረታቸው፤ ግጭት ላይ አይደለም:: በሌላ በኩል ያልተማረውን ኢትዮጵያዊ ጨምሮ፣ አርሶ አደሩ፣ ካህኑ ሕዝብን ያከብራል÷ ይከባበራል÷ ይፈቃቀራል÷ ትዕግሥት አለው÷ ረጋ ብሎ ነው የሚሔደው÷ ቀስ ብሎ ነው የሚያወራው:: እኔ እንዲያውም ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ እንኳ መለያየታቸው ያሳዝነኛል:: ይህ ሌላ አገር ቢሆን ኖሮ እየተተኳኮሱ አልቀው ነበር:: ስለዚህም የደራሲው ምስክርነት ትክክል ነው:: በምንም እንለያይ÷ ሰላምን መሻት፣ እየተከባበርን መኖር፣ በተለይ መንፈሳውያን የሆንን ደግሞ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌላውም ኢትዮጵያዊ አርአያ መሆን አለብን:: በአጠቃላይ ለማለት የፈለግሁት ምንድን ነው? ይሁዲዎችም ይሁኑ እስላሞች ሌሎችም ወገኖች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ማክበር አለባቸው:: ምክንያቱም የኢትዮጵያ መሠረት ናትና:: እናንተ ወጣቶች እዚህ ላይ መጠንከር አለባችሁ፤ ምክንያቱም ታናናሾችም ለታላላቆች ምሳሌ መኾን ይችላሉና::

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን÷ አንድነትና ሰላም

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመነ ፕትርክና አበው ጳጳሳት ሁሉ ጋብዘውኝ ባደረግነው ስብሰባ ላይ ምን አልኳቸው:- «ኢትዮጵያ የሚባለው፣ ሕዝቡንም አንድ የሚያደርገው÷ ፊደል በኢትዮጵያ መኖሩ ነው:: የፊደላት መልክና ቅርጽ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉሞበታል፤ አዋልድ መጻሕፍት ተጽፈውበታል:: በዚህ መልኩ ተጠብቆ ሌላው ዜጋ እንዲጠቀምበት ያደረገች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት:: በርግጥ የሌላውን እምነት ማክበር አለብን:: መሠረቱ ግን ይህ ነው:: የዛሬ ወጣትም ይህን ማሰብ አለበት:: የራስን ካላከበሩ ሌሎችን ማክበር አይቻልም:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሰላም መቆምን አጽንታ መቀጠል አለባት:: ከብሉያት መጻሕፍት ሁሉ የትንቢተ ኢሳይያስን መጽሐፍ እወዳለሁ:: መጽሐፉ <ሰዎች ጎራዴአቸውን ወደ ሞፈር የሚቀይሩበት ጊዜ ይመጣል፤ በሬ ከአንበሳ ጋር፣ ፍየል ከነብር ጋር የሚተኛበት ጊዜ ይመጣል> ይላል::

ከሁሉ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰላምን ካላስተማረች ማን ነው የሚያስተምረው? ውኃ አጠገብ የቆመው ካልጠጣ ሩቅ ያለው ምን÷ እንዴት ብሎ ይጠጣል?» ብዬአቸው ነበር:: ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባልና ቤተሰብ የኾናችሁ እናንተ ወጣቶች የሰላም መሪ መኾን ትችላላችሁ::

## ቋንቋዎች የተለያዩ ስለሆኑ ቋንቋን ተጠቅመን በመካከላችን ገለልተኝነትን መፍጠር ትክክል አይደለም::

ቋንቋ መማር ጥሩ ነው:: እንዲያውም ያበለጽገናል÷ ያቀራርበናል:: መቀራረብም አለብን:: ምክንያቱም ሁሉም በአንድ ምሽት ተመሳሳይ ቋንቋ መናገር አይችልም:: ሕዝብና ቋንቋ ይገናኛል:: ሁሉም በቋንቋው ነው የሚጠራው፤ አሁን ለምሳሌ ስዊዲን ማለት ስዊድሽ ነው የሚናገሩት፤ ጣሊያን ማለት ጣሊያንኛ ነው የሚናገሩት:: ነገር ግን ቋንቋ ደግሞ እንደ አካባቢው ነው እንጂ በመሠረቱ ሰውን የሚለየው ቋንቋው አይደለም:: ለምሳሌ አሜሪካን አገር የተወለዱ ልጆቻችን ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ነው:: አማርኛም፣ ኦሮምኛም፣ ትግርኛም አይችሉም:: ግን እንግሊዘኛ ይናገራሉ:: እና ቀደም ሲል እንዳልኩት በአገራችን ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን መናገር ያስከብራል እንጂ አያሳፍርም:: ቋንቋ ሰውን አይለይም:: ዋናው አሠራር ላይ ነው:: አሁን እኛ በኢኮኖሚ፣ በእርሻ አገሩ ምድሩ ራሱ ያስተባብረናል:: አንድ ነን:: ቋንቋዎች የተለያዩ ስለሆኑ ቋንቋን ተጠቅመን በመካከላችን ገለልተኝነትን መፍጠር÷ ሕዝባችንን መለያየት ትክክል አይደለም:: ቋንቋውን የዕውቀት የመግባቢያ ጉዳይ እናድርገው:: የሕዝብ መገናኛና መቀራረቢያ ስለሆነ ሁላችንም እንማረው:: ቋንቋን ማክበርና ማጠንከር አለብን:: እኔ እንደ ምታውቁት ብዙ ቋንቋ እወዳለሁ:: በፈለግሁት አገር ሔጄ ቋንቋቸውን ስናገር ጥሩ ስሜት ይሰጠኛል::

17 ዓይነት ቋንቋዎችን እናገራለሁ:: ከአገራችን ኦሮምኛ አማርኛን አሳምሬ አውቃለሁ:: ትግርኛም ለእግዚአብሔር ሰላምታ ያህል እሞክራለሁ:: ጊዜ ቢኖረኝ ደግሞ ሌሎቹንም እማራለሁ:: ግእዝን እዚያው ነጆ ነው የተማርኩት:: ወላጅ አባቴ ቋንቋቸው ዕብራይስጥ ነው:: የመን ውስጥ ስለ ተወለዱም ዐረብኛን ይችላሉ:: ስለዚህ በልጅነቴ እነዚህን ሁለት ቋንቋዎች ከአባቴ ተማርኩኝ:: ኮተቤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ስከታተል ፈረንሳይኛ፣ እንግሊዝኛና ላቲን አጠናሁ:: በኮተቤ ቆይታዬ ግእዝም በመጠኑ ተምሬያለሁ::

አሜሪካ ከሔድኩ በኋላ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የጀርመንና ግሪክ ቋንቋዎችን ተምሬያለሁ:: ሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ ስሔድ ደግሞ ከሞስኮብም፣ ከሶርያም፣ ከስዊድንም ጨማምሬያለሁ:: በእውነቱ እኔ ቋንቋ እወዳለሁ፤ ቋንቋ ማለት ለእኔ መዝሙር ነው:: ሰዎች በገዛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስታናገራቸው በጣም ነው ደስ የሚላቸው:: ስለዚህ ሁላችንም የሕዝቦችን ልዩ ልዩ ቋንቋ መማር አለብን::



'
www.eotcmk.org

## የግእዝ ቋንቋ ትምህርት
### «የግእዝ ቋንቋ ከሥርዓተ ትምህርቱ መሰረዙ ትልቅ ጥፋት ነው::»

ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለሁ ስለ ኢትዮጵያ እንጠየቃለን:: እንደ መታደል ሆኖ እኔ ከልጅነቴ ነው ግእዝን የመማር ዕድል ያገኘሁት:: ታስታውስ እንደሆን ግርማዊ ጃንሆይ በ1933 ዓ.ም በድል አድራጊነት ወደ መናገሻ ከተማቸው እንደ ተመለሱ ትምህርት ቤቶች በየጠቅላይ ግዛቱ ተከፈቱ:: በወቅቱ ግእዝን በየትምህርት ቤቱ እንዲያስተምሩ የትምህርት ሥርዓቱ ያዝዛል:: አንድ ሁለት ዓመት ትምህርቱ ተሰጠን:: ጥሩ ነበር:: በኋላ ለምን እንዳስቀሩት አላውቅም፤ የግእዝ ቋንቋ ከሥርዓተ ትምህርቱ መሰረዝ አልነበረበትም:: ይህ ለእኔ ትልቅ ጥፋት ነው:: እኔ ግን ዕድለኛ ስለሆንኩ ግእዝ ከመታገዱ በፊት ሁለት ዓመት ተማርኩኝ::

እናም አሜሪካውያን «ኢትዮጵያ ምንድን ናት?» እያሉ ሲጠይቁኝ መልሱን አሟልቼ ለማቅረብ ወደ ቤተ መጻሕፍት ሔጄ ፈተሸኩኝ:: በእኛ አገር ላይ የተጻፉ ብዙ መጻሕፍትን አገኘሁ:: ይህንን ዩኒቨርስቲው አላስተማረንም:: ስለ ሌሎች አገሮች ታሪክና ፍልስፍና ነው ያስተማሩን:: ይህ አሁንም ይገርመኛል:: አንድ ችግራችን እዚህ ላይ ይጀምራል:: እኔ አሜሪካን እንደ ገባሁ የከተሞቻቸውን ስም ሁሉ በቃሌ ሸምድጄ ዐውቃቸው ነበር:: ዋሽንግተን፣ ኒውዮርክ፣ አላባማ... ስንቱን ጠርቼ እዘልቀዋለሁ:: አገሬም ተሳስታ እኔንም ያሳሳተችኝ መሆኑም የገባኝ በኋላ ነው:: ትልቅ ስሕተት ነው:: ማወቅ ጥሩ ነው:: ግን ማወቅ ካለብኝ መጀመሪያ የራሴን፣ በመቀጠል የጐረቤቴን እያልኩ ዓለምን ማዳረስ ነው የሚገባው:: የራስን እየረሱ የሌላን መሸምደድ ግን «የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች» ይሆናል:: ራሱን የማያውቅ ሕዝብ ውጤቱ ጥሩ አይሆንም:: እናም ራስን በማወቅ ነው ማደግ የሚቻለው ብዬ ራሴን ለማወቅ ጥናቴን ቀጠልኩ::

ከዚህም ባሻገር አገሬን እንዴት የበለጠ ለማወቅ እችላለሁ ብዬ የሴማውያን ቋንቋ ጥናት (Semitic Studies) ውስጥ ገባሁ:: እዚያ እንግዲህ የዐረብኛ፣ የሶርያ፣ የዕብራይስጥ፣ የአረማይስጥ ቋንቋ ሁሉ ያስተምራሉ:: ታድያ ለምን ግእዝ አታስተምሩም ብዬ በመጠየቄ በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የነበረ አንድ ፕሮፌሰር ግእዝ እንዲያስተምር ምክንያት ኾንኩኝ::

ፕሮፌሰሩ በዜግነት አሜሪካዊ ነው:: ቶማስ ላሞዴን ይባላል:: የተለያዩ ሰዎች የግእዝ መጻሕፍት ሲልኩለት አንዱን ኮፒ ለእኔ ነው የሚልክልኝ:: ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚያስተምሩ ባለሞያዎች ንግግሩን አልያም ንባቡን አይደለም ትኩረት የሚሰጡት:: የእነሱን ትኩረት የሚስበው ሰዋስው ነው:: ሰውዬውን እኔ ሳስተውለው በዚህ ረገድ ታላቅ ሊቅ ነው:: «የግእዝ እንዲህ ነው የሚያልቀው፤ የዐረብኛ እንደዚህ ይጠናቀቃል» ብሎ ሁሉንም ሸምድዷቸዋል::

በርግጥ ጊዜ ልውሰድ ካለ ቁጭ ብሎ በማንበብ አሳቡንም መረዳት ይችላል:: ብዙ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚያስ ተምሩት ዕብራይስጥ ከግእዝ፣ ግእዝ ከዐረብኛ እንዴት ነው የሚገጣጠሙት ብለው ነው የሚተነትኑት:: ግእዙን በደንብ ያውቀዋል:: የግእዝ መዝገበ ቃላትም ጽፏል:: ሆኖም የግእዙን መጽሐፍም የጻፈው በላቲን ፊደል ነው:: በዚህ ቅር ብሎኝ ወቅሼዋለሁ:: አንዳንድ ወዳጆቼም ለምን በእኛ ፊደል አትመልሰውም ብለውኝ አሳቡን የምደግፈው ኾኖ ጊዜ አጣሁኝ:: ቶማስ ላሞዴን የመዝገበ ቃላት ጥናቱን ሲያካሒድ እያማከረኝ ከእኔ ጋር ብዙ ሠርተናል:: ቀደም ብሎ እሱ ያስተምር የነበረው ዕብራይስጥ፣ አረማይክና ሲሪያክ ነበር:: ግእዝም ትንሽ ተምሮ ስለ ነበር የሚያውቀው በሰዋስው ብቻ ነው:: አሁን ላስተካክል ቢል አይችልም:: ጡረታ ወጥቷል:: ሌላ የራሱም ችግር ይኖረዋል:: ዞሮ ዞሮ በሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የሴማውያን ቋንቋ ጥናት ክፍል ውስጥ የግእዝ ትምህርት እንዲሰጥ አነቃቃኋቸው፤ ውጤቱም ያማረ ኾነ::

### ግእዝና ዕብራይስጥ
### «ዕብራይስጥን ጠንቅቄ መቻሌ ግእዙን በቀላሉ እንዳውቀው አግዞኛል፤»

ግእዝና ዕብራይስጥ የሴም ቋንቋዎች ቤተሰቦች ናቸው:: የየመን ይሁዲ የኾኑት አባቴ የዕብራይስጥን ቋንቋ ጥሩ አድርገው አስተምረውኛል:: ለቤተሰባችን የመጀመሪያ መምህር አባቴ ናቸው:: ዕብራይስጥን ጠንቅቄ መቻሌ ግእዙን በቀላሉ እንዳውቀው አግዞኛል፤ በብዙ መልኩ ይቀራረባሉና:: ለምሳሌ ግእዝ «አቡነ ዘበሰማያት» ይላል:: በአረማይክ ደግሞ «አቡነ ዱበሰማያት»፤ ግእዝ «ይትቀደስ ስምከ» ሲል አረማይኩ «ይትቀደሽ ሽምካ» ይላል::

ግእዝ «ትምጻእ መንግሥትከ» ሲል አረማይኩ «ይምጻእ መልከተካ» ይላል :: እንዲህ እያልን ስንፈትሽ አያሌ ቃላት ተመሳስለው እናገኛለን:: በዚህም ዕብራይስጥን ቀድሜ ማወቄ ግእዝን እንዳውቅ ጥሩ መሠረት ሆኖልኛል::

ቃላት ብዙ ጊዜ የቋንቋን ዝምድና ሊያሳዩም ላያሳዩም ይችላሉ:: ነገር ግን አንዱ ከሌላው ይበደራል:: አሁን አውሮፕላን፣ ስልክ፣ መኪና፣ ኮት... ስንል ከሌላ ቋንቋ ተበድረን ነው የራሳችን ያደረግነው:: ዋናው የቋንቋ ዝምድና መገለጫ ግን ሰዋስዋዊ ትስስሩ ነው:: ግሡ፣ ተውላጠ ስሙ አንድ ሲያደርጋቸው ነው ትስስሩ ጠንካራ ነው የሚባለው:: አምፃ፣ ትምፃ፣ ይምፃ፣ ልምፃ፣ ትምፀ ይላል ግእዝ፤ በዕብራይስጥም እንደዚያው ነው::

### «ግእዝ እኮ ለላቲን ቅድመ አያቱ ነው»

የሁላችንንም ማንነት ለማወቅ ቋንቋችንና ባሕላችን መሠረቶች ናቸው:: ባሕላችን ከፊደላችን ጋር የተያያዘ ነው:: እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከአፍ መፍቻ ቋንቋው በተጨማሪ ኾነ ብሎ ሦስት ቋንቋ ቢያውቅ ጥሩ ነው:: ከዋናዎቹ ኦሮምኛ፣ አማርኛ፣ ትግርኛ፤ ከሌሎቹም መርጦ አራተኛ አድርጎ አንድ ቋንቋ ቢማር ጥሩ ነው:: ፊደሉ ግን አንድ መኾን አለበት:: የግእዝ ፊደል ከላቲን ይቀድማል፤ ግእዝ እኮ ለላቲን ቅድመ አያቱ ነው:: ስለዚህ ለአገራችን ቋንቋዎች የላቲኑን ፊደል መጠቀም እኛን ይለያየናል እንጂ ዋጋ የለውም:: ምክንያቱም የግእዝ ፊደል የአገራችን ክብር ነው፤ ለአገራችን ታሪክ ነው::

በርግጥ የግእዝ ፊደል የሁሉንም የአገራችንን ቋንቋዎች ድምፅ ለመወከል እጥረት ይኖርበት ይሆናል:: እንግዲያ ፊደል የተፈጠረው ለንግግር እንደ ሲምቦል ነው እንጂ የቱንም ቋንቋ መቶ በመቶ በፊደል መግለጽ አይቻልም:: ይህ በአገራችን ብቻ ሳይሆን በእንግሊዘኛ እንኳ ፕሮብሌም አለ:: ለምሳሌ በአንድ ወቅት ጆርጅ በርናንድ ሾው 'fish' ማለት ዓሣ ነው፤ 'fish'ን ጻፍ አሉት፤ እንደ ቀልድ አድርጎ 'ghoti' ብሎ ጻፈ፤ 'እንዴት እንዲህ አድርገህ ትጽፋለህ?' አሉት:: «ኢናፍ» (enough) ስንል 'gh'ን እንደ 'f' አይደለም ወይ የምናነበው አላቸው፤ እዎ÷ አሉት:: Nation /ኔሽን/ እንላለን፤ ስለዚህ 'ti' «ሽ» ነው አላቸው፤ በመሆኑም እኛ የምናነባቸውን ሁሉ መቶ በመቶ መጻፍ አንችልም:: አሁን በፈረንሳይኛ ቋንቋ ብዙ ፊደላት ይጻፋሉ፤ ግን አይነበቡም:: ይህም ማለት የሚጻፍ ነገር መቶ በመቶ አይነበብም:: 'ሲምቦል' እንደ ተማሩት ነው:: በኋላ ላይ ይለጠመዳል:: የቋንቋ ድምፆች ሁሉ በፊደላት ለመወከል ያለመቻል ችግር በአገራችን ቋንቋዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ያለ ነው:: *ይቀጥላል::*


**ነፍስዎን በንባብ ይመግቧት!!**

**ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ**

ትውፊት ምን እንደሆነ በዝርዝር በማቅረብ የሐዋርያትን ታሪክ፣ ሥራና ገድል በማሳወቅ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡ ቅዱሳንን ተጋድሎ ያቀርባል::

**አዋልድ መጻሕፍት እና መንፈሳዊነት በግቢ ጉባኤያት**

በብሔረሰብ፣ በባሕል፣ በጠባይ፣ በዕውቀት ያለውን መለያየት እዴት አቻችሎ መኖር እንደሚቻል በማሳየት ስለ አዋልድ መጻሕፍት በዝርዝር ታቀርባለች::

በሁሉም የሐመር መጽሔት እና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎቻችን ያገኟቸዋል !!

ስልክ - 22-86-01/23-45-29/23-45-30




www.eotcmk.org

ዲያቆን ደሳለኝ ቀለብ

## ተውሳከ ግሥ=አንቀጽ አጎላማሽ /Adverb/

ተውሳክ ማለት ወሰከ =ጨመረ፣ ተወሰከ ተጨመረ ካለው የግእዝ ግስ የተገኘ ተጨማሪ የሚለውን ትርጉም የያዘ የግእዝ ቃል ነው:: ተውሳከ ግሶች ማለት ከግሱ ላይ እየተጨመሩ የግሱን እንዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ የት፣ ወዘተ የሚሉትን የትርጉም ሁኔታ የሚወስኑ አንቀጽ አጎላማሾች ናቸው :: ቅጽል ስምን እንዲያጐላምስ ግስንም የሚያጐላምስ ቃል ተውሳከ ግስ ይባላል:: ምሳሌ:- ቀዩ ልጅ ትላንት መጣ:: ቀዩ የሚለው ቅጽል ልጅ ሚለውን ስም ሲያደምቅ /ሲገልጽ/ ትላንት የሚለው ደግሞ መጣ የሚለውን ቃል መቼ እንደሆነ የሚያመለክት ገላጭ ቃል ነው:: የቅጽል ዓይነቶችን ከፋፍለን እንዳየን ሁሉ የተውሳከ ግስ ዓይነቶችን ደግሞ እንዲህ ከፋፍለን እንመለከታለን::

### የታወቁ የተውሳከ ግስ ዓይነቶች /Kinds of Adverb/

1. **ኩነታዊ /Adverb of manner/**
ፍጡነ - በፍጥነት quickly
" " Fast
2. **መካናዊ /Adverb of place/**
ዝየ - እዚህ here ታህተ - ታች below / down /
ከሀ /ሀየ/ - እዚያ there ጥቃ /ገቦ/ - አጠገብ near
ላዕለ - በላይ - above/ up ለፌ ወለፌ -ግራና ቀኝ /Left and Right/
3. **ጊዜያዊ /Adverb of Time/**
ዮም - ዛሬ - Today ይእዜ - ዛሬ Today
ጌሠም - ነገ - Tomorrow ናሁ - አሁን Now
4. **የደጊመ ጊዜ /Adverb of Frequency/**
ኩለሄ - ሁሌ Usually ዳግመ = Secondly /ሁለተኛ ጊዜ/
ክልኤ ጊዜ - ሁለት ጊዜ Twice
ዋሕድ ዋሕድ ጊዜ - Some time
ወትረ - ሁል ጊዜ Always ዘልፈ - ሁል ጊዜ
5. **ርግጠኝነት የሚገልጽ /Adverb of Certainty/**
እሙነ - በእርግጠኝነት Surely
እሙረ - በታወቀ ሁኔታ definitly
ክሡተ - " " Obviously
6. **የከፍታን ገላጭ /Adverb of Degree/**
ጽድቀ - በአግባቡ Fairly ኃይለ - በኃይል
ጥቀ፣ ደርገ - በጣም - Very
ንዕሰ - ባነሰ - Poorly
7. **መጠይቃዊ - Interrogative**
ማዕዜ - መቼ - When ማእዜ ሖርከ፥ መቼ ሔድክ
አይቴ - የት - Where
ለምንት - ለምን - Why
8. **ተዛማጅ /Relative/**
በጊዜ - - - - በ - ጊዜ
ምሳሌ:- በጊዜ መጻእከ -
/ በመጣህ ጊዜ /

በዘነበርከ - በተቀመጥክበት ቦታ
ለምንት ከመ ሖርከ- ለምን እንደሄድክ
+ ከዚህ በመቀጠል ለስምንቱ አንዳንዶቹንና ሌሎችን የንዑስ አንቀጽ ተ. ግሶችን /Adverb clause/ ትርጉምና አገልግሎት እንማራለን::

**ሀ. የጊዜ ተውሳከ ግሶች /Adverb of time/** :- የጊዜ፣ የግስ ተውሳኮች ጊዜን የሚገልጡ ወይም ድርጊት "መቼ" እንደ ተፈጸመ የሚጠቁሙን የተውሳከ ግስ ዓይነቶች ሲሆኑ እነዚህም

ዬም - ዛሬ / Today/
ትማልም - ትላንት /Yesterday/
ጌሠም - ነገ- Tomorrow
ቅድመ ትማልም - ከትላንት በፊት- Before yesterday
ድኅረ ጌሠም - ከነገ በስቲያ - After tomorrow
ቅድመ ዝ ዓመት ከዚህ ዓመት በፊት - Before this year
ዘዮም ዓመት - የዛሬ ዓመት - Year after now
ሳምንት - ሳምንት - Week
ዘልፈ - ዘወትር /Every day/
ወትረ - ዘወትር /Every day/
ለለ /በበ/ ዕለቱ - ዕየለቱ /Every day/
ዋሕድ ዋሕድ ጊዜ - አልፎ አልፎ /Some times/
ወርኅ - ወር /Month/
ዘዮም ወርኅ - የዛሬ ወር /A month before or after now/
አውራኅ - ወሮች /Months/
ዓመት - ዓመት /Year/ - ዓመተ Yearly /በ ዓመት/
ዓመታት - ዓመቶች - /Years/
ሣምንታት - ሳምንታት - /Weeks/
ዕለት - ቀን - /Day/
ጽባሕ - ጧት /Morning/
መዓልት - ቀን - /Day/
ቀትር - ቀትር - /After noon/
ክ. ዘመን - ክ. ዘመን - /Century/
ሺህ - ሺህ - /Millennium/
ናሁ - አሁን - /now/ እነሆ/ Behold/
መንፈቀ ሌሊት - የሌሊት ግማሽ /Midnight/
ቀዳማይ መንፈቅ - የመጀመሪያ ወሰን /First semester/
ካልአይ መንፈቅ -የሁለተኛው ወሰን /Second semester/

በተውሳከ ግስነት ጊዜ መለወጥ ያለባቸው ቃላት የመጨረሻ ፊደላቸውን ወደ ግእዝ ይለውጣሉ:: በእንግሊዝኛው "Y" ን ይጨምራሉ:: የመጨረሻው ግእዝ ፊደል = "Y"
በ /የ /.......... ካልሆነ «በ»ን መጠቀም የግድ ነው
ዓመት - ዓመተ በ ዓመት - Yearly
መዓልተ - በቀን - Daily
በበዕለቱ - በየቀኑ - Daily
በበዙ ዕለቱ - በየቀኑ- Daily
በበወርኁ - በየወሩ - Monthly
በበ ወርኁ - በየወሩ - Monthly
በበዓመቱ - በየዓመቱ - Yearly

በጊዜ ተውሳከ ግስ ጊዜ ምሳሌ

#### ምሳሌ

ዮም ተወልደ ለነ መድኅኔዓለም
የዓለም መድኃኒት ዛሬ ተወለደልን::
" ግእዝ ትማልም፣ ዮም ወጌሠም ::
" ግእዝ ትላንት ዛሬ እና ነገ "Geez yesterday today and tomorrow "
ወተፈጸመ ቀዳማይ መንፈቀ ትምህርት

በጊዜ ተውሳከ ግስ ጊዜ መጠይቃዊ ተውሳከ ግሥ የሚሆኑት When - መቼ - ማእዜ፣ የመሳሰሉት ናቸው::
አመ፣ ጊዜ ጊዜ
መዋዕል፣ ዘመን /ወቅት/ - መዋዕለ ጾም - የጾም ወቅት
ዕለት - ዕለት - ዕለተ ሰንበት - የሰንበት ዕለት - ዓመተ ምሕረት /የምሕረት ዘመን/

**ለ. ኩነታዊ /Manner Adverb/**
ቅጽል - ፍጡን - ፈጣን - Quick/ Fast/
ተ. ግስ - ፍጡነ - በፍጥነት- Quickly /Fast/
ቅጽል - ጽሚት - Slow- ቀስ ያለ
ተ.ግስ - ጽሚተ - Slowly- በቀስታ
ዳኅና - ደኅና፣ በደኅና /Well/

#### ምሳሌ

አነ መጻእኩ ፍጡነ - በፍጥነት መጣሁ - I come quickly
ፍጡን ውእቱ - ፈጣን ነው - He is fast
ሮፀ ኃይሌ ፍጡነ - ኃይሌ በፍጥነት ሮጠ - Haile ran fast
ዳኅና ውእቱ - He is well - ደኅና ነው::

ይቀጥላል



www.eotcmk.org

# ምሥጢረ ሥጋዊ በውዳሴ ማርያም...

/ከገጽ ፲፭ የዞረ/

## ቃል ኪዳኑን ስላሰበ

አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለማክበር የጠላትን እኩይ ምክር ሰምተው የተከለከለውን ፍሬ በበሉ ጊዜ ጸጋቸው ተገፏል:: ባሕርያቸውም ጎስቁሏል:: የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ አክብረው ባለመገኘታቸው ከገነት ተባርረዋል:: ዘፍ. 3÷23:: «የተከለከለውን ፍሬ በበላህ ጊዜ ሞትን ትሞታለህ» ተብሎ ስለ ተደነገገ ትእዛዙ ደግሞ ስለ ተጣሰ የሞት ፍርድ በአዳምና በልጆቹ ሁሉ ላይ ተበይኗል:: አዳምና ሔዋን በመሐሪው አምላክ ፊት በተወሰነባቸው የሞት ፍርድ ብዙ ስላዘኑና ስለ ጸለዩ እግዚአብሔር ከሰይጣን ተገዢነት ነጻ እንደሚያወጣቸው ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል:: «በኀሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለደ እምወለተ ወለትከ፤ በአምስት ቀናት ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ::» መጽ.ቀለሜንጦስ:: የዚህን ቃል ኪዳን ተፈጻሚነት በነቢያት አማካይነት ለልጅ ልጆቻቸው ገልጾ አናግሯል:: ሚክ.5÷2፤ ዘካ.2÷10–11::

## ትንቢት ለመፈጸም

እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ለማዳን ወደ ሰው ያደረገው አምላካዊ ጉዞ እንደ ውኃ ፈሳሽ እንደ እንግዳ ደራሽ ሳይሆን ቅድመ ሥጋዌ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ሰውን በምን ዓይነት ጉዳና እንደሚያድነው በቀደምት ነቢያት ትንቢት አናግሯል:: የተነገሩት ትንቢቶች ያለምንም ታሪካዊ ተፋልሶ በየጊዜአቸው ተፈጽመዋል:: በቀደምት ነቢያት የተነገረው በጌታችን ጊዜ በትክክል ፍጻሜ ያገኙ ትንቢቶች መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያናገረውን ትንቢቱን ለመፈጸሙ ዘመን የማይሽራቸው አማናዊ ምስክር ናቸው:: ከዚህ በማስከተል ለአብነት ያህል በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከተነገሩት ትንቢቶች መመልከት ጌታችን ነቢያት የተነበዩለትን ትንቢት መፈጸሙን ይመሰክራል:: «እነሆ:– ድንግል ትጸንሳለች፤ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙን ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ኢሳ.7÷14:: ጌታችን በዘመነ ሐዲስ ትንቢቱ ስለመፈጸሙ እንዲህ ብሏል:: «ከእናንተ ጋር በነበርሁ ጊዜ በሙሴ ሕግ በነቢያትና በመዝ ሙር መጻሕፍት ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ መፈጸም አለበት ብዬ የነገርኋችሁ ቃል ይህ ነው::» የሐዋ.3÷ 22– 24:: በተጨማሪ የሚከተሉትን ነጥቦች ይመልከቱ:: ኢሳ.9÷6፣ኢሳ.53 ÷4–5፤ ዳን.7÷13–14:: ቅዱስ ጳውሎስም ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ እንዲህ ይላል:: «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናገረ...» ዕብ. 1÷1::

ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ ተናገረን ይላል:: ዕብ.1÷1:: ሐዋርያው በብዙ ዓይነትና በብዙ ጉዳና በማለት በግርድፉ ያስቀመጣቸው ቃላት ትንቢትና ምሳሌ ናቸው::

*ይቀጥላል*

# ወጣትነት እንደ ዮሴፍ...

/ከገጽ ፳፯ የዞረ/

## 5ኛ በራስ መተማመን

በራሱ መወሰን የማይችልና የማይተማመን ሰው ሌሎች በእርሱ ላይ እንዲወስኑ የፈቀደ ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የማይፈልገው ነገር በእርሱ ላይ እንዲወሰን መንገድ መክፈት ነው::

በራስ መተማመን የሚመጣው በማናቸውም መልኩ ሙሉ ሆኖ ሲገኙ ነው:: መንፈሳዊ ወጣት ደግሞ ሥራው ሁሉ ውጤታማ እንዲሆን የሚጥር በአምላኩም ታምኖ የሚኖር በመሆኑ ለሚወስነው ውሳኔ ለሚያደርጋቸው ማናቸውም ነገሮች ትክክል እንደ ሆኑ አረጋግጦ ማድረግ ይገባዋል::

ቅዱስ ዳዊት እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደ ነበር ስለሚያምን በራሱ ይተማመን ነበር:: በችግር ውስጥ ቢሆንም አይፈራም:: «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሔድ አንተ ከኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም» /መዝ.22÷4/ በማለት ነበር የሚጓዘው:: አስፈሪ ነው የተባለውን ጎልያድን ለመፋለም ሲወጣ በእጁ የያዘው መሣሪያ አልነበረም:: ነገር ግን እንደ ተራራ የከበደው ታላቅ ተብሎ የሚጠራው ጎልያድን ድል አደረገ:: ሰው በእግዚአብሔር ታምኖ ራሱን ባለበት ቦታ ሁሉ እየገለጠ ከኖረ አሸናፊ ነው፤ ድል አድራጊ ነው:: ዮሴፍ በስደት ላይ ራሱን ገልጧል፤ በእስር ቤትም ራሱን ገልጧል::÷ በሹመትም እያለ አልደበቀም ራሱን ገልጧል:: ስለሆነም ሁሉንም በድል አድራጊነት ለመወጣት በቅቷል::

## 6ኛ. መልካም አስተዳደር

በጥጋብ ዘመን የረኀብ ዘመን እንዳለ፣ በሰላም ዘመን የጦርነት ዘመን እንደሚመጣ በደዌ ዘመን የድኅነት ዘመን እንደሚመጣ መረዳት መልካም አስተዳደር ነው:: ዮሴፍ የሥራ ክቡርነትን የሚያውቅ ዕረፍት የለሽ ሥራዎቹ ሁሉ የተቃኑለት ታታሪ ሰው ነበረ:: በጥጋብ ዘመን ያከማቸው እህል ለረኀቡ ዘመን መውጫ እንዲሆን አድርጓል:: የዘመኑ ወጣትም በተሰማራበት የሥራ መስክ በቅንነትና በታማኝነት ህገሩንና ወገኑን በመልካም አስተዳደር ማገልገል ይጠበቅበታል:: አድልዎ የሌለበት ሥራ መሥራት ከሙስና /ከጉቦ/ የጸዳ ተግባር ማከናወን የሚቻለው መንፈሳዊነት ሲኖር ነው:: መንፈሳዊ ወጣት ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር እውነተኛ ሥራ ይሠራል:: ትክክለኛ ተግባር ደግሞ ከመንፈሳዊ ወጣት የሚጠበቅ ሲሆን ይህን በማድረጉም በኀብረተሰቡ ዘንድ ፍቅርና ከበሬታን ብሎም የሀገርን ዕድገት የሚያመጣ ነው:: በእግዚአብሔር ዘንድም ሰማያዊውን በረከት ያሰጣል::

የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የእመቤታችን አማላጅነት፣የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን:: አሜን

# ታላቁ ቅዱስ አርሳንዮስ...

/ከገጽ ፳፪ የዞረ/

ይህንን ስትሰማ በጣም ከማዘንዋ የተነሣ ታማ እስክንድርያ ስትደርስ ለሊቀ ጳጳሳት ቴዎፍሎስ «አንቺ ሴት እንደ ሆንሽና ቅዱሳንንም ሰይጣን በዘመደ አንስት እንደሚዋጋቸው አታውቂምን? እርሱ እንዲያ ያለሽ ስለዚህ ነው÷ ስለ ነፍስሽስ ሁልጊዜ በጸሎት ያስብሻል÷ አሁንም ስለ አንቺ ከመጸለይ ችላ አይልም፤ ስለዚህም አሁን ከሕመምሽ ትድኛለሽ» አላት:: ወዲያውም ከሕመሟ ተፈወሰች፤ እርስዎም ቅዱስ ቴዎፍሎስ የነገራትን ተረድታ ደስ ብሏት ወደ አገሯ ገባች::

ሊቀ ጳጳሳት ቴዎፍሎስም እርሱ ወዳለበት በረሃ ሔዶ ይገናኘው ዘንድ ለመጠየቅ መልእክት በላከበት ጊዜ አርሳንዮስ «አንተ ከመጣህ እቀበልሃለሁ÷ አንተን ከተቀበልኩ ደግሞ ሌላውንም የሚመጣውን ሁሉ እቀበላለሁ÷ ሁሉንም የምቀበል ከሆነ ደግሞ እዚህ ቦታ ብቻዬን መኖር አልችልም» ሲል መለሰለት:: ይህንን በሰማ ጊዜ ሊቀ ጳጳሳቱ «የእኔ መሔድ ለአረጋዊ የማይመች ከሆነ ይቅርብኝ» አለ::

ቅዱስ አርሳንዮስ ውዳሴ ከንቱን እስከ መጨረሻው ፈጽሞ የጠላና ከዚህ ታላቅ ፆር የራቀ ነበር:: ከዚህም የተነሣ «ከሞትኩ በኋላ ስሜን በጸሎትና በቅዳሴ አስታውሱኝ እንጂ በስሜ የሚጠራ ምንም ቤተ ክርስቲያን እንዳትሠሩ» አላቸው:: ከንጉሡ ባለሟሎች አንዱ የባዕለ ጸጋ ዘመዱን የውርስ ደብዳቤ ይዞለት መጣ:: አርሳንዮስ ይህንን ሀብት እንዲወርስ ሟች ዘመዱ እንደ ተናዘዘለት ይገልጻል፤ አርሳንዮስ ይህን ደብዳቤ ሊቀደው ሲል የተላከው ሰው ከእግሩ ላይ ወድቆ «በእኔ ላይ ችግር ስለሚደርስብኝ አትቅደደው» ብሎት ተወው:: «እኔ ከዚህ ሰው በፊት የሞትኩ ስለሆነ የእርሱ ወራሽ ልሆን አልችልም» አለው:: አኃው ምክረን ባሉት ጊዜም «በተናገርሁ ቁጥር የምጸጸትበት ነገር አጥቼ አላውቅም÷ ከዝምታዬ ግን ምንም ጸጸት አልገጠመኝም» አላቸው::

ቅዱስ አርሳንዮስ እስከ ዘጠና አምስት ዓመት ድረስ ፈጣሪውን እያገለገለ በተጋድሎና በብሕትውና ኖረ:: ወደ አገለገለውና ወደሚወደው ፈጣሪው የሚሔድበት ጊዜ ሲደርስ አኃው ሲያለቅስ ዐይ ተውት:- «አንተም እንደ ሌሎች ሞትን ትፈራለህን? ለምን ታለቅሳለህ?» አሉት:: ቅዱሱም «አዎ÷ በጣም እፈራለሁ÷ ሞትን ማሰብና መፍራትም ወደዚህ በረሃ መጀመሪያ ከመጣሁበት ጊዜ ጀምሮ ተለይቶኝ አያውቅም» አላቸው:: ቅዱስ አርሳንዮስ በፊቱ ደስታና ሰላም እየተነበበ ተጋድሎውንና ሩጫውን ጨርሶ ግንቦት 13 ቀን 445 ዓ.ም ዐረፈ:: የተጋዳዩ አባታችን የቅዱስ አርሳንዮስ ልመናው ይደረግልን÷አሜን::



www.eotcmk.org

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አስቸኳይ መመሪያ የሰጠበትን የአምስት ዓመት የፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ ስትራተጂ በማስመልከት የተሰጠ መግለጫ

## «ትውልድን የማዳን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮ»

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከሚያዝያ 27 እስከ ግንቦት 6 ቀን ባደረገው ጉባኤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስንና ያስከተለውን ጉዳት ለመቀነስ፣ ብሎም ለመግታት የምታደርገውን ጥረት በተጠናከረና ፍሬያማ ሊሆን በሚችል መልኩ የሚያስቀጥል የአምስት ዓመት ስትራተጂ በሥራ ላይ እንዲውል መመሪያ ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሀገራችን መጸኢ ዕድል ላይ አደጋ እንደ ደቀነ ታምናለች። በሀገሪቱ ታሪክ ከነበራት ጉልህ ሚና አንጻርም የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭትና ያስተከለውን ጉዳት ለመግታት ከፍተኛ አስተዋፅዖ የማድረግ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ኃላፊነት እንዳለባትም ቤተ ክርስቲያኒቱ ትገነዘባለች። ከዚህ በመነሣት እስከ አሁን በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ አካሎች ሲካሔድ የነበረውን ጥረት የበለጠ የሚያጠናክር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮግራም የአምስት ዓመት ስትራተጂ አዘጋጅታ እንቅስቃሴ ጀምራለች።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ከ40 ሚልዮን ያላነሱ ተከታዮች፣ 500,000 አገልጋዮች፣ 40,000 ገዳማትና አድባራት /አብያተ ክርስቲያናት/አሏት። ይህንን ሰፊ ኃይል ለማቀናጀትና ለመምራት የሚያስችሉ 40 አህጉረ ስብከት እና 35,000 የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትም በመላ ሀገሪቱ ተደራጅተው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት በማበርከት ሰፊ ልምድ አካብተዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና አገልጋዮቿ፣ በተከታዮቿም ሆነ በተቀሩት የሀገሪቱ ዜጎች እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት ዘንድ ባላቸው ተቀባይነትና ተአማኒነትም በፀረ - ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴው ከፍተኛ ኃይል /የሰው፣ የቁሳቁስና የገንዘብ/ ልታንቀሳቅስ እንደምትችል ይታመናል። ይህም ቤተ ክርስቲያኒቱ በፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትግሉ ውስጥ ውጤታማ ሥራዋን ለመሥራት የተሻለ ዕድል እንደሚሰጣት በቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችና በባለሞያዎች ታምኖበታል። አሁን የጸደቀው የአምስት ዓመት ስትራተጂም ይህንኑ ወደ ተግባር የሚለውጥ ነው።

ስትራተጂው በዋነኛነት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማት እንቅስቃሴዎች በሚመሩበት የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ስር በሚገኘው የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ አስተባባሪነት የሚመራ ነው። ስትራተጂው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በቤተ ክርስቲያኒቱ የአገልግሎት መድረኮች ሁሉ በአጀንዳነት የሚቀርብበትን፣ አገልጋዮች ስለ በሽታው ሰፊና ተከታታይ ሥልጠናዎችን አግኝተው የሚያስተምሩበትና ትክክለኛ መረጃ የሚተላለፍበትን መንገድ ያመቻቻል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ስትራተጂ በሀገር አቀፉ /ብሔራዊ/ ፖሊስ ማዕቀፍ የትኩረት አቅጣጫ ተደርገው በተመረጡት ጉዳዮች ላይ አተኩሮ ይንቀሳቀሳል። በከፍተኛ የውጭ አማካሪዎችና የቤተ ክርስቲያኒቱ ባለሞያዎች የተዘጋጀው ይህ የአምስት ዓመት ስትራተጂ ቤተ ክርስቲያኒቱ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት፣ ሕሙማንን ለመደገፍ፣ ኅብረተሰቡን መሠረት ባደረገ አሳዳጊ አልባ ሕፃናትን ለመከባከብና የትምህርትና የመረጃ መለዋወጫ መድረኮችን ማዘጋጀትን፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ምክርና ምርመራን በማበረታታት በተለይም በምክር አገልግሎት አካባቢ የሚታየውን ክፍተት ማጥበብን በአጠቃላይ መልኩም በአስተማማኝ ደረጃ የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ያላትን እምቅ ኃይል /Potential/ በዝርዝር በመመልከት ጥቅም ላይ የሚውልበትን አቅጣጫ ለይቶ አስቀምጧል።

ይህ የፕሮግራም ስትራተጂ ከዚህ ቀደም ከተሞከሩት በተለይም የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች በዘላቂነት የሚቀጥሉበትን አቅጣጫ አስቀምጧል። ከዚህ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ዝርዝር ተግባራት በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት /እ.ኤ.አ. 2004-2008/ ውስጥ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙት 35,000 የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያትና በማኅበረሰቡ ማዕከልነት ተግባራዊ ይደረጋሉ።

### ምን ያስፈልጋል?

ይህንን የአምስት ዓመት ፕሮግራም ስትራተጂ ለማስፈጸም አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ርዳታ ያስፈልገዋል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኒቱ እስካሁን በአነስተኛ መጠን የምታገኘው ርዳታ በቂ አይሆንም። በገንዘብ በኩል የተቀናጀ የለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ የሚጠበቅ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ በኩልም ለዚሁ ጉዳይ ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ለመመደብ ተወስኗል። በተጨማሪም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሚሆነው ኅብረተሰብ በየደረጃው የአሳብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ ድጋፍ እንዲሰጥ የሚያስችል ሁኔታ መኖሩ ታምኖበታል።

በቤተ ክርስቲያኒቱ ለፕሮግራሙ ከሰጠነው ትኩረት አኳያም ከአሜሪካ መንግሥት በቅርቡ የተገኘው የአምስት ሚልዮን ዶላር ርዳታ በፕሮግራሙ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲተገበር ተወስኗል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ለዚህ ስትራተጂ ተፈጻሚነት ሁሉም የቤተ ክርስቲያኒቱ ክፍሎችና አገልጋዮች የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በትጋት እንዲፈጽሙ ጥብቅ መመሪያ በየደረጃው እንዲተላለፍ ወስኗል። ስትራተጂው ከቤተ ክርስቲያኒቱ ተከታዮች ሌላ ሁሉንም ዜጋ የሚያሳትፍና የሚጠቅም እንደ መሆኑም ለጋሾች፣ ሲቪል ማኅበራት፣ መንግሥታዊ ተቋማትና ሌሎችም ከቤተ ክርስቲያኒቱ ጐን እንዲቆሙ ቅዱስ ሲኖዶስ ጥሪውን አስተላልፏል።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

'

# ልጅዎ የ1ኛ ደረጃ ትምህርቱን በስኬት እንዲያጠናቅቅ...

አቡነ ጎርጎርዮስ ዐጸደ ሕፃናት ወደ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተሸጋግሮ ለ1997 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ምዝገባ ጀምሯል። በዚህ ዓመት ልጆቻቸው የዐጸደ ሕፃናት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ወላጆች ለ1ኛ ክፍል እያስመዘገቧቸው ይገኛሉ። እርስዎስ?

- የሥነ ምግባር ትምህርት በቂ ጊዜ ተመድቦለት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል::
- ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክሂል እና በቂ ልምድ ያላቸው መምህራን ተዘጋጅተዋል::
- የትምህርት አሰጣጡ የልጆችን ዐቅም በሚመጥን መልኩ በኮምፒዩተር ይታገዛል::

ከነርሰሪ እስከ 2ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የክረምት የማጠናከሪያ ትምህርትም ተዘጋጅቷል::

*አድራሻ፡-* ከቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ወረድ ብሎ አዲስ አበባ ጤና ቢሮ አጠገብ
ስልክ ቁጥር 51-37-42/51-06-59

**ማኅበረ ቅዱሳን**

# ፍኖተ አሚን

የሚል አዲስ የኦሮምኛ ቁጥር ፩ መጽሐፍ በሥርጭት ላይ ውሏል !!

አሳታሚና አከፋፋይ **ማኅበረ ቅዱሳን**

**Kitaabni haaraan DAANDII AMANTII jedhu afaan Oromiffaan qophaa'ee gabaa"ra Oleera**
**Kitaabin kun – waa'ee Soomaa, Lissaanaa fi Taabotaa nu barsiisa.**
**Kutaa lammaffaan itti fufa**

# አዳዲስ የቪዲዮ ትምህርቶች

**1ኛ/ ቅድስናና መገለጫው-** በሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን አገዘ

**1ኛ/ መንፈሳዊነት-** በዲ/ን ብርሃኑ አድማስ

ሁለቱም ትምህርቶች በሥርጭት ላይ ውለዋል!!

ከዚህ በፊት በቪዲዮ የቀረቡ ትምህርቶችም በVCD ተዘጋጅተው ቀርበዋል!!

## የግእዝ ቋንቋን መማር የፈልጋሉ? የአብነት ትምህርትስ? /ንባብ፣ ዜማ፣ ቅዳሴ/ በገና መደርደርስ?

- ግእዝን እንደ ቋንቋ አውቀውት ለሚፈልጉት አገልግሎት እንዲጠቀሙበት /የሚፈጀው ጊዜ 6 ወራት/
- ንባብ፣ ዜማ እና ቅኔ ትምህርት ተምረው በቤተክርስቲያን ከሊቃውንት ጋር እንዲያመሰግኑና እንዲጸልዩ እንዲሁ በግልዎ እንዲጠቀሙበት /አንዱ ትምህርት የሚፈጀው ጊዜ 6 ወራት/
- የበገና የመሰንቆ ወይም የዋሽንት አጠቃቀም ተምረው ሲያዝኑ እንዲጸልዩበት ሲደሰቱ እንዲያመሰግኑበት /አንዱ ትምህርት የሚፈጀው ጊዜ 3 ወራት/

**የመረጡትን እንዲማሩ አሁኑኑ ይመዝገቡ !!**

ትምህርቱ ከሐምሌ 19 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በሳምንት ሁለት ቀን በየዕለቱ ሁለት ሰዓት፤ በሥራ ቀን ማታ /ከ12:00-2:00/ ወይም ቅዳሜ እና እሑድ /ከ10:00-12:00/ የሚሰጥ ሲሆን ዝርዝር ፕሮግራሙ ትምህርቱ በሚሰጥበት ቦታ ይገለጻል::

*ቦታ፡-* አዲስ አበባ ደብረ ጸጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ
ስልክ ቁጥር 51 06 59/23 45 30

**ማኅበረ ቅዱሳን**

## ልጅዎ የአብነት ትምህርት እንዲማር/እንድትማር ይሻሉ?

- ልጆች በፊደል፣ ቁጥርና ንባብ ጀምረው ውዳሴ ማርያምን ዘልቀው ዳዊት የሚደግሙበት የአብነት ትምህርት ተመቻችቷል::
- በተጨማሪም ትምህርተ ሃይማኖትን፣ ሥርዓተ እምነትን፣ ክርስቲያናዊ ትውፊትንና ታሪክን በመሠረታዊነት እንዲማሩ ይደረጋል::
- ትምህርቱ የልጆች ፍላጎት በቀላሉ በሚረዱ፣ ከልጆች ጋር በኖሩ ብቁ መምህራን ይሰጣል።
- ከዩ.ኬ.ጂ እስከ 8ኛ ክፍል የደረሱ ልጆችን ብቻ እንቀበላለን::
- ለልጆች አመቺ በሆነ ቦታ፣ በቂ ጥበቃና ንጽሕናው በተሟላለት ሥፍራ ትምህርቱ ይሰጣል።

***ፕሮግራሙ***

- *ክረምት፡- ለ6 ሳምንታት በተከታታይ ከሐምሌ 19 እስከ ነሐሴ 21/1996 ዓ.ም ከሰኞ-ዓርብ ጠዋት ሦስት ቀን ትምህርት፣ ሁለት ቀን ማጠናከሪያ ይሰጣል።*
- *በበጋ፡- ዘወትር ቅዳሜ ጠዋት*

*ቦታ፡-* አዲስ አበባ ደብረ ጸጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ
ስልክ ቁጥር 51 06 59/23 45 30

**ማኅበረ ቅዱሳን**

ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ

ዋጋ ብር 3.50

©

!" #$ %

& ' ( ) * $++